http://ethioliberty.wordpress.com/

ክበጥ



ከብርሃን ዳኘ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሸበጥ

እና

ሌሎች አጫጭር ታሪኮች

ከብርሃን ዳኛ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ከብርሃን ዳኛ

ሸበጥ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGNECY

ስልክ
Tel } 11 27 19

ፖ.ሳ.ቁ
P.O.Box } 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የሽፋን ምዕል ለቃስ አማረ

ፍርንኝ ሰሞ ማተሚያ ፊት ታተመ

ማ ው ጫ

1. ራዔል 5
2. አርትሉት 32
3. ጠየቃ 54
4. አትሌቷ 80
5. አምሮት 116
6. ዋዜማ 128
7. ሽባዋ 147
8. ወይኔ ልጄት ! 157
9. ምጥት 180
10. ሽበዋ 190
11. ፈጣን ! . . 211

http://ethioliberty.wordpress.com/

ራሄል

ሴቺንቶዋ «አራት ኪሎ—ቦካ» የሚል ታፔላ ለጥፋ ለች ። ቁርና ሐሩር ከዝናብ ጋር ተራ ገብተው የታፔላ ውን ቀለም ጻርና ጻር ቀርፈውታል ።

የቀበና ድልድይ ጠባብ ከመሆኑ ሌላ ረባጻ ነው ። ሴቺንቶዋ ከላይ ወደ ቁልቁለቱ እንደ ተወረወረች መልሳ ፈቷን ወደ የካ አዞረች ። በትንደረደር ሞተሯ ጠፍቶ በዜሮ ብትወርድም ፣ አቀበቱን በትዉጣ በሥቃይ ነው ። ሞተሩ ተግ ያለው ። ቤንዚን ለመቆጠብ ሞተር ማጥፋት ፣ እንጀት አስሮ እንጦሮ መውጣት እንደሆን አይታወቃትም ። ግጠፈያው በስተግራ እንደ ተጣበቀ ቁም ሣጥን ወደኋላ የሚከፈቱት በሮች ዋርትም ተደር ገው ቢዘጉም ገጭ . . . ገጭ . . . ይላሉ ። የሚረገጠው ሆዲ አልር አልር ዐይን በሚጣሩ ሽንቁሮች አስፋልቱን ያሳያል ።

የሳምንቱን መጨረሻ አሳበው መኪኖች ይፈነጥ ዛሉ ። ገጽታቸው በደስታ የፈካ ሰዎችን ጭነው ፈካ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ለቡ ፥ ያቺን በእቅም የደከመች—ከርካሳ ሴቼንቶ ያስተ
ዋሉ አይመስሉም ።

«እያምም ! ... ምምም ... ም» የሞተሯን ድምፅ ታወ
ጣለች ።

በኋላው መቀመጫ ሁለት ወጣቶች አሳፍራለች ።
ወጣቶቹ እንደ መንገደኛ ግራና ቀኙን እያስተውሉም ።
በውስጣዊ ሐሳብ መመሰጣቸው ያስታውቃል ። ዐይና
ቸው ትዝዝ ባለ ሁኔታ በፊት መስታወቱ ተሻግሮ እፍ
ጧል ።

ራሄል በዚያ ባልተወለወለ መስታወት እንኳ የሚ
መለከታትን መንገደኛ ታረዛለች ። ዐይን የሚጉትት
የውበት ግጒኔት አላት ። ከብ ሬቷ ተመተኛ እንዶ የረር
ብርቱካን ግመጡኝ ይላል ። የሕየን ልጅ ጣት የሚያክ
ለው እፍንጫዋ ፥ በኒያ በቢ ዐይኖች ባይታጀብ ኖር
ቁርጥ ጀፓኖችን ነበረች ። ዘወትር የምትከመክመው
ድብን ያለው «ቤቢ» እፍር ከፊቷ ቀለም ጋር ተታርኖ
ልዩ ድምቀት ሰጥቷታል ።

ጉን ለጉን ሲንሾካሾኩ ፥ ሰው እንዳይሰማቸው
ያደቡ ይመስላሉ ።

«ራሄል !... ምነው ዝም አልሽ ! » አለ ድንበሩ
በለሆሳስ ። እንዲም ምላጭ ያልነካው ጠሙ አቀምቅ
ሟል ። ቀጭን ራቁ እሀል በልቶ የሚያድር አያስመስ
ለውም ። የልጅነት ላህዩን ጋርዶታል ።

«ምን ልበል ብለህ ነው ? ... ፊራሁ ። የምሞት ፥
የምሞት ይመስለኛል ... እንዲህ የሚያደርጉ ሴቶች
ብዙውን ጊዜ ይሞቱ የለ ! ... እግዙ ምን ትለኝ ይሆን ! »
ቋላ ስትጨነት ፥ የክፉ ቀን መረበሽ እንኳ ውበቷን
መደበት አልቻለም ።

ድንበሩ እንደ ዓመታዊ ተዝካር ጠብ እርግፍ እያለ
የሚዘጋጀበት ያ የጀኔቫ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ካንዲም
ሁሉ ጉድ ባያደርገው ፥ ችግሮች እንዲህ ይከተሉት
ነበር ! «መልሱ አልተሰጠም» ብሎ መልሶታል ። ሥራ
አላገኘም — እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ—ለዛውም ጊዜያዊ ።
በቤተሰብ ሜንታ ላይ ማናጠር ከቀን ቀን ሲቆጠቁጠው
ከርሟል— በጉሮው ምንም ባይጉልበትም ።

ድንበሩ ንብረአገዚ እንደ መፋቂያ የረዘሙ ጣቶ
ቹን እያንቋቋ ፥

«እይዞሽ ራሄል !... በራስሽ ላይ እንዲህ ያለ ክፋት
አታስቢ ። ሴትየዋን ራሴ እናግራለቸዋለሁ ። 'ነጭው
ያወጣዋል' ብለዋል ። 'ምንም ሳታመነታ ጭልጥ አርጋ
ትጠጣው' ነው የሚሉት » ይላታል ።

«ግራ ገባኝ ! ... መውጫ ቀዳዳ ያጣች ወፍ አታ
ውቅም ! ... የሆስፒታል መድኃኒት እንኳ ከፉኛ ያስ
ፈራኛል ። ድንበሩ ! ደም ከፈሰሰኝማ የምተርፍ አይ
መስለኝም ... ዐፍ»

«እኔው ነኝ አይደል—ለዚህ ያቢታሁሽ ? ... በዛሂ !»

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፈልጉንማ ተወው ፥ በቃ እርሳው ! ... እንዴ የሆነ ነገር ! ዕድሉ ካወጣኝ ያውጣኝ . . .»

ድንበሩ ከንፉን በትከሻዋ ላይ አሳስፈና ግጥም እርጎ አቀፋት ። በጣቶቹ ዶረታን ዳበሰው ። ጡቶቿን ነካ ነካ ... ሜን ፥ አውንም በሹክሹክታ « እይዞሽ ! ... ዛሬ ይለይለታል ። ማንም ሳይሰማ ይፈተለካል ! » አላት ። እንገቷ ሥር መሸጉጥ ከጀለው ። ከነጎት አበቦች ይነ ግል ከሚባለው መዓዛ የሚወጻደረውን የራሄልን ጠረን ባፍና ባፍንጫው ሳበው ። አፏም ድንገት ብርድ ውርር ያረጋት ይመስል—ጥብቅ አለችበት ።

ቮፈሩ ፥ ተሸራርፎ ሩብ ያህል በቀረው የጀርባ ማሳያ መስታወት እየተመለከታቸው ጸጉሩን አሸት ... እከክ አደረገው ።

ድንበሩ ‘እስቲ አሁን ምን ይወራል— ይቺ ልጅ ጉድ ብትሆን ? ... የሰው ልጅ አጉል አድርጌ ምን አላለሁ ?’ —በእግረ—ሕሊናው ወደ ኋላ ተመለሰ ...

ድንበሩ አሁን ጥብብ ጭንቅ የሚልላትን—ራሄል—የተዋወቃት ከሦስት ዓመት በፊት አራት ኪሎ አካባቢ በሚገኝ አንድ የጽሕፈት መሣሪያዎች መደብር ውስጥ ነበር ።

ራሄል ማስታወሻ ደብተር ለመግዛት በዋጋው መወ ደድ የተነሣ ከነጋዴው ስትከራከር ፥ ሳታስበው ከኋ ላዋ ተከትሏት ለያ በግድላት ድንበሩ ተከራከረላት ።

ይህ ሁኔታ በራሄል ላይ ያሳደረው የመከፋት ሥሜት ወዲያው ሲተዋወቁ ...

... የሕሊናው ማኅደር ትውስታውን አላከታትል ቢለው ፥ ምንጊዜም ወደማይጠፋበት አውራ ትዝታ አመራ ።

ከሦስት ወር በፊት መሆኑ ነው ።

ድንበሩ ንብረእግዚ ባንድ የግል ድርጅት ጊዜያዊ ሥራ ከተቆናጠጠ ብዙም አላሳለፈም ነበር ። የስታትስ ቲክስ መረጃዎች ማዘጋጀት ነው—ሥራው ። ጠረጴዛ ላይ ተደፍቶ መዋል ባሳር ለመደ ። ጥሱት ቢወጣ እግሩ እስኪነቃ የሚሠረው ዙረት ወለል ብሎ ታየው ። ስለ ዚህ በሚያገኘው አነስተኛ አበል እየተጽናና አደፈጠ ።

የደመወዝ ይሁን አበል አዲስ ለማጀት ምን ይሁን ምን—የሚቀበሉት ብዙ ይመስላቸዋል ። ቢመዘዝ ግለ ቁን ሞራሽ ይጠራጠራሉ ።

በዚያች የወዙ እንጥፍጣፊ—ገንዘቡ—እያሉ ነገር ሊፈጽምባት ተመኘ—ድንበሩ ። ራሄልን ለማስደሰት ፥ በፍቅር የጐለበተ አከብሮቱን ለመግለጽ ፥ እሷን ማዝ ናናት ቅድሚያ ሰጠው ። የከሰዓት በኋላ ፈረቃ ጨርሳ ስትወጣ ለግግሟ ምኒልክ ትምህርት ቤት በር ጠብቆ ይቀበላታል ። ስለ ፲፩ኛ ክፍል ትምህርቷ ይጠይቃታል ። የሱን ዕድል መጥመም እየረገመ ፥ በርትታ እንድትሠራ ይመክራታል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ወዮልሽ ! ... መንገደኛ ሆነሽ ትቀሪና ! » ይላታል « እያሰለሰ ሲያነኛት ተጨዋውተው ፣ ተቀላልዶው ይለያያሉ » እሱ ወደ አቶቡስ መቆሚያ ያመራል ፤ ወደ የካ የሚወስደውን ለመያዝ » እሷ በብርሃንና ሰላም ማተ ሚያ ቤት በኩል አልፋ ወደ ቤቷ ታዘግማለች »

ልብ ለልብ ተስማሙ » በመተሳሰብ ተቀራረቡ »

ድንበሩ «ኪስ እንዳበጠ ይከርማል ! » የሚለውን ሐሳብ በዚያ ለሁለተኛ ጊዜ ይመዝዝ በወሰዶ ሰሞን እል ተዘነጋውም » እጠብቅሻለሁ ባላት የቀጠሮ ቀን ከትም ሀርት ቤቷ በራፍ አገኛት » እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ «ዳሸን ምግብ ቤት» እዘቀዝቁ »

ተማሪዎች ሲለቀቁ በሚገነፍለው ትርምስ መካ ከል ብዙው ጉረምሳ ወይኑን በራሄል ላይ ይወረው ራል » ብቻዋን ወይም ከሴቶች ጋር ስትሆን—በቀጥታ የሚጐነትላት አታጣም »

«ቀይ ሽንኩርት ... ጉርሶ ኮሽ ኮሽ ማረግ ነበር » ይሏታል ፣ እዘውትረው የማይጠፉና ባይን የሚያውቋት» ይህ ጋብ የሚለው ድንበሩ እጅቧት ፣ ከትከሻው እጉን ብሶ እያናነራት አብረው ሲሔዱ ነው » ቢሆንም ከማ ጎደራቸው የተጉለጉሉ ዐይኖች ከፍ ዝቅ እርገው ያስ ተውሏቸዋል »

«ዳሸን ምግብ ቤት» ውስጥ ሳይገቡ ከበረንዳው ወንበሮች ላይ ዐረፍ ብለው ፣ ሻይ ወተት እዘው ተቀ መጡ »

«ኤሎድ ምን ትመሪያለሽ?» ብሎ ጠየቃት » ኤሎድ ቀን ከስንት እንዴ ነው— ቀጠሮ የሚይዙት » የራሄል ጓን ጉል ቤተሰቦች «በፅሪናት ቀን እግርሽ ይጡም ፤ እደብ ግር » ብለው ይሜኗታል » ድንበሩ በፊናው እንድትጋ ለጥበት አይፈልግም » ስለዚህ ራቅ ራቅ እርጉ ነው— የኤ ሎድ ቀጠሮ የሚሰጣት » እሷም እንዳይሳቀት «እሺ» ብላ ሰበብ ትሰጣለች— ለቤተሰቦቿ— መውጫ »

«ምንም እልሠራ ... ምነው ? » መልሳ ጠየቀችው »

«እይ እንዲያው አብረን ብንቆይ ብዬ ነው » ከቤት መውጣት ከቻልሽ ?» ይላታል » የተተበለው ደሞዝ ትዝ ብሎት የልቡ ምት እየፈጠነ ፣ ጋብዞ ሲያስደስታት ታይቶት ምራቁ በአፉ እንደ መሙላት እያለ »

«እግዙ 'ዘመድ ጥየቃ ተከተይኝ' ትል ይሆናል ፣ ብቻ ምክንያት ስጥቼ እወጣለሁ » ብላ ፣ ፍጥረት የሚ ያደነዝዝ ወይኗን በስለታም ፈቱ ላይ ወረወረችበት »

የፈት ገጽታዋን እሱም በዐይኑ ሲዳስሰው ፣ በሰውነቱ ሙቀት ተቀጣጠለ » ፈገግታዋ ባሕር ላርቻ እንደ ወጣች የጠዋት ይሔይ ተሰማው » ያጉጠጉጠት ጡቶቿ ሸሚዟን ወጥረውታልና ከድንበሩ እጅ ነገር ያላቸው ይመስል ጣቶቹ ሲንቀጠቀጡ ፣ ንዝረት ወረረው »

ድንበሩ የጊዜያዊ ሥራውን ጉዳይ እንሥቶ ትንሽ እሚውታት ፣ በዳሸን ምግብ ቤት ደረጀዎች ወርደው ቀለያዩ »

http://ethioliberty.wordpress.com/

አሉድ፣ የራዲዮው የዘፈን ምርጫ ፕሮግራም ሲጀመር በአሥመራ መንገድ «የኔነሽ ሆቴል » ነበሩ።

ደብዘዝ ያለ ብርሃን ባለው የመመገቢያ አዳራሽ፣ ለመከለያ ከቆመው የተሰበደ ሌጦ ጉን ካሉ ሁለት ዴካ ዎች ላይ ተቀመጡ። እመሐል፣ ከድንበሩ ይሁን ከራሄል ጉልበቶች ከፍ ያላለው አጭር ጠረጴዛ አንጋጦ «እንኳን ደህና መጣችሁ!» አላቸው።

አዳራሹ ጥንታዊውን ኢትዮጵያዊ ቤት ለመምሰል በወለሉ ...ዴካዎች፣ ምንጣፎች... ተሠልፈዋል። በግር ግዳው ... ሰሬድ፣ የመሶብ ክዳን፣ ጭራ፣ ቀንድ ... ተሰቅለዋል። አሳላፊዎቹ በሀገር ልብስ ተውበዋል።

ድንበሩ ገብረእግዚ— በደንብ የተጠበሰ ክትፎ ለሷ፣ ጥሬውን ለሱ ከቢራ ጋር አዘዘ። ቀረበላቸው። ክትፎ የሚያጅበው ሚጥሚጣ የድንበሩን እፍ በምራቅ ሞላው። እንጀራ ከእጃቸው እየተትረፈረፈ ቢያስቸግራቸውም መጉራረስ ጀመሩ።

«መቼስ ክትፎ ያለ ቢራ፣ ዶሮ ወጥ ያለ ጠሶ፣ ለቅሶ ያለ መሐረብ ... ከሆነ፣ ነገር ያጉድፋል» እያለ ራሄልን አግታት።

«ይቺን መጨረስ አለብሽ!» አለ ድንበሩ፣ላመል ራሄል ፉት ካለችው ብርጭቆ ላይ እመልካች ጣቱን ቀስሮ፣

«እኔ ቢራ እያሆንልኝም ... እሁንም ላንተ ብዬ ነው። ሳሙኤል ነው እንዳንጄ ጠጪ የሚለኝ፣ ... መጀመሪያ የቀመስኩ ቀን ሆን ብን አሳስኝ ታውቃለህ?» አለች ራሄል— ግርምታ ፈቷን አልብሏት።

አልፎ አልፎ እነ ራሄል ቤት ድግስ ቢጤ ሲናር ታላቅ ወንድሟ ሳሙኤል፣ «ይልቅ ቀስ እያልሽ ልመጂው፣ ለስላሳ እየተጋትሽ ዐይንሽን ብታቁለጨልጪ፣ በእፍሽ ብታነፈንፊ፣ ደስታ አይሠርፅብሽም» የሚላት ታወሳት።

«ምን ምን አለሽ ታዲያ?» ስለታም ራቱ ለጨዋታ እንዳቆበቆበ፣ የቀረውን ቢራ እንዶቀዶቀው ድንበሩ።

«በልዩ ትምም የተፈላ፣ ግን ስኳር የሌለው የቀዝቃዛ ሻይ ጣዕም ይሰማኝ ነበር ... ደግሞ ይጉመዠዠኛል።»

«ሲጀመር የማይጉመዠዠ ምን አለ?» ብሎ ጣቀ። እሷም ፈገግ አለች።

ቀጥሎም «ቢራ አፍታሪዎች እንዳይሰሙሽ!» አላት።

ራሄል ጓንጉል በተጉነጨች ቁጥር የተፈላ ወተት የምታባርድ ትመስላለች። የቀረበላቸው ገበታ ተንጣ። እጃቸውን እያደረቁ ሳለ፣

«የጥናቱን ነገር የት እደረሺው?» ሲል ጠየቃት።

«እንደሚሆን እየተፍጨረጨርኩ ነው። ካሁኑ ፈር ቼዋለው ባይገርምህ... እያስፈራም!»

«እሱማ ማስፈራቱ መች ይቀራል?... ግን ካሁኑ ብታውቂበት ይሻላል። አስዚያ—ዐሥራ ሁለት ሲደመር ሙጭ— ሆነሽ ታርፈዋለሽ»

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ዚሆንም 'ሰኮሳ' ማፈላለግ ነው እንጂ ፡ ዝም አይባል ። እማዬ 'በርትተሽ ካጠናሽ የማደርገውን አታውቂም ' ብላኛለች ። »

«ጥሩ ፤ በጣም ጥሩ ... ታዲያ ለምን አትጠጪም ፤» ሲል ድንበሩ ፡ ቀስ እያለች ጠጣች— ራሄል ።

ስለ ጊዜያዊ ሥራውና የቢሮ ጣጣዎች ፡ ዲስፐሊን ... በትንሹ ዘገበላት ። «በይ ድንግ ከቢራው !» ብሎ ተጨማሪ ሲያዝ ፡ ራሄል ተታወሰች ።

«እይው ፤ ባንድ ተለከፈሽ ራስ ምታት ከሚይዝሽ ድግሚውና ይስተካከላል ፤ »

«ተው ድንበሩዬ !. . . ይብቃኝ ፤ እየው ላቡ እንኳ » ንግግሯን ሳትጨርስ ፤

«ታዲያ የትድሙ ሚጥሚጣ ነዋ! ቢራው ምንም እያደርግሽም»

«እኔ 'ንጂ !» ብላ ፡ ቅር እያላት ደገመች ። እሱም እንደዚያው ።

የድንበሩ ሰውነት ተጋጋለ ። ሽንት ቤት ደርሶ ሲመለስ ባዲስ መንፈስ ጨመረበት ። ቢራዎች ... የፋብሪካ ጠላዎች ... ለብታ ... ሞትታ ... ንታታት ...

ድንበሩ ፡ 'እጥብቀው ከሚያፈቅሩት ጋር እንዳንዴ ያለገደብ መዝናናት ይናፍቃል ፡ ... እንደ ልጅም እንዳኖ ቂም መጨዋወት' በሚል ሐሳብ ልቡን እደንድኖ ፡ ማመን ታቱን ወደ ጉን አረገው ።

«መሬር እንዲት ነው?» አለ ።

«ጥሩ ነው ... ብቻ ለካፈው በፃ ። እንድ ጥቁር ወፍ ራም ልጅ ፡ ከሰዓድ ሱት የማይጠፋው ፡ አይተሽዋል አይደል ?. . . እያስፈራራ የሚናገረውን ብትሰማ— ያናድጻል !» ብላ እንዴ ተጉነጨች ።

በሞትት ተነታትተው እንደ አደባባይ እምቦል የሚ ያበሩት የድንበሩ ወይናች ራሄል ላይ አፈጠጡ ።

«ምን ለመሆን ነው ? ... 'ሁሉም ነገር በግድ ነው የሚሆነው' ማለት ነው ? ምናይነቱ ደደብ ነው ። እሺ !... እቢት ነገርሻቸው ?»

«እሱማ ... ለማዩ ነግሬአት ነበር ፤ 'እቆጣዋለው' ብላ ለች ።»

የድንበሩ ትንሿ ብሽቶት እየጨሰች ፡ የተቀሰቀሰበትን ለብታ እጋመችው ። ከብርጭቆው እየጠጣ ፤

«ይገርምሻል ! ... ምን ቢደረግ ሴቶች እንደ ፈለጉ እንደሚሆኑ አላውትም ። ትምህርት ቤት ለከፋ ፡ ሲላቸው ድብደባ ፡ መሬር ለከፋ ፡ ጉንተላ ... ደሞ ማስፈራራት ! . . . እንድ የሴቶች ደሴት ያስፈልጋል ፤ ሴቶች ለብቻቸው የሚኖ ሩበት— ለከፋ የሌለበት !»

«እሺ !... እኔስ ወደ ደሴቱ ብሔድብህ ? » ራሄል ካጉነበሰችበት ዐይኗን ነቅላ ወረወረችበት ። ድንበሩ ካይኖጀ በሚወጣው ጨረር ተመታ ። በከዋክብቶች መን ደር እንደሚንሳፈፍ መንኮራኩር መጠቀ ። ትንሽ እፍን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሚዋን ፣ እንጂሪ ከንፈሯን ፣ ትንቡክ ጉንጮቿን ፣ ና ወደኔ የሚል ግንባሯን . . . በሞቅታ መነጽር አዩሰው ፣ ጻሰሰው ።

«እንደሱማ የት ይሆናል ? ... ለምን ትሔጂብኛለሽ» ሲል ትዝዝ ብሎ ፣ ራሄል ልቦ ጢ እስኪል ጣቀች ።

ሲኮንድ ደቂቃን እየወለደ ደቂቃም እንዲሁ ሲከ ንፍ ራሄልን ደካከማት ። ከፊል ብሽቦታ አፈዘዛት ።

ድንበሩ ተጨማሪ ቢራ አዘዘ ። ሐሳብ የመሰጠው መሰለ ። 'ሴላ ከፍል ብቅችንን ብንሆንስ ? የመጀመሪያ ቢሆንም ክፋት የለውም ' የሚል ሐሳብ አደረበት ። ሴላ ከንፎቱ ያገባው ጉዳይ አልነበረም ።

«ራሄል ... ደከመሽ አይደል ? ነይ እንሒድ ። እንዱ ከፍል ውስጥ ዐረፍ እንላለን ። ትንሽ ቆይተን እንሔዳ ለን ። እንዲህ ሆነሽ ለሚመለከት ሰው በቁም የምታንቀ ላፊ ይመስለዋል ። »

«ለምን ? » ስትል፣ድንጋጤዋ የፊቷን ቅላት አነጣው ። ስሜቷ ተዘበራረቀባት ። ስለሚመጣው አሰተነበየችም ።

ቆሞ እጁን ሲሰጣት ተደነጋገሯት ተከተለችው ። በጓሮው በር ወጡ ። ድንበሩ ማረፊያ ክፍል መከራ የት እንደሚሻ ጠየቀ ። ያልደረቀ ያሸዋ ግርፍ ከሚታ ታይበት ቀርታ ክፍሎች ወደ ሁለት ቁጥር ተመራ ። ራሄል መረት መረት እያየች ስትከተለው ፣ እሱም እግ ሩን ብድግ ጣል እያደረገ ሲራመድ ፣ ሕፃናት እርስ በእ

ርስ ፣ እንዱ ፈረሰ ሌላው መሪ ሆነው የሚጫወቱትን ፣ ይመ ስላሉ ።

መስኮት የሌለውን ክፍል ከውስጥ ዘጋው። ጭልም አለ ። በበሩ ራስጌና ግርጌ ወጋገን እየታገዘ መብራቱን አበራው— ድንበሩ ። ራሄል ግድግዳውን ከተደገፈ ብቸኛ ወንበር ላይ ዘፍ አለች ።

ድንበሩ እንደቆመ ፣

«ምነው ራሄል ... አልጋው አይሻልሽም ?...ፈራሽ!»

«አይ አልፈራሁም ...» አለች ፣ ዝግ ብላ ። እጅዋን ይዞ ፣ ከአንድ ሰው በተጨማሪ በማይዘው አልጋ ላይ አስቀ መጣት ። የራሄል ልብ ስንጥት ... ትርትር አለ ። ባዕድ ድን ጋጤ ወረራት ።

ድንበሩ ከጉሮ ሆነና አቀፋት ። ትንቀጠቀጣለች ። ጉን ጮጅን ፣ ከንፈሯን ሲሰማት በሠረጸባት ድንጋጤ ስሜ ትዋ ቀዝቅዞ በድን ሆነች ። ሌላው ቀርቶ ሲኒማ ቤትም ቢሆን ጭምት እርጉ ሲሰማት ፣ ስሜትዋ መቀበል ብቻ ላይ ሆን መስጠትም ይችል ነበር ።

« ራሄል ራስሽን አታስጨንቂው ... አለዚያ ራስ ምታቱ አይለቅሽም ፤ እንዲያውም ጋደም በይበት ። » ጉሮሮው ስልት ባጣ ምት ሲሥህ ፣ የተቆራረጠ ድምፅ አወጣ ።

ጉልበቷን አሻሽቶ እጁዋን ከቢጫው «ባጊ» ሱሪ ሥር ወላሉት ሜጣዎጀ ሰዶ ፣ አወለቃቸው ። እግሮቿን እን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ደያዘ ቁርጭምጭሚቷን ፣ ባቷን እያበሰ አልጋው ላይ ሲዘረጋት ሕየን ልጅ ለማስተኛት የሚያባብል ይመስላል።

ልቡ ድው ድው እያለ ይደልቃል ፤ እጆቹ ይንቀጠ ቀጣሉ ፤ እግሮቹ ይብረከረካሉ '... በል በል አትረፍ ! ... በል በል አትረፍ !' አለው የሆነ ውስጣዊ ሞገድ ።

ራሄል ዐይኗን ጨፍናለች ። ጥቁር ... ቢጫ ... ቀይ ... ወይን ጠጅ ... ነጭ ... ቀለሞች ጣቢያውን እንደ ሳተ ቴሌቪዥን ብዥ አሉባት ። ልቧ ቁር ብሎ ይወጣ ይመስል ተጎደፋደፈ ። እየር በትስብና በትተነፍስ የም ታንኮራፋ ትመስላለች ።

ድንበሩ ከጉኗ ተጋደመ ። የጉንዮሽ ቀና ብሎ ግን ባጅን ፣ ጉንጯን ፣ ከንፈሯን ሳም ... ምጥጥ ሲያደር ገው ቆየ ። ባንደኛው እጁ ከሹራቧ ሥር ያደረገችውን ቡናይነት ሽሚዝ ለመክፈት እዝራሮቹን ፈታቸው ። ደረ ቷን ፣ ጡቶቿን ወርዶ ሆዷን እሸት ... ሜን አረገው ። የደም ዝውውሩ በመፍጠን እያስገመገመ በሠራ አካላቱ እንደ ፈንዳ ፱ንፀ ኃ አለ ።

አሁንም ራሄል ዐይኗ እንደ ጨፈነች ነው ። ድን በሩ እጁን ከደረቷ አወጣና ሰዋኗ መሐል ላከው ። አሸት ... አሸት ፣ ሜን ... ጣቶቹ ኤሌክትሪክ የነኩ ይመስል ነዘራቸው ።

ቢሜውን ፀባጊ» ሱሪ ለመፍታት ትግል ያዘ ።

«ድንበሩ ! ... ድንበሩዬ ተው እይሆንም ። ድንበሩ ስቀበር ! በኋላ ለሁለታችንም አይሆንም ፣ ተው ! ይቅር

ብን » አለች ራሄል ፣ በሥጋቷና ፣ ጉጉቷ ፣ ተጨ ጥራ ለመነጣት እየታገለች ።

ድንበሩ መድፍ ቢተኮስ እንኳ አይሰማም ። ጆሮው ተደፍኗል — ስሜት ዘግቶታል ። ዐይኑ ተሸብቦ ጭልም ብሎበታል ። ሚግውን መንጭቆ ወረወረው ። አልጋው ላይ ወጣ ። ራሄል ጓንጉል እንደዚያ የሚካበድ ሰውነት ወጥቶ መተንፈስ እስኪያውካት ያስጨነቃት እንድም ጊዜ አይታወሳትም ።

«ድንበሩዬ ! ... በናትህ ! አይሆንም ፣ እምቢኮ አይደ ለም — የምልህ ፣ እምቢ አላልኩም ። ግን መቆየት አለ ብን ። እግዬ ገና ብዙ ትቆጣኛለች ፣ መቆየት አለብን ። የኔ ቆንጆ ... በወለዱህ ! » ተግጠነችው ። በርበሬ የመ ሰሉት ጉንጮቿ ረጠቡ ። ከድንበሩ የሚወጣው ትን ፋሽ፣ በወናፍ እንደሚገም የብረት ማቅለጫ እሳት ገረፋት ።

ድንበሩ ራሱ ወደ ሠመው ዓለም ፣ ምድራቱን ሰቆ በእጁጉ ራቀ ። ሰማየ ሰማያት እየሰነጠቀ ከነፈ ። እሻቅቦ በሚነሣው እውሎ ንፋስ ፅፀዋትና ተክሎች እሸበሸቡ ። «እልል ! » አሉ ። ውቅያኖስና ባሕር ተናወጠ ። የምድር ዙሪት ፈጠነ ። ብር እምባር — ተሰበረ !

ያቺ ሴቼንቶ ለትጻሚው ኀበያ ከወደ ኮተቤ ተጭኖ የመጣውን እህያ ቅልጥሙን ልትለው ምንም አልቀራ ትም ። ለትንሽ ሲጢጥ እርጋ አቆመች ። ቮፈሩ ራቱን ወደ መስኩቱ እዙሮ እህያ ነጂውን በስድብ አከናነበው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የፈቺንቶየ ሞተር ተግ እስኪል ድረስ መኪናች ከኋላ ተሰልፈው ፣ «ኧድ...ኧድድ» እያሉ ሲጮሁ ፣ ድንበሩ ወደ ኋላው ተገላመጠ ።

«እቤት ግንም አይናር ፣ አይደል ? » አለች ራሄል በሹክሹክታ ፣ ኩልል ባለውም የተሸፈነውን ዐይኗን ጣል አርጋ ።

«ግንም የለ ... ሠራተኖችን ብቻ ናት » ሲል እጉ ተመተመ ። እባቱ ለመስክ ሥራ ወጥተዋል ። እናቱም ክነሱ ዘንድ አይናሩም— ከባለቤታቸው ስለ ተለያዩ ። ወን ድሞቹ ለትምህርት ውጭ ሀገር ሔደዋል ። ትልቋ እህ ታቸው አግብታለች ።

የሁሉም ምስል በሕሊናው እየተፈራረቀ ሲታሰበው የምርጥ «አክተሮች» ፎቶግራፍ እንድ ፣ ሁለት እያለ የሚ ቆጥር ይመስላል ።

ሴቺንቶየ ቮላ ገበያ ሳትደርስ «እዚህ ይበቃል ! » ብሎ ድንበሩ ሒሳብ ሲከፍል ፣ በገበያው የሚተራመሰ ውን ሕዝብ ከርቱት ገላመጠው ።

ለራሄል እጇን ሰጣትና ወረደች ። ሌሎችም መኪ ናዎች ሴቺንቶየን ተከትለው አለፉ ። የባቡር መንገዱን ግራና ቀኝ አይተው ወደ ላይ አቋረጡ ። በኮረኮንቹ ዘል ቀው ወደ መንደሩ ገቡ ። በቆርቆሮ የታጠረ አንድ ግቢ በራፍ ሲደርሱ ፣ ድንበሩ ለቴሙቴ የማያስቸግረውን ይወል ኪርር ! . . . ኪርርር ! አረገው ።

በሩ ተከፍቶላቸው ገቡ ። የግቢው ሜዳ ሰፊ አይባ ልም ። ሬያት ፩ደ፩ኗ መኪና አጥሩን ተጠግታ ቆማለች ።

«ብርጭቆና ቀዝቃዛ ውሃ በጠርሙስ ይዘሽ ነይ ! » አለ ድንበሩ ፣ ወደ ቤት ሠራተኛው እፍጠ — ገና ሳሱን ከመግባቱ ። ራሄል ፎቴው ወንበር ላይ ዐረፍ አለች ። እሱም ወደ መኝታ ክፍሉ ተንደረደረ ።

ራሄል ፣ ዘመናዊ የቤት ዕቃዎች ያሳመሩትን ሳሱን በዐይኗ ስትማትር ትቆይና ፣ ወዲያው ደግሞ ጉዳይዋ ጠቅ ! ጠቅ ! ሲያደርጋት ሰብሰብ ትላለች ።

እንደ ተመለሰ ድንበሩ ፣ የያዘውን ትንሽ ብልቃጥ ከፍቶ ቀለሙ ይህ ነው — የማይባል ፈላሽ በብርጭቆ ቀዳ ።

«ይቺን ጭልጥ አርገሽ ትጠጪና . . . ደጅ ትሮጪበ ታለሽ » አለ ።

« ለምን ? . . . ሩሜ ? » አለች—ራሄል አፍንጫዋን እንደ ማከክ አርጋ ።

«ሴትየዋ ያሉት ነዋ ! . . . 'ትንፋሿን ሳትቆርጥ ትጠጣና ትሩጥበት ' — ነው ያሉት ፣ እንቅስቃሴ ሲኖር ፅንሱ ይወጣል ። » አለ ጣቶቹን እያንቋቋ—ድንበሩ ።

«አይመርም ? » ፈራ ተባ ግለታ ያስታውቅባታል ።

«ዶሮ ግታ ፣ ዶሮ ግታ እልሻለሁ ... ስትጨርሺ ስኳር ትቅሚበታለሽ »—ወደ ጓዳ ሔደ ፣ ስኳር ሊያመጣ ።

ራሄል — ሰውነቷ ብርድ የነካው ይመስል አተር የሚያካክሉ ድቡልቡል ነገሮች ቆዳዋን ወረሯት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ድንበሩ ሲመለስ « ፈረሱም ይኸው ፣ ሚዳውም ይኸው !» ብሎ ብርጭቆውን ሲያቀብላት ፣ እፍ አሏን ያስተውል ነበር ። ከንፈሯ ይንቀሳቀሳል ፣ የምትለው አይሰማም ።

ራሄል ገና ብርጭቆውን ስትይዘው ከረሩት ። ዐይኗን ጨፈነች ። ገሞ ፣ ገሞ ... ትንፋሿ ቁርጥ ! ... ገሞ ፣ ገሞ . . . ትንፋሿ ቁርጥ ! እያልት የለ ፣ አለቀ ።

«አሁን ዕረፍት ነው ። » እሱም አብሮ የጠጣ ይመስል ዐሥራ ምራቁን ይውጣል ።

«ግን ከምንድነው የሠሩት ? » አለች ።

«ሴትየዋ 'ብዙ ነገር አለው ሲሉ' ነበር ። »

«ታዲያ አልተጠራጠርክም ?. . . ዕውነት ይሠራል ? እኔ የምተርፍ አይመስለኝም ! እግዜ ምን ትለኝ ይሆን ! »

«አይዞሽ ! ይሠራል ። በስንት ድካም መሰለሽ ይኼው ም የተገኘው ። ከኛ ጋር የሚሠራ ልጅ ነው 'ከሰዎች ሰግሁ' ብሎ ወደ ሴትየዋ የመራኝ ... 'ፍቱን ነው' ብለ ዋል ፣ አይዞሽ !» ብሎ ፣ ራሄል ከተቀመጠችበት ፎቂ በስ ተጀርባ ቆሞ «ቢቢ» አፍርሞን በዝግታ ነካካው ። በቀ ኙን ጣቶቹ እንገቷን ፣ ደረቷን አሻሸው ። ዐይኗን ጨፍና እንገቷን ወደኋላ ለጠጠችው ። ድንበሩ እጉን ብሶ ግንባሯን ሳመው ።

«ራሄል ! . . . አሁን ሩጫ ነው » አለ በሹክሹክታ። ወደ ደጅ ተያይዘው ወጡ ።

ወዲያው ዱብ ! ዱብ ! አለት — ራሄል ። የለበሰቸው የ«ጂንስ» ቀሚስ እግሯን እንደ ፈለገችው እንድትዘረጋ አላ መቻትም ።

«በርቺ ! ... ታዲያ ፈጠን ፣ ፈጠን በይበት ። ቶሎ ቶሎ እንዲሠራ ፍጥነት ያስፈልገዋል ። » አለ ድንበሩ ። ሳያመ ነታ አብሮ ሩጫውን ተያያዘው ።

ራሄል ግንጉል ትንፋሿ እየተቆራረጠ « ኡህ ... ኡህ ... ኡፍፍ » እያለች አለከለከች ።

«በይ ! ማቆም የለም ! ... ሩጪ ! » — አለ ድንበሩ ተብረክግዚ ፣ ከጉሯ እያሾለመ ።

«ደክመኝ ድንበሩዬ !... ደክመኝ ፣ ቆይ ትንሽ ልረፍ»

«የለም ! . . . እንደምንም በኃይል ሩጪበት ።»

የሞት ሞቷን ሮጠች ... ሮጠች ...

ራሄል ፣ እግሮቿ ሲተሳሰሩባት ቀጥ ብላ በኃይል መተንፈስ ያዘች ።

«ሽንት ቤት አለ ? » በተጫከመ ድምፅ ።

ድንበሩ ደስ አለው ። 'ሥራውን ሲሠራ አያደል ?' በሚል ሐሳብ «አዎ ! . . . ነይ ! »

እየደገፋት ወደ ሳሎን አመሩ ። የካ ኮረብታ አናት ላይ የመሸገው ጠጅራ ደመና ፣ ፀሐይዋን ጋርዶ ያስገመግማል ። «ዱዱ ዱዱ ... ! » እያለ ሲምህ ፣ ሰግያት ቁልቁል እየተመ ለከቱ የሚሥቁበት መስሎት ድንበሩን ፣ እንጋጦ ገላመጣ ቸው። እየሩ ስለግይንቀሳቀስ እንደግይዘንብ ርግጠኛ ነበር።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከራሄል ጋር ሳሎኑን አልፈው «እዚህ ነው—ሽንት ቤቱ» አላት። ለመግባት ቢከጅልም ፣ የምንተፍረቱን ተመለሰ። ራሄል ወደ ውስጥ ገበታ በሩን ስትዘጋ ልጥፍ ብሎ እያጻመጠ 'ወዲያ ጠራርጉ ባወጣው !' አለ በሐሳቡ። ልቡ ከበር እየደለቀ ፣ መንፈሱ ተወጠረ።

ከውስጥ ጸጥታ ነገሠ። ጭጭ ! ... እረጭ ! ትንሽ የጨርቅ መተሻሸት ሰማ። ስታወልቅ ወይም ስትለብስ መሆን አለበት። የውስጥ ሱሪዋ ተለጣጭ ላስቲክ ጫ ! . . . ጫ ! ሲል ጆሮው ቀልቅ አለ።

ተከታትሎ የሚሄጉዶጉዶው ውሃ ጀ አለ።

'ከምኔው ወጣ ? እንዲህ ፈጥኖ ? . . .' እያለ ድንበሩ ሲያስብ፡ ራሄል በሩን ከፍታ ስትወጣ ፊት ለፊት ተጋጠሙ።

«እህስ ? ... ወጣ ?»

«ደክመኝ !... ኤጭ ምን ይወጣል ? ... ሽንት ብቻ»

ድንበሩ ፣ ለከረሜላ የጓጓ ሕፃን ልጅ እንቁልልጭ እያሉ ጣሪያ ላይ ሲወረውሩበት ወሽመጡ ብጥስ እንደሚለው ሆነ።

ጀ... ጀህ የሚለው የውሃው ድምፅ ሰይጣናዊ ግለ ካካት መስሎ በሕሊናው አስተጋባ ...

«ድንበሩ !... ወደላይ ወደላይ ይለኛል ፣ ሊያስታው ከኝ ነው !... ድንበሩ ! ደረቴን ደግፈኝ ...»

* * *

ከሁለት ሳምንት በኋላ ነው።

እዚያው እነ ድንበሩ ቤት ሁለቱም እንድ ላይ ነበሩ። ድንበሩ የራሱ መንፈስ ከብድ እያለው አንዳች ነገር በሐሳቡ ሻጥ ይልበታል። ነገሩን በውል ለይቶ አልጨበጠውም።

እንዲያው የአባቱ ወደ መስክ ሥራ ከወጡ ብዙ ጊዜ ማለፍና 'ይመለሱ ይሆን ?' — የሚለው አስተሳሰብ ሸውታ ነው። ባንዳንድ አስኾኳይ ሥራዎች ሳቢያ የሚመለሱበት እይተነበይም። ይህንንም ያውቃል።

ወዲህ . . . የፅንሱ ጊዜ መርዘም ፣ ያለፈው መድኃኒት አለመሥራት . . . ያሁኑስ ? . . . ሞራሽኑ ልጅቷን ቢያጠፋትስ ? . . . በሐሳብ መዋዠቁን ቀጠለ።

እንደ ምንም ሐሳቡን ሰበሰበና ፣

« ራሄል ! ያሁኑ የመጨረሻ መሆን አለበት ... በደንብ ተጠንቅቀው የሠሩት ነው። ገንዘብም ብዙ አስከፍለውኛል። »

« አሁንማ የሚያስጨንቀኝ ጊዜው ነው። እኔ እንጃልኝ ዘንድሮ ፣ በጤናዬ አልከርምም ! እግዜ ያለውት ሮዋ ትከታተለኛለች ፣ ወይኔ ድንበሩዬ! . . . » ትለዋ ለች ራሄል።

« እይዞሽ ! እንደ ምንም እንወጣዋለን። እስካሁንም የቆየው ሴትየዋ በደንብ እንዲያዘጋጇት ነው። ከተ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ለያዩ ነገሮች ቀምመው ፣ እዋህደው ነው — የሰጡኝ ። የታወቁ ናቸው ... አትፍሪ ! ... ሳያስተግምን እይቀርም 'ዝላይ ከተጨመረበት ይፋጠናል' —ብለዋል።

« ዝላይ ? ... እኔ አልገባኝም ... ራሱ መድኃኒቱ ከሠራ ለምን ሠርስሮ እያወጣውም ? ... ባለፈው ጊዜ ነፍሴ ልትወጣ ነበር — እንደዚያ ስርጥ ...»

« እይው!... 'ሰውነት ሲንቀሳቀስና ሲናጥ ለመውጣት ይፈጥናል' ብለው ነው — የሚያምኑት ። ታዲያ እንዳሉት ማድረግ እንጂ ... ሌላ? »

ቀጥሎ ድንበሩ ከሲርፐ ጠርሙስ ውስጥ « እዋቂየ» ሌትዮ የቀመሙትን ፈሳሽ በብርጭቆ ገለበጠው ። ራሄል ጥቀርሻ መስሎ ስታየው ፈቷን አጠቆረች ።

« ዶሮ ማታ ፣ ዶሮ ማታ ! » እያለ በጣት ።

ተቀብላ ገና ሳትቀምሰው መረራት ። ድንበሩ « ጠጪው ፣ ጣጥም! ... ጥጥት! » ይላታል ። ራሄል በመ ንገሽገሽ ' እህህ' እያለች ፈቷን ቅጭም እርጋ ሠረገበችው ። ወዲያው እንደ ማቅለሽለሽ ሲሳት ሽንት ቤት ሄደች ።

ማንባሯን ጭምር በውሃ አብሳ ስትመለስ ፣

« በይ ትንሽ ቁጭ በይ ... ደጅ እንወጣለን ። » ይላታል ። እንዲያ መቸገሯ ፣ እሱን እምና ሁሉን ማድረጓ እንጂቱን በላው ።

ወደ ደጅ ሲወጡ ፣ « ራሄል ! የምትዘይቡት ወን በር ላምጣልሽ ? » ብሏት ፣ ከሳሎን ውስጥ ረዘም ብሎ የታየውን ወንበር በጀርባው ተሸክሞ ተከተላት ።

« መጀመሪያ ሮጥ ! ሮጥ ! በይ » — አለ ድንበሩ። እያት ። አላስችል ብሎት እሱም ተጨመረበት ። በራሄል ላይ ድካም ሲያንጎላብብ !

« በይ እሁን ዝላይ ነው ... ወንበሩ አጠረ ! ቆይ በርጨማ ልጨምርበት » ብሎ ፣ በራሜ ይዞ ተመለሰ ። ወንበሩ ላይ ደረበና አመቻቸው ።

« በይ ልደግፍሽና ውጭ ፣ ከዚያ መዝለል ነው ። »

ራሄል የድንበሩን ትከሻ በእጅየ ተደግፋ ወጣች ። እንዲ ዱብ አለች ። ተያዩ ። ምንም የለም ።

« ድገሚ ! »

ቁና እየተነፈሰች ወጥታ ዝርግፍ ብትለው ፣ ማሩ እንሸራታት ባፍጢሟ ተደፋች ። ጉልበቷ ተጋጋጠ ። ድንጋጤ ቢይዛትም ፣ እግሯን ወለም አላት ። ደረታ መሬቱ ላይ እንደ ተጣበቀ ባሷ እቧራውን ታመኛው ። እፍንጫየ ደም ይረጫል ። ይሄኔ ትውከቱ ሲወጥራት ማጓራት ነበር የቀራት ።

ድንበሩ እንዲህ ዓይነት እደጋ ያገኛታል ብሎ በፍጹም አልገመተም ነበር ።

« ድንበሩዬ ! ... ወይኔ ! በታ መሞቴ ነው ። ሆዴን አቃጠለኝ ፣ አቅለሸለሸኝ ፣ ድንበሩ መሞቴ ... እታ ጠለኝ ! » ስልምልም ባለ ድምፅ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ድንበሩ የደራረበውን ወንበርና በርጩማ ወርውሮ ደግፎ አነሳት ።

« ወዶ ቤት ውሰደኝ ! . . . እግዱ ? . . . »

ወንቧን ጠበቅ አርጎ በመያዝ ፣ ደገፋት ። እሷም እጅዋን በትከሻው ላይ ዘፍ አርጋ ተደገፈችው ። እንዲህ ሆነው የግቢውን በር ወጡ ። የቤት ሠራተኛዋ ግድቤት ሆና ይህን ሁሉ ትዕይንት አልተከታተለችም ።

እንድ መኪና በኮረኮንቹ ላይ እየዘለለ ክላክስ ያደርጋል ። ድንበሩ በድንጋጤ ደንዝዞ መኪናውን ልብ አላለውም ።

መኪናው በድንገት እነ ራሄል አካባቢ ሲደርስ ቆመ። ዘለው የወረዱት አቶ ገብረእግዚ ናቸው ። ድንበሩ አባቱን ሲያይ ፣ ዞረበት ።

« ምነው ደህና አይደለህም? » አሉት ።

« ደህና ። እንድ የሠፈራችን ልጅ እሷት ፣ ወደ ሆስፒታል ላደርሳት ነው ።» እንዲያው የመጣለትን ተና ገረ ። ድንጋጤ ፣ ድካም ፣ ወበቅ . . . እንድም ሳይቀር ሰፍረውበታል ።

« የምን የሠረር ልጅ ነው የምታወራው? »

« ምነው አባዬ ፣ እየነገርኩህ !— አታያትም ! . . . »

« ጉድ ነው ! የሚገርመኝ ሰሞኑን ጤና ያጣሁት . . . ይህንኑ ሊያሳየኝ ናፇል ለካ ! . . . ምን አርገሃት ነበር ? » — ከመንገድ ሲገቡ ያልጠበቁት ችግር ሲጠ መጠምባቸው — ሐሳባቸው ተመሳቀለ ።

'የምን ጣጣ ነው ! የምን ፍርጃ ነው ! ' እሱ በልባቸው ፣ ቢያንስ ባለቤታቸው ቢናሩ ልጇን « ሀይ» እን ደሚሉት በመገመት — ለቅጽበት ።

ራሄል ራሷን ስታለች ። ባፏ የሚወጣውን መቆጣጠር እቅቷታል ። ለሐዲ ተዝረክርኳል ። ባይኗን ከድና በድንበሩ ድጋፍ ነው ያለችው ። መንገደኞች ቆም ይሉና በሐዘኔታ ስሜት እየት እርገው ያልፋሉ ።

የድንበሩ አባት « ተመለስ! » ብለው ያዘዙትን « ቶዮታ ላንድ ክሩዘር » ተገላምጠው — ተከዙ ።

« ይጥት ላዝግም ፣ ታክሲ ይኖራል! » ከግሉቱ ድንበሩ ፣

« ቆይ መጣሁ! . . . ጠብቁኝ ! » ብለው ዞድንበሩ አባት በቀጥታ ያመሩት ወደ ቤት ነበር ። ፈጥነው ፊያት መኪናቸውን አስነሥተው በኮረኮንቹ ተመለሱ ። ድንበ ሩና ራሄል ሦስት እርምጃ ያህል አልተራመዱም ።

« በል እስገባት . . . ወዴት? » — እቶ ገብረእ ጊዚ ከግለታቸው ፣

« ዳግሚ ምኒልክ ሆስፒታል » አለ ካባቱ አፍ ነጥቆ— መኪናው ውስጥ ከራሄል ለጥቆ እየገባ— ድንበሩ ።

አባትየው መኪናዋን አስጋለቢት ። ያጋጣሚው ምሥጢር ባይገባቸውም ፣ በደመነፍስ የሚሰማቸው እንዳች ነገር በሕሊናቸው ውስጥ ጠጥሯል ።

★ ★ ★

http://ethioliberty.wordpress.com/

ቡናይትን ቀለም የተቀባው በር እናት ላይ « ልዩ የማ ሕፀን ክፍል » የሚል ጽሑፍ ይነበባል ።

የራሄል እናት ድምፅ አልባ እንባ ያነባሉ ። የጎባ ዘለላዎቹን በመሐረብ ሲጠርጉና አፍንጫቸውን ሲናፈጡ ብቻ ድምፅ ያሰማሉ ።

ይኸው ከሁለት ሰዓት በላይ ጠብቀዋል — ራሄልን ለማየት ። በልባቸው ያልተማፀኑት ታቦት የለም ። እያንዳ ንዱ ደቂቃ ጭንቀታቸውን የሚያባብስ እንጂ ፣ የሚቀንስ አልሆነላቸውም ።

ዐሥራ ሁለት ተኩል ላይ የድንበሩን የስልክ መል ዕክት ሲሰሙ ነው — ሆስፒታል ለመድረስ የተቅበዘበ ዙት ። የራሄልን ማሕፀን ክፍል መግባት ሲጎነዘቡ ፣ እፋ ቸውን ደም ደም አላቸው ። መንፈሳቸው ተናጋ። ዞረባቸው። ሞት የሚያንጎራብብ መሰላቸው ። ከሲኦል ሠራዊት ከበባ የጣሯለተ ትንትንት ተሰማቸው ። ሞትን በምን ተአምር እንደሚያባርሩት ውሉ ጠፋባቸው ። ሰው በተላለፈ ቁጥር መርዶ የሚያረዳቸው አርነው በመገመት — ተሸማቀቁ ።

ድንበሩ በድንጋጤ ደርቋል ። እጁን አጥፎ የበሩን ጽሑፍ ይመለከታል ። ጭው ያለ ሐሳብ ወስዶታል ። አግዳሚው ወንበር እያለ መቀመጥ አልታየውም ። አባቱ ቁጭ ብለዋል ። ካንገታቸው አቀርቅረው '...ምን ይደረግ ! ቤቱ እንደው ባዶ ነው !... ያቺ ሴት ብትኖር እንዲህ አል የረድም ነበር ...' እያሉ በሐሳብ ይቆጫሉ ።

በሩ ተከፈተ ። ነርሷ ገባች አለች ።

« ግቡ !.. » እንዳለች ፣ የራሄል እናት ድንበሩን ገፍተ ረውት ገቡ ። ተከትለው የድንበሩ አባት ገቡ ። ራሄል ነጩ አንሶላ ላይ ተኝታለች ። የሕክምና መሣሪያዎች ከበዋታል ።

« ራሄል ! ... ራሄል ! የኔዋ ራሄል አለሽ ? »

« አዎ ! ... አለሁ እማዬ !» — በለሆሳስ ።

« እንግዲህ ምንም አያስቡ ... በርግጥ ጠዋታው የጎበረሙ ፈላሽ ሆዷን አውኳታል ። ግሕፀኗንም አይ ተን ጠራርገነው ነጻ ሆኗል ... ሰሞኑን ሆስፒታል ስት ቆይ ሙሉ ጤናማ ትሆናለች ... ጭረምሳው ! » በማለት ለራሄል እናት ማጽናኛ ተናግሮ ፣ ቀጥሎ የድንበሩን ትከሻ መታ መታ አርጎ የወጣው ፣ የቅዳሜው ተረኛ ዶክተር ነበር ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አርትእት

ጠዋት ነው። ወደ ቢሮዬ ስገባ ለምን እንደ ገረመኝ አላውቅም ... ምስትልትሉ የወጣ ትዕይንት ስለሚታየኝ ይሆን? ... እናንተስ፣ ቢሯችሁ ተለዋውጦ አስገርሟችሁ ያውቃል?

... የሥራ ጠረጴዛዬ በመጽሔቶች፣ በወረቀቶች፣ በመዛግብተ ቃላት ... ከምር ተጣቧል — በነዶ እንደ ተሞላ አውድማ። በስተግራ ወደ ጣሪያው የሚንጠራራው የመጸሕፍት መደርደሪያ ተተራምሷል። የሲጋራ መተር ከሻው ወመድ ብቻ ነው። የተረከስኳቸው ሲጋራዎች ተጻፍኖ ያደረ እንጨት መስለዋል።

የመሥሪያ ቤታችን ቢሮዎች የሚጸዱት በምሳ ሰዓት በመሆኑ፣ ቢሮዬ አልጸዳም። ሆኖም ትላንት በውስጡ ሆኜ ያላየሁትን ዛሬ ዘው ስል፣ መልሼ እየሁት። ቢሮዬን ታዘብኩት።

...እንዳንዴ ራስን መልሶ ማየት ማለፊያ ሳይሆን አይቀርም!... ታዲያ ስልኩ እየረበሸኝ ...

«ሃሎ!... አቤት ...»

«ሩፋኤል ነህ?»

«አዎ!»

«ያለፈው ወር ፅትማችሁ ላይ ... ማስታወቂያችንን በደንብ አላወጣችሁትም። ቅር አሰኝቶናል ... ቀለሞቹ ድብልቅልቅ ብለዋል፣ የሥዕል ጉዳይ ስለሆነ ምንም መስህብነት አላገበት ... ካጣ መጠየቃችን አይቀርም!»

«ከየት ነው!... ማን ልበል?»

«ከአርት ጋለሪ ነው።»

ፀአ! ከተበብ አለቆች ነው፣ መጅስ የአርቲስት ወይን የቀላ አይደለችም ... ለማድነትም ሆነ ትንጣት መዛነፍ ሰመን ቀስ አትመለስም!»

«ዝም እንል ነገር ቸገረን! ጥሩ ካልወጣልን ብዙ ደምበኞች ማፍራት እንችልም። ይህን መገመት አያዳግት ህም!»

«ይገባኛል! ዕውነት ነው! ችግሩ የማተሚያ ቤት ሆኖ ብን ነው ... ቆይ እስቲ ... ይኸው እንዲያውም መጽሔቱ ሬት ለፊቴ አለ ... ገጽ ፵፯ ላይ ይታየኛል ... ብዙም አያስታውቅም ... ማለቴ ... ይቅርታ ለማናቸውም — በሰው ሙያ እንዳልዘባርት ... ይሁንና አስተያየታችሁን እቀበላለሁ፣ አመሰግናለሁ።»

«ቢሆንም አስቡበት... መጽሔታችሁ በሁሉም ረገድ ድንቅና ተነባቢ ነው። በዚህ ብቻ እትኩራራ። በወዳጆቻችሁ ዘንድ ትገመቱና ደግ አይሆንም»

«እሺ፣ አመሰግናለሁ ... ሁኔታውን ለ'ኑሯችን' ቦርድ አቀርባለሁ»

ስልኩን ዘጋሁት። ወ... 'ይ ጉ... ድ! ትንሽ የቀለም ንጥብ ከመስመሩ ብትወጣ ወቀሳው ይጉርፋል! ሠዓሊያን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ድሮውኑ ስሚታቸው ስል ነው ። ዐይናቸውማ ምን ይጠ
የቃል ? . . ግን ፅውንታቸውን ነው።ደሀና አርገው ካላስተ
ዋወቁ ሥዕልም ሆነ ቅርፃ ቅርፅ ማን ይገዛቸዋል ?

... አውንስ ሲጋራዬን ጨርሻለሁ መሰለኝ ...በጠ
ዋት ግዛጋት ... ኡህህህ ... ኡህህህ ...

እቪ ! ትላንት የት ነበር ያቆምኩት ? ... እ .. ... እ
ዮየሞነዱ' መጣጥፍ ላይ ነው ። እሱ ደሞ ጥሱበት የብ
ፅር ስም ይወዳል . . . እስቲ ጽሑፉን ቢያስተይበው
ምን እለበት ? . . . ስንት ገጽ ነው . . . ሁለት ሦስት
እራት ... ጥሩ... እም ... «እዋር መግቢያ» ይላል . . . እ
. . . እም . . . አሁን አሁንማ 'ሞነዱ ' ሊቃላት ደን
ታቢስ ሆነ ። እይመርጥም ፣ እያማርጥም ። ደንቅር ፣
ደንቅር ፣ ንባብ ያውላል . . . የዛሬ እንባቢ እንደሁ
ተለውጧል ። ተመጥኖ የተከሸነ ፣ በተመረጡ ቃላት የታ
ነፃ ጽሑፍ ነው የሚፈልገው—የዘመኑ እንባቢ ።

እኔን የሚያስቀኝ 'ሞነዱ' ኪሐያ ዓመታት በፊት
የተሸለመውን የሥነ ጽሑፍ ሽልማት ዐሥራ እየጠቀሰ
«. . .ያኔ ድሮ ፣ ኤስመንተሪ ብትሆን ነው ። ያኔ ነው
ደንቅ የተባለውን ድርሰት የደረስኩት ፣ ምኑን እንግር
ሃለሁ—ታውቀዋለህ ። ማሽነፈንም እትርሳው . . .
ታዲያ አሁን የምሰጥህን ጽሑፍ ላዘጋጅ ስንቱን ዐውዶ
ጥበብ መሰለህ ያገላበጥኩት—የትየለሌ ነው ። በየላይብ
ረሪው' ስዞር እግሬ ነቃ ! . . » ይለኛል ።

ምን ልመልስለት ? ፊእቪ» ከማለት ሌላ እግራሞ
የለኝም ። በግድ ወትውቶ 'አንተ በለኝ' ያለኝን እባት

ጸሐፊ ማስቀየም ይቻላል ? . . . እያልኩ ይሉኝታ ገባኝ ።
የ'ሞነዱ' ሽፋንም ፣ መክራከሪያውም ያው የጣጉት ሥራው
ነው . . . ከወቅቱ ጋር ካልተራመደ ምኑን ይራቢ ተባለ ?

የብዙዎቹ ጽሑፍ አትራቢዎች ጉጉት ላት ያለ ነው ።
ከሚያነኙት የድርሰት አበል ባሻገር ፣ ድንቅ ሥራዎች
ካቀረቡ—ተመርጠ ወደ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ተተር
ጉም ፣ በመጽሔታችን ይወጣል ። ለውጭ ገበያም ይቀ
ርባል ። በዚህ መታወቅን ሁሉም ይፈልጋሉ ።

መጽሔታችን በውጭ ሞምር ተፈላጊነት ማግኘቱ
ገሃድ ነው ።

. . . እቪ ! ስልኩ እንሶ የቢሮ—ለቢሮ መገናኛው
(ኢንተርኮም) በርጋታ ለማሰብ ጊዜ አይሰጥም . . . ውጥ
ረት ብቻ !

«ሩፋኤል ! »

«እቤት ። »

«ብቅ በል እስቲ ፣ ደህና አደርክ ? »

«ደህና ! እቪ . . . »

የአሊቃ ጥሪ—የማልጋፋው ነው . . . እዚያና እዚህ
በመባከን ጊዜው ካለቀ ፣ የመጽሔቱ አርትኦት (ኤዲቲ
ንግ) ሥራ መቼ ይሠራ ይሆን ?

አሊቃዬ ቢሮ ደረስኩ ።
« ሃይ ! » አልኳት—የአሊቃዬን ጸሐፊ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የይ ሩፍ ! »

«ደሀና ነሽ ? »

«አለሁልህ ፤ ደሀና ነህ ወይ ? »

«ደሀና»

«ጠምህ ከሲጋራ ቃጠሎ እምልጪልና ! ምናለ ሲጋራውን እርግፍ አርገህ ብትተወው ? 'ሲጋራ ግጪስ ያጨሳል ! ' እያልክ ግን ትጽፋለህ »

«እንቺ ደግሞ ከኔ ጢም ምን አለሽ ? . . . ዘለሽ ጢሜ ላይ መጠምጠም ነው የሚቀናሽ ፤ ስለሲጋራም መተቸት ጀመርሽ ? እም . . . አለቃሽ ፈልገውኝ »

«ምን ጥርጥር አለው ። ሰው ዐይኑን ካልፈለገ ግንን ይፈልጋል ? . . . ግን ፥ የምልህ መቼ ነው ጢምህን የም ትላጨው ? »

«እንቺ ጸጉሯ ወርዶ ! ወርዶ ! . . . ስትሆኝ ነዋ ! » አልኳት ። ከርዳዳው ጸጉሯ ከአናሮ ሴላ እንደግይሆን ዐውቃለሁ ። በሸቀች ።

«እንዴ ? ይጠብቁህ የለ ! እግርህን ይገርአለሁ— አትገባም ? ! » አለች ከንፈሯን ጥላ ።

እንኳኩቼ ገባሁ ።

«ሩፋኤል ! ግባ ። ብዙም አላቆይህም ። ለዛሬ የሚ ደርስ ጽሑፍ እንድታዘጋጅልኝ ነው የፈለኩህ ። አያስ ቸግርህም—አንድ ገጽ ነው ። ሆኖም የተጨመቀ ፍሬ ነገር ያስፈልገዋል» በማለት አለቃዬ ፥ ካቀረቀሩበት ቀና ብለው የወፈረ ሰውነታቸውን በሂርባቸው ዘኩል ጣሉት ። ጎሽከርካሪው ወንበር ላይ ።

ያህ ፥ ጸጉራቸውን በቀኝ እጃቸው እያሻሹ ፥

«ቁጭ በል ! » አሉኝ ።

«የለም ፥ ግዴለም ! . . . ርዕሱ» ብዬ ከደረት ኪሴ የማይለየኝን ማስታወሻ ደብተር ከእርሳስ ጋር አወጣሁ»

«ልንግርህ እይደል ፤ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በቋፅ ኛው ምዕተ ዓመት የሚል ነው ። ለምሥራቅ አፍሪካ የሥነ ጽሑፍ ኤክስፐርቶች ነው— የማቀርበው . . . ነገ ወደ እሩሻ እበራለሁ . . . እንድ ገጽ ብቻ . . . »

«ባንድ ቀን ? ለዛውም ለክፍለ— አህጉር ኤክስፐር ቶች የሚቀርብ ? . . . የትና እንዴት ? ብዬ ። ጥራት የሚኖረው እይመስለኝም ። በሴላ በኩል የዚህን ወር ዕትም ረቂቅ አጠናቅቄ ፥ ማተሚያ ቤት ማድረስ አለ ብኝ ፤ ገና ጽሑፎችና ዘገባዎች እጠብቃለሁ . . . የመጽ ሔቱን የጎትመት ጥራት ደግሞ ይምበኞቻችንን ቅር እያ ሰኝ ነው . . . ቀድመው ቢነግሩኝ ኖሮ »

«ሩፋኤል ! ለነገሩማ ልክ ነህ ፥ መልዕክቱ ለእም የደረሰኝ ከትላንት ወዲያ በመሆኑ ነው ። መነሻ ሐሳብ የሚያስጨብጥ ጽሑፍ ነውና እያዳግትህም . . . እስከ ግቃም ቢሆን እድርሰው ። የውጭ ጽንቋ ተርጓሚዎች ቆይተው እንዲሠሩት ይደረጋል ! »

በቆምኩበት ለደቂቃዎች አቀረቀርኩ ።

«እሺ ። እስቲ እያለሁ»—በለሆሳስ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«በል ጀምረው ... አንድ ገጽ »

በሩን ዘግቼ ስወጣ ፣ ጸሐፊዋ ስልክ ይዛ ነበር ። የተሰጠኝ ትዕዛዝ የማይታይ ሽክም ነውና እጅጉብሽ ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ ።

ያለኝ ጊዜ ውሱን ነው ። የያዝኩትን እርግፍ እርጌ እዲሱን ትዕዛዝ ስለ መፈጸም ማሰላሰል ጀመርኩ ። ለጽሑት ምንጭና መረጃ ያስፈልገኛል ። በስተግራዬ ያለው መጽሐፍ መደርደሪያ ለዚህ ጉዳይ የሚያስፈልጉትን መጻሕፍት አልያዘም ።

ስልክ መታሁ ።

«ሃሎ ! ... ሃሎ ! ... ኦፐሬተር ! እባክሽን ግስ ታወሻ ያዥ ... ወመዝክር ፣ ኪኔዲ ቤተመጻሕፍት ፣ ብሪቲሽ ካውንስል ... ሌላ ማን አለ ? በየተራ ደውልሽ እንናገኝ ... የኛ ቤተ መጻሕፍት ኃላፊ ... ማነች ... ወይዘሮ ደስታን ጥሪልኝ ... »

«እሺ ... » አለች ። ቅር እንዳላት ያስታውቃል ። እኔም ፈጌ አይደለም ፣ ጸሐፊዬ ፈቃድ ባትወጣ አላስ ቹግራትም ነበር ።

አንድ ወዳጄ ስለ አለቆች ብልጠት ያጫወተኝ ትውስ አለኝ ። አለቆች ምን ያደርጋሉ ? ... ቀድመው ፣ የሚያሠሯቸውን ሠራተኞች በደንብ ያጠናሉ ። ንቁና ብሩህ የሆነውን ይለያሉ ። ከዚያ የደመወዝ ጭማሪ ያደርጉለታል ። ዜቃ ! ከዚያ እያዘዙ ሲያሠሩት ፣ ሲያጣድ

ፉት ይኖራሉ እለኝ ። በኔም ላይ ይኸው 'ቲዬሪ' ሊሠራ ይሆን ? መቼ ነው የደመወዝ ጭማሪ የሰጡኝ? ... እምስት ወር ሞላው ?

ይህን ሳውጠነጥን ነው ፣ በር የተንኳኳው ።

« እቤት ... ይግቡ ! »

ቀይ ወጣት ነገር ፣ ሲፈራ ሲቸር ገባ ፤

«ምን ልርዳህ» ጠየትኩት ። ሳወጣ ሳወርድ የቆየሁትን ወደ ጉን እርጌ ፣ ልጄ ላይ እፈጠጥኩ ። ታዲያ የሥነ— ጽሑፍ ሙያተኛ ትኩረቱን ካንዱ ወደ ሌላው እየቀያየረ መንፈሱን ካላደሰ ፣ ሌላ ምን ከሐሳብ ጭን ቀት ማምለጫ ዘዴ አለው?

« እጭር ልቦለድ ጽፌ እምጥቻለሁ ! » የልጄ እፍ ጠባብና ግንባሩ ሰፊ ነው ።

«እና ? ... »

«አይታችሁ እንድታትሙልኝ ነው ... ክፍያው ንም » የቆዳው ልስላሴ የሴቶችን ይመስላል ።

« ገባኝ ! ... ገባኝ ! የምትለው ... ለመሆኑ አጭር ልቦለድ ምንድነው ? »

«ለኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ... አጭር ልቦለድ ለመ ንፈስ ብርታት ፣ መዝናናት በሚወሰድ እንክብል የሚ መሰል ነው ... እስፕሪን ፣ ቫይናክ ብቻ አይደሉም ለራስ ምታት የሚሆኑት ። መንፈስ ሲወጠር ፣ ድካም ሲያጠቃ ፣ ሐሳብ ሲበተን ... አጭር ልቦለድ ፍቱን መድ ኃኒት ነው » ፈቱን ይደባብሳል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እም ! ... ከየት እገኘሽው ? ጥቅስ ነው ወይስ ... ?»

«የለም ከራሴ ገጠመኝ ያወጣሁት ነው ። ራስ ምታት ይሁን ሌላ የመንፈስ ውጣ ውረድ ሊይዘኝ ፣ ፈውስ የማገኘው ወይ የጻፍኩትን ሳነብ አሊያም የተጻፈውን ስይዘው ነው ። »

«ብዙ የሠራኽው አለ ማለት ነው ? »

«ብዙም አይባልም ... ይህ ግን የተሻለ ስለ መሰለኝ ለናንተ ማቅረቤ ነው ። መጽሔታችሁን 'ኑሮችን' አገር ሁሉ ያደንቀዋል »

«እሺ ። በል እድራሻህን እዚህ ቅጽ ላይ ሙላና ሒድ! ጽሑፉን ስጠኝ ! ... »

እም !... የዋዛ አይደለም። በኛ ዘንድ ወጣቶች እንዲህ ደፍረው አይመጡም ። እስቲ ይታያላ ! ምን እንደጸፈ »

መሸቷል ።

ከግቢያችን ውስጥ መኪናዬን አቆምኳት ። ስወጣ የመኪናዬን በር በጣም ወረመርኩት ። 'አውንስ እርይ ልበል እንጂ—ያለታቡን ትፅዛዝ ከፈጸምኩ ፣ ሌላው በተራው ይደርሳል !'— አልኩ ለራሴ ።

ባረግመዴ መንገጻገድ ነው የቀረኝ ። ሳምሶናይት ቦርሳዬን ይዤ ወደ በረንዳው የሚያወጣውን ደረጃ ስቆጥር ፣ የመወላለት ያህል ተሰማኝ ... ልብ የሚያ ጠፋ ድካም አድትቆኛል ።

የሳሎኑን በር ከፍቼ ገባው ። እናቴ እንደ ወትሮዋ ጹካዋ ላይ ፣ ምቾት እንዲሰጣት ጨርቅና የበትሉ ግላስ የመሰለ ትራስ ጉዝጉዛ ፣ ተቀምጣለች ።

«ምነው አልመሸም ዛሬስ ? » አለች ፣ ዐይን ዐይኔን እያየች ። እርጅና ተሟጭኗታል ። እኔን እንደ ልጅነቴ የምትመለከተኝ ይመስለኛል ... ልጅ ያው ልጅ ነው— የሚሉት ዓይነት ።

« እንዴን አስገብተህ ትዳር ብትይዝ እንዲህ እንደ ልብህ ማምሸት የምትችል አይምሰልህ ። ሚስቴ ፣ ልጀቼ እያልክ በጊዜ ትሰበሰብ ነበር ።»

የሳሎኑን ወፍራም ምንጣፍ ተረግምጂ ከሶፋው ላይ ተቀመተኩ ። ሰዓቴን ስመለከታት ለእራት ዐሥር ጉዳይ ትላለች ። ' ኡፍ ! ... ' ብዬ ፣ ፊቴን በጀቼ ደባበ ስኩና በጀርባዬ ተንጋለልኩ ።

« ወይ ልጀ ! ... ይህ ብቸኝነት አክንፎ ጉድ እን ዳያረግህ ። በጊዜህ ዕወቅበት ። እህቶችህን አታይም ! ... ቤት እሠራለው ፣ ዕታ እደራጀለው ስትል ፣ ጊዜ ቀድ ሞህ እየበረረ ነው ... በጥሩንባ የሚታጀበው ሠርጎኛ ሁሉ ቤት ሠርቶ የሚገባ መሰለህ ? እናቴ ወይም አባቴ ላይ ተዳብሎ ነው!»

እናቴ በቀላሉ እንደማትለቀኝ ዐውቃለው ። ለወ ትሮው የእን ትዳር መመሥረት አንሥቶን ፣ አብዝተን እንነጋገርም ። ለርዕሱ መንገድ ካገኘች ግን አትመለ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ስም ... ስለዚህ የምትለውን በጥሞና ማዳመጥ እመ ርጣለሁ »

«በትድሚያ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን እንቺም ታውቂዋለሽ ... ደግሞ እያስቸኩልም ማለቴ ነው » » ብዬ ከመናገሬ ቀለበችኝ ፣

«እንዲህ ነው ! ... ጸጉርህ እንኳ ሁለት ቀለም አው ጥቷል » ታዲያ ከዚህ በላይ ምን ትጠብቃለህ ? »

« እምልሽ ፣ ዓመት ወይም ሁለት ዓመት ... »

«አም! ይህንኑ ስትደጋግም ትኖራለህ ፣ እኔም የማ ያልቅ ዓመት እቆጥራለሁ » ሰውነትህን ታዘበው እንጂ » ቢሮ ... ቢሮ ስትል ራስህን ጥለህ ዐረፍክ ፣ ሱሪህ እን ዴት እንደ ሰፋብህ አይታወቅህም ? ... 'ጉድ !' የሚያ ሰኝ ነው » አሁንማ ፣ ጸምህ ፊትህን ሊሸፍነው የሕፃን ማስፈራሪያ ሳትመስል አትቀርም!» ብላኝ ፣ መሐረቧን አውጥታ «አህ ! ... አህ ! » እያለች ፣ ሳለች »

በርግጥ በዕድሜዬ ሠላሳ ሁለተኛውን ይዤአለሁ » ለምን ሽበት በዝቶ እንደ ወረረኝ አልገባኝም » ' ... በዕ ድሜዬስ ምን ቀም ነገር ሠራውበት ? '— ጥያቄው ለራሴ ነው ... ብናገር ሦስት ልቦለዶቼ ናቸው » ሌላው ትርኪ ምርኪ ፣ እፍ የሚሞላ አይደለም »

« ስማኝ 'ጊዜ ሲያመልጥ— ጸጉር ሲመለጥ አይታ ወቅም' ... ተው ! ግዴለህም ! »

« እሺ » ስል መለስኩኝ »

« ስልክ ተደውሎልህ ነበር ፣ »

« ከየት ? »

« ከውጭ ነው » »

«ካዲሲባ ውጭ ? »

« እም ! »

« መልዕክት የለም ? »

« መልሰው ይደውላሉ ፣ እንደሱ ነበር ያሉት» አለ ችኝ »

የጠዋቱ ልጅ ፣ «ጽሑፌን በመጽሔታችሁ እት ሙልኝ. . . » ያለው ፣ እንዲያው ነገረ ሁኔታው ሲከነ ክነኝ ውሏል » የጸፈውን ለማንበብ ፋታም አላገኘሁ » እሁንስ ባየው? ...

«ስልኩ እየተጣራ ነው » አለችኝ እናቴ » የስልኩ ድምፅ ስለሚቀነስ « ክርርር ! ... ክርር!» ይላል— እንደ ሙዚቃ »

ተንደርድሬ እጀታውን እንሣሁት »

'እሽሽሽ ...ሽሽ ...' በሚል ድምፅ መሐል «ሃሎ ! ሃሎ !» አልኩኝ »

«እቶ ሩፋኤል ! ... የረጅም ርቀት ጥሪ ነው— ከጋ ምቤላ! » አለችኝ እጥፌተሯ » ' ... ደግሞ እዚያ የላክ ነው ሪፖርተር ማነው ?'— በሐሳቤ ሳወጣ ሳወርድ መስ መሩ ተገናኘ »

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ሃሎ ! ... ሩፍ ! ... ሩፍ ! ታዲያስ !» ከወዲያኛው ጫፍ ሰማሁ ።

«አቤት ! . . . አቤት ፣ ግን ልበል ?» መለስኩኝ ጮክ ብዬ ።

«ገረመው ነኝ ፣ ኪጋምቤላ ... እንደምን አለህ ?»

«እ ገረመው ! እዚያ ነህ ለካ ! ታዲያስ ! ... ሙቀቱ እንዴት ይሏችኋል ?» ... እንዴ በተመሳሳይ ሥራ ሔጂ በሙቀቱ ምክንያት የመጀመሪያውን ሌሊት መተኛት ያቃተኝ ታወሰኝ ።

« ይኸው ተያይዘነዋል ... ሙቀቱ አይነገርም ። ዘገባውን ግን በተለምር ለዚህ ወር ዕትም ለማድረስ ተደፍተንበታል ። »

«ጥሩ ! ጥሩ ነው ... አሁን ምን ልርዳህ ?»

«ሩፍ ! ... የልማት እንቅስቃሴውን በከተማው ተዘዋውረን አይተን ጨርሰናል ። ያነሣናቸውን ፎቶግራፎች ብታይ ድንቅ ናቸው ። አሁን ወደ ገጠሩ ስለምን ወጣ ባለቀለም የፎቶግራፍ ፊልም ያስፈልገናል ። ለፊልም ክምችት ደግሞ የቪዲዮ ፊልም ማግኘት አለብን ። አራዊት በያይነቱ ይገኛሉ— ብለውናል ፣ በተጨማሪ ያገሬውን ኑር እንቀርፃለን ... ይታይሃል አይደል ?»

«አም ! ... ገባኝ ፣ ታዲያ እኔ ምን ላድርግ ? ንብረቶችን ጠዋት ብታናግራቸው አይሻልም ?»

«ሩፍ ... እያወቅከው ? ሳምንት ይተኙበታል ፥ ይልቅ ነገውኑ እንተው ብታስጨርስልን ? ... ቢቻል በአውሮፕላን ብታስልከው— የልባችን በደረሰ !»

«እንዴ ! ነገ ?... ነገ በየትኛው ጊዜዬ ነው ይህን ሁሉ ተለምር የምሠራው ገረመው ?»

«ሩፍ እንዶ ምንም ብለህ አድርገው ። ምን አለ በለኝ ፣ በዚህ ወር ጋምቤላን በዘገባና በፎቶግራፍ እንሸፍናታለን ። . . . ሄይ ሩፍ! ደግሞ ያንተ መጽሐፍ ጉዳይ ። መጪረሻ ያባተምከው 'ናቭል'— 'ጥንቸሸ' እን ባቢውን አተራምሷል ። ቢቻልህ ተጨማሪ ትኂምችን ላክ !... የያዝኩትን ሦስቱንም መሰዬብኝ ፣ ይገርምሃል !»

«እኬ ... እሞክራለሁ ።»

ስልኩን ዘግቼ፣ወዶ ነበርኩብት ተመልሼ ተቀመጥኩ።

«ነገ ወዴት ሒድ ነው— የሚሉህ ?... ምን ዓይነት ጣጣ ነው ?... ያ ይድነቃቸው ፣ የወይዘሮ አስካለ ልጅ ፣ ታውቀዋለህ ? ... እሱ ልጃቸን ፣ ሚስቱን ይዞ ከቤቱ ንቅንቅ ብሎ እያውቅም . . . ካዲሳባስ መች ወጥቶ ያውቃል ? አንተስ እንደሱ አደብ ብትገዛ ምናለ ?»

«የለም ! ... ጋምቤላ የሚገኝ የሥራ ባልደረባችን ነው ። ለሥራ የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች ላኩልኝ ብሎ መጠየቁ ነው ። እኔ እንደከታተልለት ፈልጓል ።»

«እስብብት» አለችኝ ፣ «ኡህ ! ... ኡህ !» እያለች በመሐል ... እና ይህ ጠዋት የመጣ ልጅ . . . ከሐሳቤ

http://ethioliberty.wordpress.com/

አልጠፋም ... ይሄ ሳምሶናይት ደግሞ እርጅና ጀም ሮታል ልበል! ለመከፈትም አስቸገረኝ »

«ሌራቴ ይትረብ!... አውን እንኳ አረፍ ብትል ... ከባሞው ውሃ ሞቆልሃል » እናቴ ነበረች »

«እሺ እደርሳለሁ » ብዬ ፣ የተተየበውን የልጄን ጽሑፍ ፊት ለፊቴ ጠረጴዛው ላይ ወረወርኩት »

መጽሐት አዘጋጅ ፣ የምትሠቃይ ነፍስ ነው ያለው » ስለ መጽሐቱ ግግር ሌት ተቀን ሲጨነት ፣ የሚያቀርበውን ሲያሰላስል ፣ የቀረበለትን ሲያርም (አርትእት ሲያከናውን) ምን ጊዜ ለራሱ ያስባል!... እኔስ!

«አባት» ይላል ፣ የወጣቱ ጽሑፍ— ርዕስ » የዚህ ዓይነት አርዕስት አወጣጥ የራሱ ድክመት አለው » ታሪኩን አጠቃሎ ያመለክት ይሆናል ፣ ግን መስህብነት ፣ ድብቅነት ፣ አመራማሪነት ፣ ሐሳብ ተንኳሽነት እንዲኖረው ጸሐፊው መጠበብ አለበት ... ይሁን እስቲ! ይነበብ »

* * *

በዚያች ደግት ከተማ ጥቂት ቆይታ ያደረገ— ትዝ ታዋን አይረሳውም » ነዋሪው ይካለባል » አየሩ ይጋፋል » ሞት ያለ እንቅስቃሴ የከተማዋ መታወቂያ ነው » የልብ ምቷ ንግድ ነው » ንግድ!... ንግድ!... ትንሹ ትልቁ! ዐዋቂው ልጁ ሁሉ!

ከነዋሪዎቹ መካከል ፣ መንታ ሴት ልጆች የወለዱ ፣ በዕድሜ የገፉ ጉልማሳ ይገኛሉ » ሪዛቸው ሽበት ብቻ ነው » ንግግራቸው ረጅምና ምሳሌ ይበዛበታል »

ባለቤታቸው በሞት የተለዩት ፣ መንትዮቹን ተነ ላግለው በሳምንቱ ነበር »

ታዲያ እኒህ መንትዮች ፣ የናትም ያባትም ፍቅር ያገኙት ከአዛውንቱ አባታቸው ነው »

አባት ግንዘብ ይወዳሉ » ልጆቹ ነፍስ ከግወታቸው እንሥቶ ሊላላኩ ፣ ጥቃትን ሸቀጥ በገበያ ሲሸቅጡ ነው— ያደጉት » ላባቸውን እንጠፍተፈው ፣ ወተ ተው ወርደው ፣ ገበያ መሐል ሮጌው ያገኟትን ለአባታቸው ያስረክባሉ »

አባት በፈናቸው ግንዘብ ያበድራሉ » ይደልላሉ » በምላሹ ግንዘብ ይሰበስባሉ » ይሀን ቂጥረው ፣ ሚጋባ ቤታቸውን አሻሽለዋል » የዘወትር ሕልማቸው ግን ባቅራቢያቸው የሚመለከቷቸውን ቁጩር ነጋዴዎች መብለጥ ፣ ካልሆነም በሀብት መስተካከል ነው »

መንትዮቹ ልጆች ፣ በትምህርት ያልገፉ ነገር ግን በባሕርይ ፍጽም ተቃራኒ ናቸው » «ኮረሪማ» እያሉ በትጽል ስም የሚጠሯት— ብልህ፣ በድርጊቷ ፈጣን ነች » ንግግሯም እንዲሁ » እንድ ነገር ካደረገች ፣ ፍጻሜውን ለማየት ትቸኩላለች »

መንትየዋ በጣም ትለያለች » ጭምት ፣ ዝምተኛ ፣ በድርጊቷ ሁሉ ቀስስተኛ ነች » እትበሳጭም » ባንጻሩ የሚያስደስታት የለም » ረዥም ጊዜ አቀርቅራ ብትቀ መጥ እትሰለችም » ገበያ ሸቀጥ አውጥታ ይሠረትባ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ታል ፣ እንዳንዴ ቤት የምትገባው ባዶ እጅዋን ነው ። ትፈላለች ...

እባት ይህ ሲፈጸም ግልፍ ይላቸዋል ። ይቆጧ ታል ። በስድብ ይወርዱባታል ። እሷ ግን እትገነዘብም ። እባት ፣ ወዲያው መለስ ይላሉ ። ተፈጥሮዋን እያወቁ ስለ ተናገሯት ይጸጸታሉ ። ልባቸው በሐዘን ይሞላል ፤

« ሰዎች! 'ዮናት ሆድ ጌንጉርጉር' የሚባለው ዕው ነት እይደል? » በግለት ይተክዛሉ ።

የከተማው ሰው መንትዮቹን መለየት አይችልም ። ሲበዛ ይመሳሰሉብታል ። እባት ለልጆቹ ልዩነት አላደ ርገም በግለት ልብስ እንኳ ሲያሰፉላቸው ባንድ ዓይ ነት ቀለምና ባንድ ቅድ ነው ።

ኮረሪማን የተዋወቀ ሌላኛዋን ሲያገኝ ፣ ልቧን ሲያ ደርቅ ይወላል ። « ... ረሳሺኝ እንዴ ? ተዋውቀን እል ነበር ? ይሀን ይሀን አልገዛሁሽም ? ... » የማያልቅ ወቀሳ ይደረድራል ። ኮረሪማም በተራዋ አይቀርላትም ። «ያን ሰውን ፈጀሽ ነበር ፣ እሁን ምን እግኝተሽ ተቅለበ ልብሽ ? ... » ሲሉ ይወርፏታል ።

እንድ ቀን ፣ እባት በወለድ ያበደሩትንና ያተረፉ ትን ሲያሰሉ ፣ ኮረሪማ ስትከንፍ ደረሰች ።

« እባ ... ባል እገኘሁ ! » ትንፋሿ ይቆራረጣል ።

« ምን? ... ምንድነው የምታወራው ? » እንዳቀረቀሩ ነው ።

« ባል እገኘሁ... ላገባነው ፣ » ናንድትድት እያለች ።

« ከገበያ ነው የገዛሽው ?... ደግሞ እንቺን ግን ያገባል?» ብለው ማሰላታቸውን ቀጠሉ ። ኮረሪማ ፣ ችላ ስለተባለች እየተቆናጠረች ወደ ቤት ገባች ።

ትንሽ ቆይቶ ፣ እባት ስሌቱ ላይ ግተኮር እታታቸው። የልጃቸው ንግግር ኮረኮራቸው ። ስለ ባልና ፣ ልጆቻቸውን ስለመዳር አስበው እያውቁም ። እሁን ግን ሐሳባቸውን ጠቅ !... ጠቅ ! የሚያደርግ አዲስ ጉዳይ ገጠማቸው ።

« ኮረሪማ !... ኮረሪማ !... ነይ ልጄ! » አሉ ፣ በተ ዘበራረቀ መንፈስ ።

«እቤት!... እባ!» ብላ ስትመጣ ፣ ደስታ ከፊቷ ላይ ያበራል ።

«ምንድነው ነበር ያልሺኝ ?»

«ባል ላገባ ነው ... በጣም ሀብታም ነጋዴ እገ ኘው ። ቤቱ ወስዶ ጋበዘኝ ። ሀብቱን ሁሉ አሳየኝ ። 'እወድሻለሁና እንጋባለን' አለኝ ፤ እኔም እሺ አል ኩት ። »

« ወይ ጉድ ! ባንድ ጊዜ ነው— ይሀን ሁሉ የሚቶ ባተረው ? »

«እይደለም ፣ ... ለካ እኔ ሳላየው እሱ ሲከታተለኝ ቆይቷል ። ለንግድ ወዲያ ወዲህ የሚዘዋወር ነው ። 'እንቺ ብልህ ስለሆንሽ ሀብቴን ትጠብቂልኛለሽ' ብሎ ኛል ... እባ ታድ'ዬ ! ሀብታም ሰው ላገባ ነው ! »

« እሺ ! ... ነገ ወስደሽ ታስተዋውቂኛለሽ ፣ »

http://ethioliberty.wordpress.com/

በማግሥቱ አባት ከቁሸሩ ነጋዴ ተዋወቁ ። ሀብቱ በቁና ይታፈላል ። ያከማቸው ጌጣጌጥና ገንዘብ መጠን የለውም ። አባት በዕውን ሳይሆን በሕልም ዓለም ይኖሩ ይመስል ማመን ዐቃታቸው ። ነጋዴውም በልዩ መስተ ንግዶ ጋበዛቸው ።

የሠርጉ ዝግጅት ተጀመረ ። የከተማው ታዋቂ ሰዎች ሳይቀሩ እንዲገኙ ተደረገ ።

አባት ከሠርጉ ዕለት በፊት ፣ ቁኮራማ ! ዘመድ ጠያይቀሽ ተመለሽ!» ብለው ወደ ገጠር ላኳት ። በእጅ እዙር ሰው አስልከው ፣ ወር አከረሚት ። ሰበብ ሲሰጡ «እሟታልና ጠበል ያስፈልጋታል— ቢታገሥላት!» ነበር ያሉት ። ኮረራማ ፣ «ሠርጌ !... ሠርጌ!» እንዳለች ከረመች።

መንፈሷ ደፈረሰ ።

«ሩፋኤል !... ሩፋኤል ! ምን ነካህ ? እራት እኮ ቀር ቦልሃል !» እናቲ ባለቀ ቅዕግሥት ተናገረችኝ ። የመባ ነን ያህል ነው—የተሰማኝ ።

«እፍ !... መሸ !... በቅድሚያ ብታጠብ ይሻለ ኛል ፣ ኋላ እበላለሁ ። እሁን ትንሽ ነው የቀረኝ ። »

«በል እንደ ፈለክ ...»

ኮረራማ ወሩን ጨርሳ ተመለሰች ።

«እባ !... ምን አረኩህ ? ምን በደልኩህ ? ለምን ሠርጌን አበላሸህብኝ ? ... እሺ ብለህ አልነበር ሠርጌን የተቀበልከው? » እያለች ተንሰቀሰቀች ።

«በይ ጉዳዩን ተመልከቺበት ... ሀብታቸው ብዙና አማካዩ ... ኮረራማ ! አንቺ ንቁ ፣ ብልጥና ዘዴኛ ነሽ ። እህትሽ እንደምታውቂያት ክርፍፍ ትላለች ። ስለዚህ በጣም ታሳዝናለች ። እሷ ባል ፈልጋ ታመጣ ለች ማለት ዘበት ነው ... አይደል ? አስቤ ፣ አስቤ ... አንቺ ያመጣሽውን ለሷ ሰጠኋት ። እና እሷ ሰውየውን እንድታገባ አደረኩኝ ። አንቺ ሌላ ብትፈልጊ አታጪም ፣ እሺ ? አየሽ !... ለእህትሽ እዘኝላት ። ሰውየው ያመጣው ጥሎሽ ቀላል አይምሰልሽ !... ላንቺም ይሰጥሻል » ብለው ... አልማዝ ፣ ዕንቁና በርካታ ገንዘብ አሳዩዋት ።

ልባቸውም የበለጠ እርካታ አገኘ ። የረኹም ጊዜ ምኞታቸው ዕውን መሆኑ ፣ ምቤ አስረገጣቸው ። ቤታ ቸው ፣ ግቢው ... በልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ተሟላ ።

ኮረራማ አለቀሰች ። ለብዙ ጊዜ አለቀሰች ። ሐዘኗ ቶሎ አልወጣላትም ። በዚህ ሁኔታ ዓመት አለፈ ።

አባት ቅልቅ ንግድ ለመክፈትና ለከተማው ለግ ሳየት ጥድፊያ ይዘዋል ።

ኮረራማ ብርታት አንሣት ። ብልጠቷና ሩጫዋ ቀነሰ ። ተስፋ መቁረጥ አሸንፋት ። ግቢያ ዞር ፣ ዞር ስትል አንድ ቀን ፣ ትንሽ ግብዣ አታለላት ... ጉድ ሆነች !

በከተማው የታወቀ ፣ የለየለት ሰካራምና ቁማርተኛ ነበር ያስረገዛት ። አከታትሎም «ሳይዋረዱ ልጅዎን ይስ ጡኝ !» ሲል ለአባት አግላጅ ላከ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

አባት አላትማሙም ። ስማቸውን ለመጠበት ሲሉ ፈቀዱ ። እየቆረቆራቸው ከገንዘባቸው ቆንጥረው ደገሱ— ለኮረሪማ ።

የኮረሪማ ባል ፣ ከትዳሩም በኋላ በጠባይ ምንም ለውጥ አላመጣም ። ይሰክራል ፣ ይቆምራል ። ገንዘብ ያጠፋል ። በዚህ ከአባት ጋር ብዙ ተጻርቧል ። እንዳንዴ አባት ደም ብዛታቸው እየተነሣ ሌት እንቅልፍ ያጣሉ ።

አንድ ቀን ምሽት የኮረሪማ ባል ሲጠብት ቆየ ። መሽቶ ፣ ሌሊቱም ተጋመሰ ። « እውንስ ለይቶለታል ... እዚያው ግደሩ ነው » ብለው አባት ወደ መኝታቸው አመሩ ። ኮረሪማም ልጅዋን አስተኝታ ተኛች ።

ንጋት ላይ የዘረ ድምር ደም እያስተፋው ፣ ግራ ቀኝ እያስረገጠው ደረሰ— የኮረሪማ ባል ። አባትና ኮረሪማ ከደጃፍ ቆመው ነበር ።

« ኮረሪማ !... ኮረሪማ !... ቤቱ ፣ ይሄ ቤት ... በቁማር ተበልቷል ፣ » ከማለቱ ባሏ ፣ አባት እየተንዘፈዘፉ በረንዳው ላይ ተዘረሩ ።

ደማቸው ቀዘቀዘ ... ልባቸው ሥራውን አቁሟል— አባት ።

* * *

እም!...አይከፋም ። ነጻ ፈጠራ ነው። ቁም ነገሩ መካሪ ነው ። ቅርው ሊስተካከል ፣ ርዕሱም ሊሻሻል ይችላል ።

« አሁንም አልጨረስክም?» አለች እናቴ ፣ ከመኝታ ቤቷ ወደ ሳሎኑ ተመልሳ ። ዘርፋፋ የሴሊት ልብሷን ለብሳለች ።

« ውሃው ከሞቀህ ዘመን አልፎአል ። ይልቁ ታጠብ . . እራቱን እንደሁ— ትተኸዋል ! ወይ አበሳ !»

... ታዲያ የልጄ ጽሑፍ ፣ መታተም ይችላል!... ወይስ ... ባሞ ቤት ገባው ... ውሃው እንዴት ደስ ይላል ... ውሃው ....

http://ethioliberty.wordpress.com/

መከተ ዐዋቂ መሆን በእጅጉ ያጓጓዋል— ከሁሉም ። ታዲያ ፎዚያ የምታመጣቸው ጥያቄዎች ብዙ ነገር እንደማያውቅ መሰከሩበት ። «እንዴት እላውቀውም ?» በሚል ግፊት ፣ ተስፋ ባለመቁረጥ መፍትሔያቸውን ፍለጋ ይፍጨረጨራል ። በሐሳብ ይወጣል ፣ ይወርዳል ።

ለፎዚያ ጥያቄዎች ምላሽ ፍለጋ ራሱን ማስጨነቁ ፣ «የለም! እንዴትስ!» ስትለው መከራከሩ እርካታ እንደሚሰጠው የተገነዘበው ዘግይቶ ነው ።

መከተ ፣ ያሥረኛ ክፍል ተማሪ ነው— በእንጦጦ አጠቃላይ ። ብዙ ጓደኞች የሉትም ። አይጥትም ። ፎዚያ ፣ ከመርካቶ የምትመጣዋ ነች የምትቀርበው ።

«ፎዚያ! ጥያቄዎቹን ከየት ነው የምታመጪው ?» ሲል— ይጠይቃታል ። እፉ ለምዶበት እንጂ ፣ ያውቀዋል ።

«ስንቴ ነው የምነግርህ ! የሒሳብ አስተማሪያችን የሚያመጣው ጥያቄ ነዋ! ሒሳብ ያስተምረንና እስቲ እዕምሯችሁን አሠሩት እያለ ጥያቄዎቹን ይዘረዝራቸዋል ። »

«እ . . . ሺ ! ይሁንልሽ ! »

«ትቀልዳለህ ! . . . ሲያገባባን ፣ ምን ይላል መሰለህ ! 'ማትሪክ ለመውሰድ ምን ያህል ጊዜ ቀራችሁ ! ሁለት ዓመት ነው ፣ አይደል ? በል ! ... ከአድማስ ባሻገር ለማየት ፣ ዕውቱት ለመንጠየቱ ፣ ጥያቄዎች ውሰዱ !' ይለናል ። እኔ ግን እሱ የሚያመጣቸው ጥያቄዎች ማት ሪክ ላይ ወጡ ሲባል አልሰማሁም ። »

ፎዚያ ፣ ዐሥረኛ ክፍል ብትሆንም በ «ሴክሽን» ከመ ከተ ትለያለች ።

እነዚያ ከባድ ጥያቄዎች ሲነሽጡት — መከተ— የማወቅ ጉጉት እናቱ ላይ ያናዋራል ። « ከፎዚያ ጋር እንድ 'ሴክሽን' በሆንኩ » ይላል— በልቡ ።

«ለሁን መልሱን አትሰራልኝም ? » ትላለች ፎዚያ ።

«እንዴት ? ... እንቺ ተጠይቀሽ እኔ ምንድነኝ ? » መልሱን ለመሞከር እየተሽኮረመመ ።

«ሒ ... ድ ! ለምኑኝ አታብዛ ! ለነገሩማ እኔም እሠራ ዋለው . . . ግን አንተ ምን እንደተሰማህ ለማወቅ ነው ።»

« ባይሆን እንዳንድ ሐሳብ ካገኘሁ ፣ ጠያይቄም ቢሆን ልሞክርልሽ ! . . . »ይላል ፣ ሁል ጊዜ ሳትሰለች የምታስጠናውን የታላቁን ታላቅ እህቱን እያሰበ ። ባያውቀውም የእህቱ እንባቢነት ፣ ሁሉን ዐወቅነት መን ፈሱን ተጭኖታል ።

«አስተማሪያችንም ያለው ይህንኑ ነው ! 'ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ተማከራችሁ ፣ መልስ እምጡ' ነው ያለው ። »

«ጥሩ . . . ይሁንልሽ ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

እንድ ቀን ጠዋት — በዕረፍት ሰዓት ነው ። ተማሪዎች በሜዳ ላይ ይተራመሳሉ ፤ በመናፈሻ ይናፈላሉ . . . ወዲያ ወዲህ ሲሯሯጡ ፣ ድምፃቸው ከፍ ብሎ ይሰማል ።

ፎዚያ እየቦጠች ፣ ወደ መከተ ከፍል ቀረበች ።

« ታዲያስ ! »

« አለና ! ምንድነው ሩጫው ! »

«ባከህ የዛሬውን ጥያቄዎች . . . ልነግርህ ነው »

« እንቺ ! ! . . . ማቴማቲክስ መግር አቆማችሁ ማለት ነው ! »

«አቦ ! እኔ ምን ላርግ ! አስተማሪው ያበዛዋል . . .»

«ይሁንልሽ ! . . . ቆይኝ ከከፍል ወረቀት ላምጣ » ብሎ ማስታወሻ ደብተሩን ይዞ ተመለሰ ።

« በል ታዘ ! . . . ልንደኛ ለምን ከሁለት በላይ የጾ ታዎች ግይነት አይኖሩም ! . . . ሁለተኛ— ድመት ለምን ልጇቿን ትበላለች ! . . . ሶስተኛ— ዓለም ትጠፋለች ወይ! መቼ ! . . .አራተኛ— ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ወይ ! እንዴት ! »

«ይሄ ሁሉ ! . . . ከባድ ናቸው ! »

«በል ሊደወል ነው . . . » ብላው ፣ እየበረረች ተመ ለሰች ።

' . . . ለነገ ከሰዓት እምጣው ሳልለው ፣ ' አለች ፎዚያ በቅሬታ— ከዋል ስትገባ ።

በመጨረሻ ፣ ሰዓት ደርሶ ተማሪዎች ተለቀቁ ። መከተ ወደነፎዚያ ክፍል ለወትሮው ዐይኑን ጣል እንደ ሚያደርገው ፣ ዛሬም ልግዱን ለማድረስ ቆሞ አለ ። . . . ወደሱ ስትሮጥ አያት ።

«መከተ ! ሳልነግርህ ፣ ነገ ጂት 'ከላስ' አልመጣም ። ያስፕታል ለጥርሴ ቀጠሮ አለኝ ። ስለዚህ ከሰዓት በኋላ ታመጣልኛለህ ፤ ምክንያቱም ከነገ ወዲያ መልሱን እምጡ ብሎናል . . . »

«ለዛውም ለነገ ! . . . ጥያቄዎቹ ከባድ ! »

በመደንገጥ መለሰ ፣ መከተ ። የፎዚያ የላይኛው ከንፈር ለምን ጥርሷን መሸፈን እንዳልቻለ ምላሽ ያገኘ ይመ ስል ፤ እፍ አሏን ያያል ።

«አቦ ! አንተ ልጅ ! . . . በናትህ ! አያስቸግርህም »

«እሺ ፤ ይሁንልሽ ! »

«የት ታመጣልኛለህ ! »

«ሠፈራችን ነይና ውሰጂያ— ካዛንችስ »

«አቦ ! ትቀልጻለህ . . . ይልቅ አራት ኪሎ ከም ትወደው ሻይ ቤት ጠብቀኝ— በዘጠኝ ሰዓት »

«እሺ ! ይሁንልሽ ! »

እየተነጋገሩ በትምህርት ቤቱ ዋና በር ይወጣሉ ።

ተማሪዎቹ ይተማሉ ። ውካታው የቅቤ ገበያን ያስ ታውሳል ። ጉን ለጉን ተቀጣጥለው የመንገደኛ ሰንሰ ለት መሥራት የሚተናኙው እንዳንድ ሴቶች አሉ ። ለማት ይቸኩላሉ ። ግን ! ይሁን ግ ! ከተናገረ መሳት

http://ethioliberty.wordpress.com/

ነው » የፈረንጅ ሥዕል ፣ ሙዚቀኛ ፣ ኪስ ተጨዋች ፣ የል
ብስ ሞዴል አስተዋዋቂ . . . የተለጠፈበት ይብተር
መያና ፣ በትከሻ የሚነገት ስልቻ መሳይ ቦርሳ . . .
ከንዚያ ሴቶች አይለይም » የዘንቢል ቦርሳው . . .
ሹራብ ፣ የፎቶግራፍ አልበም ፣ መቀየሪያ 'ቲሸርት'
ሳይቀር ስለሚይዝ ይመርጡታል »

. . . አለባበሳቸውን ልብ ብሎ ያጤነ ፣ ይገረማል »
ለሌላ አይደለም » ባሕር ማዶ ገበያ ያጣበበው ፋሽን
ሳይዛነፍ በኒያ ልጆች ላይ መታየቱ ነው »

ታዲያ ልጆቹ እንደ ኤሊ ከተንቆረበሱ ጨዋታ
መረሊጋቸው ፣ መጣጣት እንዳሻቸው ያስታውቅባቸ
ዋል » 'ጣት የደስታ ምንጭ ነው ' የሚል ሐሳብ ገፀ
ይላቸዋል »

. . . እንዴ ሙክ ብላ ትናነራለች . . .

«ልጆቹዬ ታያላችሁ ! . . . እዮት ያን ልጅ !
ሊያመልጣችሁ ነው . . . በዚያ በኩል » እጅዋን እንደ
ቀጭን ማስመሪያ ቀስራለች »

«እያችሁት ! ! ሱሪውኮ ተቀዷል . . . »
የመከተ ጀሮ ወሬዎን ቀለበው »
«እህህህ ! . . . ኢሂሂሂሂ ! » ያስካካሉ »
አጠር ያለችው ቀጠለች »
«ጥቁር ፓንቱ' ኮ ብልጭ ብልጭ ይላል »
ሌላዋ ትቀበላለች ፣

«መርሌ የጨው ፖ . . . ኒ . . . ቱ . . . »
«ኃጢአት እታውሩ ! . . . ላውንደሪ አስገብቶት
ቀደውበት ይሆናል እንጂ ፣ ሌላ ምንም አላረገም » »
«ኢካካካ ! . . . ኪኪኪ ! . . . »
«ሁላችሁም አላወቃችሁም . . . ' ዩ ኢድየትስ ! ' በሕ
ልሙ ሸርተቴ ሲሜወት የቀደደው ነው » »
«ኢሂሂ ! . . . »
ባለተራዋ ታዳንታለች ፣
«እስቲ ይሄ ምስኪን ምን አረጋችሁ ! . . . መጀ
ለሱ ይሆናል ! »
«ለዚህ ነዋ መዘነጡን የወደድሽለት ! ለሱ ጥብ
ቅና የቆምሽለት ! » ዐይኗን እያሸሞ ትጠይታለች
«ኪ ኪ ኪ ! . . . ኪ ኪ ኪ ! ! »
«ለዚህ ነዋ ! ሞጋ ሜማ አርገህ ፣ ረጅም መፋቂያ ሰክ
ተህጸንርህን ጣሳ ቁርጥ ተቆርጠህ፣ ከመቀመጫህ የተቦደሰ
ሱሪ አርገህ ፣ ፒያሳ አውጣኝ ያልሽው»ተደርባ ታፈላለች»
ይሥቃሉ . . . .
«እዩልኝ በናታችሁ . . . ያቺኛዋን ! የውስጥ ልብሷ
ረዘሞ ፣ ተንዘርፍፏል »
« . . እ ? ያቺ ! ብታያትኮ '
እልም ያለች ፋራ ! ነች » ጤባ ! . . . ቀለም ግን
ፖ ! አስተማሪያችን ካለሷ አይጠይትም ! »
«ግርጻሜ ሱሉ ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የእግሯ ወፍረት ! ኡ ! ደዘደዝ ነች » »

«ደንደሳም . . . ይሄን ሊጥ ትጋት ፣ ትጋትና . . .» ያሥታቸዋል »

«እያሃሃ ! . . በሃታውን ትገለብጠዋለች በይኛ . . . ኪ ኪ ኪ ኪ ! »ይሥቃሉ »

«ትሰሚያለሽ እነዚህን ጅሎች ! » መከተ ወደ ርዚያን የጉንኖሽ እየተመለከተ ይነግራታል »

«ይጫወቱዋ ! . . . ጊዜያቸው ነው » ዕኩል ፈጥና እየተራመደች ፣ ትመልስለታለች »

«እንዴት ! . . . ከተቸገረ ቤት የሚወጣ ልጅ የሚለብሰው ያጣ ይሆናል ፣ እ ! እና ልብሱ ተቦተረፈ' ብሎ አታቂር ግውጣት— መጫወት ነው ! »

«ታዲያ ፡ ልላ ምን ያውሩ ! »

«ይውጋልሽ ! . . . ግን ብዙ የሚጫወቱበት ቁም ነገር አያጡም— በደንብ ካሰቡበት ! »

«ካልፈለጉስ ! . . እንተ ምድነህ ?»

«እእ . . . እኔ ? እም ! ምንድነኝ ? »

ርዚያ ቀይ ፊቷን ታሻሻለች » በጥድፊያ እልም . . . እልም የሚሉትን ተግሪዎች ባይኗ ተከትላለች »

«ስሚ ! »

«እቦ እንተ ልጅ ! ስም አለኝ— ምን ነካህ ! »

«ርዚያ»

«እቤት»

«ቆንጂ ሱሪ አርገሻል »

«ወይደ'ከው!» በቢጫ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ወይን ጠጅ፣ ሰማ ያሮ ... ቀለሞች የተንቆጠቆጠው ሱሪ ደምቆ ይታያል »

«ረቂት ሥራ መሆን አለበት !» ባድናቆት የተለ ማቱን ጎብረት ያጠናል »

«ምንም ጥርጥር የለውም ! ለወንድ አይሆንም እንጂ ታረገው ነበር » »

«እንዲያውም እስታውሽኝ የምታስጠኝ እህቴን ሞከሪው እላታለሁ » »

«አንተ ! እቦ አታፍርም ? . . . ትገርግለህ ? የአ ደሬ ሱሪ አርጊ ልትላት ? »

«ነውር አለው ? »

«እንጂ ! »

«ይልት ያልገባኝ እግሬ ጠባብ ለምን ሆነ ? »

«አታይም ! . . . እንደልብ ያራምዳል ፣ አያደናቅፍም ፣ እንደ ቤልቦተም ነው— ኤሌፋንት እርስ በርሱ እየተጣፋ እግር አይጠልፍም » »

«ይህ የምትይኝን የሚታየኝ ነው » ኧረ ዱሮ . . . ለምን እንዲህ ተሰፋ ? »

«እንጂ ! »

«ጠይቂና . . . ትነግሪኛለሽ ! »

«እቦ እንተ ልጅ ! የነገን እንዳትረሳ ! »

«እሺ ! ይውጋልሽ » »

* * *

http://ethioliberty.wordpress.com/

የመከተ እያት ድምፃቸውን ከፍ እድርገው ይጣራሉ ።

«መከተ ! . . . መከተ ! ምንድነው የምትሠራው ? »

በረንዳ ላይ ወንበር አውጥተው ዐረፍ ብለዋል ።

«እቤት እናዬ ! . . . እዚህ ነኝ » ጣሪያ ድረስ እየ ጮኸ ይመልሳል ።

«ተው እንተ ልጅ ! እዛትህ የሌለችበት ከቢቷ እትገባ አላልኩህም . . . እሁን የሰው ዕቃ መቀስቀስ— ደግ ነው ? ነውርም አይደል ? »

መከተ ትልቋ እህቱ መኝታ ቤት ገብቶ ዕቃዎቿን እንዳይነካ ተነግሮታል ። ሆኖም ከባድ ጥያቄዎች ከትምህርት ቤት ይዞ ከመጣ ፣ ሐሳብ የሚሰጡትን መጻሕፍት ፍለጋ የእህቱን መለስተኛ « ቤተ መጻሕፍት » ይጐበኛል ።

መኝታ ቤቷ በጣም እይሰፋም ። ባንዱ ግድግዳ በኩል ባለ እንድ ትራስ አልጋዋ ተዘርግቷል ። ከዚህ ትይዩ ፣ ተገጣጣሚው ባለብረት መደርደሪያ በመጻሕፍት ተጨናንቋል ። በግድግዳው ማዕዘን በኩል የተነባበሩት ካርቶኖች በመጻሕፍት ተሞልተዋል ፤ የጅምላ ሱት ሽቀጥ ይመስላሉ ።

«እንተ ልጅ ! እሁንም አልወጣህም ? የምታንኮሻ ኩሽው ይሰማኛል ! »

መከተ መስኩቱን ባለመዝጋቱ እየበሽቀ ይመልሳል ።

«እሺ . . . ልወጣ ነው ፤ ይሁንልሽ ! »

«ምን ትሠራለህ ? »

«የቤት ሥራ ተሰጥቶኝ ነው ። »

«ታላቂያ ቤትህ ዝብተህ እትሠራም »

«እናዬ ! እንቺ ደሞ— መጻሕፍት ፍለጋ ነው ። »

«ደሞ ከእህትህ ዕኩል መሆን እግረህ . . . በል እንዳግረብህ ውጣ» ልብስ ሲሰፉ ቆይተው ፣ የዛሰ ክንዳቸውን ያፍታታሉ ። ብዙም ሳይዘልቁበት እጽርጠው ወደ ሂርና ቢመርጹም ፣ በቀድሞው የእቴጌ መነን ልጃገረዶች ትምህርት ቤት የተማሩትን የልብስ ስፌት አልረሱትም ። ሲመቻቸው ይጠቀሙበታል ።

ዐይናቸውን ፊት ለፊት ካሉት እበቦች ላይ ጣል አርገው ፣ የባጥ የቆጡን ያስባሉ ።

መከተ ለፎዚያ ጥያቄዎች መልስ ያመነጫሉ ያላቸውን መጻሕፍት ለየና ወደ መኝታ ቤቱ ይዞ ገባ ። ወዲያው የእህቱ ቁጣ ብልጭ አለበትና መጻሕፍቱን ይዞ ተመለሰ ። ከመጻሕፍት ማዋሻው ይብተር ላይ ፣ እርዕስ ስታቸውን መዘገበ ። . . . እህቱ ማስታወሻ ላያስፍር የሚነካባትን እንደማትወድ ያውቃል ።

አጠቃላይ ዕውቀት ከሚያስጨብጡት ፣ ቀልድና ቁም ነገር ካጣመሩት እንሥቶ እስከ ፍልስፍናና ኑክሊየር ፊዚክስ ድረስ መጻሕፍት በያይነቱ አሏት ። ሁሉንም ለማወቅ ታነባለች ። የምትችለውን ትገዛለች ። በየወሩ ወጪ ማድረጓን እያትየውም ሲረዱ ፣ ታዝበዋል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

‘ምን ነካኝ ነው ፤ የምትለው ? . . . በዚህ የጉሮ ውድ ነት ይሄ ሁሉ መጽሐፍ ተገዝቶ— ይቻላል ? ወይስ መጽሐፍ ተሰብ ይሆናል ? ወቸ ጉድ ! ’ ይላሉ በልባቸው ።

መከተ ያነባል ። ጠጠር ያሉ የእንግሊዝኛ ቃላት ሲያጋጥሙት ፣ መዝገበ ቃላት ያገላብጣል— የግዴን ። ገጼን ገለጥ . . . ገለጥ ሲያደርገው ከምብል የሚልበት ይመስለዋል ፣ ከብደቱ የብረት አሎሎ ያህል ስለሚሰማው ። የፊደል ተራውን ለማግኘት . . . ወደፊት . . . ወደኋላ ሲገልጥ መሰልቸት ይከጅለዋል ። ‘ላንድ ቃል ምን አለፋኝ ! ’ . . . የሚል ዓይነት . . . ‘እንዲት ! ግወት አለብኝ ’ . . . ግንላበጡን ይቀጥላል ።

. . . ጥቂት እንዳነበበ መሸ ።

እዘውትራ ከምሸቱ እንድ ሰዓት ላይ የምትገባው ትልጃ እህቱ ፣ ከእያታቸው ጋር ስታወራ ሰማት ።

«ደህና ዋላችሁ ? . . . እናቴ ታዲያስ ? » ነው መነጽሯን እያወልቀች ።

«እንደምን ዋልሽ ልጄ ? » ይላሳግሉ ።

«ምነው— ብቻሺን ? . . . መከተ አልመጣም ? »

«ኧረ ንብቷል! . . . ወረቀትሽን ሲያተራምሰው ነበር ።»

«ሊያጠና . . . ነው ዓለምሽት አልገባችም ? »

«ቅድም ደውላ ‘አመሻለሁ’ ብለላች . . . »

«ምነው ? በደህና ? »

«ነገ ፈረንጅ ሀገር የሚሔድ ሰው እሸኛለሁ ብላ ለች . . . የሷ ዓይኖች ሔደው አያልቁ ! »

«እ ! . . . እናቴ ! በይ ግቢ ። ብርድ እየመጣ ነው ። »

«እሺ ። » ከኋላ ሰጥቀዋት ገቡ ። ‘ . . . እንዲህ ከሲታ ትሁን ? ’ ይላሉ ፣ ቅጥነቷን ባጤኑ ቁጥር ። ምክ ብለው ይጣራሉ ።

«መከተ ! . . . መከተ ! »

«እቤት እናቴ ! »

«ደቻት እህትህ . . . »

«እሺ . . . ይሁንልሽ ! » መከተ እመር ብሎ ተነሣ ። «የይ መከተ ! »ትልቋ እህቱ ዐይኗን ስታሻሽው—ቀላ።

«ባክሽ . . . እንድ ጥያቄ አስቸገረኝ ! » ተከትሏት ወደ መኝታ ቤቷ ገባ ።

«ግነው ? ‘እንድ ጥያቄ አለኝ ’ የሚል ዓምድ በጋ ዜጣ ያዘጋጅ የነበረ ? እሱን አትጠይቀውም ? »

«ትትልጃለሽ »

«ና ! . . . ሲሪየስ » ቦርሳዋን ከጥናት ጠረጴዛዋ ላይ አስቀምጣ— አልጋዋ ላይ ተንጋለለች ። የራስጌዋን መብራት ቀጭ ስታደርገው፣ ይብላላ ብርሃን ወደ ኮርኒሱ ታ አለ ።

«መስኩን ዝጋው ! »

እየዘጋ ፣

«የሆኑ ጥያቄዎች ነበሩ . . . ግን ከባድ ናቸው ። ደግሞ ለነገ መድረስ አለበት ። » መስኩን በጀርባው ተደግፎ ዐይን ዐይኗን ያያል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«መከተ ፤ ባለፈው ሰሞን የምታመጣው ዓይነት ነው ?»

«እያ» ጉንበስ ብሎ «ጀንትራ» የተስተካከለውን ጸጉሩን እከክ ያደርገዋል ።

«እንዴ ? እንዴት ነው ነገሩ ? . . . ለዐሥረኛ ክፍል የወጣ 'ካሪኩለም' አለ አይደል ? በርግጥ ለጥያቄዎቹ መልሱን ብታውቅ ጥሩ ነው . . . ግን ለክፍልህ የሚመጥነው ዕውቀት ሳትይዝ ፤ እዛም እዛም ብትል ዋጋ የለውም ። »

«እያ !»

«ታዲያ ይሄን ስታሳድድ ፤ ዋናውን ጥናት መቼ ልታጠናው ነው ? »

«እሱማ አጠናለሁ . . . እነዚህን ጥያቄዎች እስ ተማሪዎቹ እየሰጡን ነው ። 'ስለ አካባቢያችሁ ዕውቁ' እያሉ ነው» የፎዚያን ነገር ማንጣት አልፈለገም ። 'ለሰው የቤት ሥራ ከምትሠራ— የራስህን አታጠናም ?' ብላ ትቆጣኛለች ሲል ገምቷል ።

«እኪ ! በኋላ እንነጋገራለን »

መከተ ደስ አለው . . . መልሱን ሲነነዘብ ፤ ሲገባው . . . ለፎዚያ ሲያስረዳት . . . ሲከራከሩ . . . ሊያሳምናት ምላሴ ሲደረድር ውልብ አለው ።

ወደ ንባቡ ተመለሰ ። አቀርቅሮ ሲቆይ ድካም ይሚሚነዋል ። እግሩን ያንቧቧራል ፤ ይደነዝዘዋል ። ጠረጴዛው ላይ በክንዶቹ ይመረኮዛልና ጉንጮቹ ይገታተራሉ ። ከመሰልቸት መንፈሱ እየታገለ ፤ ሐሳቡን ወደ ጥያቄው ለመመለስ ይጥራል ።

ኪችን ጉድጉድ ያሉት እያት ፥ ከማሱን ይጣራሉ ። «የሻሽ ወርቅ !» የትልት እህቱ የቤት ስም ነው ።

'እናዬ! ለምንድነው በስሟ የማትጠሯት ? . . . ለምን የቤት ስም ትወዳለች? እኔ የለኝም ! . . . ማሙሽ ሲሉኝ ቆይተው ትተውታል ! ' ለራሱ ይጠይቃል ። . . ወደ ንባቡ ይመለሳል ።

«እቤት እናዬ ! » ትልት እህቱ ።

«ተኛሽ እንዴ ? እራት ደርቧል ! . . . ታጠቢና ነይ ። እህትሽ ስትመጣ ትደርሳለች . . . ዘዋሪ ! » እሉ የመጨረሻውን ቃል ሲናገሩ ድምፃቸውን ሰብረው ።

«እሺ ።» ወደ ባሻ ቤት ታመራለች ።

እናትና አባታቸው አብረዋቸው አይኖሩም ። ሦስት ልጆቻቸውን ለእያትየው ሰጥተው፥ብቸኛነትን መርጠዋል። በጥላቻ አይደለም ። እያትየው ብቻቸውን እንዳይሆኑ ነው—የሚያናግር እንዲያገኙ ። በዚህ ላይ የእያትየው ቤት ሰፈ በመሆኑ ፤ ልጆቹን እንዳመላቸው ይችላቸዋል ፥ ተብሏል ።

እራት ይበላሉ . . .

«ቅድም ያልሺውን ረሳኸው ፥ ጥያቄዎቹን »

«እንግዲህ ጀመርክ ! አላስቆም አላስተምጥ ነው —እንብላበት ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

ላመል ቢናገሩትም ፤ እሁቱን አከብሮ ያልገባ ውን በመጠየቁ ቅር አልተሰኙም ።

«እይ ቀላል ጥያቄ ነው— እሷ . . . እንድታስረዳኝ ብዩ ነው ! » በልመና ድምፅ ይናገራል ።

«ቀላል ከሆነ እንተው አትመልሰውም ! ምን ልጊን ታወልቀዋለህ ? ! »

«እናዩ እንጂ ደሞ ! ትንሽ ብትረዳኝ ምናለበት ። . . . እንዲያውም ይውንልሽ ! »

ልቡ የቆመበት ጥያቄ ባለመመለሱ ፣ ወስፋቱ በወጉ አልተከፈተም ። ሆኖም 'እራት በቃኝ ! ' አላለም ።

«ምን ያድርግ እናዩ ! መጠየቁ እይከፋም ! እስተ ማሪያቸው ጥያቄ እየወረወረ— እንዲያስቡ ሲያደርጋቸው ነው ። » እያቷን ለማግባባት ትናገራለች ።

«እኔ ምለው ! ለምን እዚያው እስተምሮ— እዚያው መልስ አይሰጣቸውም ? . . . የምን ሰው ማስቸገር ነው ? »

«እንደሱማ የት ይሆናል እናዩ ? ልጆቹ እንዳይ ሰንፉ በማሰብ ነው . . . ጥናቱ ቢይዛቸው አይሻ ልም ? አይመስልሽም ? »

መከተ ያዳምጣል ።

«ወይስ እንደ እትዩ እዛለች ልጆች ፣ ባቡር መንገድ ይገተር ነው— የምትይው ? »

እሁቱ ደግፋው ስትከራከር— መከተ— የልብ ልብ ተሰማው ።

«እሁን አሁንማ የሚገርሙ ልጆች ሆነዋል ። ጠዋት ስወጣ— ከዚያ ከኦሪ ሱት ተኮልኩለው አያቹ ዋለው . . . አሁን ስገባም እዚያው ነበሩ ። አምባ ጓሮ ፈጥረው ነው መሰለኝ ፣ ሲዉዉው ነበር ። »

«ፅውንትሽን ነው . . . ከነሱ ቢገጥም ሰውም አይ ሆን ! . . . ታዲያ ልጆቹም የሚያደርጉትን እጥተው ነው ።»

እየተጫወቱ ይጮርሳሉ ፤ አያትየው ወጥ ላነሰው ይጨልፋሉ ። እንጀራ ለሌለው ይተካሉ ።

«እየሽ ልጂ ! አዲሳባ አይመችም . . . በልጆቹ ለመፍረድ ያስቸገራል . . . የት ይሒዱ ? ምን ያርጉ ? እንደኛ ቢሆን ምንም ችግር አልነበረም ። ሂርና— ከተ ማው ትዝ አይልሽም ? . . . ገጠሩን ትረሺዋለሽ ! እዚያ የምንሠራው እናጣም ! ልጆች ያርሳሉ ፣ ያጭዳሉ ፣ እንጨት ይሰብራሉ ፤ ውሃ ይቀዳሉ ፤ ይላላካሉ . . . ምን ጊዜ እርፈት ተገኝቶ ! ! »

« ለነገሩማ— እዚህም ቢታሰብበት ብዙ መሥራት ይቻላል ? »

«ወሬውን ግን ያዳምትሳቸዋል ? » ድምፃቸው ከፍ ብሎ ይሰማል ።

«ጋሼ ግረልኝ ተሻለው ? . . . እማዬ ጠየቱቻቸው?» አያቷን ትጠይቃለች ።

መከተ በሐሳቡ ወደ ጥያቄዎቹ ተመልሷል ። መም

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጀቱንና የኢያንዳንዱን ጥያቄ ግብራሪያ በቅጡ ለመረዳት የሚወስድበትን ጊዜ እያሰላሰለ ፣ '... ታዲያ ምን ላርግ ልሽ ? ጊዜ አልቢታኝም ... ብትፈልጊ ለነገ እሞክራለሁ— እላታለሁ ለፎዚያ ! ደሞ የኔም የቤት ሥራ አለ ። ጣጣ !' ለብቻው ያወጣል ፣ ያወርዳል ።

ያያቱ ንግግር ቆም ማለቱን ከማየቱ ፤

«እንዴ ጥያቄ ' ኮ እያስቸገርም ። » የትልት እህቱን ዐይን ዐይን ያያል ።

«ምንድነው ? » ከተቀዳላት ውሃ እየጠጣች ።

«ድሙት ልጂቷን ለምን ትበላለች ? »

ብርጭቆዋን አስቀመጠች ... እንደ መደነት ብላ ታስባለች ።

«እረ ወዲያ ! ... ዐውቀህ ልብህ ወልቋል ። ይሄ ነው ጥያቄው ? » አያት ጣልቃ ይገባሉ ።

«አይ እናቱ ! እቪ እንቺ መልሽልኛ ... »

«ወነኛ ! እኔ ስንት ድሙት አሳድጌአለሁ ! ሦስት የወለደች እንድ ቢወጣላት ነው ። ዕውነትም ትበላኛ ዋለች ። ምክንያቱም የናትየዋ ፍቅር ነው ። ድሙት ልጂቷን በጣም ስለምትወዳቸው ፣ ትበላቸዋለች ! »

«እህ ! የወለደውን የማይወድ ፍጥረት አለ ? »

«ሁሉም ይወዳል ፤ የማይወድ የለም ... ግን የድሙቱ ይለያል ! እንሰላ አይደለች— አታስብማ ! ትበላ ቸዋለች ። 'ለምን አታስጥሏትም ነው ? ' — አስተግሪያችሁ የሚለው ? »

«አይ ! ምክንያቱን አስረዱ ግለቱ ነው ። »

«እንስላ ምን ምክንያት አለው ። 'እንስላ እንጎል የለውም ! ' አትለውም ? »

«ታዲያ ውሻ ለምን ልጂቷን አትበላም ? »

እህቱ የመከተን ጠየቃ ባንከር ትከታተላለች ።

የሚያነጣቸውን ሐሳቦች ትመዝናለች ። የመብሰል እዝግጂያ ታይበታለች ። ለግናኛውም ስለ ጉዳዩ ሐሳብ የምታጎናበትን መጽሐፍ ለግስታወስ ትሞክራለች ።

«እንግዲህ ነገርኩህ ! ውሻ ርኩስ ነዎ ! ... ለል ጂቷ ደንታ የላትም ... ይቺኛዋ— ድመቷ ፣ የልጅ ፍቅር ነው እንዲህ የሚያደጋት ! »

«እቪ ይሁንልሽ እናቱ ! ልጂቷን እንዳትበላ በም ንድነው የምታስጥሏት ? »

«ምን ይሠራልሃል ? »

«አስረዳ ስባል ... እብራራለሁ ! »

«ከፈለገ ንገረው ... በፈጠ ነው በለው ። ፈጠ ወትጠን እንረጭባቸዋለን ፤ ከዚያ አትጎካቸውም ። »

«እንዴት ? »

«የልጂቷ ጠረን መቀየሩን ስታሽት የግዷን ትለ ቃቸዋለች ... ከዛም ያድጋሉ ። ፈጠ መጥቀሙን ሳላ ወቅ እንዴ በልታብኝ ነበር ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ሌላስ ?»

«በቃህ ! ይሄንን ንገረው !»

ገበታው ተነሥቶ ሠራተኛዋ ዕታውን በተራ ወደ ኪችን ትመለሳለች ።

«ግን ዕውነት ነው ?» ትልቋ እህቱን ይጠይቃል — መከተ ።

«ልቧን ልታፈርሰው ነው ? . . . ነገርኩህ ! »

«እስቲ ከመጽሐፍ ላይ ተጨማሪ ሐሳብ ፈልጌ እስረዳህለሁ ። »

«ሌላም አለ »

«እሺ ። »

«የኛሽ ! እክስትሽ ጠበል ቅመሱ ብላለች» እያት የጨዋታውን ርዕስ ይቀይራሉ ።

«መቼ ? »

«ሳምንት እሑድ !»

መከተ አላስችል ብሎታል ።

«ዓለም ትጠፋለች ሠኔ ! ... ይሄ ሁለተኛ ጥያቄ ነው ። »

«ምጽአት ሲመጣ ትጠፋለች ... በለው !» ባለቀ ትዕግሥት ፥ እያትየው መለሱለት ።

... እን መከተ ጣቱ ። እህቱ በመከተ አለመለሰችት ተደለተች ።

«እናቱ ! ልጁ ዐዋቂነት ናፍቆታል . . .»

«እንዲህ አርጉም የሰ ! . . . ትንሹንም ትልቁንም እያንሱ መወትወት ነው — ነውት ! »

«እቱ እናቱ ! ደግ አረገ በይ !»

«እንቺ 'አይዞህ' እያልሽው ነው ! ... አንቺን እያየ ነው ። ይሽው አንቺስ — ዐይንሽን አሳብጦ በሽተኛ አረገሽ እይደል ? ሰው ሌትና ቀን — መረቀት ላይ ይያፋልኮ ለልዘኔታ ድምፅት ይናገራሉ ።

«ቅዱስ ያሬድም እኮ ሳይሰለች በግተናቱ ነው— የታወቀው !!»

እናት ይጮኻሉ !

«እንተ ልጅ ! ደሞ ብለህ ብለህ ቅዱሳንን ታጣ ለህ !... የት ታውቀዋለህ ? ይሄ የሊታውንት ሥራ ነው ። እንተን እይመለከትም ፣ ዐርፈህ ስለ ድመት አጥና ።

መከተ ጣት እየለ ይመልሳል ፣

«እስቲ የቅዱስ ያሬድን ታሪክ ለናቱ ንገሪያት ። እህቱን ይለምናታል ። እያቱን ግን 'እናቱ የት ታውቂ ዋለሽ' ብሎ ለመጠየቅ ፣ እፉ ላይ ያርሶ ነው— የመላ ሰው ።

«እናቱ ! ዕውነቱን ነው ። ያሬድ ዐዋቂ የሆነው ሳይ ታክት ዜማ በመግሩ ነው ። ይሽው ቤተ ክርስቲያን የሱን ትኜት እይደል የምትቀኘው ! »

«ታሪኩን ንገሪያት በናትሽ !!»

«እንተ ንገሪት !! » — ምን ያህል ሐሳብ እንደሚ ይዝ መፈተኛ እጋጣሚ አገኘች — እህቱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የግስታውሰውን እቺ!» — ጉርርውን '... እእእ' አለና ጀመረ።

«ያሬድ የዜማ ተማሪ ነበር። ሲማር፣ ሲማር ቆይቶ አንድ ጊዜ ጠፋው። አቃተው። መምህሩ ትዋትዋ አር ገው ገረፉት። ወዲያው ሮጠ ያመልጥና ካንድ ዛፍ ሥር ይቀመጣል። ሲያስብ ... ሲያስብ፣ ባጋጣሚ ከትጠሰ ሥር አንድ ትል ያያል። ትሉ በትጠሉ ላይ ለመውጣት ... ሳብ ... ሳብ ... ይልና ይወድቃል — ወደ መሬት! እንደገና ሳብ ሳብ ይልና ... ይወድቃል! ... ያሬድ— ይህን ልትም አርን ያስተውላል። በመጨረሻ፣ ትሉ ... ሳብ ሳብ፣ ይልና ይወጣል ... ከዚህ — ያሬድ ትልት ትምህርት አገኘ። ተግቶ መሥራት፣ መጣጣር ከተፈለ ገው ቦታ እንደሚያደርስ ወሰቀ! በኋላ ወደ አስተማ ሪው ተመለሰ። ሲማር ይገባው ጀመር። የተነገረውን አይረሳም ... የዜማ ሊቅ ሆነ — አልሻለሁ።»

«ውይ ውይ! ... ዕውነትም የግዜር ሥራ ነው! ታሪክ! ታሪክ ነው!»

«ሌላም አለ ... ከነበሩት ንጉሥ ፊት ቀርቦ ዜማ ሲያዜም፣ እግሩ ድንገት በጦር ተወግቶ ነበር። ታዲያ ከመሰለው የተነገ ላይሰማው ቆይቶ— ዜማውን ካበቃ በኋላ ነበር — ከግሩ ደም መፍሰሱን ያየው። ታዲያ አይገርምም?!»

«ወይ ጉድ! እኔን! የግዜር ሥራ ነው ... እንተ ልጅ፣ ወሬህ አያልቅ!» ተነሥተው ወደ ኪችን ገቡ።

«ጥያቄዎን [illegible]

«እናፍና ስጠኝ! ... አሁን ትንሽ የግነበው አለኝ፣ ስጨርስ እንዳንድ ሐሳብ እነግርሃለሁ ...»

«ልጆች! አላችሁ? ታጠቡ እጃችሁን ...»

ከአዛቁ ቀጥሎ እጁን ታጠበ። ፒጃማውን ለበሰ። ታደም አለና እህቱን ይጠብቃት ጀመር—እንድታስረዳው!

በሦስተኛው ቀን ...

መክተ ትምህርት ላይ ነው። አስተማሪው ጂኦግ ራፊ ያስተምራል። በግራውም በቀኙም እጁ ቁልጭ አርን ይጽፋል። ግልጽ አርን ስለሚያስረዳ፣ ተማሪዎች ይወዱታል።

መክተ ከመጨረሻው «ቢንች» ላይ ተቀምጧል። አብሮት የሚቀመጠው ለግ ቀሪ ሆኗል። ከጉጉ የለም። ድንክዬው ዓለማየሁ በደብተሩ ጀርባ ሥዕል ይሠራል። አፍንጫዋ ዘወትር የሚንፋንፈው ፍሬወይኒ ብጣሽ ወረ ቀት ላይ ጸፍ ጸፍ ... ታረማና በ « ቢንቹ » ሥር ለጓ ደኞጀ ታቀብላለች ...

በር ሲንኳኳ፣ አስተማሪው ይከፍታል። እንገቱን ወጣ አርን ቆየ ... ይነጋገራል። ሲጨርስ ወደ ተማሪ ዎቹ መለስ ብሎ፣

«መክተ! መክተ! ሰው ይፈልግሃል ... ብዙ እንዳ ትቆይ!» ወደ ማስተማሩ ተመለሰ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ልቡ እየደነገጠ ‘ማነው የሚፈልገኝ ?’ በማለት ፣ ትንፋሹን ውጦ ከመቀመጫው ተነሣ — መከተ ። ተማሪዎቹ እየተገላመጡ ዐይናቸውን ሲያጉረጠርጡበት ... ይደነግጣል ። ፊቱ ላይ ላብ ችፍ ይልበታል ። የደም ሥሮቹ — ይገታተራሉ ።

እንገቱን ሰብሮ ይወጣል ...

በሩን ከመክፈቱ ፣ ፎዚያ ተገትራ አገኛት ።

«ኡህ ! ... እንቺ ነሽ ? ምን መጣ ብዬ — ቀልቢ ጠፍቶ ነበር ።»

«እይዞህ !»

«ምን ትፈልጊያለሽ ? ... ትላንት መልሱን ነግሬሽ የለ ? ... አስተግሪንኳ አትፈሪም ?»

«አቦ እንተ ልጅ — እትቸኩል !»

«እሺ ይሁንልሽ ! ... ትምህርት አለኝ ፣ ምን አርግ ነው — የምትይኝ ?»

«ሙች አጣሁት ትምህርት እንዳለህ !»

«እና»

«እና እውን የምትሠራልኝ ነገር ስላለ ና እንሒድ!» ቀደም ቀደም እያለች ትመራዋለች ።

መናገር እየፈለገ ፣ ትምህርቱ እንዳያመልጠው እየ ተጨነቀ ... ይከተላታል ። የን መከተ ክፍል የሚገኝበት ሕንፃ— ከጣሪያው በላይ ከቤተ ክርስቲያን ይመሳሰላል ... ሌሎች ክፍሎችን አልፈው ፣ በሕንፃው ዋና በር ተከ

ታትለው ይወጡና ፊተ ለፊት ካለው የትምህርት ቤቱ መናፈሻ ይገባሉ ። ዙሪያውን ያለው ባቡር መንገድ እን ደቀለበት ይከበዋል — መናፈሻውን ።

«በይ ! ቶሎ ንገሪኝና ልመለስ !»

«እንካ መረቀት ! ... እስክሪብቶ ይዘህል ? » ከድን ጋይ ላይ ይቀመጣሉ ።

«እም !»

«በል ! ለክርክር የሚሆን ሐሳብ ነው —የምትሰጠኝ» እሁን ባማርኛ ‘ፒሪየድ’ የማቀርበው ነው ... ‘ ሞት አፋፍ የደረሰን ሰው ፣ በሕክምና የማይረዳ ሲሆን ሕይ ወቱ እንዲያልፍ ማድረግ ተገቢ ነው ? ወይስ አይደለም?’ ... ምን ማለት ነው መሰለህ ? ... እ ... እ... ‘ ሜርሲ ኪሊንግ’ — ይደገፋል ወይስ አይደገፍም ? ይሄ ነው ! እኔ ‘ተገቢ ነው ’ ብዬ እከራከራለሁ ።»

«ለንቺ ! ጨካኝ ነሽ ለካ » አፉን ይዞ ።

«አይደለሁም ! ... አስተግሪው ተከራከሪ ብሎኝ ነው ። በል ሐሳብ ስጠኝ »

መከተ ከየት እንደሚነሣ ግራ ተጋብቷል ። ሕሊ ናው ሞትን በመደገፍ የመከራከሪያ ሐሳብ ለማፍለቅ ፈጣን አልሆነም ።

ፎዚያ ትናገራለች ...

«በል አትፍራ ! ... ይሄኮ ትምህርት ነው ። በመ ጫረሻዋ የሕይወት እስትንፋስ ላይ የሚገኝ ሰው— ፈቃዱ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ተጠይቆ ፣ እሱም ተስማምቶ ፣ በምድር ላይ ፍጻውንና ሥቃዩን ከሚቆጥር 'ይረፍ !' ብሎ መከራከር ፣ ማሸነፉ ከባድ የመሆኑን ያህል ... ከዚህ በተቃራኒ 'መኖር አለበት !' ብሎ መከራከር የሚያትተኝ አይመስለኝም። ምን ይሁን ምን — ሁላችንም ሕይወት እንፈልጋለንና ! »

«ይሁንልሽ ! ... ኃጢአተኛ ልታረጊኝ ነው !»

«አቦ በቃህ ! ... ይልቅ ተልጠፍ ብለህ ሥራ!»

መከተ በረኸሙ ተነፈሰ። እንዳንድ ነጥቦች በወረቀቱ ላይ ሊያሰፍር ተሰናዳ ...

«እንግዲህ ስትጀምሪ ... ቆይ ! ... አንድ በሽተኛ አለ ብለን እንውሰድ። በጣም ያጣተራል። ሥቃይ ላይ ነው። ሐኪሞች የሚችሉትን ያህል መርምረው ፣ አከመው ሲያበቁ ... 'ተስፋ የለውም' በማለት ያድሙ ዋል። በሽተኛው በፈናው 'እባካችሁ ! ስለሞንት ብሳችሁ ! ንሳግሱኝ ! ተሠቃየሁ !' ብሎ ተማፅኗል። ቤተሰቡ '... ምን ይታወቃል ፣ ከዛሬ ነገ ይሻለው ይሆናል!' በማለት ተስፋ ቢጥልም ፣ በሽተኛው ባሰበት እንጂ ፣ አልተሻለውም ካልን ... 'ሕይወቱ ትለፍ!' ሊባል ነው። እና መከራከሪያሽ ነጥብ ፣ ንባሽ ?! ... ሕይወቱ እንድታልፍ ቢደረግ ሕመምተኛው ለረጂም ጊዜ ከመሠቃየት ቶሎ ይገላገላል ... ቤተሰቡም እየተሳቀቀ ፣ የማይድን ሰው ከሚያስታምም— እርሙን አውጥቶ 'እፎይ!' ይላል ! ለበሽተኛው የሚያወጣውን ወጪ ይቀንሳል ...

የጨና እገልግሎት ትግር ባለበት ... ለበሽተኛው የሚሰጠው መድኃኒት ፣ የሚተኛበት አልጋ ፣ የሚያስታምሙት ነርሶች ፣ የሚያክሙት ዶክተሮች ... ለሌሱች ሕመምተኞች እገልግሎት ይሰጣሉ ... አይቢኃሽም !»

«እሺ ! በኔ ወይም ባንተ ዘመዶች ላይ ቢሆንስ ... 'ይሁን !' ብለህ ትስማማለህ ?»

ፍዘያ ተቃዋሚ ተከራካሪዎ እንዴት ሐሳቧን ቀርሽ ለማረግ እንደሚዘጋጁ የምታሰላስል ትመስላለች።

የመከተ አያት ይጣራሉ ...

«መከተ ! መከተ ! ... አትነማም ! እንቅልፉም ረፍ ይል ! ... ትምህርት ቤት የለህም ?»

ፍንጥር ብሎ ካልጋው ሲወርድ ፣

'የቤት ሥራው ... ጥያቄዎቹ ...' እሁቱ እንዳታመልጠው ተጣድፏል።

የግተኛ ጠረጴዛው ላይ ወረቀት ሲያይ ፣ ድንጋጤው መለስ አለ።

«እናቴ ! ... ግታ አልጋው ውስጥ ያገባኝ ማን ነው ?»

«ጥያቄህ ... ተንሥ ረፍዷል !»

http://ethioliberty.wordpress.com/

እ ቅ ሌ ታ

የበልጉ ጀናብ እንዶ ዘንድሮ ሆኖ እያውቅም ። እንዴ ከጀመረ ልጓምም የለው — ያወርዶዋል ...

«ሩጫ ! ... በይ እንጂ ሩጪ ! ... የምን መቆም ነው ?» እሱ አሠልጣኝ ሐናንያ ፣ በሚወርደው ዶፍ መሐል ለመደመጥ እየሙሁ ።

ረጅሙ ሰውነታቸው ተመጣጥኖ ፣ ፍርጥም ብሉ የተገነባ ነው ። ዐሥራ ሦስት ዓመት ሙሉ እንደርጠ ነው ። ሆኖም ሰውነታቸው ፍንክች አላለም ። ስፖርት ያሳምራል ፣ ወጣት ያደርጋል ያሰኛል ። ታዲያ ፣ የሐናንያ የደስ ደስ ጉንጮቻቸው ላይ ይፈካል ።

በቸርችል ጉዳና ሐናንያ የሚመሩት የአትሌቶች ቡድን በከፍተኛ ልምምድ ላይ ነው ። አትሌቶቹ የልዩ ልዩ ርቀት ተወዳዳሪዎች ናቸው ። ጦር ፣ ዲስከስና አሎሎ ወርዋሪዎች አሉ ። የለበሱት ቁም — ከላይ ቀይ፣ ከሥር አረንጓዴ ስለሆነ ፣ የአንድ ሰው ልጆች አስመስሏቸዋል፣ በጀርባቸው «የጌጣ ጌቶች ፋብሪካ ስፖርት ክለብ»

የሚል ይነበባል ። ሐሳቡ የአንዱ ሥጋል ይቆያል — ሳርማው ነው ።

... ሞራል ... ስሜት ... ውስጣዊ ሊቃ፡ተደማምረው የማያወላውል ዓላማን ሲያራምዱ፡ውሕደት ፈጥረው ሲንቀ ንቡ ፣ ዶፍ ቀርቶ የድንጋይ ናዳ ቢወርድ ልምዱን የሚያጸርዋ አትሌት ከመሐላቸው የሚገኝ አይመስልም ...

«ሐሮ ! ... ሐሮ እንቺን ነው የምለው!... ሩጪ! ሳቢ! ... ጥለንሽ መሔዳችን ነው » እሱ ሐናንያ በድጋሚ ፣ እንገታቸውን የጓሊዮሽ አጠማዘው ወደፊት እየሮጡ ።

ሐሮ ፣ ለወትሮው ከሯሯች መሐል ትንፋኟን ቆጥባ የምትገኝ ነበረች ። ሱጥ ሱጥ ብላ እንደ ቀጭኔ የተመዘዘ አካሏን እታደክመውም ። ዛሬ ፣ ጓላ ቀርታ ጭራ ሆናለች ። ጥርሏን ብትነክስ ነው እንጂ ፣ ዳገቱን ችላው አይደለም ። መንፈሷ መረበሹ ፣ ሰውነቷ ሰላም ማጣቱ ከገፀ ይነበ ባል ።

« . . . የጀመሩትን መጨረስ ፣ የያዙትን ከዳር ማድ ረስ ...» የሚል ጭብር ዕምነት ነው የያዛት ። ምን ይሁን ምን ፣ ፍጻሜውን ማየት አለባት — ዕልኽኛዋ ሐሮ ።

እሷን ከፍታ «ኤፍ ... ኤፍፍፍ» እያለች — አለ ከለከች ። ከባዱን ቀዝቃዛ እየር ባፍንጫዋ ፣ ባሷ ስትስ ቧው ፣ ሳንባዋ ዝሎ ፣ ተወጠረ ። «ኤሀ! ... ኤሀ!» እያሰኘ አሳጣት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሐር ጽንር እፍር አይባልም — ያጥራል ። ሰግስ ዋብ ደንታ አትሰጠውም ። እሁን እንዳልነበር ሆኖ ርቧል። ከላይዋ የሚወርደው እንጥፍጣሬ ወደ አኗ ሳይቀር ይሠ ርጋል ። ይህን ጠራርጋ ለመመለስ ፣ አትም ያጣች ትመ ስላለች ።

ገና ከመነሻው ፣ ጥሩ መንፈስ አልያዘችም ነበር— ሐር ።

. . . አትሌቶቹ ልምምዱን የጀመሩት ፣ በአዲስ አበባ ስታዲየም ነው ። ከባቡር ጣቢያ በሚነሣው ጉዳና ሽቅብ ሲመው ፣ ቁድሮስ አደባባይ አካባቢ ሲደርሱ ውሽንፍር ያቀላቀለ ዝናብ ይወርድባቸው ጀመር ።

አሠልጣኝ ሐናንያ ፣ በዚህ ውስጥ የያንዳንዱን አት ሌት እንቅስቃሴ ልትም አርገው እያጠኑ ነው ። የተለየ ... አዲስ መስሉ የሚታያቸውን ነገር በሐሳባቸው መዝ ገበው ፣ ሳያዛንፉ በአትሌቱ ማንደር ያሰፍራሉ ። ቀድሞ ከተጠናቀረው ጋርም በማነጻጸር ይተንትኑታል ።

ሐናንያ ወደ ኋላ ተጠግዘው ሐርን ቢያስተውሉ፣ ያው ነች ። እንዲህ ሆና ፣ መልሰ መጮኽ የሚያዋጣ አል መሰላቸውም ። ከሩጫቸው ዝግ እያሉ ... ዝግ እያሉ ... ከሐር ጋር ተስተካከሉ ።

«ሐር ምን ሆነሻል ?... ምን ነካሽ ? ብዙ ምላ ነው የበላሽው ? ይሄ የመጨረሻ ልምምዳችን መሆኑን ታው ቂያለሽ ፣ አይደል ?... የሻምፒዮና ውድድር ይጠብቀናል፣

ታዲያስ ?... ፍጥነት የታለ ?... በይ እንጂ» እሉ ፣ ከሯት ሌሎቹን አትሌቶች ፣ ከኑን — እሷን እየተመለከቱ ።

ሐር መልስ እንድትሰጥ ጠበቋት ። ቆዩ ። የለም ። ኩስትርትር ካለው የሐር ፊት እንዳች ነገር ጠረጠሩ ። የጤና አይደለም !

«ሐር ! በዚህ ልምምድ በደንብ ካልሠራሽ ውጪ ትሽ መጥፎ እንደሚሆን መገመት አለብሽ ፣ ስንት የለ ፋሽበት መሆኑን አትርሺ . . . እንደ ምንም ትንፋሽ ያዥና ግፊ ... ሳቢ ! ኡፍፍ ... ደግሞ እግርሽ ፣ እግ ርሽ ! ... በጥፍር ነው !»

ንግግራቸው ቁርጥ ቁርጥ ይላል ። ፈታቸውን በእ ጃቸው ሲሞዥቁት ፣ ዝናቡ ወዲያው ያከናንባቸዋል ።

ሐር ፣ «እሺ» ብላ ለመመለስ ፣ ምላቧን ያላወሰችው በሥታይ ነበር ።

ሐናንያ አተኩረው ተመለከቷት ። የምት ሞቷን ነው — የምትሮጠው ። « ጨግምር መናገር አላስፈላጊ ምሬት መቀስቀስ ነው » ሲሉ እሰቡ ። ደግሞ ሐርን የሚያሰራት ትዕዛዝ ሳይሆን ፍላጉቷ ነው ። ሁል ጊዜ በልዩ የስፖርት ፍትር ስሜት ልምምዷን እንደምትሥ ጽም ያውቃሉ ።

... ሐናንያ እንድ ባሕርይ አዳብረዋል ። ይኸውም በስፖርት ሥነልቡና ዕውቀት መጠቀም ነው ። ትጣትም ቢሆን ፣ ከአንድ አትሌት ስሜት ጋር የሚጣጣምበትን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ስልት ይፈልጋሉ ። ለዚህ ነው በስፖርተኞች ዘንድ ተወ ጅነትን ያተረፉት ።

በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ የእሠልጣኝነት ትምህርት ተከታትለው ከተመለሱ በድስት ዓመት ሊሆ ናቸው ነው ። በዚህ ጊዜ ካንድም ስፖርተኛ የመረረ ግጭት አልፈጠሩም ። ይልቁንም የተግሩትን ፣ ያወቁትን ዘርግፈው ለግሳወት የግይታክቱ ሆነዋል ። «በርቱ ! ... በርቺ ! ... በርታ ! ... እንዲህ ቢደረግ ኖሮ» — ይቱና ቸዋል ።

ሐናንያ የሐሮን ነገር እያሰላሰሉ ፣ ፍጥነት በመጨ መር ወደ መሪነት ቦታቸው ተመለሱ ።

ሌሎቹ ሯጮች ደህና ይዘዋል ። የሚወርደው ዝናብ ጋብ አላለም ። ሐናንያ ፣ በእትሌቶቹ ብርቱ ጲሊፒሊን የልብ ልብ ተሰምታቸዋል ።

... ልምምዱ ሩጫ ብቻ አይደለም ። የአካል ማጻ በሪያ እንቅስቃሴ ያካትታል ። «እትሌት — ባካሉ ካል ጠነከረ — ሮጠ እያሸንፍም ! » ይላሉ ሐናንያ ። ስለዚህ አካሉን ለማፈርጠም ፣ የደም ዝውውሩን ለማሻሻል ፣ ትን ፋሹን ለማስተካከል ... ጥብቅ ልምምድ ግድረግ አለ በት ... እየተሮጠ ... እጅ ወደ ጉን መዘርጋት ፣ ወደ ላይ ማውጣት ፣ በደረት ስፋት ልክ ወደፊት መዘርጋት ፣ ግውለብለብ ፣ በፈረታ ግሽከርከር ... ይቱጥላል ... ይቱ ጥላል ።

ሐናንያ ሥር [illegible] ሩጫውን ብቻ ነው ። «ምን ነገር ገጥሟት ይሆን?» የሚል ጥያቄ በሕሊናቸው ተንገዋለለ ።

ልምምድ እየሙሩ ቢሆንም ፣የሐርን የጓላ ታሪክ ግሰላ ሰል ከጀላቸው ፣'የቅርብ ችግር እንዳንዴ ሥር በሰደደ መን ሥኤ ከጓላ ታሪክ ጋር ይያያዛል' የሚል ግምት ወስደዋል ።

ለዚህ ነው ፣ ሌሐናንያ ፋይዳ ያለው ነገር ያንድ እትሌት ታሪክ የሆነው ። «... ይህን ሳልንነዘብ እንዴት ግሥልጠን እችላለሁ ? ... እትሌት ለመምከር፣ የሚነድለውን ለግሳየት ፣ ድብቅ ችሎታውን ለመግለጥ ... የግድ ግጎደሩን ደጋግሚ ግጥናት ያስፈልገኛል » እያሉ ይከራከራሉ ።

... እና የሐሮ ግጎደር ትውስታ ...

... ዕድሜ— ሐያ አንድ ዓመት ። ትምህርት— ዘጠ ነኛን ያልጨረሰች ። ሥራ — በፋብሪካው እትሌቲክስ ቡድን ውስጥ አራት ዓመት ። ትዳር — የላትም ። ኑር— ከእናቷ ጋር ። የምታዘወትረው ጓደኛ— ወንድ ። ጠባይ— ዕልኸኛ ፣ የወንዶችን ሥራ ወይም ወንዶችን መምሰል የምትመርጥ ። የተለየ ገጠመኝ — በልጅነቷ ጅግ አት ራቢያ ፣ ሽቤ ስትኖር ፣ ለሽርሽር በሜካ ውስጥ ስትዘዋ ወር ከእነር እፍ በሩጫ ያመለጠች ፣ ስንቴ ነበር? በእ ህያ ስትጋልብ የወደቀችው ... በትምህርት ቤት እዘው

http://ethioliberty.wordpress.com/

ትራ ተደባዳቢ የነበረች ... የአትሌቲክስ ውጪት—በእ ዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውድድር አሸናፊ ፣ በክለ ቦች ውድድር በአራትና ስምንት መቶ ሜትሮች 7ኛ እና 5ኛ ደረጃ የያዘች ። ጤንነት — በጣም ጥሩ ። እጢታላይ አስተያየት — በጣም ተስፋ የሚጣልባት ...

... ሐናንያ የሐርን መዝገብ በሐሳባቸው ሲከልሱ ፎቶ ኮፒ የማንጣት ያህል ዋና ዋና ነጥቦችን አስታወሱ ።

ታዲያ ችግሯ «... ከቤቷ የመነጨ ይሆን ? ወይስ የወጣትነት ጣጣዎች?... የስሜት መሸበር ፣ ምናልባት ...» — መላምቶች ደረደሩ ።

ሐሮ በምታደርገው የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ፣ ይተ ማመኑባታል ። «ነገር ግን እንደ ዛሬው ድንገት የመጣ ችግር ከቀጠለስ ? . . . የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውጪቷ ቢበላሽስ ? ...» የሚለው ሐሳብ ከነዜናቸው ።

የልምምዱን ሩጫ እየመሩ ለአትሌቶች ምልክት ለጡና ቫርችል ጉዳናን ጨርሰው ወደ ቀኝ — ወደ ፒያሳ ታጠፉ ። ሁሉም ጥሩ ይዘዋል ። እንዲያውም «በዚህ ዶፍ ይሀን ያህል በመሥራታቸው ጉብዘዋል » ብለው ደመ ደሙ — ሐናንያ ።

ሐሮ ፣ እካሷ በሙሉ ርሷል ። ጡት መያዣዋ ፣ ስስ ካናቴራዋ ፣ የውስጥ ሱሪዋ አልቀረም ። ፕርሷን ነክሳ ፍጥ ነት ለመጨመር ተንገታገተች ። ከሳንባዋ ሥር አንዳች ነገር እንደጦር እየወጋ ፣ ቀስር ያዛት ... እያለከለከች የኤሌክትሪክ ሕንፃን ከጀርባዋ በመተው ፣ ወደ ምኒልክ

አደባባይ ቡድኑን [illegible] ።... ጎልፍ ክለብ ትጫኑ አለች ። «... ወደ ቤትሽ ብረሪ ! ሒጂ ! በዚህ ዝናብ ለምን ብለሽ ?» የሚል ሐሳብ መጣባት ።

የፒያሳ መንገደኛ ዝናቡን ፈርቶ ፣ በየሱቁና በየቡና ቤቱ ውስጥ ተጠልሎ ነው እንጂ ፣ ተረቡ የሚቻል አል ነበረም ።

ሐሮ ከዚህ ሁሉ እምልጣለች ።

«ከዚህ ጥፊ ! ጥፊ ! ... የማትችይውን ?» የሚላትን ሐሳብ በግድ ለመርሳት ከእዕምሮዋ ሙግት ገጠመች ።

ሩጫዋን እጎንብሳ ቀጠለች ። ዝናቡ እርጥቦ ባቀዘ ቀዘው ጭኖጅ መሐል ፣ ትኩስ ሙቀት ተሰማት። ውሃው ተደባልቆ ቢያቀጥነውም ፣ ደም ነበር ።

ሐናንያ ፣ እትሌቶቹን ምኒልክ አደባባይ አቆሟቸው። ሁሉም ከዝናቡ ተጠልለው መቆንጥነጥ ያዙ ። ገሚሱ ከወገቡ እጎንብሶ እየር በመሳብ ፣ ቀና በማለት ደግሞ በጀርባው ተሰጥመ ሰማይ እያየ «ኡሀ ! ... ኡሀሀሀ!» እያለ ትንፋሽ ያወጣል ። ከፊሉ የጭን ጡንቻዎቹን ወጥሮ ፣ ባለበት ዱብ ዱብ ይላል ። ሐሮ ተኩራምታ ተቀምጣ ለች ።

ሐናንያ ምክር ሲለጉ ፣ «እትሌት ረጅም ይሁን እጭር ርቀት ርጠ — ወዲያው መቀመጥ የለበትም ፤ ይህ ከሆነ ጅማቶች ባንዲ ይረግባሉ ። ይኮማተራሉ ። ጡንቻ ዎች ይተሳሰራሉ ። ለእካል ደግ አይደለም » ይላሉ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሐናንያ ከተሰወሩበት ቆይተው ሲመለሱ ፣

«ሐሮ ! ... ደግሞ ቁጭ አልሽ ... በይ ተነሽ ! አይ ዞሽ ! ቀስ እያልሽ ጫብ ፣ ጫብ ! በይ .. ምንም ችግር ቢኖር ቀስ እያሉ መንቀሳቀስ ፣ ሰውነትን ማላላት ያስ ፈልጋል ... በርቺ ! ጉበዝ ! አውን እንመለሳለን »

ሐሮ እሠልጣጀን እከብራ ፣ እንዳሏት ፈጸመች ። ድካሟ ከግምቷ በላይ ሆነባት ።

ሐናንያ ፣ አትሌቶቹን አንድ ላይ ሰበሰቡና ፣

«ልጆች ! ... እውቶቡሳችን አውን ይመጣል ! ... ወደ ስታዲየም እንመለሳለን » አሉ ፣ ቀደም ብለው በሕዝብ ቴሌፎን ቦሌ ከሚገኘው የስፖርት ክለቡ ጽሕ ፈት ቤት ደውለው ያገኙትን መልስ መሠረት አርገው።

ሰውነት ዘና ሲል ፣ የልብ ምት ሲቀንስ ... መረጋ ጋት ሲጠማ ፣ ዝናቡን እያሰቡ ጨዋታ ያዙ — አትሌ ቶቹ ። ፀሐይ በጨረሮቿ ደመናውን መሰንጠቅ ጀምራ ለች ። ማባራት ሲጀምር የፒያሳ መንገደኛ መተራመሱን ተያያዘው ። የሙዚቃ ቤቶች ጨኽት ሲያስተጋባ ፣ ተኮ ልኩለው የሚደንሱ የመንገድ ልጆች ተጠራሩ ።

የአትሌቶቹ አቶቡስ ከች አለ ። ቦታ ለመያዝ እሽ ቅድምድም ሆነ ። ሐናንያ ከፊት ተቀምጠው ፣ ጉዞ ጀመሩ —ወደ ስታዲየም ።

ሲደርሱ ፣ ሐሮ ተንደርድራ የመጸዳጃ ቤቱን በር ዘጋች ። ... የወር አበባዋ ነበር ...

«ነገ የጨና ሪፖርት እንድታቀርቢልኝ !» አሉ ሐና ንያ ፣ አትሌቶቹን ሲያሰናብቱ — ሐሮን ፈልገው ።

* * *

ሐሮ ፣ ቦሌ ክለቡ ክሊኒክ ጉራ ብላ ስለቆየች ፣ ቤት የደረሰችው ዐሥራ ውለት ሰዓት ገደማ ነበር ።

ስኩተሩ የሚያስፈልገውን ምርመራ እያረጉላት ። ዘዘህ ላይ አባታዊ እንክብካቤ በማድረግ የታወቁ ናቸው ። ሙያቸውንና ሰብእዊ ፍጡርን ይወዳሉ ። ለስፖርተኛ ሲሆን ይብሳሉ ። በውጪ ፡ ሐሮ ምንም ችግር አልተገኘ ባትም ። ለተሰማት ትኩሳት ማስታገሻ ፡ ለብርድ መቋ ቋሚያ የሚረዳት እንክብል ታዘላት ወሰደች ።

ምሥራቅ ንበያ አዳራሽ በስተጀርባ ከሚገኘው መኖ ሪያ ቤቷ ስትደርስ ፡ እናቷ ከእንግዳ ጋር ነበሩ ። የሐሮን ጥሟሽት የመሰለ ፈት ሲመለከቱ ፡

«እቤት ! . . . እቤት ! እበስ ንበርኩ ፡ ደሞ ምን ነካብኝ ? አውን እንዲያው ላልጠፋ ሙያ እየሮጡ ራስን ማጥፋት — ምን ይባላል ? . . . በዚህስ የሚመጣ ንንዘብ የደም ንንዘብ ነው ፡ ቢቀርም እይጎዳ . . . የእባትሽን ነፍሱን ይማረውና — ጡረታው ይበቃን የለ ! . . . እረ ተይ ስሚ ! » አሉ ፡ የሚያዘወትሩትን ሮሮ ።

ውሏቸው በቅርብ ይሁን በሩቅ የሚያውቋቸውን እየ ጾሩ ማስተዛዘን ስለሆነ ፡ ነጠላቸውን እንዳዘቀዘቁ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እንዴ ! . . . ምነው ! እግዱ ! ስንት ጊዜ ነው የሥ ነግርሽ ፣ ሩሚውን ብታይው ትወጂዋለሽ ፣ ደስ ይልሻል አላልኩሽም . . . ከኛ ጋር ብትሮጪግ ፥ ... » እናት፣ው አቋረጢት ። ሐሮ አትም እንሏትም ቀልደኛ ሆነችባቸው። እንግዳዋ ገርሟቸዋል ።

«ቀልዱን ተይው ! . . . የሠፈሩ ግቲ ሲሮዋ የግላይ መሰለሽ ደሞ 'ብታይው ! ' ትሰኛለች ... ይልቅ . . . እት ተዋወቁም ! » አሉ — እናት ፣ ወደመጡት እንግዳ በእገ ሜቸው እያመለከቱ ።

ሐሮ ፈገግ ለግለት ሞከረች ። አተኩራ ተመለከተ ቻቸው ። በዕድሜ ጠና ያሉ ፣ ውፍረት ያድበለበላቸው ወይዘሮ ናቸው ። ግስታወስ አልቻለችም ።

«እይ አረሳዘም ! ... ተመዘዘች አይደል ? ደግሞ ጨዋታዋ ! ይገርማል ። አባቷን ቁርጥ ነው ። የአፍንጫዋ መቅጠን ፣ የቁመታ መርዘም ፣ ጠይምነታ ... » አሉ፣ እን ግዳዋ — ወይዘሮ ግለቺ ።

«አም ! . . .አሱ ለሷ ሲሮዋ ነበር ፣ የመኪና አደጋ ጉድ ያረገው ። አሁን ያ የተገለበጠበትን የናዝሬት መን ገድ ሳስበው ፣ እንዲት ይቀራኛል ! ... ይኸው ጡረታው ደህና ይዞናል ። ... ይቺም ደራቁቻ ፣ ሩሚ ሙያ ነው ብላ ፣ ቆዳዋ ከአጥንቷ ተጣብቆ ፣ ሞኔዋ ሊወጣ ነው ... አት መከር !»

«በይ አትቁሚ እቴ . . . የተሸከምሺውን አስተም ጪው» አሉ ፣ ወይዘሮ ግለቺ ፣ ከተቀመጡበት እንጋጠው

ሐሮን እየተመለከቱ ። ከትንሿ ጠረጴዛ ላይ በብርጭቆ የተሞላውን ቅራሪ ሲጉነጩ ፣ በጣታቸው ጠቆር ያለ ሻሻ ኖውን ያስተካክላሉ ።

«እትዬ ! . . . ዕውነትዎን ነው » በግለት ፣ ሐሮ ጓሳ ገባች ።

ከናታ ጋር የምትተኛበት ፣ ወይን የማይሞላው አልጋ ናፈቃት ። መጋደም አሰኛት ። ግን ፣ እንግዳዋን ፈትተ እሰበችና በሸቀች ።

ከአልጋው ጉን ፣ ሰንዱቅ ፣ ሌግት ፣ ባልዲ ፣ ቡሀቃ ፣ ሰፌድ ... ተንባብረዋል ። ግድግዳው ላይ ሆድ የሚያባቡ ጥቅሶች ፣ መስታወት ፣ ፍሬግቸው የተዛነፉ ፎቶግራፎች ተሰቅለዋል ።

ወደ ጓሳ ድንገት ዘው ያለ ሰው ፣ «መጋዘን ነው» ግለት ይቀለዋል ።

ሐሮ ትጥቋን አስቀምጣ ስትመለስ ፣

«በይ ሳሚያኛው ! . . . ያኔ ሸቤ እያለን ፣ በልጅነ ትሽ ሊጠይቁን ይመጡ ነበር ። ሁል ጊዜ ወተት የሚ ያመጡልን እትዬ ግለቺ . . . አታስታውሺም ?» አሉ ፣ እናቷ ።

«አም ! በልጅነታ ነው . . . አሁን ቅረላኛለች» ሲሉ መለሱ ፣ ወይዘሮ ግለቺ ።

«እግዱ ! ... ብዙ ሰዎች ሲጠይቁን ፣ ወተት ያመ ጡልን ነበር ፣ አይደል ? ... እነግ'ናቸው ! እትዬ ጌምቤ ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

እህትሽ — እትዬ ዓለም ... ደግሞ » ብላ ፣ ሌላ የናቷን ጠያቂ ማስታወስ አቃታት ።

«እኔ ስመጣ ... ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ይሆ ናታል ልበል ? ሕፃን ነበረች ፣ ወደ አጋሮ ጤጋ ከማለታ ችን በፊት ... » — ወይዘሮ ማለቺ ናቸው ።

«ትንሽ ... ትንሽ ትዝ ይላል ፣ ብቻ ...» አለች ሐሮ ።

«ወይ ሐሮ ! . . .አሁንም እንደ ልጅነትሽ ኃይለኛ ነሽ !» — ሐሮ አፈር አለች ።

«ኋላስ ? ባሰባት እንጂ ! 'ተማሪ !' ብላት ፣ 'አፍረ ሪኝ !' አለች ። ዘጠነኛ ሳትጨርስ 'ስፖርተኛ እሆናለሁ' ብላ ፣ መበላሸት ነው የቀራት ። ነጋ ሩጫ ነው ፣ ጠባ ሩጫ ነው ። ልጅ ፣ ለፍቶ ያሳደገውን ሰው ምክር ቢሰማ ነውር ነው ?»

«ምን ይደረግ ! ... የዛሬ ልጆች 'ሁሉን እናውቃ ለን !' ባዮች ናቸው ። የሚሳሳቱ አይመስላቸውም ። ዋናው ነገር ጤንነት ነው ፣ ሁሉም ይደርሳል ! ታዲያ ለጤናሽ እንዴት ነሽ ? ... » — ሐሮን ጠየቋት ።

«በማም ደህና ነኝ» ብላ ፣ እጁዛ ከለበሰው የእንጨት ሰንዱቅ ላይ ተቀመጠች ። እርይታ ዝግ እያለ አበሳት ።

«ሽቤ ሐደሽ ታውቂያለሽ ? . . .አልናፈቀሽም ?» ፣ እትዬ ! እንዴት ይናፍቀኛል ? መሰለዎት ፣ ጓደ ኛዬ — የልጅነት ቢሆንም ፣ ዘመዶቻችን . . . ሳይሙቾኝ ቀርቶ አልሔድኩም ። ግን አልቀርም ፣ አሁን መቸስ ተለ ውጧል ? »

«እም ። እኔ እንኳ ብት አላልኩም . . . ግና መንደሩ ተሰውጧል — ይባላል ... ቡናው ያው ለጉድ ነው ፣ » አሉ ወይዘሮ ማለቺ ።

ሐሮ ዘጠኝ ዓመቷ ድረስ የናሪችበትን ሽቤ ፣ በእ ግረ ሕሊናዋ መጻሰስ ያዘች ። በጉም እንደ ተጋረደ ፀሐይ ትውስታዋ ብሩህ አልነበረም ... የሠፈሯ ፣ የገጠሩ ቀዬ ፣ የጓደኞቿ — የእጊ ፣ የሚልቱ ፣ የአልማዝና የአይም ጨዋ ታዎች ... የአባቷ እንኮኮ ? ... ቁርጥ ቁርጥ እያለ ትዝ አላት ።

«ታዲያ ኑር ደግ ነው ?» አሉ እናት ፣ ጨዋታውን ወደ ወይዘሮ ማለቺ ለማዞር ።

« ደህና ነው . . . አሁን ንግዱን ነው የያዘነው ። አጋሮ አትራቢያ የነበረውን መሬት ከለቀቅን በኋላ ጅማ ንግዱን ጀመርኩ ። ተመስገን ! ደህና ነኝ . ..»

«በሰላም ነው የመጡት ? »

«እም ! ... የታናሽሽ አሁቴ ባለቤት 'ታሚል' ብለው ስመጠየቅ ነው ። ይሄንን ቤት በስንት ጥየቃ ነው የደረ ስኩበት » በግለት የሐሮን አባት መሥሪያ ቤት እጠያ ይቀው ሲያነጉ ፣ ሰዎች እንዴት እንዳመጧቸው ዘርዝ ረው ተረኩ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሐር እባት የጥንት መተዳደሪያ ግብርና ነበር ። ቀጥለው መንግሥት መሥሪያ ቤት ገቡ ። በጥቢቃና በመ ላላክ ሥራ ለመንግሥት አገልግለዋል ። ጮሌ ነበሩና ፈጥነው የሾፈርነት ሙያ ያዙ ። ወደ አዲስ አበባ ዞረው እምስት ዓመት ሠርተዋል ። ሕይወታቸው ያለፈው ለመ ስክ ሥራ ወደ የረር ለመድረስ ፣ በምሽት ሠራተኞች እላ ፍረው ናዝሬትን አልፈው ሲበሩ ነበር ።

ታዲያ የሐር እባት ፣ ከአንድ በላይ ልጅ አለግን ኘታቸው መልስ ያጡለት ጥያቄ ፣ ሾላ በድፍን ሆናባ ቸው ፣ አብሯቸው ቀረ ።

«ስንት ዓመት ሆናቸው ኮ» — ወይዘሮ ግለቺ ጠየቁ።

«ሰባት ሊሞላው ነው ፣ እይ የኒዜው መፍጠን !» አሉ የሐር እናት በለሆሳስ ፣ የባለቤታቸው ትዝታ ስለ ተቀሰቀሰ ሐሳባቸው ሸፍቶ ።

በጅግና ሸቤ የሚያውቋቸውን እያነሡ «እከሌ ... ያቺ እከሊት ...» እየተባባሉ ፣ ትዝታ ሲያወጉ አመሹ።

ሐር በተቀመጠችበት እንጉላጀች ። ቀጥላ አሸለ በች ።

«ሐር ! ሐር ! ተነሽ ፣ ተነሽ ! ሰውነትሽ ወላልቋል ። እግርሽን መሰብሰብ አትቀሻል ... ሒጂ ጋደም በይበት» አሉ እናቷ ።

«ወይ ልጄን ! ... ተኝ እቴ ! ይሻልሻል» ሲሉ ወይ ዘር ግለቺ በግስተዛዘን ነበር ።

ሐር ወይኗን እያዩች ፣ ተንገላግላ እደጋው ላይ ተን ጋለለች ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ፣ ራት ቀርቦ ነው — የተቀሰ ቀሰችው — ሐር ። ወይዘሮ ግለቺ ሔደዋል ።

ሐሳቧ ወደሚጠብቃት ውድድር ተመለሰ ።

★ ★ ★

ከአምስት ቀናት በኋላ ...

ከጠዋቱ ሦስት ነው ። የአትሌቲክስ ቡድኑ አባላት ቤሐናንያ አማካይነት ቦሌ ከሚገኘው የኔሚጌቦች ፋብ ሪካ የስፖርት ክለብ ተገናኝተዋል ።

የመሰብሰቢያው ከፍል ወርቡ ጠቦ ፣ ቁመቱ ይረዝ ማል ። እነስተኛው ተንቀሳቃሽ ጥቁር ሠሌዳ ቆሟል ። ሐናንያ ከጉኑ ሆነው መግለጫ ይሰጣሉ ።

አትሌቶቹ በሚይላው ቀይ የላስቲክ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል ። ወይናቸውን ፈት ለፈት ተክለዋል ። በጥ ሞና ለማዳመጥ ጀርእቸውን አትንተዋል ።

« ... ያለፈውን ልምምድ እንመለከት ። እንደም ታስታውሱት እየሩ ቀዝቃዛ ፣ ዝናቡም ጋይለኛ ነበር ። ሆናም ብዙዎቻቸሁ በርትታችሁ ወርታችኋል ፣ ይህ የሚያስመሰግናቸችሁ ነወ ..»

ሐር ፈጥና ልታጨበጭብ ነበር ። የልምምድ ጫጩዋ ሲታሰባት ነው የቀሰረችውን እጅዋን የመለሰችው።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ዉኣ . . . እትሌት በተለያየ የእየር ሁኔታ ሥር ልም ምድ ካደረገ ፣ በውድድር ወቅት ያልታሰበ የእየር ለውጥ ቢመጣበትም ባዕድ አይሆንም ፤ ይህን እንዳት ዘነጉ ። » ሐናንያ ትንተናቸውን ቀጠሉ ። ዋቁር ሠሌ ዳው ላይ ሜር ሜር ያደርጉና ተመልሰው እያንዳንዱን እትሌት በእንክር ይቃኛሉ ።

«ልጆች ! እንደምናውቀው የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ቀርቧል ። በሀገራችን የሚገኙ ምርጥ እትሌቶች ይሳተ ፉበታል ተብሎ ይታሰባል ። እኛም በፈናችን ተዘጋጀተ ናል — እንላለን ። በመቶ ፣ በአራት መቶና በሺህ አም ስት መቶ ጥሩ ውጤት እንጠብቃለን ። ሌሎቻችሁ ምንም እታስገኙም ማለት አይደለም ። ከበረታችሁ ያልተጠበቀ ድል ታስመዘግቡ ይሆናል . . . ማን ያው ቃል ?»

«ሚዳው ! » አለ ፣ እንዱ እትሌት በጩኸት ።

ሐናንያ ድምፁን ተከትለው ሲዞሩ ፣ ዋሲሁን ነበር።

«አ! . . . ዋሲሁን ባለስምንት መቶ ነህ ! ጥሩ መል ሰሃል ። ሚዳው ይለያል ። ይሁን እንጂ ጠንክሮ ያልተ ለማመደ ፣ ሜዳ ገብቶ የሚያመጣው ተስምር ያለ አይመስለኝም ። ሌላው ነጥብ ፣ የእካል ብቃት ዝግጅት በሥን ልቡናዊ ዝግጅት መታገዝ አለበት ። እንዳትረሱ ! አለመፍራት ፣ 'እሸንፋለሁ !' ብሎ አለመግባት ፣ በው ድድር ሰሞን ጭንቀት ማስወገድ . . . ያስፈልጋል ።

ጥድ እንዳትሆኑ እደ ! ይሁን እንጂ እንዲህ እያሻሻ . . . መደንገጥ መሸነፍ ነው ። » እያሉ ሐና ንያ ካንድ ርዕስ ወደ ሌላው እየዞሩ ፣ መግለጫቸውን አራዘሙት ። ጢማቸውን ሲላጩ ሐናንያ ፣ እንዲት አገር ከገጸቸው ላይ እንዳትገኝ አርገው ነው ። ዕድሜ ያቸውን ተመራርዶ የሚገምት ፣ ስድስት ወይም ሰምንት ዓመት መቀነሱ አይቀርም ።

የአም ነገር ተንሥቶ ከእቻዎቻቸው ጋር ሲጨዋ ወት ፣

«እየህ ! ለምን የምለሽልሽው ይመስልሃል ? ስለ ሚከሰኩሰኝ ነው ! . . . ልጂ ጉንጩን ሲስመኝ ያስብና እንደሚሻከረው ስለሚያውቅ ቶሎ ወደ ግንባሬ ያመ ራል ። ትንሽ ሲያቀመቅም ማሳከኩ አይጣል ነው !» ይላሉ ። ጸጉራቸውን በእጭሩ ያስከረከሙታል ። ጉን ጮቻው ይወጣል ። እንዳንድ እትሌቶች ይህንኑ 'ካር ጀው' ጸጉራቸውን ሲያሳጥሩ ፣ «ሐን ስታይል »— ቢሐናንያ ስታይል ነው — የምትስተካከለው ? . . . እያ ሉ አሥቋቸዋል ።

«ወደ እሰላለፋችሁ ከመዞሬ በፊት ፣ በሚቀረን ስድስት ቀን የምታደርጉትን ትኩረት እንግራችኋለሁ ። 'የምንብ ነገር ሆድ ይቆርጣል' ነው ? . . . »

«እይደለም ! 'የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል' ነው— የሚባለው » ጣልቃ የገባቸው ሐሮ ነች ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሐናንያ እየሣቁ ፣ «ሐሮ ገብቶኛል ፣ 'የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል' — ልክ ነሽ » ስለዚህ ልጆች ! ምግብ ላይ ጥንቃቄ ውሰዱ » የሚሰጣችሁን የኪስ ገንዘብ እያ ብቃቃችሁ ፣ ከዚህ ካፍቴሪያ ተመገቡ » በተለይ ለና ንተ እንዲያዘጋጁ ታዟል » ከሀገራችን የአመጋገብ ሥርዓት በመነሣት ፣ ጉልበት የሚሰጥ ምግብ ፣ ከምን ፣ ከምን እንደምታገኙ ከ'ልምምድ መመሪያ' ጥራዝ ውስ ጥ ማንበብ ትችላላችሁ » ያን ማጥናት ነው » ቤታ ችሁ ብታዘጋጁ ይደገፋል . . . »

. . . በሦስቱ ሴት አትሌቶች ላይ ያፈጠጡት ወን ዶቹ ነበሩ »

«እኛ ላይ ከሚያፈጡ ፣ ብናስተምራቸው አይሻ ልም ? » አለች ፣ ከሐሮ ኋላ የተቀመጠችው አትሌት »

«ማነሽ ? ወርቂ ነሽ ? . . . ዕውነትሽን ነው » ከፈ ለጉ አስጠጊያቸው . . . » አያይዘውም ፤

«ግን አንቺ በደንብ አንብበሺዋል ? » አሉ ሐና ንያ » ወርቂ የመሰናክል ዝላይ ሯጭ ነች » በተንጫነ ጨች ቁጥር ቀይ ፈቷ በርበሬ ይመስላል »

«እሺ እንቀጥል ! . . . ይህ ሲጋራ ፣ አልኮልና አደ ንዛዥ ዕፆችን በሚመለከት . . . ምንም ንግግር አያስፈ ልገንም » ለዓመታት የተናገርኩትን አልደግመውም » ስፖርተኛ ከነዚህ አጥፊዎች መራቅ አለበት » ደግሞ ከመሐላችን ሁሰኛ ያለ አይመስለኝም . . . » በግለት ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥ አሉ »

እነ ሐሮ ተጠቃቅሰው ገብሩ ወዳጀነህ ወደ ተቀ መጠበት ተመለከቱ » የስፖርት ቁታ አይበረከትለትም» ተሰ ይቀደድበታል » በሌላ ሳይሆን ፣ በሞኝ ውፍረቱ ነው » «ዲስከስ ወርዋሪ ካለኔ የለም ! » እያለ ይኩራራል» አዲስ ያመጣው ጠባይ በድብቅ ሲጋራ ማጨስ ሆኗል » ጥያቄውም ተሰምቷል » ሐናንያ እንሥተው መዘባ ረት አልፈለጉም »

«ማንም ያለ አይመስለኝም » » ብለው ወይናቸ ውን ወደ ገብሩ ቢጥሉ አቀረቀረ » «ግለፊያ መግባ ቢያ» አሉ በልባቸው — ሐናንያ »

«ሌላው የንጽሕና ጉዳይ ነው » ዘወትር ከልም ድ መልስ ሻወር መውሰድ አለባችሁ » አሁን እየ ሩም ጥሩ ስለሆነ ፣ ሰውነታችሁን የማይከብድ ሳሳ ያለ ልብስ መልበስ ትችላላችሁ » ነገ ለነገ ዳመና አይታ ችሁ ፣ ቅንጫ ቁም ሳጥን ብትመሰሱ ዋጋ የለውም » የጸጉር ፣ የጥፍር መስተካከል ጉዳይ እኔ የማስታውሳ ችሁ አይደለም » በተለይ . . . በተለይ ፣ እግራችሁን በጣም መንከባከብና ስለ ጫማችሁ ማሰብ አለባችሁ » ኦትሌት ምን አለው ?' ብትባሉ »

«ጫማና እግር አለው » » — ሐሮ ከመቅጽበት ከእፋቾው ቀለበቻቸው »

«እም ! የአትሌት መመኪያ እግሩና ጫማው ነው » የአበበ ቢቂላን ታሪክ ከመሰጻችሁ ጫማም ዋጋ የለ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ውም— ማለት ትችላላችሁ ። ለጊዜው ሁላችንም በሚማ ስለምንርጥ ፣ ያልጠበባችሁን ፣ የማያስጨንቃችሁን መጪ ማት አለባችሁ ። የካልሲ ነገር ፣ እንዳያስተዛዝበን እደራ ! . . . ለመሆኑ ካልሲውን በየቀኑ የማይቀይር አለ ? » — በዘዴ አለባቸውን አዩት ። ሴሎች አትሌቶች እንዲሁ ።

የእምስት ሺህ ሜትር ሯጩ አለባቸው ፣ የሚማ ሽታ ነገር መከራው ሆኗል ። ተፈጥሮበት ፣ በማግዘ ቀን የሚሚማውን ቢቀይርም ሽታ ይገንበታል ። ልክ ምና ነው — ያስታገሠለት ።

በፈገግታ ፣ « ሁሉም ይቀይራል ! ብራቮ ። የተለየ ችግር ያለበትም ይታከማል ፤ እሺ ? »

«እሺ ! ! » አሉ — አትሌቶቹ በጩኸት ፣ ከአለባ ቸው በስተቀር— እፍሮ ።

«እ ! ሌላው ነጥብ . . . የአካል ጥንካሬ ልምምድ ጉዳይ ፣ ለአራት ቀን ያህል በዚህች ሣኢጋ ጂምናዚየማ ችን ዱብ ዱብ እንላለን ። አሞር ርቀት ሯጮች ፣ ዘላ ቦች . . . በፍጥነት ለመስፈንጠር የሚረዳችሁን አጥብ ቃችሁ ትሠራላችሁ ። የረጅም ርቀት ሯጮች ፣ ትንሩ ሽና ጥንካሬ ላይ እንድታተኩሩ ይደረጋል . . . መጀስ መለማመጃ መሣሪያዎች ተሟልተው ባይገኙም ፣ ባለው እንሠራለን ፣ እይደል ? »

«እንሠራለን ! ! » ብለው አትሌቶቹ ሲመው ፤ ሐና ንያ ፈነደቁ ።

ሰበብ እየፈጠረ ከድርጊት ንሽሽ ከሚል ሰው ፣ ባለው ለመንቀሳቀስ የሚሽቀዳደም — ለሐናንያ ቅዱስ ነው ። እንደ «ስሚት ልንም » በምድር ላይ የሚጠሉት ነገር የላቸውም ። « አላሠራ የሚልህን የስሚት ልንም በተሰህ ካልጣልክ ፣ መስማማት አንችልም » ይላሉ አዘ ውትረው ።

«የቀረውን ትልቅ ጉዳይ ላንሣው ። ወንዶቹ — ልጃነረድ የምታሸኮረሙትን ፣ ሴቶችም — ጉብል የም ታማልሉትን ይመለከታል . . . አትፍሩ ! ነውር ነው— ለማለት አይደለም ። አልወጣኝም ። ሁለችሁም ለአካለ መጠን ደርሳችኋልና አትከለከሉም ፤ ለምኑ ? አትበሉኝ . . . ልነገራችሁ የምፈልገው ፣ የወሲብ ግንኙነት ድግግ ሞሽ በማብዛት የሰውነታችሁን አቋም እንዳታኮሰ ምኑ እንድትጠነቀቁ ነው ። ከዚህ በላይ ልጨምር ? . . . አልጨምርም ! » ።

ሴቶቹ ፀፍረው እጉነበሱ ። ወንዶቹ ተሣሣቁ ። ከፊት የተቀመጠው ዓለሙ እንዴ እግሩን እየበረገደ ፣ ተተሙ እያነባበረ ይንከተከት ነበር ።

« እና . . . አሁን ዕረፍት ነው . . . ከዐሥራ አም ስት ደቂቃ በኋላ እንገናኛለን ። »

ስብሰባው ተበተነ ።

ሐናንያ ወደ ካፊቴሪያ እምርተው ፣ ቡና አዘዙ ። ዕድሚያቸው እየገፋ ሲሔድ ለመነቃነቅ ያላቸው አማ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ራጭ ይኸው ሆኖ እገኙት ። ሐሳብና ማተኮር ሲያበዙ እንጂ ፣ ቀኑን ሙሉ ቡና ሲያማስሉ አይውሉም ።

ሐሮ ፣ የማንጉ ጭማቂ ይዛ ፣ ካንዱ ወንበር ላይ ወረፍ አለች ። ወርቂ ፣ ንብሩ ... ሌሎችም ተከተሏት ።

« እሳይሻለሁ ! » አለ ንብሩ — ወይኑን ጉልጉሉ ጥርሱን እያፋጨ — ወደ ወርቂ በመመልከት ።

« ምን ትሆን ? ታውቆብሃል ! »

«እንጂ ነሻ የነገርሻቸው ፣ »

« እይ ! ... ዕውነት አውቀውብሃል ። » ሐሮ ጣልታ ንባች ።

« ይቺ መልቲ ነች ያሳበቀችው ፣ ሌላ ማን ይናነራል ?» ብሎ ንብሩ ፣ ከጠረጴዛው ሥር እጁን ለቡጢ ወጥሮ ፣ ወርቂ ጭን ላይ አሳረፈው ።

«እሪ በናትህ ! ... ሐሮ ! ገደለኝኮ ። እኔ መች ነው — የተናገርኩት ? ... ወይኔ እግሬ አልተረፈም .. » እያለች ፣ ፈቷን ኮሶ አስመስላ ጭኗን ታሻሻለች ። ቀጥላ ፣ « ሒድ ጴባህን ፈልግ ፣ ልትሰብረኝ ነው ? » አለች ወርቂ ።

« በቃ ተይው ! ... ዘንድሮ የሚስክስ ሬኮርድ ለመ ሰበር እየተሰማመደብሽ ነው ፣ ያንቺ እግር ለሱ ግር መሆኑን አጣሽው ? » አለች ፣ ሐሮ በቀልድ ።

«ብራቮ ! ሐሮ ... ታያለሽ ፈቷን ? ለድመታችን የምንገዛውን ሳንባ — ቁርጥ ነው ! » ሲል ንብሩ — ሁሉም

ተሣቁ ። ቀጥለው ... ለንጉ በለ ልጓስ ጉሪን ፣ ሪዲ ስለ ውድድሩ ... አወሩ ። ሰዓት ሲደርስ ወደ መሰብ ሰቢያው ክፍል ተመለሱ ።

« ልጂ ... ሁላችሁም መጥታችኋል ? የቀረ አለ ?» ገልመጥ ፣ ገልመጥ ብለው ከፍሉን ቃኙት — ሐናንያ ። ከቦርሳቸው ልዩ ልዩ ማስታወሻዎች አወጡና ከጠረጴዛው ላይ አኖሩት ። ገለጥ ፣ ገለጥ አድርገው ቀና አሉ ።

« ጥሩ ... አሁን ስለ አሰላለፍ እንቀጥላለን ። ምዶ ባውን ያዘጋጀሁት ፣ ከወር በፊት ባደረግነው የዝግጅት ውድድር ላይ በመመሥረት ነው ።ውጤታችሁን ታስታውሳላችሁ ። ሆኖም ከዚያ በመንደርደር እንዳንድ ለውጦች እርጌአለሁ ... ተቃውሞ በመጨረሻ ! » ሐናንያ ፈገግ ሲሉ ፣ እትሌቶቹ ተሣሣቁ ።

« ወንዶች — መቶ ሜትር — ወዬሳ ኩማ ! » —ከተ ቀመጠበት ተነሣ ።

« እሺ ... ቁጭ በል ። ድክመትና ጥንካሬያች ሁን በገሃድ እንነጋገራለን ። እኛ ባንድ ክለብ ጥላ ሥር ነን ፣ እትዘንጉ ። ድክመት ማውጣት ማለት ‘ታረሙ!’ ማለት ነው ። ከዚህ ውጭ እርስ በርስ መተራረብ ፋይዳ የለውም ... ተግባባን ? »

«ተግባባን !» ሲሉ ፣ በጩኸት መለሱ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ወዬላ ! እትቸኩል ! እርግጥ ነው መቶ ሚትር አጭር ስለሆነች ፣ ቶሎ ለመጨረስ ታጓጓለች ። ሆናም ጅግራህ ላይ ቸኩለህ ፣ ላይፈቀድ መስመሩን ካለፍክ ፣ መቶ ሜትር ለመሮጥ የታጨኸው ቁራሽኑ አንድ ሜትር ሳትሮጥ ትባረራለህ . . . »

. . . ግቅ . . . በግቅ . . . ወዬላ በተሞና ያላም ጣል ።

« ስለዚህ . . . ተዘጋጅ — በቦታህ — ተኩስ . . . እስክትሰማ ድረስ ስሜትህን መዋተ ነው . . . ከዚያ ጥቅልል እርገው ። ዋናው ፣ ስሜትህን ተቆጣጥረህ በም ታደርገው ድርጊት ላይ ግተኮር ነው . . . » እያሉ ሲያ ስረዱት ፣ በሙሉ የሰውነት ንቅናቄ እያሳዩት ነበር ።

ሐናንያ በቅደም ተከተል ዕጩ ተሰላፊዎችን እየ ጠሩ ፣ ጉድለታቸውን እንዲያርሙ እሳሰቧቸው ።

ሐሮ ፣ በስምንት መቶ ሜትር ላይ ብትጠብቅ እል ተጠራችም ። በቂ ምትክ ምስተኖዋ እትሌት ጽዮን መታፈሪያ ነች የተመደበችው ። ሐሮ ፣ በዚያ የመጨረሻ ልምድ መድከሚን እስባ '. . . ከውድድሩ ሊሠርዙኝ ይሆን ? . . . ሰፍቶ መና ? '— የሚል ጥያቄ መጣባት ።

ሐናንያ ፣ ውሳኔ ላይ ጥብት ናቸው ። መስሎ ካል ታያቸው መወላወል አያውቁም ። ሐሮ «ጉድ ሊሠሩኝ ነው ? » ስትል — ልቧ ይደልቃል . . . ሴኮንድ . . .

ደቂቃ . . . ሐናንያ ሯጮችን ዘርዝረው ጨረሱ ። ወደ ዳላዮች ሊያመሩ ሆነ ።

«ቆይ እስቲ ? . . . » ብለው ፣ ማስታወሻቸውን ወደ ኋላ አገላበጡት ።

« ቆይ ቆይ ! . . . የአሰላለፍ ለውጥ ስለ ተደረገ ነው ፣ ከወዲህ ያሠፈርኩት ። ሴቶች — ሺህ አምስት ሜትር — ሐሮ ጀቢር ። »

ሐሮ በመጠራቷ ደስ አላት ። እዲስ ምድብ ስለተ ፈጣት ደግሞ ግር ተሰኝች ። ከስምንት መቶ ሜትር ሰላይ ተወዳድራ አታውቅም ።

«እም ! . . . በሺህ አምስት መቶ እንድትሳተፊ ተደርጓል ። ይህ መካከለኛ ርቀት ስለሆነ መዝለቅ የም ትችይ ይመስለኛል ። ተምዘግዛጊ እግርሽን ታውቂዋ ለሽ ። አሁን መጨመር የሚያስፈልግሽ — ትንፋሽ ነው ። በተረፈ በሩጫ የመቆየት ችሎታሽ የሚናቅ አይ ይለም ። አይዞሽ ! እትደንግጪ ! እኔም ስወስን ብዙ አስቢበታለሁ . . . »

አበረታቷት ።

መልሳ መጠየቅ ፈለገች « የግልችለው ውስጥ ከመግባት ! » — በሚል መንፈስ ። የሆነ ነገር ያዛት ፣ ፍቢሆንስ ምናለበት ፣ እስለፋለሁ !»— በሚል ... እት ግግች ።

ሐናንያ ወደ ዘላዮች ተመለሱ ። ጂስከስ ወርዋ ሪው ንብሩም ተወርዷል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ተታውሞ አለ ?» ሲሉ ጠየቁ— ሐናንያ በመጪ ረኛ ።

ወርቁ የሚከነክናትን ጉዳይ ለመጠየቅ ፣ ጨልሌ ያየ ዶሮ ይመስል በወይኗ ተቅለበለበች ። « ሴቶች ከወ ንዶች እኩል የራሜ ጥንካሬ የላቸውም ። » የሚለው የታ ላት ወንድሟ አስተያየት ስለሚረብሻት ፣ መልስ ፈልጋ ነበር ።

«ምንም የተለየ ሐሳብ ከሌለ ይሆንኑ አብላሉት ። ለማጠቃለያው ከነገ ወዲያ እንመለከተዋለን » በማለት ሐናንያ ወደ ስብሰባው መዘጊያ ተቃረቡ ። አትሌቶቹን ከማሰናበታቸው በፊት ፣

«ማሸንፍ የማነው ?» ሲሉ ጮክ ብለው ጠየቁ ፤

« የኛ!

የኛ!

የኛ ! ... » በማለት በጩኼት መለሱ ። የያንዳንዱ ፊት ያበራል ። ወርቁም «ቆይ እጠይቃለሁ ... እይቀር !» አለች በልቧ ... ሽር ጉድ የተባለለት ውድድር ይረሰ ...

★ ★ ★

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ፍጻሜ የኖ ለው እሑድ ቀን ነበር ። አራት ሰዓት ላይ ፍንትው ብላ የወጣችው ፀሐይ ፣ ለበጎሉ የተፈጥሮ ድምቀት ፈገ ግታለታለች ።

የማጣሪያ ውድድሮች ለአንድ ሳምንት ተከናው ነዋል ። ለፍጻሜው ያለፉት አትሌቶች በቀለማት ያሸ በረቁ ካናቴራና ቁምጣ ታጥቀው ውር ውር ሲሉ ፣ በመ ስከረም ፀሐይ መስክ ላይ የሚፈነድቁ ቢራቢሮዎች ይመስላሉ ።

የአትሌቲክስ ውድድር ፣ ዓይንቱ ብዙ ነው ። ሩጫ ፣ የከፍታና የምርኩዝ ዝላይ ፣ አሎሎ ፣ ዲስከስና ጦር ውርወራን በማካተት ሌሎችንም ይጨምራል ። የኒህ ተወዳዳሪዎች ፣ ብሩህ ተስፋ ይዘው ሰውነታቸውን ለማ ሟሟት ሮጥ ሮጥ ፣ ዘለል ዘለል ፣ ቁሞ ብድግ ፣ ሐዶት መለስ ... ሲሉ ያስተናሉ ። የማሸነፍ ስሜት በሕሊናቸው ያቃጭላል ። የውድድር 'ፍትወት' ያንጠራራቸዋል ።

የአዲስ አበባ ስታዲየም በተመልካች ተጣቧል ። ካታንጋ ፣ ምስግር ተራ ፣ ጥላ ፎት ... ጠጠር ቢወረወር ሥውደቂያ የለውም ... ነጭ ኮፊያ ፣ ሰማያዊ ሸሚዝ ፣ በና ጃኬት ፣ «ጂንስ» ሱሪ ፣ ዥንጉርጉር ልብስ ... ድንት ስብር ሠርተው አያሰለቹም ።

በሜዳው የሚተመው ባንድ የሚያሰማው ማርሽ ፣ ልብ ይነካል ። ተመልካቹ የውድድሩን መጀመር ከፉኛ ናፍቋል ። የባንዱ መሪ ዱላውን (ኩማውን) በያረሰበት ቅስር ! ነቅነቅ ! ሽክርክር ! ቅብልብል ! ውርውር ! ለቀም ! ሲያረገው ፣ ደማቅ ሙዚቃ ይዘንብለታል ።

ቀጥሎ «አትሌቲክስ» በሚል ርዕስ ሰፊ ሐተታ በድምፅ ማጉያ ተነበበ ። መግለጫው ፣ የአትሌቲክስን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጥንታዊነትና የሰው የዕለት ተዕለት ተግባርነት ይዘረ
ዝራል ። እትሌቲክስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፮፻፴፭
ዓመት መታወቁን ጠቁሞ ፣ ከሰው ልጅ ሥልጣኔ ጉን
ለጉን ዳብሮ መምጣቱን ያመለክታል ።

ከስታዲየሙ እንደ ገደል ማሚቶ የሚያስተጋባው
ድምፅ ፣ ባካባቢው ጭምር ይሰማል ።

ሐሮ ጓደኞቿን መስላለች ። በማጣሪያው ውድድር
ሁለተኛ የወጣችበትን 79 ቁጥር ካናቴራ እጥልታለች ።
መደቡ ሰማያዊ ሆኖ ፣ ቁጥሩን ያዘለው ነጭ ጨርቅ ፣
የብሔራዊ ሎተሪን ዓርማ ይዟል ።

ጠዋት ከቤት ስትወጣ ፣ ከናቷ ጋር አንድ ፣ አንድ
ተባብለዋል ።

እናቷ ሁለት ሰዓት ላይ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ፣
«ደሞ ወዴት ነው ? ... በሰንበት ?»

«ምነው ? እማዬ ! ነግሬሽ ! ዛሬ የሻምፒዮና ውድ
ድር ነው ።»

«እንዲያው የማያልቅ ሻምቢዮና ! በዚህ ሰሞንማ
እቤት የማያስቀምጥ ቀምሰሻል መሰለኝ—መዞር ነው ! »

«እማይ ! በያ እንሒድ? ዛሬ የግድ መገኘት አለብሽ! »

«ተይኝ ወዲያ ! ... እንዲያው ዝም ብለሽ ፣ ልጆች
ለማየት ተከተይኝ ትይኖለሽ!»

«ዕውነት ... ዕውነት ! እማዬ—ዛሬ የመጪረሻችን
ነው ። መሔድ አለብሽ ። ዐሥሬ ከምትወቅሺኝ ፣ ዛሬ
አብረን እንሒድና ምን እንደምሠራ ተመልከቺ ! »

«ምን አይሻለሁ ! ... አሁን እዚህ ታች ለቅሶ
አስብኝ... መሔዴ ነው » ብለው እናት ጥቁር ጥለት
ያለው ነጠላ ፍለጋ ወደ ጓዳ ገቡ ።

ሐሮ እመር ብላ ተከተለቻቸው !

«እማይ የዛሬን ብቻ፣ በወለዱሽ ! ሁለተኛ እላስቸ
ግርሽም ፣ የዛሬን ብቻ ? እይው ! ሴሎቼ ዘመዶቻቸውን ፣
ጓደኞቻቸውን ይዘው ይሔዳሉ ፣ እኔስ ? ... እማይ ! እንቺ
ከሌለሽ ‘ኮ ደስ አይልም ?» ድንገተኛ ሲቃ ሲተናነ
ቃት ፣ ዐይኖቿ ረጠቡ ።

እናት ፣ የግይጋፋት ስሜት መታቸው ።

ለደቂቃዎች ዐይኗን እይተው ሲያበቁ ፣

« ይሁን እስቲ ! ... እፎይ !» ብለው ፣ ጀንጥላቸውን
ይዘው አብረው ወጡ ። ስታዲየም ሲደርሱ ፣ ሐሮ ወደ
ጓላ ከማምራቷ በፊት እናቷን እንደኛ ማዕረግ እስቀ
መጠቻቸው— በተሰጣት የጥሪ ወረቀት ።

ከድምፅ ማጉያው የሚወጣው ሙዚቃ ጋብ አለ ።
«ጀመናችን ፣ ኢትዮጵያ ለእትሌቲክስ ፣ እትሌቲክስም ለኢ
ትዮጵያ መሆኑን አረጋግጧል ...» ሲል እንቲጴን የከፈ
ው ሐተታ ፣ ስለ ኢትዮጵያ እትሌቲክስ ሲዘገብ ነበር ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«... ከ፲፱፻፮ እስከ ፲፱፻፸፭ ባለው ጊዜ ዘመናዊ አት
ሌቲክስ ሀገራችን ገብቷል። አልፎ አልፎ በአንዳንድ
ትምህርት ቤቶች ተዘውትሯል ...» እያለ ጥንተ አመ
ጡን ዘረዘረ።

«... ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሜልቦርን ላይ
በ፲፱፻፶፱ አሊምፒክ ስትካፈል አትሌቶች አመልጓለች።»
በማያያዝ «የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ወርቃማ ዘመን
በአበበ ቢቂላ ተከፈተ ...» በማለት በ፲፱፻፶፱ዓ.ም
የሮም አሎምፒክ፣ በማራቶን አበበ የፈጸመውን ገድል
አተተ። ይኸው በቶኪዮ ተደግሞ ሚሸብረቁን አስታ
ወሰ። በሜክሲኮም ግሞ ወልዱ ድል በማምጣቱ፣ ኢት
ዮጵያ ለሦስት ተከታታይ ጊዜያት የአሎምፒክ ማራቶን
አሸናፊ ብቸኛ ሀገር መሆኗን ገለጠ።

የሐተታው ጽሑፍ ቅንብር ብቻ ሳይሆን፣ በደ
ምፅ የሚያነበው ተመለመ በመሆኑ ለጆሮ እይሰለችም፣
ድምፁን ከፍ... ዝቅ ... ፈጠን ... ዝግ— ባጭሩ በዜማ
ቅላጼ ሲያንቆረቁረው፣ ስሜት ይኮረኩራል። መንፈ
ይግርከል።

አንጋፋ አትሌቶችን አስታውሶ፣ ከገጠመዋቸው
እየቀነጨበ ዘረዘራቸው። ባንጻሩም ያንጋፋዎቹን ሩ
ተከትለው ኢትዮጵያን ለውዳሴ ያበቁ ዐዋቂና ወጣ
አትሌቶችን በየተራ አነጣቸው። ያለም ጋዜጦች ቢ
ገራቸው «የደጋ በራሪዎች... የአትሌት ኮማንዶች
አረንጓዴው ጉርፍ» እያሉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች

እንደሚጠሩ ጠቅሷል ... በማጠቃለያው፣ «ከዚህስ
ይልላ እንግን ይወጡ ይሆን? የከዋክብት አትሌቶች
ምንም ከሆኑችው ሀገራችን ነው» ሲል ጠይቋል።

ውድድሮች በየፈርጁ ተጠሉ። የመቶ ሜትር፣
የአራት መቶ ሜትር፣ የጹላ ትብብል ሪሌ ... ሚጻው
መልል የአሎሎ፣ የጂስከስ ... ውርወራዎች ይታያሉ።
በሜዳንና ደቡብ ጠርዝ፣ የአግድሞሽና የከፍታ ዝላይ
ይከሬላል።

ሐሮ ለቡድኗ ልጆች ድጋፍ ስትሰጥ፣ ወጂያ ወጂህ
እያለች ስትጮህ፣ የራሷን ውድድር የረሳች ትመስላ
ለች።

ቆይቶ ድምፅ ማጉያው፣

«... የሺህ እምስት መቶ ሜትር ሴቶች ተወዳዳሪ
ዎች! ... ቦታችሁን ያዙ!» ብሎ ለፈፈ።

ሐሮ ሆዱዋ ተንቦጫቦጨ። ልቧም ደነገጠ። ሰው
ነቷ ቀለላት። እንደ ምንም ትኩረቷን ወደ ውድድሩ
ሰጠሰበች። እካሏን በፍጥነት እንቀሳቅሳ ሙቀት አገኘች።
ደንጋጤዋ ቀስ እያለ ተነነ።

«ሐሮ!... ሐሮ! ያው ነው! ተለምር ማሳየት አለ
ብሽ ... ሐሮ ብራቮ!» እያለ ገብሩ ሲጮህ፣ እነ አለባ
ቸው፣ ወርቂ ... ድምፃቸውን ከፍ አርገው እጀቡት።

«ሐሮ!... ሐሮ!...» በጩኸት።

እናቷ የልጃቸው ስም ሲጠራ፣ እንጀታቸው አል
ችል አለ። ባር ባር አላቸው። ሩቅ ብትሆንም፣ በቁምጣ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሱሪዋ ሲያዩዋት እንደ ማሽላ አገዳ የምትሰበር መ
ላቸው ፣ ባሉበት ተቁነጠነጡ ።

ሐሮ ፣ ውድድር መጀመሪያው ስፍራ ቀረበች ።
ብቻ እንድ የሆነ ነገር ቅር አላት ። መንፈሷ አመነታ ፣
እንዲያው ... ቅር ... ቅር ... ልታሰላስለው ስትል ፣

«መስመር ያዙ ! ... ተዘጋጁ !... በቦታችሁ !...»
እያለ የሚያጋፍረው ፣ የዋናው ዳኛ ረዳት ፣ ውትወታ
አቋረጣት ... ስትለማመድ ይሁን ስትወዳደር የማይ
ርቃት ፣ የሐናንያ ድምፅ ነበር ቅር ፣ ቅር ያላት ።

ተኩስ!

የመጀመሪያ ዙር ነው ። ከስምንቱ ተወዳዳሪዎች
ጋር ተደባልቃ ከመሐል ሆነች ። ትንፋሽዋን ዋጥ አር
ጋለች ። እየሩም ቀላል ነበር— አላስችግራትም ... ብቻ
ቅር ቅር ያላት ከነከናት ... ሁሉም ይሮጣሉ ።

ሁለተኛው ዙር ሲጀመር ወደ ኋላ ቀረች ። ሌሎ
ቀደሙ ። ፍጥነት የጨመሩ ይመስላል ። እጅብ ብለው
ሲከታተሉ እንዴ ሌላውን አለመተለፉ ያስገርማል ፣

«ሐሮ ! ሩጪ !... ተእምር ... » እየተቆራረጠ ይሰ
ማታል— የገብሩ ድምፅ ።

ሦስተኛው ዙር ላይ ወደ መሐል ሆነች ። ቀደ
መው ቱስ ቱስ ያሉት ከኋላዋ ቀሩ ። ሐሮ ትንፋሿን
ቆጥባለችና ፣ « አሁን በትንፋሽ መጠቀሚያ ጊዜ ነው»
የሚል ሐሳብ መጣባት ። ሰውነቷ ደህና ይታዘዝላታል ...

... እትሌቶቹ ሲጀምሩ በነበሩበት አይደሉም ።
ራት ራት ብለው ይከታተላሉ ። ፊታቸው ተኩሳትሯል ።
የተገተሩ ደም ሥሮች ወርደውበታል ።

... ሐሮ ፣ ያ ቅር ያላት ነገር ... ይረብሻታል ።

ውድድሩን በመምራት ላይ ያለችው አትሌት እራ
ቷንም ዙር ስትጀምር ደመል ተደመለ ። እጠር ቢልም
የመጨረሻው ዙር መሆኑ ነው ። ደመሉ— ሦስት መቶ
ሜትር ይቀራል— የሚል ማስጠንቀቂያ ነው ።

የሐሮ ቦታ ተለወጠ ። ሁለት አትሌቶች ብቻ
ናቸው ከኋላዋ የቀሩት ። ሌሎቹ እየተፈተለኩ ቀደሟት...

«ሐሮ!... ሐሮ !... በይ ፣ በይ ሩጪ! ሳቢ! በመ
ጨረሻ ኃይል ግፊ!.. ሐሮ ወደፊት! »

ሐሮ በጣም ፣ በጣም የምታውቀው ፡ድምፅ ሆነባት ።
እየተርገበገበ በጀርባዋ ሲገባ ፣ በሰውነቷ ውስጥ ይህ
ነው— የማትለው ጉልበት ፈጠረባት ። ያላሰበችው ኃይል
ቅልጥሟን እያነሣ ያፈናጥረው ጀመር ፤ ጨፍጋጉት የነ
በረው መንፈስ ተገፈፈ ፣ ቅር ቅር ያላት ስሜት ምት
ሀት የሰለበው ይመስል ጠፋ ... ከፊቷ የነበሩትን
ቀደመቻቸው ።

ለውድድሩ ፍጻሜ መቶ ሜትር ሲቀራት ፣ መም
ራት ያዟች ። ያ በጣም የምታውቀው ድምፅ አልጠፋ
ባትም ።

«ሐሮ ! ሰዓት ... ለሰዓት ነው ! ሒጂ ሰዓት ! »
ድምፁ ይከተላታል ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እን ወርቂ ፣ ንብሩ ፣ አሰባቸው ... ይጮኻሉ ! እት ሰማቸውም ። ብቻ ያ ሞራሷን የሚያደነድን ፣ ብርታት የሚለግስ ድምፅ ጉልበት ሆኗት ተምዘገዘገች ።

«ወይኔ ልጂን አሁን እንዲህ ሮጣ ትተርፋለች ፣ ምንስ ሰው ትሆናለች! ... ወይኔ ልጂን ! እምላኬ! እደ ራሀን!» እናቷ ብቻቸውን ያማትባሉ ።

ሐሮ ትሮጣለች ... ትሮጣለች ... ወዲያው ያ የሚ ያበረታታት ድምፅ «ተአምር ! ተአምር ነው !» አለ ፣ በለሆሳስ ።

ሐሮ የፍጻሜውን ገመድ በጥሳ እንደ ንባች ፣ ተተ መልምላ ተዘረረች ። እናቷ «ወይኔ ልጂን ! ጉድ አረገ ሺኝ ! ባደባባይ ጉድ አረግሺኝ ! » ደረታቸውን ይደል ቃሉ ። ከተቀመጡበት ተነሥተዋል ። ከተመልካቹ እየተ ጋፉ ደረጃውን መውረድ ያዙ ። ቆም እያሉ የሐሮን ሁኔታ ተንጠራርተው ይመለከታሉ ። ግምት የሰጣቸው የለም ። ሁሉም በቆመበት እንተቱን አዙሮ የሚመለከ ተው ፣ የወደቀችውን እትሌት ነው ።

... ሐናንያ ተንደርድረው ሐሮ ላይ ወደቁባት ። ደንግጠዋል ። ልባቸው ይመታል ። ትንፋሽ አጥሯቸዋል ። መንፈሳቸው ተሠውሯል ...

እነይት ። ሐሮ ተዝለፍልፋ ቆመች ። ውጤት ወደ ሚመዘገብበት ሰዓት ከሚይዘው ዳኛ ጋር ሲሐዱ ፣ ሐና ንያና ሐሮ ተቃቅፈዋል ። የሁለቱም ፊት በፅንባ ርሷል ... የሚደነፍቅ ሲቃ ከውስጣቸው ይፈነዳል ...

«ተመስገን!... ...ለ ...ን ...ለ ...ለ ...ት ። በንጠላቸው ሜፍ ወይናቸውን እያበሱ ።

ያኔ በ 4 ደቂቃ 07.31 ሴኮንድ የኢትዮጵያን ክብ ረወሰን በሴቶች መያዟን ያወቀው ሰዓት ቆጣሪው ነበር ... ከሁለት ዓመት በኋላ በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና እንደኛ መውጣቷን ያለመ ግን አልነበረም ...

አትሌቷ ...

http://ethioliberty.wordpress.com/

አ ም ሮ ት

«እሪ እንዴት ነው ? ምንድነው ነገሩ ? . . . የሚ ቀመስም የለ ? » አሉ ሙሪተኛው ደግፌ ፣ አፍንጮ በር ከሚገኘው ቤታቸው ሲገቡ ።

«ምን ጠፍቶ . . . በሙሪታ ግንዘብ ሞልቷል ! » — አፋቸውን ጠመም አርገው ባለቤታቸው መለሱ ። እንዴ የሚፈትሉትን ባዘቶ ጥጥ ፣ ቀጥለው ደግፌን ይመለከታሉ ።

«ቁርጥማቴ ተንጣብኝ መሰለኝ ! ይገተግተኛል ! »

«ከወዴት ነው ? . . . ከሥራ ? » — በፈዝ ።

«እንቺ ደሞ ! ማሽሚጠጥ ብቻ ነው የምታውቂው . . . እስቲ የሚላስ የሚቀመሰውን ወዲህ በይ ! »

ባለቤታቸው የያዙትን እንዝርት ፣ ልቃቂት ከሞ ላው አገልግል ውስጥ አስቀምጠው ፣ ወደ ግድቤት ወጡ ። ሲራመዱ የለበሻ ልብሳቸው ተንዘረፈፈ ።

«እስቲ እሳት ካለ ? . . . በሥራ ላይ ለዋለ ሰው መቼስ ምግብ ያስፈልገዋል! » አሉ ፣ ደቆን ተረግምደው ።

ደግፌ — ጀግሬ ሙሪተኛ ነኝ ፡ ባለቤታቸው ግን በዚህ ሁኔታ አልተስማሙም ። በነገር መኻል ጣል አደረጉ « ሥራ ፈልገው ወጣ ፣ ወጣ ይበሉ 'ይ » በማ ለት ይናገሯቸዋል ። በቀልድም ወጋ ያረጓቸዋል — ደግፌን ።

ደግፌ በፈናቸው ፣ « ዋ መካንነት ! . . . ከዚህ ሌላ የሰው ልጅ ጠላት — ምን አለ ? » እያሉ ፣ የልጅ ዕድል በምን ምክንያት እንዳጡ ለማወቅ ያሰላስላሉ ።

ሲመልሱ ባለቤታቸው ፤

«እሱን ይተዉት ! . . . አሁን እንደነ እቶ ክብረት ፣ እያ ተርፈላ . . . በየመንገዱ ተግትረው ወሬ እያወሩ ፣ ከቶሎ ሻጭ እየተጫወቱ ፣ ከዕብዱ እየተላከፉ መዋል ያስባሉ ? አሊያስ ፣ በየሆቴሉ ደጃፍ ጫማ እያስጠረጉ ወጪ ወራጁን በመቀላወጥ ሊዘልቁት ነው ? . . . ወንድ እንድ ነገር ይጨብጣል 'ይ ! . . . ወዲያልኝ ፣ ወዲያ ! » ይላሉ ።

'ጨትጫቃ ! ' በልባቸው ።

«ከሰሉም ተወዲል አሁንስ ! . . . የሙሪታ ግንዘብ ሚችለው እይመስልም ! . . . » ባለቤታቸው ፣ ከግድ ቤት ሲመለሱ ፣ ማንደጃውን እያቀረቡ ተናገሩ ።

« እንግዲህ ጀመርሽ ! . . . ይልቅ የሚበላውን ወዲህ በይ ! . . . ቆይ አሳይሻለሁ ፣ እኔ ደግፌ እይደለ ሁም ! »

http://ethioliberty.wordpress.com/

« አይ 'ጉድ ! . . . ቆከራ ብቻ ! »

ባለቤትየዋ ከሰሱን እያይዘው ጨረሱ ። አንድ ራስ ሽንኩርት ከትፈው ፣ በብረት ድስቱ ዘይት ጠብ አር ገው — ማቁላላት ያዙ ። ሽር ያፈላሉ ። ግጣፈጫ ቅመም መጥነው ይጨምራሉ ።

. . . ያቺን ጠባብ ከፍል እጅ የሚያስቆረጥም ሽር ወጥ አወዳት . . . ደግሌ ገርሟቸው ' ይቺ ሴት ! መች ይሆን ሙያው የሚጠፋት ? ' — አሉ በልባቸው ። መል ሰው ጉሮሯቸውን በምራቃቸው ያርሳሉ ።

« አልደረሰም እንዴ ? . . . እዚህ ቤት የተራበን ሰው የሚያውቅ የለም ግለት ነው ? . . . ሰዓቱም ወሥራ አንድ ሊሆን ነው . . . »

« ደርሷል ! . . . እስከዚያ ጋደም ይበሉ ' ይ ! »

« የለም ! ወስፋቴ ተላወሰኩ» ብለው ፣ ምራቃቸ ውን ሲውጡ ፣ ጩኸቱ ይሰማል ። « እንኳን ዘንቦብሽ ፣ እንዲሁም . . . » እንዲሉ ፣ ራብ ተጨምሮ ፣ የደግሌ አምሮት ከፉኛ ተቀሰቀሰ ። የስሜት ሕዋሳቶቻቸው ቅጽ በታዊ ግፊቶችን ወደ ሰውነታቸው ውስጥ እስተላለፉ ።

ደግሌ አንዳንዴ ስሜታቸውን መቆጣጠር አይች ሉም . . . ራብ ጀምሯቸው ምግብ ካዩ ፣ አፋቸው ደርቆ ቢኖ ይሁን ቢራ ውልብ ካላቸው ፣ አለፍ ሲሉ የምግብ ሽታ ከተሰማቸው . . . ስሜቱ እንጉላቸው ላይ ይወጣል ። መንፈሳቸው ይረበሻል ። ትኩረታቸው ይብ ተናል ።

« መጣሁ ! ይንተክተክ . . . ቃሪያ ላምጣ » ብለው ፣ ባለቤታቸው ወደ ግድ ቤት አመሩ ።

ደግሌ ጠበቁ ። ታግሡ . . . ሲቆይ ሆዳቸው ተግ ልበሙ የሚወጣ መሰላቸው ። ጊዜው ሲጎድ ስሜታ ቸው እሸንፋቸው . . .

« ወይኔ ደግሌ ! . . . መካንነት . . . የሰው ልጅ ሌላ ምን ጠላት አለው ? » በማለት አጉረመረሙ ።

አላስችል አላቸው ። ተነሥተው ፣ ከተዘረጋው የቦ ንዳ አልጋ ጉን እተኩፈሰው ሌማት እጃቸውን ዘው አድር ገው ፣ እንጀራ ይዘው ወጡ ። ያልፈላውን ሹሮ በሞ ልፋ እየጨለፉ ፣ በእንጀራው እያጠቀሱ በሉ . . . የተ ራበ ሸውላ ይመስላሉ ።

እምስቴና ስድስቱ እንደጉረሱ ፣ « ተመስገን ! . . . አሁን ይሻለኛል » አሉ ።

ባለቤታቸው ተመለሱ ።

« ቃሪያ ጠፍቶ ፣ ጉረቤት ፍለጋ ሔጄ'ኩ ነው . . . ቆየሁ ! »

« እሞ ፣ . . . ቆየሽ ! »

« ምን 'ድነው ? ይሄ የተድፋፋ ነገር ! ጭልፋው ወድቋል ! . . . ግን ከፈተው ከዳኑን ? . . . ድመቷ በላሽው ፣ ዝም ብለው ያያሉ ? . . . »

አልጋው ላይ ቁብ ያለችው ጥቁርና ነጭ ድመት ፣ « ሚያው ! . . . ሚያው ! . . . » እያለች ፣ በፊት መዳፏ ግንባሯን ታሻሻለች ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«የለም ! . . . እንዳይገነፍል ብዬ ነው የከፈትኩት ፤ — አሉ ደግፌ — የምንተፍረታቸውን ። ሆዳቸውን ቂጣ በግሰብ ብረት ድስቱን ባለመከደናቸው ተቆጪ ።

« መች ታጣዋለች ! . . . ይሄኔ ዐውቃለች ! » ሲል ልባቸው ተከራከረ ።

« እሄሄ ! . . . ገባኝ ፤ የጡረታ ገንዘብ ዝም ተብሎ አይደል የሚዛቀው ! » ገበታው ቀረበ ።

. . . አብረው ቆረሱ . . . « ተመስገን ! » አሉ ገበታው ተነሣ . . . ጨዋታ ቀጠለ . . . መሸቷል . . . ነጋ ።

« እንዲያው ሌሊቱን አላስተኛ ብሎኝ ! »

« እ . . . አመላለሰም ፥ አይደል ? »

«ይገርምሻል ፥ ምን እንዳገነገኝ ፥ ሲያመላልሰኝ ቆይቶ አስቀመጠኝ . . . »

« እኔም ጠርጥሬ አለሁ ! . . . »

« ምኑን ? እንቺ ደሞ . . . »

« ያለ ሐሳብ የጡረታ ገንዘብ መዛቁን — ለዚህም ሳይበሰል ! . . . ግብሰያውማ ሥራ ነበር ! » — ተናግረው ሳይጨርሱ .

'አሽሙረኛ' አሉ ፥ በልባቸው — ደግፌ ።

«እንቺ ደግሞ . . . ወሬሽ ሥራ ! ሥራ ! ነው ፥ እስቲ ገና በግለጻ ይሄ ሁሉ ነገር . . . ቆይ እሳይሻለሁ ።

«እናያለን . . . ፉከራ ብቻ ! »

* * *

ከሳይንስ ፋኩልቲ ፊት ለፊት የምገብ ሽቀጦች የሚቸረችረው መደብር ከዓመቱ ሁሉ ከባድ ሥራ ያለበት ይመስላል ። ደጃፉን የሚረግጡት ደምበኞች ብዛት ቢዘረዘር ፥ የወጪና የገቢ ደብዳቤ መዝገብ እይበታውም ።

የመደብሩ ሠራተኞች እንደንዝርት እየሾሩ ፥ ካዘቡት ቀን እጥፍ ጉልበታቸውን ያፈሳሉ ።

ጡረተኛው አቶ ደግፌ በዚህ መደብር ከተቀጠሩ ፥ እንዲ ደመወዝ በልተዋል ። ሥራቸው የተወሰነ እይደለም ። ወሮበሎች ሥርቆት እንዳይፈጽሙ መጠበቅ ፥ ደምበኞች ያለ ችግር ገብይተው እንዲወጡ ማገዝ ፥ ለሽያጭ የሚቀርብ ሽቀጥ ወደ መደብሩ ማስገባት ፥ መላላክ . . . ሌላም ነው ። ሁሉንም ባንዴ የሚሠሩበት ጊዜ አለ ፥ ይሄኔ ይጣደፋሉ ። በዝግታ ሲሆን እካባቢውን ከብይ በማያንስ ዐይናቸው ይቃኙታል ፥ ቆም ሲሉ ደግሞ በሐሳብ ይነጉዳሉ ።

የጎና ዋዜማ ፋታ አልሰጣቸውም ። ከግለጻ እንሥቱ ሲንደፋደፉ ነው — የዋሉት ። ካንዴም ሁለቴ ለስላሳ መጠጥ ተሸክመው ሲያስገቡ ፥ ጉንበስ ግለት ረስተው በመሰላል ካልሆነ ከግይደረስበት ጉበን ተጋጭተዋል ።

ከቀትር በኋላ የቢሮ ሠራተኞች መውጫ ሰዓት ሲሆን ፥ ያራት ኪሎ መንገድ ሁሉ ተጣበበ ። ወደ ላይ የሚወጣውን ያህል ይወርዳል ። ፀሐይዋ ሰያፍ እት

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጣጫ ይዛ — ትዋጋለች ። ልጅ ፣ ተማሪ ፣ ጉልማሳ ፣ የቢሮ ሠራተኛ ፣ የቤት እመቤት ፣ ሽበቶ ሽማግሌ ፣ ለማኝ ፣ ዘበናይ ወጣት ፣ ሊስትሮ . . . ወዘተ . . . ሁሉም ተወክለው ይገኛሉ ። ባንድ ቀለም ሳይሆን ከያይነቱ ነው ፣ ነጭ ነጠላ ፣ ጥቁር ኮፊያ ፣ ሰማያዊ ሱሪ ፣ የተቀደደ ቁምጣ፣ ወባጊ»፣ «ጀንስ»፣ ሽንሽን ቀሚስ፣ ቃታይዋን ጃኬት...

የመኪናች ተካልቦ መተላለፍ ፣ የሞተሮች ማጓራት ፣ አካባቢውን በሞተር ጢስ ያፍነው እንጂ ፣ በሙቀት ላይ ሙቀት ይጨምርበት እንጂ ፣ ልብ ብሎ የሚያስተውል አይታይም . . . ያመት ባል ስሜት ነግሷል ።

ይሄኔ በቀይ ቀለም « አዲስ ቢራ » የሚል ጽሑፍ ፣ ቢጫ መደብ ላይ የተጻፈበት ትሬንታ መኪና ፣ ከመደብሩ ተፋጠ ተንተረገ ።

አቶ ደግፈ አላስተዋሉትም ፣ ግን አይተውታል ። የነናን በዓል እንዴት እንደሚያከብሩ ሲያሰላስሉ ፣ ወዲያው ደግሞ ከባለቤታቸው ጋር ከምሽቱ አንድ ሰዓት እንደ ተቃጠሩ ፣ ዋጋው አልቀመስ ቢልም ዶሮ እንደሚያንደፋድፉ ሲያወጡ ፣ ሲያወርዱ ነበር ።

እንድ ሁለቱ የመደብሩ የሽያጭ ኃላፊ ቢጣራ አላጸመጡም ። « ምነው ! አቶ ደግፈ ! . . . መኪናው ኮ ቆሟል ! » አለ ፣ በቁጣ ሳይሆን በጨዋት ።

«ዕውነት ! ... ዕውነት ! ... ቀልቤን ምን ወሰደው» አሉ ፣ ፈጥነው 'ካሴት ቢራ' (ማጥን ቢራ) ከመኪናው እያወረዱ ። ቆልለው ከደረደሩ በኋላ በተራ ማጠጣቱን ተያያዙት ።

«ካሴቱ እየተናጠ ቢራው እረፋ ሲደፍቅ ፣ እፋፍ ይረጥብ ፣ ምራታቸው ጢም ይል ጀመር — ደግፈ» ሲትበት እምርታቸው ተቀሰቀሰ ፣ ልባቸው የፋብሪካ ጠላ ኾደለ ።

ሠርሰው « ካሴቶቹን » ቢያረድሩም ፣ ትሬንታው ከሌት ለታቸው እያጉረመረመ ቢሔድም ፣ የእፋቸው ምርጠ ቀጥሏል ። ሰውም ሲያዩ ፣ ሊስትሮ የሚያባርራቸን ውሻ ሲያዩ ፣ ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው የሚንጉዱ ኮረዳና ጉበል ሲያዩ ፣ እርሳሱ የጠፋበት ተማሪ እዩዩ ወን ሲለተው ሲያዩ ... በፖምፕ እንደሚሳብ የበረሃ ቀዛ ምራቃቸው ይመነሚል ።

እምርታቸው መሐል እናታቸው ሲወጣ «እባክህ ልጄ ! ... እንዴ ከቢራው አስጉንጩኝ ወደ ባዳ ዞር አበል ! » ብዬ ልጠይቀው አሉ ፣ የሽያጭ ኃላፊውን በማሰ ። «ለገንዘቡ እንደው ችግር የለም ፣ ሳምንት ከምት ሰጠኝ ያሥራ አምስት ቀን ሒሳብ ቆንጥርለት ግለት ነው ኮ

«ቢሆንስ ፣ እጉል ዐመል አድርጎ ቢያመናጭቀኝስ ፣ እዋርዶ ቢንሞተኝስ » — የሚል ተቃራኒ ሐሳብ መጣ ዓቸው ። «እሁን ጠጥተው ፣ ሙቀቱ ተጨምሮ ፣ ጋል ቢሉስ ! . . . ደምበኛ ሊያስቀይሙ አይደል ? » በሚል

http://ethioliberty.wordpress.com/

መልስ ፥ ራሷው በቆበቆስኩት ቢወርድብኝስ « ምን አላ ለሁ ?...» በዚህ ሐሳብ ተሸንፉ ።

«አቶ ደግፈ ! ... አቶ ደግፈ ! ... ወዲህ ! » አለ የሽያጭ ኃላፊው — ሁለት ቀን ሲያድር ነጭ ጅግት የሚያወጣውን እስክሪብቶ ጀሮው ላይ ሰክቶ ። ወዲያ ወዲህ ሲል ፥ እጀቹን በቆሸሸው ነጭ 'ጋውን' ኪሶች ውስጥ ይደብቃቸዋል ።

«እቤት ! ... እቤት ! » ብለው መጡ ። ምራቃቸው ወደ ውጪ ይፈናጠራል ።

«ይህን ዕቃ ... ለሴትዮዋ አድርሱላት ! » ብሎ በጣቱ እያመለከተ አዘዛቸው ።

የተጠቀለለ ሥጋ ፥ የታሸገ ፓስታ ፥ የቆርቆሮ አትክልት ፥ በላስቲክ የታሸገ ድንች ጥብስ ፥ ብራንዲ ጠር ሙስ ... በካርቶኑ ውስጥ አሉ ። ከጉኑ ካሴት ቢራ እነ ዲሁ ።

ያቶ ደግፈ ወይን ቢራው ላይ ተተክለ ። ቢራው የደ ፈቀው አረፋ ፥ ባለሙያ ልብስ አጣቢ የመታቸው አሞ ይመስላል ። ምራቃቸው እንደገና እየጨመረ ... እየጨ መረ ... እንደ ለሐሙ ተዝለገለገ ።

«እንዴ ! አቶ ደግፈ ! ፈትዎን ይጥረጉት እንጂ ! » ቁጣ የተቀላቀለበት ንግግሩን ሲለቀው ፥ ወይኑ እላቸው እፍ ላይ እንጣጥሮ ነበር ።

አቶ ደግፈ ፥ በደመነፍስ እፋቸውን እባበሱና ዕቃ ዎቹን ተሸክመው ወደ ሴትዮዋ መኪና አደረሱ ።

ሲጨርሱ ፥ ተመልሰው ከቦታቸው ቆሙ ። የገናን ዋዜማ ትዕይንት ያስተውላሉ ። ሰዎች ይሔዳሉ ። ከትድ በት የሚሻሙ ፥ አሰቡበት ለመድረስ የሚሮጡ ናቸው ። በታክሲና አቶቡስ ከሆነ ፥ ትዝ አይበላቸው እንጂ ፥ ከሌባ ተሻሽተው የሚሳፈሩ ... ብዙ ናቸው ።

ጊዜው ይሔዳል ... ጀንበር አትጣሜዋን በምዕራብ አድርጋ ፥ ለመጥለቅ ገሥግሣለች ። ያቶ ደግፈን እፍ ግን የመድረቅ ነገር ንክች አላረገውም ።

ዐሥራ ሁለት ተኩል ሆነ ። ዓመት በዓሉን አስታ ከው ከመደበኛው ጊዜ ግማሽ ሰዓት ቀድመው ወጡ ። ባራት ኪሎ ፖስታ ቤት እድርገው ፥ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አልፈው ቱጦታ የፒያሳን መንገድ ሲይዙ ወደ ኳስ ሜዳ የሚገሠግሥ ከሚመስለው መንገደኛ እየ ተጋፉ ቢተላለፉም ፥ አልታወቃቸውም ። ዐሥራ ምራቃ ቸውን እየዋጡ ወደ ሬታቸው ተራመዱ ።

እንዲያ ሲባዙ ፥ ሁለት የሚያውቋቸው ሰዎች «ሰላም !» ብለዋቸው ነበር ። በሦስተኛው ነው «ዘሐሪም ስጌን ! ደህና !» ብለው ፥ ላብ ያነቷበውን ቆብ ላመል ያኑት ።

አቪዮ ማደያ አካባቢ ሲደርሱ ፥ ወደ እንዲት ቡና ቤት ጉንበስ ብለው ጉራ አሉ ። ጠበብ ያለ ክፍል አላት ። ባውራ መንገዱ ከሚዘለው መኪና ሌላ የሰው ውካታ አይሰማባትም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በመጠጥ መደርደሪያው የተሰቀሉት በጣት የሚቆጠሩ ጠርሙሶች ፣ ባዶ መሆናቸው ያስታውቃል ። ኡቭ ፣ ሔይግ ፣ ጂን ፣ ኮኛክ ፣ ቢኖ ፣ ጉደር ፣ ብራንዲ . . .

አቶ ደግፈ ቆመው አጨበጨቡ ። አጠር ያለች፣ ሸግ ተሚያ ላይ ነጠላ የደረበች ሴት ፣ ኮርኒስ የምትጠርግ ይመስል ፣ እንጋጣ ፣ «ምን ልታዘዝ ?» አለምቾው ።

«እንድ ቢራ ወዲህ በይ ! ... ፍጠኝ !» አሉና ግድ ግዳውን ከተጠጋው ኩርሲ ላይ ዐረፍ ሲሉ ፣ ሱሪያቸውን ሰብሰብ አረጉት ። በግራ እጃቸው በላስቲክ የተለበደውን ጠረጴዛ ተደገፉት ።

«እሺ !» ብላ ከሌደች — ሩብ ሰዓት አለፈ ። የቢቱን ጸጥታ በመፈለግ መልክ ፣ ድካማቸውን ያጻምጣሉ— አቶ ደግፈ ። ዝር የሚል ሰው የለም ። ሰውም አይገባም፣ ልጅቷም ዓላ የምትሠራው አይታወቅም ።

አሁንም ምሬታቸውን ይውጣሉ ። እምሮታቸውን ለመወጣት አሰፍስፈዋል ። ደጋግመው አጨበጨቡ ።

ስትሮጥ መጣችና «ውይ ! አባባ ... ቆየሁ ፣ አይ ደል ! » አለች ።

«አደርሽ እንጂ . . . ጥም ያቃጠለው ጉሮሮ አታውቂም » ሲሉ ፣ ምሬታቸው ይዝረከረክል ።

«እሜቴን እንሶስላ ሳሞት ኳ ነው » ብላ ፣ ቢራውን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው ። የሲጋራ መተርኮሻውን እንሥታ ወደ ባንኩኒ ስትመልስ ፣ አቶ ደግፈ ቢራውን በመገረም ተመለከቱት ። «ለዚህ ነው ፣ እንዲህ ልቤ የተሰቀለው » በሚል ስሜት ።

ዐይናቸው ከፍት ብሎ ሲቁለጨለጭ ፣ ኬክ እስቲ ምጠው «እትንካ ! » የተባለ ሕፃን መሰሉ ።

«ክፈቺው እንጂ ! » አሉ ። ትዕግሥታቸው አለቀ ። እጃቸውን ሲያመናጭቁ ፣ ታሪያ ጥራ ሊያልቢት ነበር ።

«በግርያም ! ዛሬስ ምን ነካኝ !! » ብላ ፣ ተመልሳ መክፈት ያዘች ።

ይዝኔ የሰው ጨዝት ተሰማ — ከውጭ ። «የግጭት ፣ ያደጋ ሊሆን ይችላል» — ስትል አሰበች ፣ ከመደንገጫ ልጅቷ — የምታውቀው ድምፅ ሆነባት ።

ባንዴ ቁር ብላ ወዳውራ ጐዳናው ስትወጣ ነው ፣ የደረበችው ነጠላ ቢራውን እንሸራቶ ከወለሉ የከሰከሰው ። አቶ ደግፈ — ዐይናቸውን ወለሉ ላይ ከመወርወራቸው ፣ ወደ ቤታቸው እፍንጮ በር — አቀኑ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ዋ ዜ ማ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ካሉት ተቋማት መካከል፣ የሳይንስ ፋኩልቲ እንጋፋ ነው። በተፈጥሮ ላይ ጥናት የደገነ፣ ፍተሻ የመራ፣ ምርምር ያራመዶ ... ምሁራንን የሰበሰበ የትምህርት ማዕከል ነው።

የኬሚስትሪ ዲፓርትመንት በተፈጥሮ ምንነትና ግንኙነት ላይ ከሚጠበቡት አንዱ ነው። በአዲሱ ሕንፃ ውስጥ ጽሕፈት ቤቱንና ቤተ መከራቱን (ላቦራቷር) እያራጅቶ ይገኛል።

በዚያ፣ በርዝመት በተንጣለለ 'ኮሪዶር' ላይ ተን ቀሳቃሹ ጥቂት አይደለም። ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የጽዳት ሠራተኞች፣ ቴክኒሺያኖች ይገኛሉ።

«ፕሮፌሰር ዶክተር አሸብር ክንፉ» የሚል ጽሑፍ፣ በቢጫ ቀለም በቀጭኑ የተጻፈበት በር፣ ቅቤ የተለቀ ለቀ ይመስላል። ግጥም ያለ ነው — የሚያብረቀርቅ፣ አሁን፣ ተሰምቶ የማይታወቅ ትኩረት ስቧል።

የሳይንስ ፋኩልቲ የማስተማርና የመመራመር ተግባሩን ቀጥሏል። ሁሉም በየፊናው ድርሻውን ለማ

በርክት የሚራወጥ ይመስላል። ቢሆንም፣ በኬሚስትሪ ዲፓርትመንት የሚፈጠረውን ግናቸውንም ነገር ለማ ወቅ ይጓጓል።

በንጉት የተፈጠረው የሐሳብ ሞገድ በዲፓርትመ ንቱ ዙሪያ ይነጉዳል። እንዳንዱ የሚያዘግም ይሆንና ደንገት ፍተነት በመጨመር ይናወጣል።

... የፋኩልቲው ጎብረተሰብ እጅግ ከሚያከብራ ቸው ምሁራን፣ ዝነኛው— ፕሮፌሰር አሸብር ክንፉ ናቸው። የግቢው ጎብረተሰብ አሳቸው ስለሚያከናውኑት ምርምር እያነሣ ይወያያል። መልካም ምኞቱን ይገ ልጣል።

በፕሮፌሰሩ ቢሮ በኩል የሚያልፍ ሰው፣ ለደቂቃ ም ቆም ብሎ «... የት ደርሰው ይሆን?... ምን እንኑ...በተሳካላቸው!» እያለ ለራሱ ይጠይቃል፣ ለራሱ ይመልሳል፣ ይገምታል።

ኬሚስትሪ ሳይንስ ነው። የቁስ አካልን ስብጥና መዋቅር ያጠናል። በዚህም የሚታየውን ለውጥ ከንሰ በብ አስባቡ ይተነትናል። የመስኩ ሥነ ዘዴ መከረትና አስተውሎት ነው። በሌላ በኩል፣ ኬሚስትሪ በራሱ ለብቻው የሚጠበብ አይደለም። በሌሎች ሳይንሶች ይደ ገፋል። በውጤቶቻቸውም ይጠቀማል። የምርምር አድ ማሱን እያሰፋ፣ እያሰፋ እያሌ ጉዳዮችን ይነካካል።

ምንብ እንዲጣፍጥ፣ የእርሻ ላይ ተባይ እንዲጠፋ፣ አፈር እንዲለማ፣ የአህል ዘር እንዲያፈራ፣ ተስማሚ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ልብስ እንዲመረት ፣ መድኃኒት እንዲፈበረክ ፣ ቀለማ ቀለማት እንዲቀየጥ ፣ የኃይል ምንጭ እንዲስፋፋ ... ኬሚስትሪ ዋንኛ ነው ።

የፕሮፌሰር አቬብር ቢሮ ተንኳኳ ።

ነጭ 'ጋውን' ካልሲው ድረስ የለበሰው ፣ ዶክተር ክታቡ እንገቱን ሠገግ እርጎ አስገባ ።

ፕሮፌሰሩ አቀርቅረው ይሠራሉ ። ሐያ እራት ሰዓት ከወንበራቸው ሳይነሡ እንድ ጉዳይ ላይ አተኩረው ማጥናት እንደሚችሉ ብዙ ሰዎች ይናገራሉ ። መሰላቸትን አያውቋትም ። የጀመሩትን መጨረስ ባሕርይ አላቸው — ልማዳቸው ...

በወላሙ የፕሮፌሰር በራ ላይ ፣ « በሥራ ላይ ነኝ!... በሥራ!» የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት መሠለው— ዶክተር ክታቡን ። እንደ አገባቡ ተመለሰ ። ተመስጠው ሲሠሩ የሚያቋርጣቸውን ከልብ እንደማይቀበሉ ያውቃል ።

ፕሮፌሰር የጀመሩትን ጉዳይ በርጋታ ማከናወን ይቀናቸዋል ። የተካለበ ነገር እይሆንላቸውም ። ሲያስተምሩ ለነገ አይሉም— አይሰለቹም ።

ማስተማር የሚጀምሩት ፣ ውል ጊዜ ከክፍለ— ጊዜው ቀድመው ነው ። ይህን ፣ 'ፍሪሽማን' ተማሪዎች ፋክልቲውን በረገጡ በሦስተኛው ቀን ይሰሙታል ።

ፕሮፌሰር አስተምረው የሚያበቁት ከተሰመደው ጊዜ እላልፈው ነው ። በተለይ ፣ በጠዋቱ የመጨረሻው ክፍለ—ጊዜ የሚማሩት የፕሮፌሰሩ ተማሪዎች ፣ ምግብ ቤት የሚያርሱት ፣ ምግብ ሊያልቅ ሲል ነው ። «የአቬብር ልጆች መጡ... መጡ!» ፣ እየተባለ በምግብ ቤቱ ይወራል ፣ ተማሪዎቹ ደብተራቸውን ይዘው ፣ እጃቸውን እያወረወሩ ወንጥቀው ሲያልፉ ።

ይህን በተረዱ ጊዜ ፕሮፌሰር ፣ ከልባቸው አዘኑ ። ትልትነት በመመኘት ተማሪ ማሳጣት ፈልገው አልነበረም ፣ ትልቅ የዕውቀት ጉተራ በያንዳንዱ ተማሪ ኅሊና ለማዘጋጀት እንጂ ። «ዳግም አላረገውም !» ብለው ዝናል ይገባሉ ። ዕውቀት ያማለላቸው ፣ ምርምር ናፋቂ ዐይናች ቁልጭ ፣ ቁልጭ ሲሉባቸው—« ዳግም አላደረገውም !» ያሉትን ረስተው ፣ በኬሚስትሪ ሳይንስ ተመስጠው ያስተምራሉ ። ወደ ተፈጥሮ ምስጢር ይዘልቃሉ። ተማሪዎቹ ይከተሏቸዋል ... የምሳ ሰዓት ያልፋል ።

የፕሮፌሰሩ ትከሻ እንደ ሰንጋ ሻኛ ያበጠ ነው ። ጠረጴዛው ላይ ያለው ስልክ « ጢርር! ... ጢርር ! ጢርር!...» አለ ። የስልክ መነጋገሪያውን እጃቸው እንሱና በጀርባቸው ተንጋለሉ ። ለብቻው የሚንጐማለለው ትከሻ ፣ ቦርሜም ወይዘሮ ያስንቃል ።

«ሃሎ! ... እቤት !» አሉ ፣ በረጋ ድምፅ ።

«ምነው? ... ይሄን ያህል ሲደወል? ... ሰምን ስል ኩን እታነግም !» ከወዲያኛው ሚኖ ሽቦውን ሰንጥቆ የሚከንፈው የሴት ድምፅ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እ... እ... እንቺው ነሽ? ... ምን አዲስ ነገር መጣ? »

«ምንም! ... ግን ስልኩ ለምን ቶሎ አልተነሣም!»

«እያወቅሽ? ... የፕሮጀክቱን ሥራ በማጠናቀቅ ላይ ነን፣ 'ፋይናል' ሙከራውን ለማድረግ መሰናዶ ይዘናል፣ 'ሥራ በዝቷል' ማለቴ ነው ... በዚህ ላይ ስልክ ሲጨመርበት ይታሰብሽ! ... አሁን ምን ልታ ዘዝ?»

«ያው መከረኛ ኤድስ ነው! አይደል? ... ምናደክመህ? መድኃኒቱ ኻ ተገኝቷል! እንዲያውም ሰንብቷል! ከናንተ ቅመማ ሳያዋጣ ይቀራል ብለህ ነው?»

« ንገሪኛ? ... እኛም ፕሮጀክቱን እንሠርዘው፣ ከድካም የሚያድን ከተገኘ ማን ይጠላል?» በማፈዝ እየጣቁ ።

«እንተስ መቸ አጣኸው! ... በርበሬ ነዋ! የኤድስ መቅሠፍት መሆኑን አገር እያወራው አይደል?»

«እ... ጂ! ይኸው ነው ያንቺ ምርምር?»

«ቆይ እንጂ ልንገርህ! ... እኛን እንደው እርግና አርገህ ረስተኸናል። ዛሬ የቢጢዩን ልደት እንዳት ረሳው፣ አደራህን ማታ ቶሎ እንድትመጣ ... አባዬ! ...

አባዬ! ... ትሳለች። ፕሮጀክት እያልክ በ'ላብራቶሪ' ከሆነ አዳርህ—ቢያንስ እንግዶቹን አስብ ... ማታ በአንድ ሰዓት ነው።»

«ታዲያ ጠዋት ተነጋግረን አልነበር? ... ለሚሉኝም አልረሳም።»

«ቢሆንም ካልደጋገሙልህ ልብህ አይዘውም ብዬ ነዋ! ... ይሄ ኤድስ እያለ ምን ጤና አለ?»

«አውን ገና ዕውነት ብለሻል ... ምንም ጤና የለም!»

«የሚጠጣ ቢጤም ፈልገህ ብታመጣ ጥሩ ነው፣ ለእንግዶቹ ... ወይን ከግሮሰሪ አታጣም!»

«ገባኝ ... ቻው!»

«ወይ ጥድፊያ! ... 'ላብራቶሪ' ውስጥ የጣድከው ሊጥነፍል ነው መሰለኝ?» እንደ መሣት በሚል ድምፅ ።

«በይ ... በቃሽ! ቡና መሰለሽ?» ብለው፣ ስልኩን ዘጉት — ፕሮፌሰር አሸብር ክንፉ ።

አይ 'ሰሎሜ!' አሉ በልባቸው፣ ውሃ የመሰለውን መነጽር አውልቀው፣ በፊደልና በቁጥር እደግው ወረቀት ላይ እያኖሩ ።

'ሰሎሜ ... መሞገስና በሰው አፍ በየምክንያቱ ካልተነገች ላይሆንላት ነው? ... ለልጅ ልደት የዐየቆች መንጋጋት ምን ይሉታል? .... ከባለቤቴ ጋር ተዋወቁልኝ! የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የኬሚስትሪ ፕሮፌሰር! ... ብላ ራይን ለማስተዋወቅ እንጂ!' እያሉ ሲያስቡ፣ የስድስት ዓመቱ የትዳር ጉዞ እንደ ትላንት ትውስታ፣ ተንቀሳቃሽ ሥእል መስሎ በሕሊናቸው ታያቸው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

'አሁን ደግሞ የሠርጋችንን ልደት ላክብር ብትልስ! ሰባት . . . ስምንት . . ዘጠኝ . . . እያልኩ በያመቱ ልቆጥር?— ሰሎሜ መዝገቡ! . . . '

በጀርባቸው እንደ ተንጋለሉ ዐይናቸውን ሲያሻሹቱ። ተነሥተው ፣ በመስኮቱ እሻግረው ወደታች ተመለከቱ።

የግቢው ተማሪ ተከልኩሏል። ለብቻው ፣ በቡድን ይታያል። የአራት ሰዓት ፀሐይ የግይከመኩም የለማ!

የተማሪነት ትዝታቸው ተቀሰቀሰ . . . ድሮ የዩኒቨርሲቲ ክሌጅ ብርቅ ከሚባሉት ተማሪዎች እንዱ ነበሩ . . . ሐያ ዓመት መሆኑ ነው— በአሜሪካ ሚቺገን ዩኒቨርስቲ የኬሚስትሪ ከፍተኛ ትምህርታቸውንና ጥናታቸውን በማስታወስ ፣ ሐሳባቸው እየሞላ እየሞላ በልዩ መን ኮራኩር መጠቀ።

የፕሮፌሰር እሸብር በር እንደገና ተንኳኳ።

ፈታቸውን ከመስኮቱ መልሰው «የስ! . . . » ሲሉ፣ ሜግው ድረስ በተንዠረገገ 'ጋውን' ውስጥ የተከተተው ሰው ብቅ አለ።

«ታዲያስ ምን 'ዲቨሎፕመንት' አለ?» ብለው ጠየቁት። ከአቻዎቻቸው ጋር ሲነጋገሩ ጉራግይሌ ነው።

«ሁሉም 'ናርማሊ' እየሔደ ነው . . . ብቻ ያለንን ኬሚካል 'ኢንቴንሲቭሊይ' ከተጠቀምን እጥረት እንዳይገጥመን ነው— የፈራሁት . . . » እያለ ሲናገር፣ እጁን ያወዛወዘዋል። ምናልባት የፈለገውን ሐሳብ በእጁ ንቅናቄ ጭምር መግለጽ ፈልጉ ይሆናል— ዶክተር ከታቡ።

የኬሚስትሪን ዲፓርትመንት ዘመናዊ ቤተ ሙከራት (ላቦራቷር) የቆረቆረ ነው ፣ ዘወትር ተፍ ተፍ የሚለው ለቤተ ሙከራቱ ነው። ኪሱን እያራቆተ ቁሳቁሶች ለቤተ ሙከራቱ መግዛቱን የተመለከቱ— ትንሽ ያበዛ ዋል ይላሉ— ባልደረቦቹ። « . . . ጥቁር ሰሌዳ ላይ የኬሚካል ውሁድ እየቀየሙ 'ቦልሽን' (ብጥብጥ) መፍጠር ትዝና ነው። ኬሚስትሪ ያለ ቤተ ሙከራት ፣ ፋይዳው ውሱን ነው! »እያለ በያጋጣሚ ይከራከራል— ይሟገታል። «ተማሪ በ'ቲዎሪ' ብቻ እይሠለጥንም ፣ ሙያውን እይካንም ፣ ከሥራ የተፋታ ትምህርት ባፍንጫዩ ይውጣ! ተማሪው በቤተ ሙከራት ሙከራ እያካሔደ መማር አለበት . . . » ይላል።

« ይሄኛው . . . እንደምታውቀው ወሳኝ ነው ፣ የመናር አለመናር ነው!. . . ለኤድስ ፀር ፍለጋ መጨረሻው ድረስ መሥራት አለብን! . . . ' ፋይናል ' ሙከራ ላይ ደርሰን ማፈግፈግ ያምስት ዓመት ሥራችንን ሚዳ ላይ መበተን ነው . . . ዘርና ቀለም ለማይለይ በሽታ እስከ መጨረሻው የኬሚካል ጠብታ ድረስ መጠቀም ነውን 'ጂ! . . . » ብለው ፣ ፕሮፌሰር እሸብር ንግግራቸውን ሳያቆሙ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

«እሱማ ይገባኛል! . . . ሌሎች ፕሮጀክቶች እንዳይታጉሉ ማለቴ ነው . . . ነገሩማ ልክ ነው፣ ደግሞ የኒቨርሲቲውን የሚያስጠራና የሚያኮራ አይደል . . . »

«ብቻ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው እሱ ፕሮፌሰሩ፣ «እያንዳንዱዋን የኬሚካል ጠብታ 'ኢፈክቲቭኒይ' የመጠቀሙ ጉዳይ ነው። ብዙ ካባከንን የምንሠራው ትንሽ ነው። 'እኪ!' . . . ትንሽ ቆይቼ እመጣለሁ፣ 'ዜን እይ ሚል ሲ'. . .» ብለው፣ ተሽከርካሪው ወንበር ላይ ሲቀመጡ፣ ባለፈው ሴሚስተር ያስተማሩባቸውን ወረቀቶችና ከተማሪዎች የሰበሰቧቸውን ጽሑፎች ተመልከቱ።

ዶክተር ከታቡ በሩን ዘግቶ ይወጣ ነበር . . .

★ ★ ★

«በጀመሩት ምርምር ' ለኤድስ መከላከያ ይገኛል ብለው ያስባሉ ?» ይሄኔ፣ በመምህራኑ ክበብ ውስጥ የሚመገቡ፣ የሚዝናኑ ሰዎች ጥያቄው ወደ ተወረወረበት አቅጣጫ ዞሩ። እንደ ጥቅምት ውርጭ ተንቦካቦኩ። እንዲያውም አንዱዋ ሴት፣ የያዘችውን ሻይ ደረትዋ ላይ ልትደፋው ነበር።

'ለዚያውም በምላ ላይ እንዲህ ዐይነት ጥያቄ! . . .' —የሚል ስሜት ይነበብባቸዋል።

ፕሮፌሰር አሸብር ምላ የሚሉትን እቤታቸው እሠርተዋል።

ምስት የሰላሳ ሳንድዊች ከአምቦ ውሃ ጋር፣ ረባዳው ጠረጴዛ ላይ ይታያል . . . ጠያቂያቸውን ትኩር ብለው ተመለከቱት . . . ታደሰ ዋቅጅራ ነው። «ሳይንስ በኢትዮጵያ» የተባለ ወርኃዊ መጽሔት ያዘጋጃል። ያቀጣጠለውን «ዊንስተን» ሲጋራ ሲምግ፣ እንደ ተነፈሰ ፊኛ ጉንጩ ይሠረጉዳል። እንደ በረሃ ቁጥቋጦ ጣል፣ ጣል ያለው ጺሙ . . . ተበታትኖአል።

«ጥያቄው በእጅጉ ከባድ ነው . . . መልሱም ከውስብስብ ምርምር በኋላ የሚገኝ ይመስለኛል። በኛ ጥናት ውጤት ማግኘት አለማግኘታችን ገሃድ ወጥቶ የሚመለከረው ፍጻሜው ላይ ነው፣ ቀድሞ እርግጠኛ ያልሆነ ተስፋ መናገርት ያስገምተናል . . .» ብለው፣ ሳንድዊቻቸውን ሲያላምጡ፣ በለበሱት ነጭ 'ጋውን' ላይ የተንጠባጠበውን ፍርፋሪ ያራግፉ ነበር።

ይህን ሲያዳምጥ— ታደሰ፣ የሚንቀሳቀሰው ዐይኑ ብቻ ነው። ሴላ ነገር የተፈጠረበት አይመስልም። 'ጋዜጠኛና ዐይን' እሱ በልባቸው— ፕሮፌሰር አሸብር።

«የኢትዮጵያን የኬሚስትሪ ግሥጋሴ እንዴት ይመለከቱታል?»

«በዚህ የሚያስፈልገውን ያህል አልተራመድንም። 'ነገር ግን እያንቀላፋን ነው' ማለቴም አይደለም። ድክመታችን ግልጽ ነው . . . ዕቦዋት፣ የባሕር ሀብት ባያሌው አለን። በሁሉም አልተመራመርንም፣ አልመረመ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ርንም ! 'ፈትሸን ፣ አጥንተን ለልማት አልተጠቀም ንም ። ብዙ ግኝት ለማስመዝገብ— ጥልቅ ምርምር ያስ ፈልጋል . . . ለእንዳንድ ጅግራዎች ደግሞ ፀይን መጪ ፈን እንችልም ፣ 'ኢንክሬጅ' ግድረግ አለብን ። የምና ካሒያው ፕሮጀክት ፣ ላገር ባህል መድኃኒት የሰጠነው ትኩረት እያናትም ። በሙያ (ፕሮፌሽን) ተሰባስበን ያቋቋምነው ማኅበርም እንድ ምሳሌ ነው ። የአፍሪካን ስብስባዎች ማስተናገድ ከጀመርን ቆይተናል ። ባጠቃ ላይ ለተተኪዎችም ትኩረት መስጠት አለብን ፣ በተ ለይ ከትምህርት ቤት በመጀመር ለሙያው የሚያድ ሩትን 'በርቱ!' ማለት አለብን ፣ ታዲያ ቤተ ሙከራ ማበብ አለበት . . .» በማለት ማብራሪያቸውን በስፋት ሲይዙት ፣ በሐሳባቸው ዶክተር ክታቡ ለቅጽበት ብቅ አለ— ከቤተሙከራት መማሪያዎች መሐል ፣ እጄን እያ ወጣወዘ . . .

ታደለ ዋቅጅራ ፍጥጥ ብሎ ሲመለከት የሰው ፀይን ይወጋል ። በያዘው ቀጭን እርሳስ ፣ ማስታወሻ ሲያሰፍር— የበሬ ግንባር በምታህል ደብተር ላይ ይጽ ፋል ። ሁለት ሦስት ቃል ነው— የሚከትበው ፣ 'ቀሪ ውን ሐሳብ ባይኑ እየተየበ ወደ እንጉሉ ሳያስተላልፍ አይቀርም' ብለው አሰቡ— ፕሮፌሰር ።

ሁለቱም እንዲህ ተፋጠው እያሉ በመሀሪት ከበብ ያለው ለስለስ ያለ ውካታ ፣ ጉራማይሌ ንግግር ...

እንግሊዝኛ— ፈረንሳይኛ— ጀርመንኛ... ያለም ቋንቋ ... ሐሳባቸውን ወስዶ አላምታታቸውም ።

«በጀመሩት የኤድስ ፕሮጀክት ውጤት ቢያስገኙ ምን ይሰማዎታል?»

ፕሮፌሰር አሸብር ለዋያቄው ፈጥነው መልስ መስጠት አልወደዱም ።

'የማይጠየቅ ዋያቄ !' ብሎ ፣ ልባቸው ተቆጣ ።

ወደ ምሳ ከመምጣታቸው በፊት ፣ ከዶክተር ክታቡ ጋር የቤተሙክረቱን ዝግጅት ተመልከተዋል ። የኤድስ ቫይረሶችን ለማጥፋት ተስፋ የተጣለባቸው ውሁዶች ከልዩ ልዩ ተክሎች ተመዝምዘው ፣ ንጥረው ወጥተ ዋል ። እርግጠኝነታቸውን መስክር በቫይረሶቹ ላይ መሞከር ነው— የሚቀረው ።

በሌሎች ሀገሮች ዩኒቨርሲቲዎች ፣ የምርምር ቤቶች የተከናወኑ ፍተሻዎች ብዙ ረድተዋል ። የተከማቹት ሠነ ዶች ቢሰባጠሩ የዩኒቨርሲቲውን አጥር ያለብሳሉ ።በፈረ ንሳይ አንድ የፓስተር ኢንስቲትዩት ጠቢብ ወዳጃቸው ፣ ዲግን ቀድሞ መከላከያ መድኅን ያገኝ ይሆን ?» ሲል በደ ብዳቤ ያንግው መጠይቅ ፣ ትዝ አላቸው— ፕሮፌሰርን ።

«እንዲገኝ ጥረት የምናደርገው ውሁድ ... ፈውስ— ኤድስ ... ግለት የኤድስ 'ቫክሲን' ሆ ኖ እንዲዘጋጅ ነው ። ሙሉ በሙሉ ቫይረሶቹን የሚያጠፋ እንዲሆን ፣ በኤድስ እደጋ ላይ ለሚገኝ የሰው ዘር ፍቱን መድኃ ኒት ሆኖ መገኘት አለበት ። ይበልጥ የሚያስጨንቀንና

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሚያላስበን የምንቀምመው ውሁድ— ቫይረስ ለማጥፋት ወደ ሰውነት ሲገባ ፣ ሌላ በሽታ እንዳይጠነስስ ፣ እንዳያ ቀስቅስ 'ላይድ ኢፈክት' እንዳያመጣ ነው ! . . . ጥልቅ ፍተሻ ይፈልጋል ፣ »

«ምን ይሰማዎታል?» ሲል ፣ ድምፁ እየሩን ሚ ጠቀው— ከዚያ ቀጭን ገመድ ከሚመስል ጉርር ይወ ጣል ተብሎ እይገመትም ።

«ምን ይሰማኛል? . . . የሰው ዘር ፈውስ አገኘ ። በምርምሩ የተካፈልነውም የላቀ ውጤት ላይ ደረስን ። ቀጥሎም ሌሎች ፍተሻዎችን ከፍ ባለ ሞራል መያያዝ ነው . . . ወይም ሌላው ዓለም ቀድሞ ያገኝ ይሆናል! ግን ያውቃል ?. . . ለማናቸውም የምርምር ጥማታችንን ግርካት አለብን— በመልካም የላይንስ 'ኤቲክስ'... ሥነ ምግባር » ሲሉ— ፕሮፌሰር ድምፃቸው ከረር ብሏል ።

ዘለግ ባሉት ጣቶቻቸው በራቸውን እሻ ፎተው ቀና ሲሉ ፣ ታደሰ እርሳስና ማስታወሻውን ደረት ኪሱ ያስገባ ነበር ። ከገጽታው የሚነበብ ነገር የለም ።

«የተቃና ውጤት ከልቤ እመኝልዎታለሁ ! ውድ ፕሮፌሰር . . .» ብሎ ሲሰናበት !

እሳቸው ወደ ኋላ ልጥፍ ብለው ፣ እግራቸውን እ ባብረው የሕሊና ጉዞ ጀመሩ ... ዶክተር ከታቡ መን ኩር ቤተ ሙከራቱ በር ላይ ተቀበላቸው ...

* * *

ማምሻውን ፣ ፕሮፌሰር እሸብር በኬሚስትሪ ሊፓርትመንት ቤተሙከራት ውስጥ በባልደረቦቻቸው ታጅበዋል ...

ጨፍ በሚያስለቅመው ነጭ መብራት ሥር ፣ በነጭ 'ጋውን' ወዲያ ወዲህ ሲሉ— ጠቢባኑ— ላይን ያጥበረ ብራሉ ።

ፕሮፌሰር «ድግሪ ያግረላት ...» ሆነዋል ።

በቤተ ሙከራቱ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ ፡ «ኺ . . . ኺ ! . . . ኺ ! . . . ኺኢ ! ኺ . . . ኺ ! . . . ፉር . . . ኩር !...» ይላል ።

መልዓክ ቁሳቁሶች ልዩ ልዩ ናቸው ። ግማሽ የመሰለ ብልቃጥ ፣ የብርሌ ድስት ፣ እንደ መቃ የቀጠነ የኬሚካል ማንጠሪያ ፣ ዋጋቢ ዓይነት ማስተላለፊያ ፣ ሽክና የሚያክል ብርጭቆ ፣ ግይክሮስኮፕ ፣ ቴርሞ ሚትር ... ብዙዎቹ ከመስታዋት የተሠሩ በመሆናቸው ፣ እየተ ናለተለቁ የሚዘዋወሩትን ውሁዶች ቁልጭ አርገው ያሳያሉ ።

ከፕሮፌሰር የሚደበት አዲስ ነገር የለም ። እያንዳ ንዱ የቤተሙከራቱ ደቀ መዝሙር ፣ ላመል ለወጥ ብሎ የታዘዘውን ፣ አዲስ ያስተዋለውን ይዞ ይሮጣል—ሊያሳያ ቸው ፣ ወይም ይጣራል—ሊነግራቸው ...

እንዱ ፣ ጀግሪ የቤተ ሙከራቱ ሙያተኛ ነው ። በማም ተመስጠ እየሠራ ፣ እጁን ለረሽም ጊዜ ቆጥ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከሚያርሰው መሣሪያ ላይ ሰቅሎት አቆየው። የያም ሥ
ተቆጥተው ግትርትር አሉ ። ይህም በኬሚካሉች ው
ናጠር የተከሰተ መሰሉት ፣

«ፕሮፌሰር !... ፕሮፌሰር! ይምጡ! ይመልከቱ
ብሎ— ሲጣራ ፣ መሣቂያ ሆኖ ነበር ። በኋላ የሥነልቦ
ውጥረት መሆኑን ሁሉም ተረድተዋል ።

ፕሮፌሰር አሸብር ዝር ባሉበት ፣ ተጠባቢዎች እ
ረው ይሾራሉ ፤ ንብ እውራውን እንደሚያግከለው ነ
ነት ... ጥያቄ ፣ ክርክር— ይህ ቢሆን ያ ይታያል
ጉራግኛሌ ንግግር በየጣልቃው ይሰማል ።

«እንዲት ነው? ትላለህ ... ከታቡ!» አሉ ፣ ፕሮፌ
ሰሩ ፣ ባንደኛው ጥግ እንደ ባንኮኒ ወንበር በረዘመ
መቀመጫ ላይ ቂቢብ ብለው ።

አለፍ አለፍ ብለው የተጣሱት ውሁዶች ፣ በክ
ተኛ ሙቀት እንዲብላሉ ፣ እንዲንተክተኩ—ምድጃ
ተለኩሰዋል ። የተንቦገቦገ እሳት በመልቀቅ በቤተ መ
ረቱ ወበቅ ቢፈጥሩም ፣ የተሰማው የለም ።

«እ... እ... ከመረጥናቸው ዕፀዋት የተመዘመዙ
'ኤክስትራክት' የተደረጉት ውሁዶች ፣ የኤድስን ቫይ
ሶች በማያጓጉም ሁኔታ ለማጥፋት ተስፋ አላቸው ። የ
ኛው የውሁድ ጥንቅር ፣ ቫይረሶች ላይ ሲያርፍ የማ
ፋት አቅሙ የሚያንስ ቢሆን የውሁዱን መዋቅራ
ንብር መቀየር ይቻላል ... እንግዲህ ፋይዳ ይኖ
ዋል የምንለው ፣ መጥኑን የቀመርነው ውሁድ መ

የሰው አካል ሕዋሳት የማያጠቃ ከሆነ ነው ... ብለ
ዚህ የበኩልዎን ማጠቃለያ ሙከራ መቀጠል ይችላሉ ፤
'ፊሰንትሲይ' የተመዘገቡትን 'ፋክትስ' በተጨማሪ እዘ
ንጀቹአለሁ ፣ » ብሎ ወደ ቤተ መከረቱ ሠራዊት ተመ
ለሰ—ዶክተር ከታቡ ።

ፕሮፌሰር ፣ በዚያ ውሃ በመሰለው መነጽራቸው ፣
የተንዘረፈፈውን የዶክተር ከታቡን ነጭ 'ጋውን' ተመ
ልክተው ... የመመራመርን ፣ የተሸሸገ የማወቅን ፣
የተቀበረ የማውጣትን ፣ የተሸፈነ የመግለጥን ... ሕይወት
ቁልው የተቀበሉ ፣ ለዚህ የማይበርድ ፍቅር የነበራቸውን
ሊታወንት አስታወሱ ።

... ኒውተን ፣ ዳርዊን ፣ ኤድሰን ፣ ፖቭሎብ ፣ አይነ
ስታይን... ወደ ምርምሩ ሲያተኩሩ ፣ የፕሮፌሰሩ ልብ
እየፎከረ ... እየዘፈነ ... እየሸለለ ተንሣሣ ። ከእናታቸው
ላይ ችፍ ችፍ ያለ ላብ ሸፈናቸው ። በውስጣዊ ጉጉት ፣
ሊቃ ተገፍቶ የሚፈናጠር ይመስላል ።

የንጥረ ነገሮችን ምንነት ፣ የውሁዶችን መዋቅር
ተንትኖ ፣ ፈጣን የማመሳከሪያ ምላሽ በሚሰጠው ልዩ
መሣሪያ ፣ የቀረበውን ውሁድ—ፕሮፌሰር ተመለከቱት ።
ይህንታ በመስጠት ፣ የተገኘውን የውሁድ መዋቅራዊ
ቅንብር አጸደቁት ።

ዶክተር ከታቡ እንደገና ወደ ፕሮፌሰሩ ተመልሶ ፣
«በያንጻንዱ ንጥረነገር እንዲሁም ውሁድ ላይ
የተከናወነው የመዋቅር ጥናት ሪፖርት ይገኛል ። ከዶ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ክተር አቡበከር የተላከው የቫይረስ ስብስብ ተዘጋጀ
ቷል ... 'ቴክኒካሊ' የጉደለ ነገር የለም ... ከፈለጉ
ቢሮዬ ነኝ » ሲል ዶክተር ከታቡ ሁለት ሰዓት
ሊሆን ተቃርቦ ነበር ።

የቤተ ሙከረቱ ሙያተኞች የየድርሻቸውን አወ
ቀው ተራ በተራ ወጡ ።

ፕሮፌሰሩ የቀረበውን የቫይረስ ስብስብ በሚ
ያመች መሣሪያ ውስጥ እንረው ተዘጋጁ ። የሥነ ሕይወት
ጠበብቱ ዶክተር አቡበከር በኤድስ ከተለከፉ ሕመ
ተኞች ለሙከረት (ኤክስፐሪመንት) የሰበሰበውን የኤድ
ቫይረስ ናሙና ፣ ፕሮፌሰር አሸብር ፍተሻ እንዲያ
ርጉበት ልኮላቸዋል ። ይህ ስብስብ በውጭ ሀገር የኒቨርሲ
ቲዎች ተመርምሮ ፣ ለሙከራ አመቺነቱ ይሁንታ አ
ኝቷል ። በዚህ ላይ ስኬት መቀዳጀት ግለት ፣ ዓለም አቀ
ተቀባይነት ያለው ገድል በላይንስ አውድማ ማስገኘ
ግለት ነው ።

ፕሮፌሰር ፣ ስለ ውሁዶች መዋቅራዊ ይዘት የቀ
ቡትን ዘገባዎች በድጋሚ ከለሱ ። ግጠቃለያ (ሠመ
ነጥቦችን መሠረት አድርገው የየደረጃውን ለውጥ አመ
ክሩ ።

የኤድስ ፀር የሆነውን ውሁድ ይዞታ ደጋግመ
በማጤን ፣ ቫይረስ የማጥፋት ኃይል በማያጸግግ ሁኔ
እንዲያገኝ ፣ አንዳንድ ለውጥ በመዋቅሩ ውስጥ እያረሙ
በማያያዝም የሰውን አካል የመከላከል አቅም (ኢምዩ

ሊስተም) እንዳያናጋ ድጋፍ የሚሰጠውን ንጥረ ነገር አዶ
ልብተዋል ።

ለተም ያዘጋጁትን ውሁድ በልዩ መሣሪያ አረጋ
ጣው ፣ በቫይረሶቹ ላይ ሞከሩት ። በየደረጃው የሚሆ
ሆነውን ፣ ተያይዞ የሚከሰተውን መመዝገብ ጀመሩ —
በማይክርስኮፕ እየታገዙ ።

ሁለት ሰዓት ተኩል አለፈ ።

ማስታወሻ በመውሰድ ይወራጫሉ ። ኬሚካል የያዙ
ብልቃጦችንና ጠርሙሶችን እያነሡ በመከራው ላይ ማስ
ተከያ ያደርጋሉ ። በልዩ መሣሪያው እያመሳከሩ ፣ ግድ
ፈት ያርግሉ ። በመሐሉ ከወደጥግ ከተቀመጡት ፣ ሦስት
ይሁን አራት ብልቃጦች ተደፋፍተው ወደቁ — ወለሉ
ላይ ተከሰከሱ ። የፕሮፌሰሩ ሐሳብ እንዳለ በምርምሩ
ተውጧል ። ስለዚህ ፣ የወደቁትን አላስተዋሉም ...
ውጪት ! . . 'ውጪት ! ይጠብቃሉ ።

የመከራውን ውጤት በማይክርስኮፕ እጉሊነት
ሊመለከቱ ወደ ሞት የቀረቡ ባይረሶች ጥቂት ነበሩ ።
«ፅውንትም ፈውሱ ሊያስተማምን ነው !» ብለው ገመቱ ።
የቫይረሶቹ ሞት የመከራውን ስኬት ማረጋገጥ ጀምሯል ።

. . . በቅጽበት ፕሮፌሰር ግተኮር አቃታቸው ! ያል
ታሰበ ግቅና ደስታ ዋጣቸው . . . ፍንድቅድቅ . . . ፍንድ
ቅድቅ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በሕይወታቸው ፍርስ እስኪሉ ድረስ እንዲያ የሣ ቁበት ፣ የተደሰቱበት ጊዜ—ትዝ አይላቸውም ። በምርምራ ቸውም ትልቁን ውጤት ስላገኙ ይሆን? ፈውሰ—ኤድስን!

«ቃቃቃ!...ካካካካ!...ቂቂቂ!» ሣቅ በሣቅ—ቀጠሉ...

ሰሎሜ መዝገቡ እሳት ለብሳ እሳት ጐርሳ ቢጢን እስከትላ ቤተ ሙከራቱን በርግጓ ገባች ። የቢጢ ልደት እንዳሰበቸው ባለመከበሩ ቅር ተሰኝታ ፣ ቁጣዋን ለመግ ለጥ ተቻኩላለች ።

ወዲያው ፕሮፌሰርን እያየች አብራ መሣቅ ያዘች— ቁጣው ቀርቶ ። ቢጢም ተፍነከነከች ።

. . .ሶስቱም እየተያዩ ይስቃሉ—ፍርስ እስኪሉ ድረስ «ቂ ቂ ቂ ቂ ! . . ካ ካ ካ ! . . . »

ቆይቶ ፣ ዶክተር ከታቡ መንክር ፣ « ምነው ፕሮፌ ሰር ዝም አሉ ? . . .የት ደርሰው ይሆን ? . . . » በሚል ስሜት ሲመለስ ፣ አብሮ ሣቅ በሣቅ ሆነ ።

. . . ከብዙ ሰዓት በኋላ ነው ፣ «ናይትሮጂን እና አክሲጅን» (ናይትሮ ሶክሳይድ) የተቀላቀለበት ፣ የሚያ ሥቅ ውሁድ ከተሰበሩት ብልቃጦች በአንዱ ውስጥ መኖሩን የተረዳው— ዶክተር ከታቡ መንክር ።

ሽ ባ ጥ

ደብዳቤውን እንዴ ካነበበ በኋላ ቀና አለ ። በግን ባሩ ላይ የሚወርደው ትልቁ የደም ሥር ፣ እንደ ወፍራም ቱቦ አብጧል ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ። ልቡ ከፉኛ ይመታል ። ብው ! . . ያለ ቃጠሎ ፣ የሠራ አካላ ቱን አልብሶታል ።

ላመል ያህል በከፍሉ ውስጥ ባለው አነስተኛ መስኮት ፣ ወደ ውጪ ተመለከተ ። ሆኖም አያስተውልም ። ዐይን ብቻውን መቼ ያስተውላል ? ልብ ሲሸፍት ፣ ምድር እጽርጦ ፣ ባሕር ውቅያኖስ ተሻግሮ ወደ መጣበት ሲመለስ ።

. . . ለዚያውም በንዲህ ዓይነቱ የሕይወት መርዶ ሲሸበር ።

ከዚያ ፣ ሞስኮ መንግሥታዊ ዩኒቨርሲቲ ማደሪያ ከፍሉ (ዶርሚተሪ) ውስጥ ብቻውን ቆሟል ።

ውጪው በበረዶ ተሸፍኗል ። ንጣቱ ነጭ ወረቀት ይመስላል ። ወቅቱን « ዚማ » ይሉታል— አገራዎቹ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የዘንድሮው ግን ኃይለኛ ነው ። በወርኃ ጥር ከዜሮ በታች ሐያ አምስት ዲግሪ ሴንቲግሬድ ቀዝቅዞ አጥንት ይወጋል ። ብትን ጥጥ መስሎ የሚወርደው በረዶ የቀኑን ብርሃን ደንገዝገዝ አርጕታል ። ከተግውንና ሰማዩን አጋጥሞታል ።

ያ ብቻውን በከፍሉ ውስጥ የቆመው ጉብል ደርሶ በት በሚያውቀው ቁጭትና ንዴት ነዶአል ። ከረጅም የሐሳብ መንገዱ ሲነቃ ፣ ታላቁን የሌኒን ስታዲየም ፣ የበ ረዶው ብናኝ ቢከልለውም ፣ አቆራርጦ ተመለከተው . . . ወደ ሰማይ የቀረቡ ፣ በበረዶ የተከለሉትን ፎቆች ለደ ቂቃ ካገሩ ደሳሳ ጕጆ ጋር እንደ ማነጻጸር አረገው ።

. . . ሰባት ዓመት በቆየበት ከተማ የማያውቀው አዲስ ትዕይንት ከፊቱ የተደቀነ መሰለው ። ይህን ለማ ውጠንጠን ፋታ አግኝቶ ሳይሆን ፣ በደብዳቤው ስለ ተረዳው አስደንጋጭ ጉዳይ የሚያደርገው ባለመኖሩ ነው ።

. . . ከርቀት በሚታዩ የአገረሸ መንገዶች ፣ እደ ባባዮች . . . አገራዎቹ በርኃታ ይራመዳሉ ። ሕፃናት ይጫ ወታሉ ። ጉዳይ ኖሮት ከሚጣደፈው በስተቀር ። ግዛ በረዶው ላይ መሮጥ ፣ መንከባለል— ልምድ አድርገው ታል— እፍኝ በረዶ እያነሱ ሲወራወሩ ፣ ካንዱ ካፖርት ላይ ተፈረካክሶ ሲበተን ፣ እንደ ፈንዲሻ ይፈነድሻል ። በዚህ ይጫጫታሉ ፣ ይደሰታሉ ።

ይህ ሁሉ ያለ ሙቀት ልብስ የሚቻል አይደለም ። ነጠላ ወይም ጥንድ ካልሲ ፣ በላዩ ላይ «ቡትስ» ወይም ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን ሙቀት ፈጣሪ የበረዶ ሜማ ይጠለቃል ። ሱሪ ይለበሳል ። ለቀሚስ ሲሆን እንደሱሪ የሚሆን ወፍራም የእግር ሹራብ መጥብ ድረስ ይደረ ጋል ። ካናቴራ ይኖራል ። ሸሚዝና ሹራብ ይጨመር በታል ። ከክራባት ሌላ ፣ ዘና ያለ ኮት ይለበሳል ። ወፍ ራም ካፖርት ከላይ ይደረባል ። በእንገት ከጥጥ ወይም ከእንስሳት ፀጉር የሚሠራ «ሻርፕ» ይጠቀለላል ። ለበረዶ የተዘጋጀው ኮፈያ ፣ የጸጸስ ቆብ የመሰለው «ሻብካ» የሚሉትን መድፋት— ግዴታ ነው ።

ለሁለተኛ ጊዜ ፣ የተጣጠፈውን ደብዳቤ ገለጠው— ደንበል መኮንን ።

ይህን ደብዳቤ ያመጣለት ማስረሻ ነበር ። ሦስተኛ ጓደኛን ያጋመሰ ፣ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተማሪ ነው ።

ማስረሻ ለደንበል የመጨረሻ ወዳጁ ፣ የቅርብ አሚኖች ነው ። እይለየውም ። ሰፊ የሐሳብ ልውውጥ ያደርጋሉ ። ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ ። ፈፖርቲው ቢታ አብረን እንሔዳለን . . . ይህን ኪፖስታ ቤት ነው ያገኘ ሁት ... ብዙም አልቆይም— እመለሳለሁ ... ፣ ፓንያትና' ንባህ !» ብሎታል— ማስረሻ ደበበ ቅድም ደብዳቤውን ይዘ ሲመጣ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በዩኒቨርስቲው ውስጥ የሚገኘው ፖስታ ቤት ፣ ለተ ማሪዎቹ የተጻፉ ደብዳቤዎችን በሀገር ፣ በሀገር ለያዳ ያሠራጫል ። ተቀብለው ለተጻፈላቸው የሚያደርሱት ከሀ ሀገሩ ተማሪዎች ተመርጠው— የፖስታ ወኪል የሆኑ ናቸው ... እያንዳንዱ ተማሪ በፖስታቤቱ በኩል ሲያልፍ እንዳች ስሜት ፊቱ ላይ ይነበባል ። ይህ ግልምጽ ፣ ስው ርም ይሆናል . . . ብቻ ያስታውቃል ። ሁሉም በጋራ የሚታያቸው አለ ። ሀገራቸው ፣ የትውልድ ቦታቸው ፣ ቤተ ሰብና ቤተዘመዶቻቸው ፣ ፍቅረኞቻቸውና ጓደኞቻቸው... የፖስታ ቤቱም መስኩት ወደዚያ የሚወስድ ይመስ ቸዋል ።

የኒቨርሲቲውና ትምህርታቸውን ያልጨረሱት ተማ ሪዎች በመተባበር የመሸኛ ፓርቲ አዘጋጅተዋል— ጥናታ ቸውን አጠናቀው ለሚመለሱት ። የጋና ፣ የቪዬትናም፣ የኔ ፍጋኒስታን ፣ የኩንጉ ፣ የኢትዮጵያ ፣ የቤኒጋል ፣ የኩሎም ቢያ ፣ የጃማይካ . . . የሌሎች ሀገሮች ተማሪዎችም ይገ ኛሉ ። ዕለቱ እሁድ ስለሆነ ፣ ከሉሙምባ ዩኒቨርሲቲና ከሌሎች ተቋሞች የሚመጡ የውጭ ሀገር ተማሪዎች ይጠበቃሉ ። ፓርቲው የጦፈ ይሆናል ተብሎ ታስቧል፣ . . . ማስረሻ ከልቡ እዝኗል ። ደንበል ወደ ሀገሩ በመመለሱ ተከዚሏል ። ተቆጪው ነው ! መካሪው ነው! ማስረሻ ፣ ትዝታና ናፍቆት ሲያጠቃው ፣ የሀገር ቤት ሕይ ወት ውል ሲልበት ፣ ፈጥኖ የሚጫወተው ከደንበል ጋር ነው ።

ይሄኔ የልጅነት ታሪኩንም ፣ የቤተሰቡንም ፣ የፈ ጮችን የፍቅር ጀብዱ ፣ የወደፊት ምኞታቸውን ... እየ ዘረዘሩ ያወጋሉ ። እንዱ ሲተርክ ሌላው ያዳምጣል እግረ መንገዱን ትውስታ የፈጠረበትን ሜፍ ይዞ ይናገራል ። በማሳረጊያው ፣ ተቃልደው ፣ ተሣሥቀው ይለያያሉ ።

ማስረሻ ፣ «ይሄ ደንበል ሀገር ቤት ሲመለስ እንዳይረ ሳኝ ፣ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ !. . .» እያለ ሲፎክር ይዝው የደንበል መመለሻ ደረሰ ።

በዓለም አቀፍ ሕግ ጥናት ፣ ከፍተኛ ትምህርቱን ጻር ልድቧል— ደንበል መኮንን ።

ደብዳቤውን ጻፃም ማንበብ ጀመረ ።

የተጻፈበት ቀን ፣ ከወር በፊት ነው ። «እስቲ ... ደብ ዳቤው አንድ ቀን ቢያድርኮ . . . እዚሁ ቀሪ ነበር! ይገ ርማል ! . . .» እያለ ንባቡን ቀጠለ ።

ይድረስ ለደንበል !

ላንተ ያለኝ ፍቅርና አክብሮት ለመቼውም ቢሆን የሚታጠፍ አይደለም ። በቅርቡ ትምህርትህን ጨርሰህ እንደምትመለስ ሳስብ ፣ እንደምንገናኝ ሳልም — ደስታ በደም ሥሮቼ ይሠርፃል ። የልቤ ምት ይጨምራል ፣ ሐሳቤ በጥልቀት ይመሰጣል ።

የኔ ጌታ — ለፍቅርና ለመውደድ በምድር ላይ ያለ ኝኛ አንተ ብቻ ነህ ። ስንት መቶና መቶ ጊዜ ነው—

http://ethioliberty.wordpress.com/

ይሆን የምናገረው ! ስደጋግመው ብናር አይሰለቹኝም ፣ በሕሊናዬ ባሰብሁህ ቁጥር ፣ በወደፊት ኑሯችን ጥሩ ዕድል እንደሚገጥመን እመኛለሁ ።

መንፈስህ ሁል ጊዜ ይከተለኛል ፣ ይሰማኛል። እስኪ ዛሬ የላካቸውን ደብዳቤዎች ፣ ፎቶግራፎች ፣ ስጦታዎች ... በጥንቃቄ ነው — ያስቀመጥኳቸው ። ሐሳብ ፣ ናፍቆት ሲጣ ናብኝ እነሱን ማገላበጥ ፣ ፎቶግራፍህን መሳም ትዝታ ዬን ይከፍልልኛል ። ጉዬ ሆነህ ፣ ረዥሙ ጸጉሬን እያየ ህ 'እወድሻለሁ' የሚል ዓይነት . . .እግዚኦ !

ይሆን ያህል ዓመት በቁርጠኝነት ታግሼ እንተነ መጠበቄ ፣ ያኮራሃል — ብዬ እምናለሁ ! ግን ችሮታ ይውነ ውለታ አልጠይቅበትም ። ዓላማ ኖሮት የቆረጠ ሰው በምድር ላይ የሚሻውን ለማግኘት የማይችልበት ምክ ንያት የለም ።

'ማሩ ታገኛላችሁ ፣ ታገሉ ይላካላችኋል' — ቢሆን አትቀበልም — አባባሉን !

የጀመርኩትን የሥራ ልምምድ እያጠናደድኩ ነው። ቀጥሎም በሒሳብ ሥራ ያሰማሩኛል ብዬ አስባለሁ ፣ ቤተሰቦቼ እየረዱኝ ነው ።

ብቻ የነሱ ነገር ከተነሣ ፣ እንተን የሚያስከፋ ጉዳይ ለመፈጸም እየተራወጡ ነው ። ንዴቴን መቆጣጠር እ ቃተኝ ፣ ሥራዬ በንባ መታጠብ ሆኗል ።

ምን መሰለህ ! እንዳርሽ ነው — የሚሉት ። እንድ ሆነ ሰውዬ ነው ፣ ቤትም መኪናም አለው ። ሥራው ንግድ ነገር ይመስላል ።

ካንተ ጋር እንደሆንኩ ሳስረዳቸው ብሞክር ፣ ላግባ ቸው ብፈልግ ፣ 'የምጠብቀው ሰው አለ' ብልም — ሲቀ በሉኝ አልቻሉም ። እስካሁን ዝም ያልኩት እንዳትደና ገጥ በማሰብ ነበር ። አሁን ግን ገፍተው ሲመጡ ፣ የግድ ላንተ መግለጽ አለብኝ ።

በሽግግሉም ተነጋግረዋል ፣ ሌላውም ዝግጅት ስለ ተጋመሰ ፣ ይህ ደብዳቤ እስከሚደርስህ ሁሉም ይፈጸም ይሆናል ።

የኔ ጌታ
ለዘለዓለሙ ግን ያንተው ነኝ !
እፍቃሪህ
ሰብለ ሕይወት ካሴ

የተተየበ ነው— ሰብለ ሕይወት እልፎ እልፎ የም ታደርገው ።

«ወይ ነዶ ! ...» ሲል ደንበል ፣ የደም ሥሮቹ ግት ርትር አሉ . . . እልህ ፣ ብሽቀት ፣ ምሬት እካላቱን ተጣ ተጉት ። ተዘውረው ቆጠቆጡት ። ቆሽቱ ድብን አለ ... በቀልና ተስፋ መቁረጥ እየተፈራረቁ አንጉሉን በጠበ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ጡት ። እጁ ሲንቀጠቀጥ ፣ እግሮቹ መብረክረክ አላቆ
ሙም ። ከድጋሚ ንባቡ በኋላ ጭራሽ አገረሸበት !

ፀሰብሊቲ ... ሰብለ ... ሰብለ ሕይወት ... በሰው
ሀገር ፣ ትምህርት ፍለጋ ስንገላታ ፣ ስወድቅ ስነሣ ፣ እን
ቺኑ እንዲን ... የውበት ፣ የድምቀት ... የሕይወት ተስ
ፋዬን ሊቀሙኝ ? ... እናት ... አባት ... ዘመንና ሰውኪ
ብሎ በሕሊናው ጮኸ ።

ሆዱን እያከከ ናሮ ፣ ቦርጭ ቢጤ ጣል ባለበት ሰው
ነቱ የለበሰውን ሽሚዝ ቁልፍ ሲፈታ ፣ ነፌቱ ካናቲራ
ታየ ። በሰግያዊ ላይ ነጭ ጣል ፣ ጣል ያለበት ከራባቱ፣
ተጠምልሏል ።

ለደንበል ፣ ሆድን እያከከ ከራባት መጠምለል ፣ ለና
ሥሐ ይሁን ፣ ለመሪር ብስጭት እንድ ናቸው — እይለ
ወጪ ። ከንደኛቹ ጋር በቀልድ ሲወራረፍ እንኳ ፣ ከፈል
በራው ላይ የተተከሉ የሚመስሉ ዐይኖቹን ፏ አርጉ
ሆዱን ማከክ ይጀምራል ፣ «ደንበል የእንጉሱን መዘውር
መጠምዘዝ ጀመረ — ግሰቡን» ይሉታል ።

እዚያው እንደተገተረ ግማሽ ሰዓት ቢያልፍም ፣
እምስት ደቂቃ የቆመ አልመሰለውም ። ግስረኛ አልተ
መለሰም ።

«መሆን ወይም አለመሆን !» አለ ፣ ታዋቂውን የሐም
ሌት አባባል በሕሊናው እንደ ገደል ግሚቶ እያስተጋባ ፣

«ምናባቱ ! በመስኩት ወርጂ ወዲያ ብንላገለው ፣
ይሻለኛል !» የሚል ሐሳብ ከች አለበት ። በርግጥ ይ[illegible]ኛ

ርት ላይ ነው — ያለው ። «ቢቃ አለቀ ፣ ደቀቀ ! ... እሷ
በሌለችበት እንዴት ! እንዴት ! እኖራለሁ ? ምን ሕይ
ወት ነው ? ... የሰባት ዓመቱ መለያየት ፣ የሰቆቃው ናፍ
ቆት እንሶ አሁን እስከነጭራሹ ልንለያይ ? ... ዐይኔ
እያየ ! ... ጭለማ ! . . .»

በዚህ ሐሳብ ናላው ጭው ብሎ ሲዞርበት ፣ ለመንዙ
ሩት ከሆነ ድልድይ ላይ ወደታች የሚመለከት ሰው
ስሜት ተፈጠረበት ። ሰውነቱ ዛለ ። ከኋላው ወዳለው
ሩቂ መንበር ራመድ ሲል ፣ 'ወፈ ቆመች' እንደሚል
አነ ልጅ ተብረክርኮ እየተንገዳገደ አለፍ ብሎ ፣ ዘፍ
አለ ። ፊት ለፊት ባለው አልጋ ላይ መንጋለል ፈልጎ
ነበር ።

ጥናት ከሚያጠናበት ጠረጴዛ ላይ ፣ ትልቁን ባለቀ
ለም የሰብለ ሕይወት ፎቶግራፍ ተመለከተው ። ወርውሮ
የአመድ ብናኝ ሊያረገውም ፈለገ — « እንቺ እምቢ
ብትይ ፣ መች ይህ ጉድ ይመጣ ነበር !» በሚል ስሜት ።
... ቅንጣት አትም አጣ . . . እሷ ግን ወይን ፣ ወይኑን
ታየዋለች ።

«እንግዲህ ምን ይደረግ ? ... ዛሬ አሞኛል ብዬ
ሪፖርት ግድረግ ፣ የነገውን በረራ ማስለወጥ ፣ በመሐል
ላ መፈለግ . . .» ሲል አሰበ ። ጉዳዩን ለዩኒቨርስቲው
ኃላፊዎች እንዴት እንደሚያስረዳ ግውጠንጠን ጀመረ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በጣም በዝግታ መንፈሱ ተመለሰ ... እንደ ቆሰለ እባብ እንገቱን ደፋ ። ደብዳቤውን አጣጥፎ ፖስታው ውስጥ ከተተው ። እገላበጠው ።

የሰብለ ሕይወት ይሁን የሱ እድራሻ በትክክል ተጽፎለል ። ያገር ቤት ነው— ኢትዮጵያ— ይላል ... ግን የተደረገው ግንተም ከቴምብሩ አልፎ ፖስታው ላይ አልዘለቀም ። ... ካገር ቤት አልተላከም ።

«ግስረሻ ደበበ ? ! ... » እያለ በ'ኮሪዶሩ' ሲሮጥ— ደንበል ፣ ለዓመታት ወዳጁ የንበረውን— ሴርጌይ ጴምት ሪዩብ— ቃል ላይተነፍስ አለፈው ።

« ... ሽባጥ ... ግስረሻ ... ሽባጥ ። »

ወይኔ ልጅት !

እንደሀ ጊዜው ቢያልፍም ፣ ያለፈውን መልሰው ሊያወሱት ቀላል አይሆንም — የሚያስደስት ... የሚያስከፋ ... የሚያስቆጭ ... የሚያስት ... የሚያቆስል ... ምን ዓይነት ልበለው ? ... እንዲያው ቃላት ተሳክተው ፣ ወረፍተ ነገሮች ተኮልኩለው የማይገልጹት ፣ ልውጥውጥ ስሜት ያጭርብኛል ። ከሕዋሳተ— ስሜቴ የሚ ነነፍሱ ትኩስ የስሜት ዘለላዎች ፣ ከትዝታ ቀፎ እየተን ጠባጠቡ መንፈሴን ያምሱታል ። እንዱን— ማንሣት ፣ ሌላውን— መጣል ... በሐሳብ መብከንከን ነው— ድር ቧዬ የሆነው ።

ልንገራችሁ ። ላዋያችሁ ። ሲወጣልኝ ይቀለኝ እን ደሁ ።

በጠባብ ጭንቅላቴ ፣ ባልፋፋው አስተሳሰቤ ሕይወትን ተርጉሜ ለመተርት ፣ ለመፈላሰፍ ይቃጣኛል። ቢለው ፣ ተመራማሪ ይለኛል ። ዕውቀት በወጉ ያልቀመሰው እንጉሌ ከመሜሜቴ የተነሣ እምቡር ... እምቡር ይልና

http://ethioliberty.wordpress.com/

የትም ሳያደርሰኝ ራስ ምታት ይሰትብኛል ። ይሄኔ ... ፈምናባቱ ! የምን አበሳ ነው ?» ብዬ እርግፍ አርጌ እተ ወዋለሁ ። ታዲያ እንዳመረቀዘ ቁስል ጊዜ እየጠበቀ የሕሊናዬን ሠርን ይዞ እንደምላችሁ ያናግረኛል ።

ልንገራችሁ ። ይውጣልኝ ።

እንደኔ ከሆነ ፣ ልጅነት በጨቅላና በጉልምስና አስ ተሳሰብ መካከል የሚቧርቁበት ዘመን ነው— የሚፈነ ድቁበት ። ለነዚያ የጨቅላ ዓለም ድርጊቶች ደግ ይሁን ከፉ ይትርታ አያርጋለሁ ። ያኔ ፣ ንጹሕ ልብ ... ፍቅር ... ወዳጅነት ... በላዬ ነግሦው ነበር ።

በወጣትነት የፈጸምኳቸው ግድፈቶች ግን ፣ ጠባሳ ጥለውብኝ አልፈዋል ። እኒህም ፣ ከዓመት ዓመት እንዳል ተዘጋ ሒሳብ ተንከባለው ለሥቃይ ረመጥ ዳርገውኛልና መዘንጋት ያዳግተኛል ።

ያለፈውን አስቆጪ ከስተት ፣ ተራ ብሽቀት ይመ ስል ወደ ጉን ግድረግ አልተቻለኝም ። ስለዚህ ፣ ቁጭ ቁን ዘንግቼ ፣ እርይ ብዬ እንዳልቀመጥ በኃይሉ ተፈን ቅሉ እየወጣ ፣ ከቁጥጥሬ እያመለጠ መንፈሴን ጠትጥቆ ያሳሳዋል ። እንደኛውን ወደ ፍምነት ተለውጠ — እታ ጥሉ አልጨረሰኝ ፤ አሊያም ረመጡ ጠፍቶ— ሰላም አል ሰጠኝ ... ብቻ ንቁ እሳተ ገሞራ ሆኖ ያናውጠኛል ።

ይህም አላሳርፍ ብሎ ሲንሽጠኝ ነው— ባለፈው ውስጥ መኖርን ፣ መመላለስን የምመርጠው ።

... በትዝታ ዓለም ... በሕልም ዓለም ...

እግረ ሕሊናዬ የተመለሰውን ያህል ወደ ልጅነቴ ፣ ወደ ጨቅላነቴ ፣ ወደ እግዬ እትፍ መልሶ እንዲያደር ልኝ እማፀንዋለሁ ። ይህ ስሜት ሲያሸንፈኝ ፣ የኔ ነገር የማይመንላት እግዬ «እሸሩሩ ... ሩ! ... እሸሩሩ ! ... የኔ ምርታ» የምትለኝ ፣ ተገልጦ ይከሰትልኛል ። « ይቺ ዓለምስ ... ለምን እንደ እግዬ አትሆንም ? ለምን በእ ቅፏ ይዛኝ አታባብለኝም ? ለምን 'የኔ ልጅ' አትለኝም ? ለምን ታዋርደኛለች ? ... » እንዲህ እያልኩ በሐሳቤ ስግ ስን ፣ ለወደፊቱ እንዳች ብርታት እገኛለሁ ባልልም ፣ መንፈሳዊ እርይታ ይጠጋኛል ። «የሆነው ሆኗል! ... ያል ሆነው አልሆነም ! ... ይሽው ነው ! ... ቢቃ! » ይለኛል ግሥቴ ።

ልንገራችሁ ።

ትዝታዬን እንደ ብረት የሚያጠነክሩ ፣ እንዳንድ ቁሳቁሶች እጠገቤ ሲኖሩ ልቤ ይቆማል ። ትዝታዬም ተንድ ያወጣል ። አልፎም ሀልውናዬን ያስከደኛል ።

ፎቶ ግራፎች አሉኝ ። እንደ ነገሩ በአልበም እርጌአ ቸዋለሁ ። የጓደኞቼ ፣ የዘመዶቼ ስጠታዎች አብረውኝ ናቸው ። እንዳይለዩኝ የምፈልጋቸው የሙዚቃ ካሴቶች ጠፍተው ፣ ጉጉትና ሠቀቀን እንዳይገለኝ እሳሳለሁ ። ይሁ ንና ፣ ከያይነቱ ዕቃዎች ተፈትልከው ያጣኋቸው ፣ ሰዎች አውጪን ብለው ቀልጠው የቀሩብኝ በቁጥር አይደሉም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የሚገርመኝ ፣ ለምን እንደ ሰበሰብኳቸው አይገባ ኝም ... በሔድኩበት ተከትለው መንፈሴን እንደ ላስ ቲክ ይወጥሩታል ። እንደ ፈለጉት ሐሳቤን እመላትለው ስላም ይነሡኛል ። ልሸኛቸው አስብና ከየሥርቻው ፈላ ልጌ ፣ አውጥቼ ልወረውራቸው እዘጋጃለሁ ። እነሱን በግ ጥፋት የመንፈስ ነጻነት የምቀዳጅ ፣ የትዝታን ባርነት የማሸቀንጥርና በእርነት የምተካ ይመስለኛል ። ወዲያው ሌላ ምንደኛ ሐሳብ ይወረወርና ፍ... ለምን ? ለምን ! ... እንጂ ቀልበ ቢስ !» እያለ ይኮረኩመኛል ።

አውን አትም የለኝም ። ተጻክሜአለሁ ። ከመንፈሴ ተምዘግዝጉ ይወጣ የነበረው ጥንካሬ ከድቶኛል ።

... ኤጭ ! ይህ ከምላስ የቀጠነ ፍራሽ ደግሞ ... ወለል ላይ ሲያነጥፉትማ አይመችም ። ቆረቆረኝ ... ቆይ ትራሱን ከሥሬ ላርገው ፣ አውን ይሻለኛል... እርይ !

እናም እኒያ በመንፈሴ የሚጫወቱትን ቁላቁሶች ሬት ለሬቴ ደረደርኳቸው ... ምን ላድርግ ?

ልንገራችሁ ። ይውጣልኝ ። እስከ መቼ አፍኛው እኖ ራለሁ ?

★ ★ ★

... ይሄ የስድስት ዓመት ፎቶግራፌ ነው ። አጭር ፣ ወፍራም ነኝ ። እግሬ የደጋን ቅርፅ ነበረው ። አይ ዐይ ንና አፍንጫ ! ... እርስ በርሱ ተጎዳብሮ በየት በኩል ይለያል ! ተድቦልቡያለሁ ። አይ ጊዜ ! ... እንደልብ የሚ ዘለልበት ነበር — የየዕለቱ እንጂ የጓሊዮሽ ይሁን የወ ደፊት ምናም የሌለበት ። በራስ ውስጥ ደስታ መፍጠር ፣ ባህባቢ ደስታ መፍጠር ... እንደዋዛ ሁሉም ደስታ ይሆ ናል ... ደርሶ ፍንድቅድቅ ማለት ። ልጅነት ።

መጀመሪያ — መውደቅ ... ማልቀስ ... አባብሱኝ ማለት ... መሞላቀት — እንደኛው ገጽ ነው ። ወዲያው ደግሞ ፣ ጠብ ያለኝ ምራቅ ሳትደርቅ ... መደባደብ ... ወሬት .. ማኩረፍ ... መጠፋጠፍ — ሌላው ገጽ ይገለ ጣል ። በዚህ ብቻ መች ያበቃና ። የነበረው እንዳለነበረ ይሆናል ። ሽኩቻውን ወደ ጉን እርግፍ አርጉ — መታ ረቅ ፣ እጅና ጓንት ይመስል — መተቃቀፍ ... እንኮኮ በሉኝ ! — ሁሉም ተረስቶ ይመጣል ።

'ልጅነቴ ! ... ልጅነቴ ! — ማርና ወተቴ ...' ይዘ መራል ።

አይ ያ ድንቅ ዘመን ! ምናለ ሁሌ እንደዚያ ሆኜ ብኖር !

አ ! ይሄኛው ደግሞ ሚኒስትሪ ልንፈተን ስንል የተ ነጣነው ነው ። አቤት ... ምንኛ ደስ ይላል !

ሰላማዊት ፣ እልፌ ፣ ሰሚራ ፣ ከፈለኝ ፣ ምሥራቅ... ዕውነት ይህን ያህል ደስ እንላለን ? ... ኤይ ! የውሪ ዓለም ምኑ ያስደስታል ? ... እም ! የትምህርት ቤታች ንም አጥር አብሮ ይታያል ። ዘበኛው ጋሼ ደላለኝ በረ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ፈደብን ቁጥር እዚህ ነበር የሚያንበረክኩን ። እይ ዱላ ... ልጆቻቸውንም እንዲያ ይገርፉ ይሆን ? ታዲያ ከዚ ታቸው በላም አልነበራቸውም ። «ከሚስታቸው መነታ ረክ በዝቶባቸው ፣ ግሮቱ ሲካረር ተሰያዩ» — ተባለ ። «አህያውን ፈርቶ ዳውላውን» እንዲሉ ፣ በሚስታቸው የቋጠሩትን ንዴት እኛው ላይ ነበር የሚለቁት — ጋሼ ደሳለኝ ። ጠብጥበው ጨረሱን ... እግዚኦ ! እትም ህርት ቤት በየክሪምቱ ከሚተከለው ዛፍ ልምጭ እቆርጣለሁ ሲሉ ፣ መዓት ጊዜ ከጻይሬክተሩ ተጋጭተዋል ። እስቲ በጎዛኛቸው ! ... ልጆች በመደብደብ እልህ መወጫ ያገኙ ይመስል ፣ ያን ሁሉ ጥፋት መፈጸም ነበረባቸው ?

ውይ እልፌ ! . . ምን ትመስላለች ? ... ኮሳሳ ! እነ ጻያው የፊት ቅላት ብቻ ነው — ያላት ፣ ይታወሰኛል ። «ሐይ ስኩል» ስትገባ ፣ ባልትና መርጣ ማጥናት ያዘች። የሚገርመው ፣ የባልትና ተማሪዎች እፍኝ በማይሞሉበት ወቅት ደፍራ መማሯ ነው ። ሌሎቹ ተማሪዎች ፣ የባል ትና ተማሪዎችን ሲወርፉ ፣ « ... ወጡ ጣፈጠ ? ቅመም እንሰው ? እንዴ ! ... ጨው በርከት አርጉበት ፣ አልጫ አልጫ እንጻይል ... » እያሉ ሲያፌዙባቸው ፣ ፍንክች የማትለው ዕልፌ ነበረች ። ውስጣዊ የመንፈስ ጥንካሬ ያረገዘቸው ያኔ ሳይሆን ይቀራል ? ... ቆይቶ ፣ የሆቴሎ ችና ቱሪዝም ኮርስ አዲስ እበባ ተከታተለች ። በኋላ «በሆራ ራስ ሆቴል— ደብረ ዘይት ሥራ ያዘች » አሉ ፣

ወይ እልፌ ፣ ያኔም « ኤሌመንተሪ » አብረን አያነን ዕቀታ ዕታ» ጨዋታ የሚችላት ግንም አልነበረም ጨዋ ታውንም የተወችው ልጃገረድ ከሆነች በኋላ ነበር . . . እንዴ ፣ ሆነችውን ግን አልረሳውም ። ግን ነበሩ? ቲቸር አስደስቷፈተና ሰጡን ። ስንሠራ ፣ «ከናት ደብተራችሁ ትኮርጃላችሁ» ብለው ሁለት ልጆች ከክፍል አባረሩ ። ተናለው እልፌ ላይ እንዳፈጠጡ ቆዩ ። እፌት ካለው ‘ዴስክ’ ስለምትቀመጥ ፣ መንቀጥቀጧን ብዙዎቻችን ፣ አይተናል ። ከዚያ እየተጠጓት ... እየተጠጓት ቀርበው ዐይና ላይ ተደቀኑ ። እጇቸውን ‘ዴስኩ’ ውስጥ ሰደዱት። ወጂያው በጣታቸው ቦርሳዋን ሲበረብሩ ... ቆርኪ ፣ እሻ ንጉሊት ፣ ቅጠላ ቅጠል ፣ የተጠለፈ ጨርቅ ፣ የከረሜላ ልጣጭ ፣ የሲጋራ ፓኮ የ« ቃ’ ቃ » መጫወቻዎን ፣ አንድም ሳይቀር እወጡት ።

«ቲቸር ! ... ካሻንጉሊቷ ኮርጃ ይሆናል ! » ሲል እጇቱ በጩኸት ፣ ከፍሉ ሣቅ በሣቅ ሆነ ። ቲቸር አስረስ አፍረው ዋጡት እንጂ ፣ በልባቸው መንከትከታቸው ያስ ታውቃል ። ዐይናቸው ፈጠ ፣ ተይፈርኩ በሚል መንፈስ ከፈለኝን በእልህ እንበረከኩት ። ወይ እልፌ ! . . ያ ሁሉ ዝላይ ፣ ጨዋታ ተረስቶ ዛሬ ቁም ነገር ብቻ ሆነ። ልጆች ወልጻ ከብጻ — ቤተሰብ ይዛለች ። ምን ይታሰባት ይሆን፣ ይሄ ሁሉ ትዝ ሲላት ?

አ ሰላም ! ... ሰላምማ ገና ያኔ ምኑንም ሳታውቀው፣ እኛም ምኑንም ሳንለይ «ሳይሞቅ ፈላ» ነበረች። እቤት

http://ethioliberty.wordpress.com/

የፋሺን ነገር ! ፋሺንና ሰላም ሰምና ጨርቅ ነበሩ።እነጋገር — ከዚ ፣ አሰባበስ — ከዚ ... የሊፕስቲኩ ፣ የጸጉሩ አሠራር እይነገር ! ምን ታርግ ? እሷ ፣ እሀቷ ነች እስ ታጥቃ የምትልክብን « እኛም ዐይናችንን እያቁለጨለ ጭን እንቀበላታለን « በልጅነት ሕሊናችን ፣ የምታሳየን እናደንቅላታለን « የምታወራልንን ፣ 'አሜን' ብለን እንተ በላታለን «

እንዲያው ያኔ «ጆሊ» ለመሆን ለሚፈልግ ፣ የቅርፃ መካሪ ነበረች «

እቦ !ስንቱን ወንድ ነው — ያደባደበችው ... እካ ካካ ! ... ግን እግኝቷት ! ... ብቻ «ደርሶ የኔ ነች ! ቤ ነች !» ባዩ በዛ እንጂ « ግን ከሁሉም የሚያሥቀኝ 'ሚ ተራችን' ነው « ሰውነቱ ግዙፍ ነው « ዕድሜውም ቅልት መሆኑ ያስታውቃል « ወንዶቹ የሱን ግብጻነት እያዩ ፍራቻ እንዳደረባቸው ተረድቶ ፣ «ሰላም የኔ ነች ! » እያለ ሲፎልል ፣ መልሶ የሚቃወመው የለም « ሰላም እሷ በበኩሏ ሌሎች እንዳያስቸግሯት ፣ እይዞህ ትሰዋለች ፣ ታዲያ 'ኮ ሽንት ቤት ድረስ ሳይቀር እስከትላው ፣ ደብ ተሯን እስይዛው ጉዳይዋን ፈጽማ ትመጣ ነበር« ምስ ኪን ሁሴን ! ... ጅሎ ! ... የሚያናድደው ለወንዶቹ የሚ ዘከዝክላቸው ውሸት ነው « «... ሰላምን እስከ ቤቷ ሸኝ ኋት ፣ ከዚያ ሻይ ተጋበዝን ፣ አውርተን ሥቀን ተጨዋ ወትን « እቤት እናቷ ሲወዱኝ ! » ይላቸዋል « ወገኛ !

ናና አጥሩን ሳይጠጋ ውሻ እለትበታለው » ነበር— የምትለው ፣ ሰላም « ያደረገችውን ሁሉ ለኛ ስትነግረን፣ ፍርፍር ብለን እንሥቃለን ... ምስኪን ሁሴን ! እሁን የት ደርሶ ይሆን ? ... እንደ ዘመዶቹ ንግዱን ያጧጡፍ ይሆናል «

ሰላማዊት ባገር ብዙም አልቆየች « «ሐይ ስኩል» ንብት ሳትጨርስ ነው — ዘመዶቿ ወደ አሜሪካ የወሰ ዷቸው ወይ ትግራለች — ሁኔታው ከፈቀደላት ፣ ወይ በኑ ርዋ ትጨሳለች — ሥርቻ ከወደቀች «

ሚሬ ከሁሉም አምሮባታል « እርጋታና ሥርዓት ላይዋ ላይ ወፍረዋል « የዋዛ አይደለችም « እንደቀት የነ ቃች ፣ እንደ ኤሊ የረጋች ትመስለኛለች « ትምህርቱን ስትጀመድድ ፣ እንደ ልግዲ እንደኛ ስትወጣ ፣ «... እኛ ይቅርብን ! እንቺ ብቻ ተማሪ ! ያውልሽ ! ...» ብለን ሳና ዕብ እንተራለን ? — ይገርመኛል « ለዚህም ነው « ቀለ ሜየ» እያልን የምንጠራት ... እንዴ ... የላይንስ 'ቴስት' ስንወስድ «እላስኮረጅሺኝም» ብሎ ፣ እሸቴ ደም ፀደም እርጎ የደበደባትን ዛሬም አልረሳውም « እሸቴ ለራሱ የለየለት ወሮበላ « ብይና ጠጠር ማን ሊያላድድ ልት ኖሯል ? ሞርና ቀስት ተጫውቶ የበላውን ብይ በት ርፍ ሲቸረችር ፣ ከሒሳቡ ሳንቲም የማያላልፈው ፣ ከፍል ውስጥ የሒሳብ መልመጃ መመለስ አቅቶት ሲደናበር ፣ ዐይኑ እንደ ብይ ይሽከረከር ነበር « ምን ያረጋል ? ዕው

http://ethioliberty.wordpress.com/

ቀትንም ሆነ ጥበብን በዱላ ወይም በጉልበት ሊያጠ
ጣው አልቻለም። ሠሚራን ዐሥሬ ቢያስፈራራትም ፣ ጉብ
ዝናዋን አልወረሰም።

የሠሚራ ትምህርት በላይ በላዩ ቀጥሎ ፣ ዛሬ ትልቅ
ደረጃ ደርሷል ነው — የሚሉት። ለዛውም ሴት እምብ
ዛም ባልደፈረው በኤሌክትሪክ ምህንድስና መስክ ነው—
የነገሠችው። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንብታ ስታጠና
ብቸኛ ሴት ነበረች። ብርትም ፣ ጌጥም መስላ ስለታየች፣
ሁሉም ይንከባከባት ነበር። ይህም በትምህርቷ እንድት
ገፋ አግዟታል። በሥራ ዓለም ተሠማርታ ረጅም ጊዜ
ሳትቆይ የውጭ ትምህርት ዕድል አገኘች። በዚህ ወደ
ስዊድን በመሔድ የኦክትሬት ዲግሪ ተቀበለች ... ወይ
ሠሚራና ዕድሏ ! ሌላ ምን ልበል ? ለመሆኑ ዕድል ይና
ርበት ይሆን ? እሁን ፣ እንደሷ የተማረ ፣ የተመራመረ አገ
ብታ ትኖራለች። እቤት ስታስቀና !

እንዲያው ያ ከፈለኝ የት ደርሶ ይሆን ? ... ለራሱ
አፈጣጠሩ የሚገርም ነው። ሥራውም ሐሳቡም ከወገ
ዶች የራቀ ነበር። በተጨማሪ ተጨዋችና ከሰው ቀራቢ
«ሶሻየብል» የሚባል ዓይነት ነው። በዚህ ላይ የሴት
ሥያ ሲበዛ ይቀናዋል ... እስቲ ከየት አመጣው ይል
ላል ? መቼ ነው ? ... እንዲ የወላጆች ቀን ተከበረ ፣
የእጅ ሥራ እስተማሪያችን 'ጉበዝ' በማለት ፣ ያመሰ
ውን ተቀብለው ፣ በኤግዚብሽኑ እንዲታይ እደረጉት ፣
በተከታዩ ዓመት ትምህርት ስንጀምር ፣ በትድሚያ በ

ንዶች ተማሪዎች የተወረፈው ከፈለኝ ነበር። «እንት
አለዳቢ ! ... ሴት እረከን አይደል ? አሁን ከኛ ጋር እዚህ
ምን ትሠራለህ ? ሒድ እናትህ ጓዳ ፣ እዚያ ጥጥ ፍተል !»
እያሉ መድረሻ አሳጡት ... እይ ከፈ ሙያተኛው ! ...
ያት ነው ያልኸው ?

የሥራት መድረሻ ብቻ አልገባኝም ... ነፍስ
ያወቁ ተሜዎች ነበረች። መጣት ሥራዋ ነው። ዕውነት
ስትሥቅ ሁሌም ደስ ብሏት ይሆን ? ሲያበሽቋትም ትሥ
ታፀች። ምን ዓይነት ስጦታ ነው ? አስተማሪ አጠፋሽ
ብሎ ሲገርፋት ፣ ከዛም እቀርቅራ በማልቀስ ሲወጣላት፣
ሁሌንም ቅረላለች። እንደገና ጣቂታ ፣ ፍልቅልቅ ትሆና
ለች። የምትገርም ፍጥረት ! ከሚኒስትሪ ፈተና በኋላ
የውፃ ሽታ ሆነች። ስለሷ ምንም ፣ ምንም ወሬ አጣሁ !

እኔግ እኔው ነኝ። ሠርክ ዓለም። የናትና ያባቷ
ልጅ። ኗ ዐሥራ አምስት ዓመት ያለፈኝ ሰሞን ይሰ
ማኝ የነበረው ስሜት አሁን ድረስ ይታወሰኛል። ሰው
ነቴ ከላሊት በሽታ የያዘው ይመስል ፣ እብጥብጥ አለ
ብኝ። ታጂያ ቤት ውስጥ ደልቶኝ ፣ አግርሙ በልቼ አይ
ደለም። ዝም ብሎ ነው። ብቻ ሰውነቴ ለራሴ ደስ ፣ ደስ
እያለ ሲያስጉመዠኝ ፣ መቁነጥነጥ ... መንቀሳቀስ ...
ሰውነት መስበቅ — ዘራብኝ።

የጡቴ ነገር ይገርመኛል። «ወያፈት !» እንደ ተባለ
ሳንዝ የወደረ ወታደር ቅስር ግለቱ ፣ ለኔም በታወቀኝ
ጊዜ ያሳፍረኝ ነበር። ባመት እንዴ የሚገዛልኝ ቢሆንም ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

የልብሴ ነገር ነፍሴ ነው ። ታዲያ እማዬ ፀተይ ልጂ ... በልክ አርጊው ፣ ሰው ዐይን መግባት ደግ አይደለም ፣ እያለች የሞንቶቷን ትመክረኝ ነበር ። ሆኖም ለምክሯ ደንታም አልሰጠሁትም ። ያሻኝን መርጫ ፣ ከሰውነቴ የተጣበቀ እንዲመስል በግድረግ አሰፋዋለሁ ። ... ሰው ነቴን እስብታለሁ ...

በያጋጣሚው የማነኛቸው ወጣቶች ባዩኝ ቁጥር ያልተለመደ ነገር ከፈታቸው ላይ አሳዩኝ ። መጀመሪያ መጀመሪያ ፣ 'በኔ ላይ ጥላቻ አድሮባቸው ይሆን ?' ... ስል ገመትኩ ። ሲቆይ ግን ፣ የሚዘፍኑውን ሰውነቴን በተ መለከቱ ቁጥር መቆጣጠር የማይችሉት ስሜት ከውስጥ እየነነፈሰባቸው መሆኑን ተረዳሁ ። ወይ ወንዶች ! ቦታ እንኳ አይመርጡም ... ዐይናቸው ትብዝብዝ ፣ ቅልብ ልብ ፣ ቁና ቁና ትንፍስ ፣ ምራቅ ዋጥ ፣ ዋጥ ፣ ከንፈር ልምጥ ... ደስ የሚል ትርኒት ነው ። ያኔ ? እም ! ... አሁን ግን ሳስበው አልፈርድባቸውም ፣ እዝንላቸዋለሁ ።

ሰበብ እግኝቶ ሰውነቴን መጉንተል የሚፈልግ ወንድ በዛብኝ ። በሆነ ምክንያት ብሽቅ ብዬ ፣ ወይ ስሜቱ ጨዋታ አልፈቅድ ብሎ ሞምድድ ሲልብኝ ... እጎንል ሲደባብሱኝ ፣ እነሩን በጩኸት እደበላልቀዋለሁ ።

ሆኖም ጥቅሻው ፣ ጥሪው በረከተ ። ምክንያት ሰጥቶ ... 'ልከተልሽ ?' ... 'ቢመችሽ በዚህ ቀን እዚህ ቦታ— ልጠብቅሽ ?' ... እያሉ ቀጠሮ የሚያስመዘግቡኝ ጥቂት አልነበሩም ።

ሰውነቴ ይሀን ያህል ወንዶች እርበድባጅ መሆኑ ሲገባኝ ፣ ሞራሉ ጠነከረ ። ኃያልነቴን ተገንዘብኩት ። የተ ለየሁ ፣ የማይደረስብኝ ፣ የማልቀመስ ፣ ሁሉም የሚያመ ልክኝ ... እየመሰለኝ ፣ ተኩራራሁ ። ብዙም ሳልቆይ ኖኗ ንር እንደነገሩ ሆነ ። ወይኔ እማዬ ! እንዲህ ወድቄ ሚኖረን የወሬ ወሬ ሰምተሽ ከሆነ ፣ ምን ትይኛለሽ ? ... ውነቴን እኮ ? ... እማዬን ባንግት ፣ ያኔ ከሐረር ስወጣ የከጠቹኝ መርጠ ታወሰኝ ። በሰማያዊና በወይን ጠጅ ደርብ ቀለም የተሸለመ ነው ። ይኸው ዐሥራ አንድ ዓመት ሙሉ አብሮኝ ይንከራተታል ። ቆይ እንዲያውም፣ ከሰንዱቁ አውጥቼ ልልበሰው !

ቦታ ... እሮይ ! በላዩ ሳጠልቀው እማዬን ያገኘሁ ያህል ይሰማኛል !

የት'ጋ ነበርኩ ? ... አፍ ቀልቤ ጠፋ ! እም የእማዬ ኑሮ ። አባታችን ከእናጢነት ሙያ ከሚያገኘው ብዙም ስለማይረዳት ፣ ሁሉም በቧ ላይ ወደቀ ። በኋላ የተወለደውን ግመሽን እንኳ በወጉ አልያዘችም ። ተርቧል ፣ ታርዟል ።

እማዬ ሽዋ በር ገበያ ፣ ሽቀጥ ይዛ ወጣች ። ትርፏም ደካም ሆነባት ። የናቴ ታላት እህት ፣ ሐረር የወረደች ጊዜ ይዟንኑ በውል ተረዳችው ። እያይዛም እኔን አዲሳባ ወስዳ ልታስተምረኝ ፈቃዷን ሰጠች ። እኔም ከቤቱ ትል ቋና ነፍስ ያወቀች ተብዬ ተመረጥኩ ።

በደንብ ይታወሰኛል፣ ገና ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ቢሆነኝ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እማዬ ኑሮ ተፈታትኗት እኔን ለመስጠት ብትገደድም ፣ የናትነት እንጀቷ ፍጹም እንዳልፈቀደ ከገጿ ይነበብ ።

አዲስ አበባ . . . አክስቴ ዘንድ ገባሁ ።

የገባሁበትን ቤተሰብ ፣ ሰፈር እንዲሁም ውቢት እዲሳባን እስከሳመድ እንቱቴ በምን እንዳቀረቀረ አላውቅም። ብቻ ጸጥ ፣ ለጥ ብዬ አሳለፍኩት ።

ቆየት ብዬ እንደ ልማዴ እግር አበዛሁ ። ወንዶች ተዋወቁኝ ። ማራኪ ቃላት ... ግብዣዎች ... ስጦታዎች— በያይነቱ ደረሱኝ ። ለመታ ትምህርት የማታው ይሻል ኛል — ስል አክስቴን ወተወትኳት ። እሷም ተስማምታ የማታ ትምህርቴን ተያያዝኩት . . . ቀን ቀን ምን ሠራሁ ? ዙረት ይቀናኝ ነበር ። ይኼው ነው — የሚታ ወሰኝ ። በትምህርቱ ስወድቅ ስነሣ ፣ ፈቀቅ አላረኩትም። ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ገብቼ እንድ ወር ያህል የተመላ ለስኩት የመጨረሻ ሆኖ ይታወሰኛል ።

አሁን ላለሁበት ያበቃኝ በዚያ ወቅት የፈጸምኩት ስሕተት ለመሆኑ እንዳች ጥርጥር የለኝም ።

ቅስሜ ተሰበረ ። የሕይወቴ ዘለበት ላላ ። ካስጠጋችኝ አክስቴና ቤተሰቧ እሳትና ጭድ ሆኜ ፣ ጭራሽ ተሰያየሁ ። ይፋ ቀና ብላ ያላየነችኝ እናቴ ፣ እንቱቴን ላወጣ ለማየት እንዳልጓጓች ሁሉ በኔው ድርጊት ምኞታ ትቢያ ሆነ ... የቀን ብርሃኔ መጨለም ጀመረ . . .

ማነው ስሙ ?... እም! ሀብቴ ነው ። ስሙን ቂስ ይጥራውና ፣ በቀን ጉዶሉ እጉዳድሉኝ ሒደ ። ሰው ስሙን ቢያን ምንኛ ደግ ነበር ። ለምን በዕኩይ ጠባይ የተሞላ ሰው ፣ ጀጋና ቸር ገላጭ ስም ይሰጠዋል?... አይገባኝም !

ሀብቴ ፣ ለኔ ምንም ሀብት አልሆነኝም ። ውድቀ ቷኖ ድህነት ነው— የሰደደብኝ ። ወይ ሀብቴ! ... ያባቴን ሰም እንኳ ጠይቄ አልያዝኩም ። ያኔ ፣ የኔስ ልብ የጠፋ አልነበር ? ለዚያውስ ስሙ በዕውነት ሀብቴ ቢሆን ነው' ኮ ! ... እጠራጠራለሁ ። ያራዳ ልጅ— ጨልሌ ፣ መቼ ሰምና እድራሻውን ይሰጣል ?

ከሀብቴ ጋር የተዋወቅኩት ፣ ፒያሳ አካባቢ ከል ጆች ጋር ወዲያ ወዲህ ስል ነበር ። ሁለቴ ያህል በመ ኪና «ሊፍት» ሲሰጠኝ ፣ የት ውውቅ ጨዋታ እደረግን ።

ረጋ ያለ መንፈስ ይታይበታል ። ራሱን ይደብታል። እንዳች ስሜት በውስጤ እየተንሳበጠ ሀብቴን ቀርቤ እን ዳውቀው ፣ ይኼው ድብቅነቱ ገፋኝ ። ዐሥር ወንድ ሥር ከመሰጠፍ ፣ በሀብትም ቢሆን ከፍ ያለውን ጠበቅ አርጎ መያዝ የተሻለ መሰለኝ ።

መቀራረብ ስንይዝ ፣ ሠፈራችን—ሜክሲኮ አደባባይ ድረስ ለመምጣት ቀጠሮ ሰጠኝ ። ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ሥር ካለው « ጋርድን ካፌ » አብረን ታየን ። ሀብቴ ምስት የወርቅ ጥርሶቹን ብልጭ እያረገ ፣ በቁጥብ ንግግሩ አሜወተኝ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በእንዲህ እንዳለን ፣ ሳምንታት አለፉ ።

«ለምን በሻይና ቡና ግብዣ ብቻ እንለያያለን ከ አለኝ ፣ አንዱን ቀን ግምሻውን— እዚያው «ጋርደን ካፌ» እንደ ተቀመጥን ።

«እንተ ደግሞ ... መተሳሰብና ጨዋታው ነው እንጂ ፣ ባፋችን የሚገባው ይህን ያህል ያንገበግበናል ግለትህ ነውት» ብዬ መለስኩለት ።

«ቢሆንም !... ተዝናንተን ለመሄዋት ሰፋ ያለ ጊዜ እንዲኖረን ፣ ቦታም ፣ የግብዣ ደረጃም መለወጥ አለብን!»

«ሻይና ቡና ስለማይደጋገም ወደ ቢራው ግዘን በልህ ነው ... እይደል!»

«ለከበሬታው በማሰብ ነው ፣ 'እትሊስት' ላንቺ ምን እንደሚሰማኝ ፣ ያለኝን የአክብሮት ግምት ለማሳ የት አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ።»

«እስካሁን አላሳየሀም ማለት ነው!»

«እንደሱ ማለቴ አይደለም! ደጋግሜ ታማኝነቴን አረጋግጫለሁ ። እንቺም ታውቂዋለሽ ... እቤት ክርክር ስት ወጪ !» አለና እንደ ሳፋ ወደ ጉን የሰፋውን ሞኙን በማቶቹ መታ መታ አድርጎ ፣ ጥርሱን እንደ ወርቅ ሻምላ አብለጨለጨብኝ ።

«እኬ!... ወርብ ኢትዮጵያ ሆቴል— ተጋብዘሻል ... ታዲያ ዝንጥንጥ ብሎ መገኘት ነው!» አለኝ ፣ እንገቱ

ሥር ያለውን ከራባት ተውረግርጐ በማስተካከል ፣ ጥቂ ሻውን እየሰበቀ ።

«እሺ . . . » አልኩት— እያቀረቀርኩ ። ከዚህ ወጣ የማልለው ... የሆነ ነገር መንፈሴን ሲወጥ ረው ፣ አካላቴ ተሸማቀቀ ።

በቀጠሮው ዕለት ዘጠኝ ተኩል ሲሆን ተገናኘን ። ሀብቴ መኪና ውስጥ ስንባ ፣

«እንዲህ ነው እንጂ ! እንዳሁኑ ... የተደበቀ ውበት ሲገለጥ ፣ ውበትም ወደ ባለቤቷ በደስታ ስትመለስ ! » አለ ባድናቆት ።

ሀብቴ ከተቀመጠበት የዳንስ ያህል ተወዛወዘ ። ቀጥሎ ግንባሬን ሳመኝ ። መልሶ ከንፈሬን ።

«ታቂያለሽ? 'ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጀል' ተብሎ የተተረተው ፣ መቼ ነበር ? ... ያንቺ ከንፈር ግን ታድኗል!»

«ዕውነት ከልብህ ነው ?» ኮስተር ብዬ ።

«ዕውነት ፣ ዕውነት አልሻለሁ ... ልቤ ሥር ከምት ገኘው ፣ የመጨረሻዋ ደቃቅ ሕዋስ እንሥቶ ነው— እን ጂህ ስለ ውበትሽ የምናገረው» ከማለቱ ፣ መኪናውን አስፈተለካት ።

ዕውነቱን ነው— ሀብቴ ። በተቻለኝ ሁሉ እጊዜለሁ ። ሊፕስቲክ ፣ የጸጉር ጌጦች ፣ የጥፍር ቀለም ... የወትሮ ልምዴ ቢሆንም ፣ ፍጹም አድምቄአቸዋለሁ ። የጨመር

http://ethioliberty.wordpress.com/

ራቅ ያለ ይመስለኛል ፣ በሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበረ ሙዚቃ በለሆሳስ ይወጣል ... ቀስ እያለ ተወጥኖ በጆሯችን ተንቆረቆረ ... የቀጭን ምንጭ መንሮር ይመስላል ።

ሀብቴ የወደፊት ምኞቴን እስመልክቶ ጥያቄ አነ ግብኝ ፤

«ምን መሰለህ ... ትምህርቱ እሺ ቢለኝ እንደ ሌሎቹ ሴቶች ጥሩ ሙያ ኖሮኝ ሥራ እንድይዝ እፈል ጋለው ። ከዚያ የሚያስከብረኝ ባለቤት ኖሮኝ ፣ ቤተሰብ መሥርቼ ፣ ወልጄ ከብጄ መኖር ነው የምሻው ... ግን ይህ ሕሳብ አልጨበጥልሽ ብሎኛል » ከግለቱ መለኪ ያውን አቀበለኝ— ሀብቴ ።

«እይዞሽ ... በትምህርቱ እንድትበረቺ እኔም እግ ዝሻለሁ ፣ ታዲያ ብርቱ ሰው መሆን አለብሽ» አለኝ ፣ ፊት ለፊት ካለው ታሪካዊ ሥዕል ላይ ዐይኑን ተክሎ በረዥሙ በማሰብ ። «እሺ... እየጠማሽ እንጂ!»

በዚያ ሶፋ ላይ ወደ ኋላዬ ልጥጥ ስልበት ፣ ሐሳብ ወሰደኝ ። ሀብቴም በልዩ ጥንቃቄ ፣ እጆቼን ፣ ጭኖቼን ፣ ጀርባዬን ... እያሻሸ ይባበሰኝ ። ደስታ ... መዝናናት ... ተደብቀውኝ የቆዩ ይመስል ፣ ከየሥርጓው ተወርውረው ተጠመጠሙብኝ ። የራሴ የሆነ ዓለም ተዋበልኝ ። እኔም ዋንሀብት ። አቀበትና ቁልቁለት የለበትም ፣ እን ዳሻኝ ሆንኩበት ።

ኩት የወርቅ ጉትቻና ሐብል ፣ 'ቡትስ' ሚማና ካፖርት አብሮት ከሚሔደው የተንቆጠቆጠ ቦርሳ ጋር ነበር ። እኒህን ብርቅዬ ጌጦች ከአክስቴ ልጆች የተዋስኩ መሆ ኑን ሀብቴ ቢሰማ ፣ ምን ይል ይሆን? ስል በልቤ አሰ ብኩ ።

ኢትዮጵያ ሆቴል ስንደርስ ፣ በክብር ቅድሚያ ገባው ። ሀብቴ ፈጠን ፣ ፈጠን ብሎ ቀድሞኝ በግለፍ ወደ ግራ ካሉት ፎቴዎች መረኝ ። ነጻ አካባቢ ነበር ።

አያሞቅም ፣ አይቀዘቅዝም ። ለስለስ ያለ ተስማሚ አየር አለው ። ቶሎ የሚማርክ ፣ ዘና የሚያደርግ ድባብ ተሰማኝ— የሚመስጥ ዓይነት ነው ። ወደድኩት ። የሶፋው ምቾት ይደላል ።

ከሀብቴ ጋር ተጠጋግተን እንደ ተቀመጥን ፣ ሙሉ ጥቁር በጥቁር ልብስ ከጸበተር ፍላይ» ከራባት ጋር ያደ ረጉ ትልቅ ሰው— አስተናጋጅ ሆነው ፣

«ምን ላቅርብላችሁ?» አሉን ፣ ቀድመው ወደ ሀብቴ ፣ ቀጥለው ወደኔ እየተመለከቱ ።

«ሁለት ውስኪ !... ከበረዶ ጋር» አለ ሀብቴ ። ዝግ ብሎ ፣ በጣቶቹ ሞኔን ሜን ፣ ሜን ... አጀት ... አረ ገኝ ።

ባንዴ ከውስኪው ጋር መጋተር ቀፈፈኝ ። ግን ስለ ታዘዘና ለመምረጥ ዕድል ስላልተሰጠኝ ፣ ምንም ማድ ረግ አልቻልኩም ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

በኋላ ፣ በኋላ ... ጊዜ ካለፈ በኋላ... ኑቃው ። ያኔ ለበኝም መሰለኝ ። የተሰማኝ ግን ፣ ከኃይለኛ እንቅልፍ እንደ ተነሣ ሰው ስሜት ነው ። ለራሴ ፣ ሁኔታው ባዕድ ሆነብኝ ።

ሰዓቴን ብመለከት እጂ ላይ የለም ። ደንጥኩ ዞር ብል ሀብቴ የለም ። የተጐነጨሁት ውስኪ የጐደለ መሰ ለኝ ፣ የሀብቴ ንክችም አልተደረገም ፣ እንደ ተሞላ ነው ። ዘና በማለት ራሴን ለማረጋጋት ብሞክርም አቃተኝ ። ተእምር የመታኝ ይመስል ፣ ትንፋሼ ተቆራረጠ ።

ተውሼ ያደረኩትን ጉትቻ ከጀርዙ አጣሁት ። የእጅ አምባሬ የለም ። ውድ የሆነው ካፖርት አይታየ ኝም ... በዚያች ቅጽበት ላየኝ ላባዋ የተጎጨ ዶሮ ሳል መስል እቀራለሁ!

ሰውም ባካባቢዬ አጣሁ ።

ወይኔ ልጅት !... ኡኡታውን ልለቀው ነበር ። በደ መነፍስ ዋጥኩት ።

ተገደርድሬ በመውጣት ፣ የሀብቴን መኪና ፈለኩ ፣ የለችም ። ጊዜው ደንገዝገዝ ብሏል ። ተመልሼ ሁኔታ ውን ለአስተናጋጆች ብነግራቸው ፣ የሚያውቁት እንደ ሌለ መለሱልኝ ።

...ወይኔ ልጅት! ... ጉድ ሆንኩ!

... ተታጠልኩ!... ንዴት በሠራ እካላቴ ሠረፀ ፣ ሆዴ ተንቦጫቦጨ ። እርር ! ድብን! አልኩ ። ደም ግፊ

ይመስል ጭው ! ... ጭውው ! አለብኝ ። ልቤ እየደቃ ፣ ሳምባዬ እየተነፋ ፣ ደሜ እየተጋፋ... ስተንፍስ ፣ ትንሽ መንፈሴ መለስ ይላል ። ለመራመድ ጉልበት ቢጤ አገ ኘለው ። እዚያና እዚህ ሀብቴን ፍለጋ ስቅበዘበዝ ፣ ከል ፍልፍ ያበደ ውሻ ይመስል— ሰዎች ታዝበውኝ ይሆናል ።

ምን ላርግ... የት ልሒድ? ንገሩኝ!! የታባቴ ልድረስ?... ኡፍ! እፎይ ... እከሰቴ 'ጋ ? ምን ብዬ እወ ራለሁ ? ምን ብዬ እገላለሁ ? እንዴት የልጂጀን ወይን አያለሁ ?

ተስፋ ቆረጥኩ ።

ቀልቤ አልሰበሰብ አለኝ ። ማድረግ ያለብኝን ሆነ መራት የሚገባኝን መለየት— አዕምሮዬ ማሰብ አቃተው ።

ያከሰቴ ዘመዶች ለኔ ሥጋ ቢሆኑም ፣ እንዴትና በየት ብዬ እንደምደርስባቸው— በረጋ ሕሊና ማገናዘብ አልቻልኩም ። እንዲያው ብቻ— ዓለም ተገልብጦ 'ወይ ንሽን ላፈር ! እርኩስ ! ቀላል ! አሰዳቢ ! ...' የስድብ ናዳ የሚያወርድብኝ መሰለኝ ።

... የኑር ሥቃይ አካሏን ያጠመሏታት እናቴ ፣ ላፍታ ትውስ ስትለኝ ፣ 'አልቅሽ ! ጨኺ ! እርም አውጪ ! ኡኡ በይ!' አለንኝ ፣ እንሰፈሰፈኝ ።

ወይኔ ልጅት ! ከልቤ እይደል የምንግራችሁ— ይው ጣልኝ ! !

http://ethioliberty.wordpress.com/

... በኔ ቤት— ብልጥ ነኝ ። በኔ ቤት— አልታለልም ። በኔ ቤት ቂልነት ጫፈን አይነካውም ። በኔ ቤት— ያራዳ መጨረሻ ከኔ ወዲያ ላሣር ነው ።

ዙሪያው ባሕር ሆነብኝ ...

የሕይወት ፣ የመኖር ምስጢር ግን ይገርማል ። ምን ይሁን ምን ፣ ግን ይሰንክል ግን ይበድ ፣ ግን ይጣ ግን ይዋረድ ... ሕይወት ታሳሳለችና ዘለበቷ ሲላላ— ለማየ በቅ ሲባል ፣ ለመቀጠል ሲባል ... የማይማስ ጉድባ ፣ የማይፈነቀል ድንጋይ ፣ የማይፈለጥ ግንድ ... የለም ።

አቅል ያጣው ሕሊናዬ መለስ ሲል ፣ ለውሳኔ አላ መነታውም ። ለድርጊት ፣ ለሕይወቴ ወደ ኋላ አላልኩም ።

ቀላል ነው ። ድቅን ያለብኝን ወሰንኩ ። እንዴ በግታ ትምህርት አብራኝ ከተማረች ጓደኛዬ ቤት በመሔድ ለመጠጋት ቆረጥኩ ... የሆቴሉ አሳላፊዎች ዞር ሲሉ ልኝ ፣ የምንተፍረቴን በርሬ ወጣሁ ። አልተገላመጥኩም ። አላመነታሁም ። አትጣሚዬ ወደ ነፋስ ስልክ ነበር ...

ጓደኛዬ እንደማታሳፍረኝ ተስፋ በማድረግም ፣ በልቤ በመማፀንም ነው— ራቤን ያጽናናሁት ። ለወት ሮው ፍልቅልቅነቷ የሚታወሰኝ በዚያ ወቅት ውልብ ባይለኝም ፣ ሰብእዊነቷ በደመነፍስ ይታወቀኛል ። በስየ ላይ የጣልኩት ዕምነት በፈናው— እሷን እንዳስብ ሳያስገድደኝ አልቀረም ። በጨዋታ ጊዜ— ስለምታውቃቸው ሰዎች የምትዘረዝረው ፣ ዕቃ በማሻሻጥ የምታሳየው

ብልጠት ፣ የተጣላ ለማፋቀር የምትመዘው ሰበብ ... በክ ፈል ሽው ሲሉኝ ፣ ብስጭቴን እያመነመነ እርይታ ያጋ ራኝ ጀመር ።

... ዕድሜ ይስጣት! አላሳጣችኝም ። ሳምንት እቆ ይታ ወደ ሞጂ ላከችኝ ። በምልክት ከነገርኳት አክስቱ ቤት ሐዳ ፣ ተመላልሳ ፣ ዶጅ ጠንታ ፣ ዕታዎቼን በከረ ጢት እጭታ ሜነችልኝ ። ቡና ቤት ሥራ ተግኝቶ ነው— የወጣሁት ። ገንዘብ ጽጥሬ ወደናቴ መመለሱን ተስፋ በማድረግ — ሰነባበትኩ ። የሴተኛ አዳሪነት ኑሮን ካን ጎት በላይ እንጂ ፣ ከልቤ አልተቀበልኩትም ። ታማሸ ቆየሁ ። ገንዘቡ ጠብ አላለም ... መቅኖ ማጣት የናቴ ትዝታ ፣ በአክስቴ ላይ ያደረስኩት በደል... ትጣት ሆነኝ ።

ሞጂን ባየው— የተስፋ ሞላንጭል የሚታይበት አልሆነም ። «ያልተገላበጠ ያራል!» ብዬ ፣ ወደ ሻሸመኔ ወረድኩ ... ምንም የለም !

ዛሬ ፣ እዚህ ደቡብ ኢትዮጵያ— ሞያሌ— በሴተኛ አዳሪነቴ እዘልቅበታለሁ ብዬ— ያኔ ወደ ጓደኛዬ ቤት ነፋስ ስልክ ስጓዝ ፣ አልጠረጠርኩም ነበር ።

«ተገላብጨ አረርኩ ! » በራሴው ልተርት እንጂ ! !

እስቲ ... «የቸገራቴ ትዝ አለኝ» ዘፈን ያባብለኝ !

«ያ ሁሉ ጨዋታ ... የቸንቴ ትዝ አለኝ

ባሳብ በትካዜ ... እያመላለሰኝ»

ወይኔ! ያ ሁሉ ጨዋታ... ወይኔ ልጅት!

http://ethioliberty.wordpress.com/

ም ሽ ት

እመንገዱ ላይ ብልጭ ባለው የመስከረም ፀሐይ የሚፍነከነከው ሾምቢ ፣ ቆም ብሎ ሰዓቱን ተመለከታት ። ሦስት ከአምስት ትላለች ። ሩብ ሰዓት ብትዘገይም ፣ እት ጨን እንድትነገረው አያስገድዳትም ። እንዲያው ሲወራጭ ፣ ከሰው ጋር ቀጠሮ ይዞ ትዕግሥቱ ያለቀበት ይመስላል ።

ሾምቢ ፍጥነቱን ጨምሮ እየተራመደ ፣ ቁርስት ሆቴል ገባ ።

ሆቴሉ የወትሮ እንልግሎቱን በመስጠት ላይ ነው። እሑድ ጠዋት ቢሆንም ፣ ተስተናጋጆች ምቾት በሚ ሰጠው ቦታ ላይ ተበታትነው ተቀምጠዋል ። ሾምቢም ጥግ ካለው ጥቁር የላስቲክ ሶፋ ላይ ተቀመጠ ። ከላዩ የማይለየውን ጥቁር «ሌዘር» ኮት አውልቆ ፣ ጉልበቱ ላይ አጋደመው ። የንጭ ሽሚዙን እጅጌ ሰብሰቦ ዘና እንደ ማለት ... አሰኘው ።

ወጣት ነው ። ሲመለከቱት ፣ ተግልብጠ የወጣው ዐይኑ ጅላጅል ያስመስለዋል ። ሰውነቱ ድብልብል ባይ

ሆንም በወፍረት እብጠል ። አገጩን ሲያሻሽ ፣ ድመውን ሁሉ ሲመለከት ፣ የትርብ ዕውቂያ ያለው ይመስላል ። በየጣልታው ፈገግ እያለ ሣቅ ቢጤ ሲሸ ፍነው ፣ «እኔህ እሚያውቃቸው ሰዎች ላይ ምን አይቶ ባቸው ይሆን?» ያሰኛል ።

አንድ አጭር ወጣት ዘው ብሎ የሚፈልገውን ሰው ታኘት ፣ ታኘት ሲያደርግ ፣ ሾምቢ የሚያውቀው ልጅ በማግኘቱ እጁን በማውለብለብ ሰላምታ ሰጠው ። ጥቁር ግንባሩ በጉልህ የሚያብረቀርቀው ወጣት ፣ አጸፋውን ካንገቱ እጉንብሶ ሰላምታ በመስጠት መለሰለት ። የመ ቹክል ምልክት አሳይቶት ፣ በመጣበት አካኋን ተመለሰ ።

ሾምቢ ፣ ወጣቱን የሚያውቀው ከአራት ዓመት በፊት ነበር ።

ሾምቢ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ለመግር በማታ ትምህርት ሲመዘገብ ፣ ወጣቱ ከሥራው በተጨ ማሪ የማታ ትምህርቱን እየተከታተለ ዐሥራ ሁለተኛ ደርስ ነበር ። ለአንድ ዓመት ሲማሩ አንድ ጠረጴዛ ተጋርተዋል ። ጉን ለጉን ተቀምጠው ተዋውቀዋል ።

«ታዲያስ!»

«ታዲያስ !» ይባባላሉ ።

«የዚህ ክፍል ሽቶ ደግሞ ... ገና ተግሪው ሳይ ገባ ያውላል !» በማለት ፣ ይጀምራል— ሾምቢ ።

«ተዋኸው !... ይልቅ የቤት ሥራውን ሠራህ !»

http://ethioliberty.wordpress.com/

«ምን እተዋቸዋለሁ ... ያቺ ከኋላ የምትቀመጠው ነች 'ኮ በሽቶ ታጥባ የምትመጣው ። ግታ ግታ የሚ ወስዳትን መኪና እይተሃል ፣ አይደል ?... ደግሞ በየጊ ዜው ነው የምትቀያይረው ! .. ወይኔ ! እኔም እንደ ምንም መኪና ብይዝ እሳያት ነበር ...»

«አንተ ! ትቀልዳለህ ?... ምኞት እንዳይገልህ ፣ ይት ርብህ !... የቤት ሥራውስ ? ...»

«አንተ አለህ ብዬ ተውኩታ !.. »

«አስተማሪው መጣ ! ... » ናትናኤል ያቋርጠዋል ፣ እየሣቀ ።

... አስተማሪው ትምህርት መስጠት ያዘ ... 'አስቲ እንዲህ ቢሆን ... ብለን እናስብና ቀጥሉ የሚመጡትን ሁኔታዎች እንረዳ ...'— እያለ ፣ ያስረዳል ።

«ታያለህ በ'አሰምሸን' መናር እንዴት ደስ እንደ ሚል?» ይንሾካሾካል ፣ ሾምቢ ።

«ዝም ብለህ አዳምጥ !»

«ቆይ! እኔ አስተማሪውን— ብሆን ... እንደሱ ኮሌ ታው የተቀደደ ኮት አላደርግም ነበር ... ምን እንደ ምለብስ ታውቃለህ? ሽክ ያለ ሱፍ በክራባት ፣ ደግሞ መነጽር አረጋለሁ ... »

«አንተ ልጅ? ...» - ያቋርጠዋል ።

«ቆይ ልጨርስልህ ... »

«እሪ ተው ይቅርብህ ... ምኞት ይጉዳሃል !... »

ይህ ዓይነቱ ምልልስ ፣ ቢያሌስም አይቀርም ።

ናትናኤል ዓመቱን ሙሉ ፣ አንዴ በሾምቢ ንግግ ር ሐሳብ ሲበሳጭ ፣ መልሶ የሾምቢን ልጅነት እያሰበ ሲያዝንለት ቆየ ። ከዛ ወዲህ ድንገት እንኳ ሾምቢን ቢያገኘው ፣ በእጭር ሰላምታ ይለየዋል ። «የቀን ሕልም የሆለው !....» ይላል በልቡ ።

ሾምቢ የናትናኤልን ዩኒቨርሲቲ መግባትና መቀጠል ሊሰማ «ታዲያ ቢሆንስ ?...እኔም እደርስበታለሁ! እኔ ደግሞ የምገባው ቀን እንጂ ፣ እንደሱ ማታ አይደለም . . . ቀድሜው እጨርሳለሁ ... » በማለት ነበር የፎከረው ።

በእረንጓዴ ኮትና ቡና ቀሚስ የተዋበችው ሴታ አስተናጋጅ ፣

«ምን ልታዘዝምት?» አለችው—ፊቷን ቅጭም አርጋ ።

ሾምቢ ተሜኔ ዐይኑን ተክሎባት ቆይቶ ፣

«ሻይ ይሁንልኝ!» አላት ።

ሻዩን ይዛ ስትመለስና ስታቀርብለት ልብ አላላትም። ... እየጀመረው ሆን— ሐሳቡ ። የማይለየው የሐሳብ ጉዞ ፣ የመንፈስ ምናኔ ፣ ዛሬም ቀሪስት ሆቴል ተከትሎት ገብቷል ።

አሁን እማዬ ባታስቸግረኝ ምን አለበት ?. . እኔ ለራሴ ወሙቴ እደርገው የለ ! 'ተማር ! ለራስህ አሰብ ! በኋላ መውደቂያህን እወቅበት! ...' የማያልቅ ንትርክ

http://ethioliberty.wordpress.com/

... እንዴት ይሰለቻል ? ኡፍ !... ግን እማዬ ምን ታርግ ! ያቺ ሙጢ ነች እማዬ እየተበሳጨች እንድትናገር የም ታረጋት ። ይሀች መናጢ ፣ ገና ሰገና የኔ ታናሽ ሆና ጥቁር እንበሳ— ሚጂካል ኮሌጅ መግባቷ ይሀን ያህል በኔ ላይ ያንጠባርራታል ? ይቺ ጉዶሉ ! እኔ ነኝ የግሳ ያት ። ቆይ ! ... እኔ አይደለሁም ፣ እቧ ከምታገኘው ገን ዘብ የበለጠ ባላገኝ !

እኔ 'አልግርም !' መች አልኩ ። እሁን ተምሬ ሥራ ከያዝኩ በኋላ ፣ ተለምር ሳመጣ እማዬን ይገርማት የዜ ! ምን እቧን ብቻ?... የሠፈሩን ሰው ሞምር ነው— ጉድ የማረገው ።

... ግን ምን ብሆን ይሻለኛል ? ... ምን ብሠራ ? ... ጥሩ ሥራ ወይም «ቢዝነስ» ካልያዝኩ ዋጋ የለውም ። ደግሞ ታይቶኛል ። «አቤት ! አቤት ! እንዴት ታድ ሏል ... » የሚያሰኝ ሥራ ነው— የምይዘው ።

ቆይ ... የፓይለትነት ማስታወቂያ ወጥቶ የለ! ትንሽ ጊዜ ቢቆይ የማትረክ ውጤት አቅርቤ እመዘገብ ነበር ። ከዚያ የኮረቤት ሰዎች ሁሉ እማዬን ለመጠየቅ ሲመጡ ፣ 'ወይዘሮ ጸጋመቤት ደህና ሰንብተዋል ? እን ደምን አሉ ? ቤተሰቡስ ? ያ ልጅዎ ... ይሄ በራሪው ! ... ፋይለቱ ? ... አዎ ! ... ደህና ነው ?' ይሏታል ። እኔ ደግሞ ከደብረ ዘይት ለማዬ ስልክ እደውልላትና «እማይ ... አሁን አየር ላይ ልወጣ ነው ፣ በአዲስ አበባ በኩል አልፋለሁ ፣ ተመልከቺኝ ! » እላታለሁ ። ወዲያው ...

ከደብረ ዘይት አየር ማረፊያ ጀቱን ይዤ እንደረደርና ሰማ ዩን ለሁለት እየሰነጠቅኩ መብረር ነው ... «አ ሁ ዝ ዝ ዝ» ... በሰማይ መሐድ አቤት ደስ ሲል ! ሆኖም ብርዱ ያስፈራል ። ታዲያ የሚሰጠን ልብስ ፣ ሙቀት የሚፈ ጥር ስለሆነ እያስቸገርም ። እማዬ ወደ ሰማይ ታንጋ ጥና እየተንጫጩ ለሚከቧት የሠፈር ልጆች «እዩት !... እዩት ! ልጄን ! እርብላኑን ሲያበረው ... እግዚኦ ! ጭራሽ ወደ ሰማይ ሊነባ አይደል ? ... በስመ አብ ወመልድ ወመንፈስ ቅዱስ ... ጌታዬ እደራህን ጠብቀው ፣ ሊቀ መላኩ በክንፍህ ሸፍነው ... ሔደ ! ... ሔደ ! » ስትላ ቸው ፣ ልጄ ደግሞ «ብራቮ ! » እያሉ ይጮኻሉ ።

ቅዳሜ በዕረፍት ቀን እማዬን ለመጠየቅ ወደ ቤት ጉራ ስል «ወይኔ በሞትኩት! አፈር ስሆን ፣ ደህና ነህ ! ልጄ ... ሥራው እንዳላታህ ? ... እንዲያው በዚህ በሰ ማይ እንደ አሞራ ስትከንፍ አትፈራም ?» ትለኛለች ።

«እያስፈራም ... አይሆሽ ! ሙያውን በደንብ አጥ ንቼየለው ። ምንም አያስቸግርም » እላታለሁ— ኮራ ብዬ ። ... ታዲያ ያቺን ሙጢ እዚያው ባንኖት በጥፊ ግጠናፈር ነበር ! ወይኔ — ማስታወቂያው የሚቆይ ቢሆን ... እንዴት ዓይነት ሀሪፍ ዕድል ነበር ! ታድዬ ... ኡፍፍ ! ...

ግን ከዚያ በፊት ፣ እማዬ ዕቁብ ሲወጣላት ታክሲ ብት ገዛልኝ ?—ጥሩ አይሆንም ?... ይሆናል ! ተበድራም ቢሆን

http://ethioliberty.wordpress.com/

ማሟላት ትችላለች ። አም ፣ ገንዘቡንም ብዙ አላቀይባ ትም ፣ በየቀኑ ከማገኘው ማማሹን እንኳ ባጠራቅም ቶሎ ልመልስላት እችላለሁ ። እንዲያውም በኋላ ከማገኘው ትርፍ፣ ለሷም እተርፋለሁ ። ግን መንጀ ፈቃድ ለማውጣት ቀድሜ መማር አለብኝ . . . አም ! የግድ መማር አለ ብኝ ። ወሥራ እምስት ቀን ወይም ቢበዛ ሐያ ቀን ቢፈ ጅብኝ ነው ። ጉረቤታችን ሱሉ ከሥራው ሲመለስ ትንሽ ትንሽ ካስተማረኝማ ፣ ይህን ያህል ጊዜ አይወስድብ ኝም ። ከሁሉም ከሁሉም የሚያስብሩት ግን አሳፍረን የሚሉ ሴቶች ናቸው ። እፈለግንበት ውሰደን ማለታቸው እይቀርም ። በነጻ ሆኖ ፣ እንደገና ሌላ ሰው እንዳይላፈር ገበያ ዘግተው «ብቻቹን እድርሰኝ» ሲሉ ያናድዳሉ ። እነሱ ባሉበት ታዲያ ምን ታክሲ ይነሳል? ምንስ ትርፍ ይገ ኛል ?

ይልቅ የሚያዋጣኝ «ቢዝነስ» ጸጉር ማስተካከል ነው ። እንደሱ የሚቀል ምን ሥራ አለ?... የሚገኘው ገን ዘብ ደግሞ ጠቀም ያለ ነው ። ጸጉር ማስተካከል ለመማር ደቂቃም እይፈጅብኝ!ማናቸው ?... ጋሼ እምቢበል ጋ ሔጄ «አሳዩኝ ? » ብላቸው ፣ ባንዴ እቀስመዋለሁ ። «ለምን አብረን እንሠራም ? እርስዎስ እንድ ክፍል ለብቻዎ ከሚ ይዙ አብረን ብንሠራ ብዙ እናገኛለን ፤ ትርፉም የጋራ ይሆናል ... » ብዬ እግባባቸዋለሁ ። በየቀኑ ደክምከሮ እስኪለኝ ሠላሳ ሰው ባስተካክል ፣ በሦስት ብር ሒሳብ— ብዙ እገኝበታለሁ ። ይሄ ደግሞ በወር ሲታሰብ የችሮሌ ነው ።

እጭ!...ስኮላርሺፕ መፈለግ ጥሩ ዘዴ ነው—ከሁሉም! ሌላው ቢቀር ሲቪል ኢንጂነሪንግ ለማጥናት ዕድል ይሆ ነሻል ። እንድ— ምስት « ኤ » በማትረክ ባመጣ እንሳገል ነበር ። እውሮፓ እሔዳለሁ ። ስድስት ዓመት ምን አላት ?... ቅንሽ ናት ። ታዲያ ቶሎ ተመልሼ የቤት ፕላን እውጪ ነው— የምሆነው ... እና እዚያ ሀገር በትምህርት ሳይ ስሆን ፣ አለ አይደል? ድብን ! እርጌ ትምህርቱን አጠናቀ ለው ። ክፍል ውስጥ ሌክቸረሮቹን «ቻሌንጅ» ሳረጋቸው ፣ ያገራው ሴቶች ያው ለመተዋወቅ ተቁነጥንጠው ይቀር ቡሻል ። እኔም ደረቴን ነፋ አርጌ ፣ « እየሽ ! ' ጥቁር እን ጂሀ ነው!' ገባሽ!» ብዬ ፣ ለያንዳንዷ አሳያታለሁ ። ወይኔ ... በቃ ለ «ስኮላርሺፕ » ማመልከት ነው— የሚሻለኝ ?... ውው !

ቆይ ... ቆይ ! ከዚህ ሁሉ በፊት እንደነታፈለ የቱ ሪስት «ጋይድ» ብሆን ያዋጣኝ የለ? በርግጥ ቋንቋ ማጥ ናት ያስፈልገኛል ። እንግሊዝኛ እከልሳለሁ ። ጀርመን ኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ብጨምርበት ይበቃኛል ... በደ ንብ ይበቃኛል ። ስንት ጊዜ ይፈጅብኛል?... እራት ካበባ ስድስት ወር ቢሆን ነው ። ታዲያ ቱሪስቶችን ከተማ ለማሳየት « ጋይድ » እያረኩ ፣ ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ እችላለሁ ። ያኛ መናጢ ሳትቀር ፈሻይ መጠጫ ስጠኝ !»

http://ethioliberty.wordpress.com/

እያለች ስትቅለሰለስብኝ ፥ « ምን ? ... ምን ፈለግሽ ! » እላታለሁ— በኩራት ። ብዙ ካስለፈለፍኳት በኋላ ብር እል ረውርላታለሁ ። እግዬ ደግሞ ፈተይ ! እንጂ ... ልጂን እታ ስቸግረው ፥ ስንት ለፍቶኩ ነው ያመጣው ... ልጂ ዝም ብለህ ገንዘብ አትርጭ ... ትንሽ ብትጽጥር ይሻልሃል ! » ትላለች ።

ያቺ ሙጢም፥ቱንዲን እንደተመታች ሊጋዘን ኩምሽሽ ትላለች ። እሾህ አፏን እንዳሸገች ፥ ካጠገቤ ትጠፋታለች!

ያም ያም ሆኖ የማያልት ውጣ ውረድ ውስጥ ከም ገባ ፥ ሎተሪ ቢወጣልኝ ዓለም ነው ። ምንድነው የማሸር ገው? ሦስት ሎተሪ ሻጮች አንድ ላይ እጠራለሁ ።ከዚያ በሚቀናኝ «ማጂክ » ቁጥር ፥ የሎተሪ ቲኬት እቆርጣ ለሁ ። ያቺ «ማጂክ» ቁጥር ደግሞ አንድ ነች ። መጀመ ሪያ ፥ መሐልና መጨረሻ ። ማን ነበር ? እሱ ! ... ስሜን በእንግሊዝኛ ከጻፈ በኋላ «ካንሰል» እያደረገ ፥ የዕድል ቁጥሬን የነገረኝ! እም ! አሌክስ ነበር ... አውን ነትቻ ለሁ ፥ ከሁሉም የሚበልጠው ሎተሪው ነው ። እንዴ ገን ዘብ ፥ በገንዘብ ከሆንኩኝ ፥ ጣጣም የለብኝ ... ይሽው ነው— የሚያጥጣኝ ።

ኾምቢ ከሐሳቡ ባነነ ። በሱሪ ኪሶቹ እካባቢ ሰውነ ቱን ሲነካካ ፥ ምናምን እንደ ወረረው ሰው የሚያክ ይመስ ላል ።

ፊቱ ፥ ቁልል ተራራ ለመውጣት እንደሚጣደፍ ሠን ሂደኖ በላብ ታጥቧል ። ዐይኖቹ ከመጠን በላይ ስለፈ ጠጡ ፥ የአዲስ መኪና የፊት መብራት ይመስላሉ ።

በቀረበለት ሲኒ ውስጥ የነበረው ትኩስ ውሃ ቀዝ ቅዟል ። ክታብ መሳዩ ፥ በስስ ወረቀት የታሸገው « አዲስ ሽይ ቅጠል » ፥ ስኒ ማስቀመጫው ላይ ተጉልቷል ። ስኳ ሩም ፈንጠር ብሏል ።

ኾምቢ በድግሚት እንደ ፈነዳ ድንጋይ ፥ ተወርውሮ ወጣ ። አስተናጋጅቱ ዘግይታ ደረሰች ። ስለ ሒሳቡ እየተ ጨነቀች ፥ ያቀረበችውን ተመለከተችው ። ምኑም አልተ ነካም ። እንደዋዛ ኾምቢ ይመለሳል ብላ ተስፋ አደረገች ።

ኾምቢ ባራት ኪሉ መንገዶች እየተቅበዘበዘ ወዲያ ወዲህ ይላል ። ሎተሪ ሻጮች ፍለጋ ይባዝናል ።

ኾምቢ ተጫኔ ... « ምኞት !! » እያለ በሕሊናው ሲጮህ— በመንገዱ ላይ ያላመጠው የለም ።

ግን ግለፍ ያታተውን ያሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህ ርት በግጠናከሪያ ፕሮግራም መከታተል እንዳለበት ትዝ ያለው— እንድ የክፍል ተማሪው እደባባዩን ሲሻገር ተመ ልክቶ ነው ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ሸ በ ጥ

«በቃኝ! ... በቃኝ! ነው የምልህ። ከዚህ ወዲያ አል ችልም። እስቲ እራስህ አስበው ! እስካሁን ኪራዱን አልከፈልከኝም ፤ ድፍን አራት ወር ሙሉ። ንቀት አይ ደል ? ለነፍሴ ባስጠጋሁህ ፣ በቻልኩህ ! 'የት ትደርሳለች !' ብለህ ቀለድክብኝ! ቆይ ግዴለም !»

«እሪ እንደሱ አይደለም! ወይዘሮ እንቺዬ ... እንዲህ አልወጣኝም። ' ትንሽ ፋታ ይስጡኝ' አልኩ እንጂ ፣ መች 'አሻፈረኝ !' ወጣኝ !... ዕብለት የለብኝም 'ኮ ! »

«ነው እንጂ !... 'ሴት ነች፣ ብቻዋን ነች !' ብለህ ነው። ሁሉንም አጥንተህ አይደል ይህን ያህል ጊዜ የምታኖር ብኝ!... ቆይ እንዲያውም ለደረሰዬ አሁኑኑ ነግሬ ፣ ይህን ቅራቅንቦ ዕቃህን ጠራርጎ ያወጣልኛል ... ኃይል ነው ! አይደል— የምትፈልገው !... ወዲያ መነሳገል ይሻለኛል ! ዶሞ በኖ ለማታጠጣ ኪራይ አበሳ ማየቴ ፣ መጠበሴ !.. ቆይ ግዴለም እንተያያታለን!... እንቺዬ አይደለሁም !»

አዲስ አበባ ...

እሪ በከንቱን አልፎ ወደ ታች ላሽቆለቆለ ፣ ተዳፋቱ ይንጣል ። ውሃ ቢኖርበት ፣ ፈረሰኛ ሆኖ ያገኘውን ሁሉ ይጠራርጋል ። ራት ሳይል የቂራ ድልድይ ይገኛል ።

እርበ ጠባብ ነው — የቂራ ድልድይ ። ከእንድ መኪና በላይ ከያዘ ይጣበባል ። በስተቀኝ ኮረኮንቹን ይዞ ለሄደ ፣ የተቸመቸሙ ቤቶች ያያል ።

ንጋት ሆኖ ሰው ገና ውር ውር ቢልም ፣ የኮረኮንቹ ግራና ቀኝ ጉልት ነው ። እርጊቶች ፣ ሕፃናት ፈረታ እየ ገቡ እንዲት ዘለላ ታሪያ እንኳ ቢሆን ይዘው ይወጣሉ— ጉልት ። የቂራ ድልድይ ድምቀትም ይኸው ነው ።

የድልድዩ ጉረቤቶች ሞለማን ተገን አርገው ፣ ምሽትን ተማምነው እመድ ፣ ገራባ ፣ እጣቢ ፣ የማድቤት ጥራጊ ፣ የእሻሮ ንፋሽ ... ቢደቃበትም ፤ ከረፈደ እንሥቶ ሲሙሁ ፣ ሲስቁ የሚውሉት የጉልት ቸርቻሪዎች ፣ በመ ናፈቅ 'እግረኛ ይሁን መኪና እናሳልፍም' — የሚሉ ሕፃናትን በግሰብ ሁሉን ችሎ ያድራል ።

ሰሞኑን « ሆያ ሆዬ ... ሆ ! » — የሚሉትን ልጆች አላስጨፍር ያለው ዝናብ ፣ ሌሊቱን ሲረግጠው ነው — ያደረው ። ቆርቆሮው የተሸነቆረ ፣ ግድግዳው የተቦደሰ ቤት ፣ ብርድና ትዝታዜውን ሳይከላከል ፣ እንዳለ ያስገ ባዋል ። በንዲህ ዓይነቱ ቤት የሚያድረው ሰው ፣ ከረም ቱን ይረግማል ። የቂራ ድልድይ — የቆሸሸ ማንቡ ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

የከረሩ ሥርቻው በዚያ አህያ በማይችለው ዝናብ ታጥቦ፣ ተጠራርጉ ሲነጋ፣ እርያ ይላል ።

በዚህ ንጋት የቢት ቆርቆር ክዳን እንጥፍጣፊ ላይደርት ፣ በቦይ «ጨር ... ጨርር» የሚለው ወራጅ ውሃ ላይ ጠራ ፣ በወይዘሮ አንቺዬ ቤት ከረር ላይ ምልልስ ተሰምቷል።

የአንቺዬ ወሰን ሰገድ ቤት ከአጉራባቾቹ ሲነጻጸር ወይን ይሞላል ። አጥሩ በቆርቆሮ ተለብዷል ። አንቺዬ መኪና ባይኖራቸውም ፣ ግቢው የመኪና በር አለው ። አተካራው ቀጥሏል ።

« እንግዲህ ከዚህ በላይ መናገር አልችልም ... ሠርቼ እከፍላለሁ ! . . . የምናገረው አግርኛ ነው ። የተ ለየ ልመና አላውቅም ። » ብለው ጮሁ— አብዩ በርባሶ ። የአጥሩን በር ከፍተው እንደ ፈንጣ ተፈናተረው ወጡ ።

« እንዴ ! እንዲህ ነው ? እንት ምናምንቴ ! . . . እኔ ላይ ነው— በር ዘግተህብኝ የምትወጣው ? . . . ወይኔ እንቺዬ ! . . . እማን ቤት በኖርክው ? እሁን ከጉባህ ታገኘው የለ ? . . . የዛሬን ሌሊት ብታድር እኔ እደ ለሁም ! እሙ ብርሃን ትፍረድብኝ . . . እሁን ደረስዙን እጠራው የለ ! ቤትህን ሲያሸገው ፣ የት እንደምትገባ እናያለን . . . እንዲህ እርጎ ይቀልድብኝ ! » አሉ ፣ እንቺዬ በቁጭት ።

አቶ ገሪማ ንብረ ወልድ ሙያቸው ሽበጥ መሥራት ሆነና ቅጽል ስም አግኝተዋል — « አብዩ በርባሶ »

የሚል ። ሕፃናት ይሁኑ መንደረተኛው የሚጠራቸው በዚሁ ነው ።

በዚያ ኮረኮንች ለዘለቀ ፣ የተፋፈጉ ቤቶች ያገኛል ። ሰዎች የማለዳውን ብርድ «እትትት ! . . . » እያሉ የግ ላቸውን ይቀበሉታል ።

የመንደሩ ነዋሪ አቶ ከፍሌ ፣ ከእጃቸው የማይለ የውን ከዘራ ከዋታው መሐል ላይናቸው በሚታይ ድን ጋይ ላይ እየተመረኮዙ ፣ በዝግታ ወደ ድልድዩ ያዘግ ማሉ ። ወይዘሮ አንቺዬ አጥር ሊያርሱ ሲሉ ነው ፣ አብዩ በርባሶን የተመለከቱት ።

አቶ ከፍሌ ለወጥ ያለ ነገር የተገነዘቡ ይመስል ፣

« ምነው እያ ገሪማ ? . . . በማለዳው ምን መጣ ? » አሉ ፣ ሮከ ብለው ። ካፋቸው የሚወጣው እየር ፣ እንደ ግድ ቤት ጢስ ይጨሳል ። ገሪማ ንብረ ወልድ የሚለው ስም ጠፍቷቸው « አብዩ በርባሶ ! » ሊሉ ምንም አል ቀራቸውም ነበር ። በሥራቸው ያለፈች የጉረቤት ልጅ ፣

« ይሀና እደሩ ! . . . ጋሼ ክፍሌ ! » ብትልም ፣ ሽበት ጣል ጣል ያለበት ቅንድባቸውን ወደ ላይ ወጥ ረው ፣ አብዩ በርባሶ ላይ እፍጠው ፣ መልስ አልሰጧትም ።

አብዩ በርባሶ ፣ ላዩን ወደ ድልድዩ ለመሔድ ያሰ ቡትን ያዝ አርገው ፣ ከወደ ኋላ ያላመጡትን ድምፅ ተከትለው ዞሩ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

« እንዴ ? . . . አቶ ከፍሌ ! . . . ሰሞኑን እልተባ ናኘንም 'ኮ ፣ እዴት ሰንበቱ ? . . . ደህና አደሩ ? »

« ደህና ፣ ደህና . . . ይመስገን ! አለው ። እሞኝ ወደ ናዝሬት ወርጄ ነበር ። እግረ መንገዴን ፣ ለቅሶ ደረስኩ ። የኛን የጡረተኞች ነገር መች አጣኸው ? . . . እደባባይ መውጣት ነው ። ፀሐይ መሞቅ ነው ። ከዚያማ ወግ አውግቶ ፣ ተጨዋውቶ ወደ ቤት መመለስ ነው ፣ ዘመድ ለመጠየቅ ወዲያ ወዲህ ማለት ፣ ሐዘን ቤት ጉራ ማለት ፣ በሽተኛውንም ከሆስፒታል መጠየቅ የት ይቀራል ? » ላመል ያህል ፣ « አህ ! . . . አህ ! » እያሉ ሳሉ ።

« ደግ . . . ደግ ! ለማናቸውም ጤንነት ይቀድ ማል ። አሁን ለጤናም እንዴት ነዎት ? » አሉ ፣ አብዩ በርባሶ ። ልቡ እስኪጠፋ ከለፋ ቆዳ የሠሩትን ባርኔጣ ዞር ዞር አድርገው አስተካከሉት ። ስልጅ ማሠሪያ በሚ መስል ቀጭን የሌጦ ገመድ ተብትበው እጊጠውታል ፣

በል ሲላቸው አብዩ በርባሶን ፣ ከሸበተ ሌላ እን ዳንድ ነገሮችን ይሠራሉ ። ቀበቶ ፣ ቦርሳ ፣ ባርኔጣ ፣ የግ ድግዳ ጌጣጌጥ . . . ሆኖም ፣ ሁሉንም የሚሠሩት ከቆዳ ነው ።

« ደግ ነኝ ! እንተስ ደህና አይደለህም እንዴ ? . . . በግለጻ ወዲያ ወዲህ ሚያደርግ ምን ጉዳይ ገጠመህ ! » አሉ ፣ ከጀንቦፊታቸው ሥር በቀጭኑ የተመዘዘ አንሜቾ ውን እሸት ፣ እሸት እያደረጉ ።

« እሪ ምንም አይደል ! . . . እንዲያው እንቺዬ ተነሠብኝ እንጂ ፣ 'ቤቴን ልቀቅ ፣ ደባልነታችን በቃ' ብለው ። ወፍ መንጫጫት ሳይጀምር ነቅተው ይነተር ኩኛል » ሲሉ ፣ እሷቸውን ጉራዳ ካፖርታቸው ኪስ ውስጥ እግብተው ወደፊት ወጠሩት ። ወፍራምና እጭር ጣታቸው ፣ ፍርጥም ብሎ ቅርፁ ይታያል ። ካፖርቱ ጥቁር ስግያሮ ቀለሙን ፣ በእመደግነት እየቀየረው ነው ።

« ታዲያ ዝም ይባላል እንዴ ? . . . መስማማት አይ ሽልም ? . . . እሪ ደግ አይደለም — ነገር ሲካረር ይበ ጠላል ! . . . »

« ጨዝት እንጂ መች ሰው ያናግራሉ ። እንቺዬ የሰው ነገር ሊገባቸው ?. . .አይ ! እርግማን ። የድህነት እርግማን ይኸው ያባላናል ። 'ሠርጌ እከፍላለሁ— ኪራዩን' ብል ፣ እልሰማ እሉ ። ተለማምጬ አልኖር !—እኔ ደሞ ። ሰሞኑን ወረፍ ብዬ ነበር ። ዛሬ ምን ክፉ ሕልም እንዳየ አላውቅም ፣ ተነ ሠብኝ ። እንዴ ነገር ከያዙ ደግሞ ምንቸነ ነው— የሚሉት ። እስቲ እግዜር ያሳይዎ ! » እሉ አብዩ በርባሶ ፣ እጭሩ ቁመታቸው ይመዘዝ ይመስል ፣ ባውራ ጣታቸው እየተንጠራሩ . . . ወደ ላይ . . . ወደ ላይ . . .

* * *

ገራማ ገብረ ወልድ ፣ ከልጅነት ዕውቀት ድረስ ሥራ አልተለያቸውም . . . ሥራ ሰው አርጓቸው ፣ በመንፈስ ጠንክረዋል ። ቁመናቸው ከዕድሜያቸው አንድ ወሥር

http://ethioliberty.wordpress.com/

ቆረቁሩት ፣ ሐሳባቸውን እንደፈለጉ ስለሚገልጹ ... ተናግ
ረው ይመጣላቸዋል ። ታሪክን እንደነበር አርገው ይሸመ
ድጹታል ። ታዲያ ሳይንስ ይጠምባቸዋል ። ያ ጠምዛዛ
ሂላብ አፅምሯቸውን ይቆጣጥረዋል —አይሆኑቸውም ።

ደጋፊ አልነበራቸውምና ሙሉ ጊዜያቸውን ለት
ምህርት ማዋል አልቻሉም ። ነታ ነታ ግለታቸውን የተገነ
ዘቡት ነጋዴዎችም ፣ መጠጊያ ሊከለክሏቸው ሆነ ።

ወዲያ ወዲህ ሲሉ ፣ ብልጠታቸውን ያጠና ግሊያን ፣
በቢንዚን ማደያው በገንዘብ ተቀባይነት ቀጠራቸው ።

«ይሀን ጭንቅላትህን ሥራበት ። አለዚያ ሽረሪት
እድርቶበት ይሻግታል ። እንዴት ሰው እንደምትሆን ልም
ከርህ ። አዳምጥ !. . . ግሊያንኖ ቋንቋ አጥና ። ታሪክ ይቀ
ናህ የለ ! . . . የግሊያንን ታሪክ ለብልበው ! ከዚያ በነጻ
እንድትግር ዘዴ እፈልግልሃለሁ ። ሮማ ሔደህ ትግራለህ
. . . ጥሩ አርጌ ስላንተ ለዘመዶቹ እንግራቸዋለሁ . . .
ገባህ ? ሰው ሁን ! ምን ትፈዛለህ ? ማማሚያ !» ይላቸ
ዋል ፤ረጅም ሰውነት ያለው እጀፍልጥ ግሊያን ።

«ግን ! ግን ! ትልቅ ቁም ነገር ዘንግተሃል ፣ ሲኞር !
የሰው አገር ታሪክ ለግጥናት ከማጉንበሴ በፊት ፣ ያገሬን
ግጥናት ያለብኝ ይመስለኛል ። እንተ ‘ያገርህን ትተህ
የኢትዮጵያን አጥና !’ ቢሉህ ፣ ‘እሺ !’ ትላለህ ? . . .
እየህ አቢሲኒያ ገና የሚመረመር ታሪክ ፣ የሚወሳ ገድል
አላት ። መጽሐፍ ቅዱስ አላገላበጥከም ? የሳባን ፣ የጠ
ቢዑን ሰሎሞን ድንቅ ሥራ አታውቅም ማለት ነው ?

ዓመቱን ይደብቅላቸዋል ። ‘የሚሠራ አያረጅም !’ የሚያሰኝ
ሐሳብ የሚፈጥር ዓይነት ።

በዚች ምድር ምን ያህል ዓመት እንደኖሩ ማንም መገ
መት አይችልም ። አላቸውም ፣ ዕቅጩን አያውቁትም ።

«ግሊያን በ፲፱፻፴፫ ወደ መጣበት ሲመለስ ፣ ሐረር
ከተማ ቁስ ትምህርት ቤት እመላለስ ነበር» ይላሉ ።
አባታቸውን ለይተው አያውቋቸውም ። ነፍስ ሲያወቁ
የተረዱት ቢኖር ፣ አባታቸው ከግሊያን ፍልሚያ ተጥመው
በዚያው ማለፋቸውን ነው ። እናትየውንም ወዲያው በሽታ
ቀሠፋቸው ።

በናትና አባት ፍቅር ፋንታ የተተካው ሥራ ፣ ከዚያ
ጀምሮ ለምጠ ፣ አትንቶ ቀርያአቸዋል ። በራስ መኖርን ፣ ራስ
መቻልን አሳያቷቸዋል ። ሥራ— እምዬ ፣ ሥራ —አብዬ ፣
ሕይወት ራሷ ሥራ ሆነች ።

ጉስቁልናቸውን የተረዱ የግሪክ ነጋዴዎች አስጠጓ
ቸው ። እየተላላኩ ፣ ሽቀጥ እየተሸከሙ ፣ መደብር እየጠረጉ
አደጉ ። የዕለት ጉርሳቸውንና ያመት ልብሳቸውን አገኙ ።

እያደረጡ ፣ እየጀመሩ በትምህርታቸው መድኃኔ
ዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደርሰው ነበር ።
ትምህርቱም ቀንቷቸው ፣ መምህራኑም ወውቀዋቸው—እስ
በጅቸው ። ሆኖም ከሕንዶቹ ጋር ግጥም መሆን አልቻ
ሉም ፤ ጉሮሮ ለጉሮሮ መተናነቅ ነበር— የሚቀራቸው ፣
ሲከራከሩ ፣ ሲከራከሩ ... የእንግሊዝኛን ቋንቋ ስለሚያ

http://ethioliberty.wordpress.com/

. . . የአቢሲኒያ ታሪክ እንዲያ ረዥም ነው ። የጥንት የጠዋቱ የአክሱም ምጡት ሥልጣኔ ደግሞ እንደነበር አስብ !አውሮፓ የት ነበር ? ያኔ ፣ የት ነበር ? ደሞ ማሊያንኛ ሆን ተወኝ ። እኔ አይሆነኝም ! 'እሺ !' አይለኝም » እያሉ ይከራከሩታል ።

አብረው ለብዙ ጊዜ ሠሩ ። ተከራከሩ . . .

የኋላ ኋላ የጣሊያኑ ጤና ታወከ ። ዕድሜ ተጫጫነው ። በግሩ ሌላውን ተክቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ። አብዩ በርባሶ አዲስ ከመጣው ጋር አልተጣጣሙም ። 'ሒሳብ ጐደለ ፣ እያያዙ የተዘረከረከ ነው' — በሚል ሽፋን ፣ ወደ ጋራዥ ዝቅ አረጋቸው ።

ይሄኔ ፣ አንዱ ጣሊያን መለስተኛ ጫማ ቤት ሲከፍት ተከትለውት በመውጣት ፣ አብረው ለእሥራ አድስት ዓመታት ያህል ሠሩ ። ይህኛውም በለውጡ ወቅት ተደናግፀ ሲወጣ ፣ የቀራቸው ሙያው ብቻ ነበር ። ጊዜው በሩጫ ሲያልፍ ፣ ሕይወትም ፋታ አልሰጥ ስትል ፣ ትዳርን በቁም ነገር አልጨበጡትም ። ይልቁንም ከመጽሐፍ ተጣብቀው ተገኙ ። ዕረፍት ሲያገኙ ማንበብን ፣ ዓለምን መመርመርን መረጡ ።

«ምህርነት ከተገኘ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ላስተምር !» ብለው ፣ ቤተልሔም ትምህርት ቤት ድንግላውያኑ ዘንድ ተቀጠሩ ። እዚያም ለተወሰኑ ዓመታት አዩትና ወደ አዲስ አበባ ገቡ ።

«ካንዱ ቤት ወደ ሌላው» እያሉ መጠጊያ ፍለጋ መባከን፣ እንገሸገሻቸው። አሁን መተዳደሪያ የሆናቸውን የሽበጥ ሥራ ሙያ ፣ የት ቁጭ ብለው እንደሚሠሩት ጨነቃቸው ። መጨረሻ ላይ ነው— ከወይዘሮ እንቺዬ ወሰንሰገድ ጋር የተዳበሉት ። ለዚህም የበቁት በአያሌ ውጣ ውረድ ፣ በደላላ ልምምጥ ነበር ።

እንቺዬም ፣ «እጅ አለው ፣ አይደል? ቆየት ብዬ ሜን ብለውም— ይችለዋል !» ሳይሉ አልቀሩም ።

በእንዲህ እንዳሉ ፣ አንድ ቀን አብዩ በርባሶ ያመረቱትን ሽበጥ ተሸክመው ፣ ኮሚሽን እየከፈሉት ወደሚሸጥላቸው ሱቅ ይዘው ሲሔዱ ፣ እንቺዬ ከበር ቆመው ፣

« እያ ገሪማ ! . . . ጊዜው ‘ኮ እንደምታየው ነው ። ነጋዴው ዋጋውን አልሰብር አለ ። እኔም ሰማይ ሲይፋ ብኝ ሆን— ብቻዬን ። አትሙ የለም ። ኩሊው ፣ የቤት ወራቱኛው በትንሹ አይደለሰም ። ታዲያ የቤቱን ጉዳይ ሳስበው ፣ ለሌላ ቢከራይ የበለጠ እጥፍና እጥፍ የሚገኝበት ይመስለኛል ። ሆኖም ፣ ያንተን ጠባይ አይቼ ፣ ድምፅህ የማይሰማ ፣ ሥራህን አሳቢ በመሆንህ አይደል ያስጠጋሁህ ፣ በል ከዚህ ወር በኋላ ዐሥር ብር ተጨምሮ ሮብህ ፣ የየወሩን ትሰጠኛለህ » አሏቸው ።

አብዩ በርባሶ በፊናቸው ፣

«እሪ ይተውኝ እንቺዬ ! ልሥራበት ፣ ‘መድረሻ የለውም ! ’ ብለው ስወጣ ፣ ስገባ ኪራዩን እየቆለሉ ተራራ

http://ethioliberty.wordpress.com/

እያላከሉት ! እንዲያው ስለ ሲቀመላኩ ብለው ኃጢያቴ እይታይዎትም?»ብለው ይጮኻሉ። መልሰው ደግሞ «ጠት ልለው ያስወጡኝ እንደሁ የት እንባለሁ ? » በሚል ሥጋት ፣ ከተጠየቁት ግማሹን ይሁን ብለው ቃል ሰጡ ።

★ ★ ★

አሁን ፣ ' አሻፈረኝ !' በማለት በሩን ዘግተው ወጥተ ዋል ።

« አሁን አሉ ታዲያ ? . . .ወይዘሮ እንቺዬ ? » ይጠ ይቃሉ አቶ ክፍሌ ደሱ ።

«መኖርማ አሉ . . . እንዲያው እንደ ጧት ጸሎት እኔን ካልለከፉ አልሆን አላቸው እንጂ ! »

«ቆይ እስቲ ። ተጉራብተን እያለ ፣ ዝም ብሎ ማየት ይገባ አይመስለኝም ። . . . ሳናግራቸው ?»

« የለም ! የለም ! . . . አቶ ክፍሌ ፣ ለምን ብለው ! እንቺዬ እንደሁ አይሰሙም ። እያጻም'ጡም እያልኩ ! ይልቅ ወዲት ነው ፣ የሚሉዬት ? ይተዋሉ አብረን እናዝ ግም ። እንቺዬ የሚያደርጉትን እያለሁ ፣ መታገሥ የፈ ራንት ምልክት ከሆነ እንሒድ ፣ አሁን ሌላጉዳይ አለኝ » አሉ ፣ ባውራ ጣታቸው እየተንጠራሩ ።

«ቢሆንም ! እናግራቸዋለሁ ። እንዲያው ሁሉም ነገር በዕልህ አይሆን ! » ሲሉ አቶ ክፍሌ ፣ ቀይ መስመሮች ሽንትር ያወጡለትን ጥቁር ከራባት ፣ ሁለት እፍኝ በሚዘ ግነው እጃቸው አስተካክሉት ።

ፈታቸውን ወደ ግቢው በር አዙረው ፣ አንኳኩ ።

«ቤቶች ! . . . ኧረ ቤቶች ! የማለዳ እንግዳ አትቀ በሉም ? » እያሉ ፣ ጉብኑ እንዳይመታቸው ጉንበስ ብለው ወደ ውስጥ ዘለቁ ።

አብዬ በርባሶ በባዶ ስሜት እጃቸውን ከካፖርታ ቸው ኪስ እንዳደረጉ ፣ የግዳቸውን ተከተሏቸው ።

«ቤቶች! ወይዘሮ እንቺዬ ! ወዲት ነዎት ? ሰውም የለ ?» ይላሉ ።

እንዲት ልጅ እግር የሳሎኑን በር ከፈተች ። ከቤት ውጭ የሚቆፈንነውን አየር ያልተለማመደው ሳንባዋ እየነፋት ፣ ካፍንጫዋ ቡልት ፣ ካፏ ብትን የሚለው አየር ያልተቀጣጠለ እርጥብ እንጨት ጢስ ይመስላል ።

ወይዘሮ እንቺዬ ብቅ እንዳሉ ፣ አቶ ክፍሌ ሰላምታ ለማድረስ ከደረታቸው ዝቅ አሉ ። በሩ ሥር እንደሆኑ አብዬ በርባሶ ፣ ካንገታቸው አቀረቀሩ ።

«ውይ ! ውይ ! አቶ ክፍሌ ! ከወዴት ተገኘህ ? ይህና ሰነበትክ ? . . . እህ! አያ ገሪማም አለ ሰካ ፣ አልሔደምና ። በር ዘግተብኝ አልወጣ መሰለህ ? ለካ አንተ ዘንድ ስሞታ ሊያሰማ መሮጡ ናሯል ? ... ገባኝ ! »

«ደህና አደሩ ወይዘሮ እንቺዬ ! ኧረ በፍጹም ለስ ሞታ አልመጣም ፣ ወዲህ ከኮረኮንቻ ተገናኝተን ነው ። እኔስ ምንድን ነኝና ስሞታ አሰማለሁ ? እንዲያው ውናቴ ውን አይቼ ነው ፣ 'ምነውሮ' ብዬ፣ አያ ገሪማን የጠየቅኩት ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እኔው ነኝ ካልነባሁ ያልኩት ። እግረ መንገዴንም ለሰላ ምታ ነው ... ብርቱ ነምት ነ»

«ምን ብርታት አለ ?— በብቸኝነት ። ወይ ያቺ ልጅ እዚሁ መጥታ ፣ ቤተሰብ ይዛ— አይዞሽ ! ብትለኝ ፣ ይሻለኝ ነበር ። አሁን ደግሞ ወደ መተከል ሔዳለች ። የኢ መሔጃ ፣ መቼም ማለቂያ የለውም . . . ታዲያ ግባ 'ንጂ ወደ ቤት ነ»

«የሰም ! እሔዳለሁ ፣ . . . እያ ገራማ በስጨት ቢል ፣ ተጮራብተን እያለ እንዴት የጮሪዋ ተያይተን እንተላለ ፋለን ? ... ብዬ ነው ፣ » ሲሉ እቶ ክፍሌ ፣ በቁማቸው እግራቸውን አጠላልፈው ፣ ባንድ ጉናቸው ከዘራቸውን ተደግፈዋል ።

«እዬ ! ... እያ ገራማ የመጣ ሰሞን የሰው መጨረሻ መስሎኝ ነበር ። ዛሬማ ተቀይሯል ። እንደ ድሮው ፣ የሚሉትን እይሰማም ። ኑሮዬን ፣ ብቸኛነቴን እያወቀ ገፍትሮኝ ያልፋል ። ይኸው አራት ወር ሙሉ ኪራዩ አልከፈለኝም፣ ምን ልትመስ ? ደግሞ ለነፍሷ ብዬ ነበር— ያስጠጋሁት ። አዩ ጽድት !... ዘሙኑ ነው ! . . . ቅድም 'እንተያያለን !' እያለ ሲርከር ነበር ። ግዴለም ፣ ዛሬውኑ ጓዙን ጠቅልሎ ይወጣታል ! »

« እዬ ! ወይዘሮ አንቺዬ ! ይህን ያህል ዓመት አብራችሁ ኖራችሁ ፣ ተቻችላችሁ ፣ አሁን ማካረር ምን ይበጃል! .. ታዲያ ሁናቴው እየታየ አስተያየት ማድረግ ነው— የሚገባው ። ሁሌ አይሞላም !... ይጉድላል ! እርስዎስ አስ

ተዋይ አይደሉ ?» አሉ ፣ አቶ ክፍሌ ሾጠጥ ያለውን አንጫቸውን እያሻሹ ።

«አሁንስ ብንከባበር ይሻላል ፣ ወይዘሮ አንቺዬ ! ይኸው እዚህ ከገባሁ ጀምሮ እንደ ፈለጉት ሲሆኑ ፣ ችዬ ቆይቻለሁ ። መደሻና የጫማ ምስማር ተንተርሼ ለማድርበት ከፍል የአጥፍ ፣ እጥፍ ማስከፈልዎ እንሶዎት ፣ ማስ ፈራራትዎ ምን ይባላል ? ይደንቃል !... ይልቅስ ትንሽ ይታገሡኝ » አሉ ፣ አብዬ በርባሶ። እጃቸውን ከካፖርታቸው ኪስ አውጥተው ሲያወራጩት ፣ ቆፈኑ ከአጥንታቸው ዘልቆ ሲነካቸው ፣ ተሰማቸው ።

«መከባበር ?! ... ይኸው ነው—የቀረህ ። ቤቱ የማን እንደሆነም ዘነጋኸው ? ማን የጠፈጠፈው ሞታ መሰለህ ? ... ድንቂም መከባበር ። ሰው ለነፍስ ሲያስጠጉት እያ ውቅም ? ... እንዲያውም የልጂ መመለሻዋ ይርሷል ። ግረፈያም የላት ። መልቀቅ አለብህ ። ዕቃህን ሰብስበህ ተከብረህ ሒድ ! 'አይ!' ካልክ ፣ ደረሰ አሁን ይመጣልሃል፣ ደውዬለታለሁ ። ትርኪምርኪህን ጠራርጉ ሲጥለው ፣ በሩን ሲቆልፈው— ዋጋህን ታገኛለህ ። ካንተ ገንዘብ ፣ የልጂ አብራኝ መኖር ይብልጥብኛል !»

«ወይዘሮ አንቺዬ ፣ ለቤት መፈለጊያ ጊዜ መስጠት እንዳለብዎ አይዘንጉ ፣ በውላችን ላይ የሠፈረ ነው ። ኪራዩን እንደ ምንም ብጨርስም ፣ ሌላ ቤት መፈለጊያ ጊዜ መስ ጠት ግዴታዎ ነው ። »

http://ethioliberty.wordpress.com/

ኦርልኝ ! ... » ይሉታል ዘወትር— በስልኩም ፣ በማንባር ሊጠይቃቸውም ሲመጣ ። ቦቴ መኪና በሱ ስም ፣ ወፍጮ ቤት በልጁ ፣ ደግሞ ሚስቱ ቅልጥ ያለ ቡና ቤት ይዛ ለች ።

የወይዘሮ አንቺዬን 'አቡነ ዘበሰማያት' በቃሉ ስለ ሚወጣው ፣ የሚሉትን ጨርሰው ከንፈራቸውን ሲገ ጥሙ ፣ የሃምሳ ይሁን መቶ ብር ኖት መሃ በመጻፋ ቸው ውስጥ ያስጨብጣቸዋል ።

ከልጅነቱ 'እንቱ' ማለትን ስላስጣሉት ፣

«ካለን መረዳዳት ይቀድማል ። ኋላ መንጫጫት ምን ዋጋ አለው ? ብቸኝነትሽ ዕውነት ሥቃይ ነው ። ይልቅ ያቺን ሠናይት 'እዚህ ተቀመጭ' እትያትም ? ደሞ እሷን ብሎ ሀገር አትኝ !» ይላል ደረሰ እጉናፍር ።

«ዕውነት ነው ... ዕውነትህን ነው » ይሉታል— እንቺዬ መሰንሰንድ የተቀበሉትን ብር እያሻሹ ።

★ ★ ★

«እኔኳ በሰው ቤት ዝም ብዬ ልጦር ፣ ልዘፍዘፍ አላልኩም ... ሰጊዜው ያለችኝን እሚተጨ ቆዳ ገፃሁ በት ፣ ቢሆንም እከፍላለሁ ። ደግሞ ቆዳውን ተሸነሸሜ ስገባ አይተዋል ። በዚህም ሠርቼ ከማገኘው መክፈሉ አይቀርም ። አትምና ሙያዬ እያለ ፣ ብድርና ልመና ልሒድ ? አልሒድም ። ምስጋና ይግባው ለእጄ ! ...

«እረ ወዲያ ተወኝ .... የምን ውል ነው ? የሚያወራ ብኝ ? ... አላቅልህም ተናግሬአለሁ ! »

አንቺዬ ሸብረክ ሸብረክ ብለው፣በረንዳው ላይ ካሉት ምሰሶዎች ወደ አንዱ ተጠጉ ። የለበሱት የሀገር ልብስ፣ ጃፖኒ ነው ። ክንዳቸውን እጥፈው ፣ በክርናቸው ሣፍ ምሰሶውን ተደገፉት ። ፍርጥም ያለው የክንዳቸው ቀይ ጡንቻ ፣ እንዲያ በጣሃድ ሲያዩት የደረሰች ልጃገረድ ሞን ይመስላል ።

«ይህን ያህል መካረርም አያሻም ። ወይዘሮ አን ቺዬ!... በተከበሩበት መንደር ወደዚህ ሞትሞት ግም ራት አይገባዎትም ። የአያ ገሪማን አትም መድከም አይ ተው ወዲህ ሙያውን ወዶ ፣ ደፋ ቀና ግለቱን ተገንዝ በው እስተያየት ያድርጉለት ... እሱም ዕዳውን መክ ፈል አለበት ... ከዚያ በስላም መኖር ነው ።» በማለት ጣልቃ የገቡት አቶ ክፍሌ ነበሩ ።

★ ★ ★

ደረሰ እጉናፍር ፣ በወይዘሮ አንቺዬ ባለቤት ክርስ ትና ተንሥኋል ።

«እምላኪ በልጅ አላደለኝ ፣ ሠናይትን ሠዋቶ አል ደግም አለኝ ። አሁን እንተው ነህ ያለሽኝ ! ማን አለኝ! ደረስዬ ! ብቸኝነቴን ብታየውኳ እንዴት ታዝንልኝ ነበር ። ይሁን ፣ እምላክን አላማርረውም ፣ ብቻ እንተ

http://ethioliberty.wordpress.com/

እዚህ አድርሶኛል ... እርስዎስ በኔ እጅ የተሠራውን ሽበጥ አይደል የሚያደርጉት ?» አሉ ፣ አብዬ በርባሶ ።

አቶ ክፍሌ ወይናችውን ጉልጉሰው ፣ የቡና ሙቀጫ ከሚያስንቀው የወይዘሮ አንቺዬ ባት ሥር ፣ እግራቸው የተጫማውን ሽበጥ ተመለከቱት። የሥረኛው እንደ ምላስ የሳሳ ነው ። ዳር ዳሩ በጥንቃቄ ተቀምትሟል ። ቁርጭም ጭሚታቸውን በከፈል ሽፍኖ የሚነማው ቀጭኑ የቆዳ ጥብጣብ ፣ ወደ መሐል ከሥረኛው ቆዳ ጋር ይጣበቃል ። ተመልሶ እንደ ሐረግ በመጠምለል ፣ እውሬ ጣታቸው ላይ እንደዋዛ ተጠቅልሏል ። ፊት ለፊት የሚታየው ጌጥ ፣ ጥበብ የፈለሰበት ፣ ዐይን ካገኘ የማይለቅ ነው ፣

«እሺ !... እንግዳ በመጣ ቁጥር ፣ 'እባክህ እንድ ሽበጥ ቆንጆ አርገህ ፣ አሳምረህ ሥራልኝ ?' እያሉ አል ጠየቁኝም? ሌት እንቅልፍ እያጣሁ ነበር የምሠራው ፣ ለስንት እንግዳ ሰጥተውት ይሆን ? ለመሆኑ ያውቁ ታል ?... ሙያ ያስከብራል ፣ ባያስከብር መች ሥራ ይሉኝ ነበር ?... እኔ በጀ ነው— የቆምኩት ። የግንባ እጅና ችሮታ አላይም ። ሽበጥ ሕይወቴ ነው ። ረጅም መንገድ ይወስደኛል ። ጉዳዬሬ ነው ... እንዲያው እስቲ ያስተውሱ ፣ በዚህ አንጀት በሚያቆስል ኮረንንች ሕፃናት ባዶ እግራቸውን ከሚሔዱ የእኔን ሽበጥ እያደ ረጉ ቢያድጉ ፣ ምን ነውር አለበት ?... ይህስ ፣ 'እዚህ ቤት ነው— የሚሠራው' ቢባል ፣ ያጸይፋል ?» ብለው ፣ ወደ አቶ ክፍሌ ዞሩ ።

«እያ ገሪማ !.. ዛሬ ሙያን ማን ይነቅፋል ? ማን ይንቃል ? ልመና ነው— የሚያስንት ፣ የሚያዋርድ ፣ ከሰው በታች የሚያደርግ... የኔን ልጆች የያዘልኝ ማን መስሎህ ኖሯል ? ያኸማሊያን ፣ ከፈረንሳይ የሚያመጡት ሜማ መስለህ ? ያንተው ሽበጥ ነው ... ለማናቸውም ዕዳ ህን ከፈል ። ወይዘሮ አንቺዬ! ይህን ያህል ጊዜ እንደ ኖራችሁ ሁሉ ፣ አሁንም ዕድሜያችሁን እያሰባችሁ መኖር ነው» ሲሉ አቶ ክፍሌ ፣ ከዘራቸውን አዙረው በሌላ ጉናቸው ተደገፉት ።

«ነበረ ! በዕድሜ መከባበር ... አያ ገሪማ ሙቼ እን ጂህ ሆነና? ሰው ሲባል ውለታ ቢስ ነው ። ለነናሁ ብዬ ያስጠጋሁት ሰሞን ሲቅለሰለስ ቆይቶ ፣ አሁን ጭራሽ ልዘዝ ባይ ሆነኻ!»

«የለም!... መቅለስለስ ማንም አላስተማረኝም ። አላውቅበትም ። የሚያቅለሰልስ ሲኖር ነው— መቅለስ ለስ የሚቻለው ... ሕይወት እማር አላይታኘለች ፣ መለማመጥ አላስጠናችኝም ። ክልጅነቴ እንሥታ ወግ ራኖለች ... እኔ እዚህም ስመጣ አሁንም ያው ነኝ» አሉ ፣ አብዬ በርባሶ ፍርጥም ብለው ። ባዶ እንጀታቸው «ጮር ... ጮርር» እየለ ሲጮህ ይሰማል ።

«ለማናቸውም ያረሰ አሁን ይመጣል ። 'ሰውን ማመን ቀብሮ ነው' አሉ?... ወዲያ ኩታንኩትህን ይወረውረ

http://ethioliberty.wordpress.com/

ውና ታርፈዋለህ » ይላሉ እንቺዬ ፣ የተደንፋትን ምሶ ለቀው ፣ በእጃቸው ነጠላቸውን እያጣፉ በመከናነብ ። ቆረኑ የተሰማቸው ይመስላሉ ።

«መቼስ መወታቀስ ያለ ነው ። ያጠፋ እንዲያርም ፣ የበደለ እንዲክስ ። በየቤቱ የምናየውን የሚያሳዝን ሁኔታ ፣ እዚህ መልሶ ማየት አያስፈልጥንም ። ስለዚህ ይታገሡት ፣ ትንሽ ይመልከቱት» አሉ አቶ ክፍሌ ወደ ወይዘሮ እንቺዬ እየተመለከቱ ።

«እንተም ፈጥነህ ዕዳህን መክፈልና ዐርፈህ መቀመጥ ነው » ወደ አብዬ በርባሶ እፍጠው— አቶ ክፍሌ ።

«በል ሒድ!... ይህና ዋል ። ደረስ ሲመጣ እሮው እንነጋገርበታለን ። » ወይዘሮ እንቺዬ ፣ ለአቶ ክፍሌ ነበር— የሚናገሩት ።

«ታዲያ እሱም ቢመጣ ፣ አብረን እንማከራለና !... ምን መሔድ ያስፈልጋል?» ከማለታቸው አቶ ክፍሌ — የመኪና ሞተር ሲሥሀ ተሰማ ።

«መጣ መሰለኝ ! » እንቺዬ ፣ የቤት ውስጥ መኖሪያውን ፣ ከበረንዳው ግድግዳ ላይ በመሜን እንጨረጨሩት ።

የቅድሟ ልጅ እግር ፣ « አቤት!» በሚል መልክ መጣች ።

«እስቲ ወጣ ብለሽ ተመልከች !... ደረሰዬ መጣ መሰለኝ !» እንቺዬ ፣ በር በሩን እየተመለከቱ ተናገሯት ።

አቶ ክፍሌ የሚሆነውን ለማየት ዓጉተዋል ። ሠራተኛዋ የሰካችውን ሽበጥ ባይናቸው ተከተሉት ። ሞታ ለኩፍ አድርጉታል ። እንደ አቅሙ የተዋበ ነው ።

‘እንዲያው ምናለ ለሚሠራ ብናገዝ ? እይዞህ በርታ ፣ ሥራ ብንል ? ታዲያ እንዴት ያልፍልናል ? እንዴት ከችግር እንላቀቃለን ? መናቆር ፣ መጨቃጨት ፣ ከጉቆሞ አታቂር መምዘዝ ... የት ያደርሰናል ? የት ? ...’ የሚል ሐሳብ መጣባቸው ።

ያረሰ የመኪናውን ቁልፎች እርስ በርሳቸው እያጋጨ ፣ ሞታ ሞታውን ለይቶ እያለፈ ገባ ።

«ደረሰዬ መጣህ ? ... ያላንተ ማን አለኝ ? የኔ ፈጥኖ ደራሽ ! ... ግባ ፣ እለፍ ወደዚህ ! ... ደረስክልኝ ! በል ይህን ሰው አባርልኝ!... ለዚህ ነው በጠዋት ያንገላታሁህ ... አባርልኝ ! ...»

«ደህና እየራችሁ ? ... ምን ነው ? ምን መጣ በጠዋት ከ» ብሎ ወደ እንቺዬ ሲያመራ ፣ አብዬ በርባሶን እንደ ነገሩ ‘ሰላም!’ አላቸው ። ለአቶ ክፍሌ እጅግም ነበር ።

«ና !... ናግባ! ብርዱም አያስቆምም ። ሰው ሁሉ ተነሥቶብኝ ፣ ምን ላርግ ? ወዲህ ደግሞ ብቸኛነቱ ... ግባ ! ... ታዲያ ይህን ሰው አባርልኝ . . . ቆይቶ ሲያጠፋኝ ይቀራል ?» ብለው ፣ ተከትለውት ገቡ ።

አብዬ በርባሶ ፣ አሁን ገና ቆፈኑ ጥብስት አርጎ የጠቀጠቃቸው ይመስል ፣

http://ethioliberty.wordpress.com/

«አተተተ !... አይ እርግማን !» ይላሉ ፣ ባውራ ጣታቸው ፣ ወደ ላይ ... ወደላይ እየተንጠራሩ ።

አቶ ክፍሌ ከዘራቸውን ወደ ሌላ ጉናቸው ሲያ ዞሩ በደመነፍስ ነበር ። የሰውን ባሕርይና ምንነት አን ጠርጥረው ለማውጣት ወደ ፍልስፍናው ነጉዱ ...

«ምነው መተሳሰብ እንዲህ ይጥፋ? ተንኮል ፣ ጥላቻ ወዲያውም የራስ ጥቅም ብቻ ! ታዲያ በምን ተለምር ችግራችን በኖ ይጠፋል ? 'ሥራ ! በርታ ! ' ይባላል እንጂ ፣ ሰበብ እየሰነጠሩ አብራሪ ፣ ተባራሪ መሆን? ... ሰው እጥፊ ፣ አልሚ ...» — ተጽረጠባቸው ።

«በል ይህና ዋል !... በሌሊት አለፋህህ ፣ ግን አለኝ ብለህ ነው ? » እንጂዱ ንግግራቸውን ሳይጨ ርሱ ፣ ደረሰ እየፈጠነ ወጣ ።

«አቶ ክፍሌ !... በዚህ ቆፈን ተጠበስክ አይደል! ይህና ዋል ፣ ተስማምተናል ፣ 'እስቲ እንድ ዕድል እን ስጠው' ብለናል» ሲሉ ፣ በእጃቸው የሚያሻሹት የብር ኖት ታየ ። እየፈነደቁ ወደ ሳሎን ገቡ ።

አብዬ በርባሶና አቶ ክፍሌ ተያዩ ። ተያይዘው ከግ ቢው ወጡ ።

ወደ ድልድዩ አቅንተው ሦስት ፣ አራት እርምጃ ዎች እንደ ተራመዱ ፣ በደረሰ እንኖፍር መኪና ውስጥ የተወዘፉ ሁለት ወጠብሻ ጉረምሶች ገላመጧቸው ።

ከእንገታቸው ሲያቀረቅሩ ፣ መንደረተኛው የተሳ ሳው ሽበጥ ነበር . . . ሽበጥ . . .

ፈጣን !

በሰኔ ያስገመገመው ደመና ፣ የከረምቱን ኃያል ነት አብሥሯል ። ቁልቡቹ ጠቁረው ፣ ተንጠልጥለው ... እያለቀ እያለቀ በሰግዩ ላይ ይታያሉ ። የሚዘንበው ዝናብ አዲሳባን አርዷታል ።

በከተማዋ መንገዶች ሰዎች ችምችም ይላሉ—የችቦ እስር ይመስል ። ከዚያ እንድ ወይም ሁለቱ ተነጥለው ሲወጡ መጠነኛ መተራመስ ይታያል ። እንዳልነበረ ሆኖ የተሰበሰበው የሚበተነው ፣ ከመሐል የሚገኘው ያፈተ ለክ እንደሆነ ነው— ንግሥቲን እንዳጣ ንብ ዥው ይላል ። ይህ የመንገድ ላይ ትርኢት ፣ «... ምን መጣ ?... ምን መጣ ?» እያሰኘ አጠያየቁ— ያልሰማውን ።

«ፈጣን !... ፈጣን! አዲሱ ፈጣን ሎተሪ ነው የመ ጣው ። ታዲያስ ? ... እርስዎስ ተጋፍተው እይሞክሩም?» መልሱ ማግባቢያ ሆነ ።

« .. ይሞክሩ ፈጣን ሎተሪ
ችግር አባራሪ ! ...»— ተብሎ ተዛመመ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

የመንገድ ላይ ትርኒቶች መመልከት ሲበዛ ያስደስ ተኛል . . . የሚሰማኝን መናገሬ ወሬኛ ያሰኘኝ ይሆን ? ቢሆንም እንዳንድ ለእዴጋ የሚሰጡ አጋጣሚዎች አይታ ጡም—ዝርፊያ ፡ ድብድብ . . .ሴሎችም ። እኒህንና ሌሴክ ትሪክን በሩት ማየት ነው ፡ ባይ ነኝ ።

ቆየት ቢልም ፡ አንድ አሣውንት ያሚውቁኝ ትዝ አለኝ . . .

አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ወረድ ብሎ አንድ ቡና ቤት በረንዳ ላይ ቡና እዝዝር ቁጭ እንዳልኩ ነው— ሰውየው መጥተው እኔ የምጠቀምበትን ጠረጴዛ የተጋሩት ። ፊት ለፊታችን ወጭ ወራጁን እናስተውላለን። ከወደ ላይ በኩል ልጆች ቀድመው ፡ ዐዋቂዎች ለጥቀው ከመንገዳቸው እየወጡ ስብስብ አሉ ። ከበው የሚመለከቱት ፡ የሆነ ነገር ያለ ይመስላል ።

«እይ የዛሬ ሰው !» ሲሉ ንግግራቸውን ጀመሩ ፡ ሰውየው 'ይቀጥሉ . . . ' በሚል ስሜት ፡ ወደ ጉን እየኋቸው ።

«ይኸውልህ ...እንድ ጊዜ በራስ መኮንን ድልድይ በኩል ሳዘግም አውን እዚህ እንደምታየው ፡ ድልድዩን አጣበው ቁልቁል ወራጅ ወንዙን ይመለከታሉ ። እኔም ምን ተፈጠረ ብዬ ፡ ለማየት በፍጥነት ገሠገሥኩ ። ሰዎቹ ተንሰፍስፈው ሲመለከቱ ፡ ከባድ እዴጋ መሰለኝ ። 'ወይ መኪና ተገል

ብጦ ፡ ወይም ሰው ወድቆ ... ይሆናል ' እያልኩ ድልድዩ ስደርስ መፈናፈኛም የለም ። የሚተላለፈው መኪና ጥሩንባውን ይለቀዋል ። መንገደኛው ይጋ ፋል ። እንደ ምንም ተጋፍቼ ቁልቁል ብመለከት ፡ ለካ እንዲት ትንሽ ውሻ ገብታ ነው — ያ ሁሉ ሰው የተ ሰበሰበው ። ነደደኝ ። አውንም እዚህ የተሰበሰበው ቁም ነገር ፍለጋ እይምሰልህ . . . » በማለት ፡ ባለፈው የተ ቆጩትን መልሰው በስሜታቸው ረጩት ።

'እውነትም ያናድዳል !' ብዬ በሐሳቤ— የሰውየ ውን ቁጭት በመደገፍ እንገቴን ነቀንቅኩ ።

የሌሊቱን ባቡር የሚሳፈሩ ፡ ቀድመው ለመገኘት ልባቸው እንደቆመ በችኮላ ሲራመዱ ፡ ፈጣን ሎተሪ በእዲስ መጥንቱ የፈጠረውን የመንገድ ላይ ትርኒት እያሰላሰልኩ ለንሐሩን አልፈ አዘገምኩ ። ወረፍ የምል በት ቡና ቤት ፈልጌአለሁ . . .

. . . በአቶቡስና ታክሲ ውስጥ ፡ በቢሮዎች ፡ በሆስፒ ታሎች፡ በተበሴ ሕዝብ ሱቆች ፡ በትምህርት ቤቶች . . . ወሬው ይኸው ፈጣን ሎተሪ ! መሆን አለበት ። በሦስትና አምስት ሴኮንድ አንድን ነገር ማወቅ አለማ ወቅ በራሱ ታላቅ ጉጉት ይፈጥራል ። ሰው ደግሞ በተፈጥሮው ጉጉ ነው ። እና «ፈጣን ሎተሪ ያንጓል ! . . .» እያልኩ ሳወጣ ሳወርድ ፡ ብዙ እንግዶች የሌሉበት ቡና ቤት በጨረፍታ አይቼ ጉራ አልኩ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

ታውቃላችሁ፣ ሰዎች የሚሰበሰቡባቸው መዝናኛዎች የለየላቸው የንግድ መናኸሪያዎች ናቸው። ከሜግ አሳግ ረው ሊስትሮ እንሥቶ፣ ጋቢ ወይም ውድ ጌጣጌጦች ሻጩ ድረስ. . . ሁሉም ነጋዴዎች ናቸው። ካንዱ ሌላው በግባ በያ ብልጠቱ ይለያያል። ፊት የሰጡት የእግር ሹራብ አሟሪ 'ካልገዙኝ!' የሚለውን ያህል ፣ በቁጣ ብርር የሚል የእቾሱኒ ቸርቻሪ አለ።

ሰዎች በቡና ቤቱ ሲጨመሩ፣ ሜሚታው በረከተ።

የሚካለበው አስተናጋጅ ወደኔ ቀርቦ፣

«እዚህስ ?. . .» አለኝ። በጠፈ ንግድ መሓል፣ 'ፍጥነት' ታግሶ የመጠበቅን ቦታ እንደሚወርስ ተገንዝቤ፣

«ቡና እንደ ወረደ . . . ያለ ስኳር !» በማለት አዘዝኩት።

ወዲያው የደረት ኪሴን ደባብሼ የሲጋራ ፓኮ አወ ጣሁ። ክብሪት ይዤ ለመለኮስ ስዘጋጅ፣ ረዘም ያለ ፣ ልጅ ነት ያለው ፣ ጥቁር መነጽር ያረገ ሰው ሲገባ እንደኖሣ ቀልቤን ወሰደው።

ሕፃን ሴት ልጅ እፊት እፊቱ እያለች፣ እጁን ይዛ ትመ ራዋለች። ፈጥና ወንበር ስባ፣ ወጣቱን አስቀመጠው። እሷም ከሌላ ወንበር ላይ በራሷ ተንጠራርታ ተቀመጠች። እግ ሮጅ ተንጠልጥለዋል። ስታወዛውዛቸው ትሥቃለች። ንፍጧ ሲያሰቸግራት ደግሞ በሰግያዊ ሽሚዟ ትጠርገዋለች።

ሲጋራዬን ግግ፣ ግግ አርጌ ጢሱን ባፍና ባፍንጫዬ ስለተው ዑልቅ፣ ዑልቅ እያለ ወጣ።

ወጣቱ—ዐይነ ሥውር ነው። በአቀማመጡ ፣ ከወንበ ጀምሮ ቀጥ ይላል። ወደ የትኛውም የብርሃን ጭላንጭል ራቱን አያዞርም። ቀስ እያለ መነጽሩን ወደ ላይ ገፋ፣ ገፋ ያደርገዋል፣ እንዳይወልቅ መመለሱ ነው።

«ይሽው. . .» አለኝ ፣ ያዘዝኩትን ቡና ከጠረጴዛ ላይ ያኖረው አስተናጋጅ።

ቡናውን ፋት ብዬ ወጣቱን ዐይነ ሥውር አስተዋል ኩት። እጁን ያፍተለትላል። ትንሿ ልጅ በበኩሏ፣ በጣቶቿ ያዝ. . .ሜምቅ. . .ለቀቅ ታረገዋለች።

በእርግጥ ሁለቱም የሚመሳሰሉ ናቸው ... እህቱ ትሆ ናለች። ወይም ወጣቱ እጮኟ ሊሆን ይችላል። የሱ ልጅ ብትሆንስ!. . .መላ ምት ደረደርኩ።

ከወጣቱ ገጽታ ብልጠት ይነበባል። ጐንበስ ብሎ ልጅ ቷን ሲያናግራት ትሥቃለች. . . መልሰው አብረው ይጣ ጣታሉ።

« ትምህርትሺን ታጠኝያለሽ ወይ ? »

«እም !»

«ግን ይብተርሺን በደንብ አትይዢም ይባላል !»

«ውሸት ነው ፣ ውሸት ! ቀልድ ነው። እኔ ባንድ ይብተር ሁሉንም ትምህርት ስለምጽፍ ነው !»

«ይሄግ ስንፍና ነው። ለምን ለየትምህርቱ ይብተር

http://ethioliberty.wordpress.com/

እትይዥም ? »

«ለኔ የሚቀለኝ ባንድ ደብተር ሲሆን ነዋ !»

«በኋላ ፣ ፈተና ሲመጣ እንዴት ማጥናት ትችያለሽ !»

«እ. . . እችላለሁ ፤ አሁን ጊዲዮንን ፣ የኛ ክፍል ተማሪ ብታየው ፡ ዊኑ ላይ በሸክሪብቶ ይጽፍና እቤት እንለብ ጠዋለሁ ይላል ።»

«እሱም ሰነፍ ተማሪ ነዋ ! አብራችሁ ነው—የምትቀ መጡት!». . .ወጣቱ ይሥቃል ።

የልጅቷ ዐይን ትብዝብዝ ይላል ። በሉላ ጠረጴዛ ላይ የቀረበውን. . .ኬክ ፣ ለስላሳ ፣ ሻይ. . .ስትመለከት ምራቋ ተፈትልኮ ይወጣል—የልጅ ነገር!. . .በዚህ ሁኔታ ባይኗ ዙሪ ያዋን ትዞርና እኔ'ጋ ስትደርስ ቆም . . . ፈገግ ትላለች ። ይሀንኑ ደ,ንገመችው . . . ምናልባት ዓይኔን ስለተከልኩ ባት ይሆን ? . . . ወይም ትልቅ ኩይላ የሚያክለው ሰውነቴ አስገርሟት ይሆናል ።

. . .ዐይነ ሥውር መሆን ከዓለም መራቅ አይደለም። ስንት አለ አይደል! ዐይናማ ግን ልቡ የታወረ ፣ እያየ የማ ያስተውል ፣ እየሰማ የማይገነዘብ . . . ዐይነ ሥውር ያይኑን ብሌን አጣ እንጂ ፣ የመናር ፣ የመፍጠር ፣ የመጠበብ ብሉ ኑን አላጣም ። ልቡ ሥልጠና ፣ ክብካቤና ማበረታታት . . . ቢያስፈልገው ነው . . .

ይሀንን በሕሊናዬ ሳውጠነጥን ዐይኔ ቀዘዘ ። ቡናው ሊቀዘቅዝ ሆነና ፉት አልኩት ። ሲጋራዬን ለመጨረሻ ጊዜ ሳብኩና ተረኮስኩት . . . መልሼ ቡናውን ፉት ፡ ፉት ብዬ ጨለጥኩት ።

ወጣቱ ያዘዘውን ጻቦና ወተት የጨረሰው እያጣጣመ ነበር ። እጄን ወደ ኪሱ ከቶ አንዲት አራት ማዕዘን የሆ ነች ወረቀት አወጣ። ለልጅቷ፡እጅዋን በጻበሳ ፈልጉ ሰጣት። በደንብ ይታየኛል—መለየት አላቃተኝም ... ፈጣን ሱተሪ ነው ።

ለምን እንደው አላውቅም ፡ ብቻ ገረመኝ ።

ምናልባት ባልነቃው ያይምሮዬ ክፍል የተቀበረው የተሳሳተ ዕምነት ብልጭ ብሎብኝ ይሆን?—'ዐይነ ሥውር ባይን ታይቶ የሚደረገውን ነገር ሊመኝ አይችልም' የሚል ጊዜ የሻረው ግምት—ራሴን ታዘብኩት ።

ልጅቷ ጮሌ ነገር ነች ፡

«ፈጣን ! . . .ፈጣን !» እያለች በጩኸት ፡ አካባቢዋን ታኘች ። ወዲያው በዐሥር ሳንቲም ሜኖ ትኬቱን መፋት ያዘች . . . ትሥቃለች .. ወጣቱ በርጋታ ይጠይቃታል። ትመልሳለች ።

ሌሎች ሰዎች ፡ ቤልጅቷ ጩኸት ገልመጥ ፡ ገልመጥ እሉ ።

http://ethioliberty.wordpress.com/

እራት ሆነው በርቀት ያለውን ጠረጴዛ የከበቡት፣ ልጅቷ ላይ ዐይናቸውን ጥለዋል ... ትንሽ ተንጋሪው፣ ወጪ ገቢውን ይመለከታሉ ... ይጨዋወቱና ዝም ሲሉ፣ ጊዜ ለማሳለፍ የተቀመጡ ይመስላሉ ።

ልጅቷ የትኬቱን እንድ መሥመር ስትጨርስ፣

«መሶ ቦርቅ ! . . . መሶቦርቅ ! » አለች ።

‘ ትልቁ አሸናፊ የሚገኘው በመሶቦርቅ መሆኑን ማወቅ አለባት’—የሚል ሐሳብ መጣብኝ ።

እንደገና «መሶቦርቅ . . .» አለች ።

‘ትጫወታለች ?’ አልኩ ባለማመን . . . ሆኖም ልቤ መደንገጡ አልቀረም ።

የቀራትን ፍቃ ስትጨርስ ፣

«መሶቦርቅ !. . . መሶቦርቅ ! » ብላ ፣ ፍትፋቲውን «እፍ ! . . . እፍ ! » እያለች ጠራረገችው ።

‘ . . . ሦስት መሶቦርቆች ? የማይሆነውን ? እንዴ ያኖቸውን ስትደጋግም ይሆናል . . . ’ ብዬ ፣ ዐይኔን ወደ በሩ ብወረውር የሥፈር ሽርኬ ይመኑ ውስብ አለኝ . . . ለምን ጉዳይ ነበር ስፈልገው የከረምኩት ? . . ክፋቱ ጉዳዩ ጠፋብኝ ። ደግሞ ብቻዩን ከምሆን ፣ ተከ ትየው ዞር ዞር ብልስ ? . . . መሯሯጡ ፣ መጣራቱ —ይሻው እዚሁ እደከመኝና ተውኩት ።

« ጋሼ !... ሦስት መሶቦርቆች » ስትለው ለወጣቱ ከሐሳቤ ነቃሁ ። እንደ ልማዴ ዙሪያውን ተመልካከታ እጀ ጋ ስትደርስ . . . ፈገግ—ልጅቷ ።

ወጣቱ ደንገጥ ያለ ይመስላል ።

«እስቲ ! . . . እስቲ ! » አላትና ትኬቱን ዳበሰው— መነጽሩን ወደ ግንባሩ እየገፋ ።

« ጋሼ ! . . . በቃ እሸነፍክ » አለችው ። ቁንጥ ንጥ አልኩ ። ዘለዬ ነጥቂያት መመልከትም ከጀለኝ ።

ዐይኔ አባበላት መሰለኝ ፣ ፍንጥር ብላ ወደኔ መጣች —ልጅቷ ። የሎተሪውን ትኬት አየሁት ። ሦስት መሶቦ ርቆች ተዘባርቀው ይገኙበታል ። ከጣቱ አሸች ፣ አሸት አረኩት ። ያው ነው ። ዐይኔን ማመን አቃተኝ . . . ክው አልኩ ። ልቤ እየዘለለ ፣ እየዘለለ ሰውነቴን ወዘ ወዘው ። ትኬቴን ስመልሰላት ፣ እጇ እንዳይንቀጠቀጥ ብጠነቀቅም አልቻልኩም ።

ወደ ወጣቱ ተመልሳ ፣

«ጋሼ ! . . . በቃ ግንዘብ ታገኛለህ » አለችው ።

«ተይ ዕውነት ተናገሪ ! »አላት ፣ ከፈል መንገት ወዲህ ያለማመን ጥርጣሬ ተደባልቀውበት ።

« ዕውነት ! . . . ዕውነት ! ሦስት ነው ፣ ሰሰው አላይቻለሁ »

http://ethioliberty.wordpress.com/

ከወዲያ አራት ሆነው ከተቀመጡት መካከል ፣ ዝል ዝል ያለ ኮት የለበሰው ቀጭን ሰው ፣

«አንቺ! አንቺ ልጅ !. . . ነይ ! እስቲ አምጪው !» አላት ።

ልጅቷም አላመነታችም « ዐይን ዐይኑን እያየች ሰጠችው ። ተመለከተው ። ተጥሎ ለጓደኞቹ አሳየቻቸው ። እንዴ ራሱን ይይዛል ። ሌላው «ኡኡ !» ለማለት የተዘጋጀ ይመስላል . . . በያፈናው እድናቆት ረብሿቸዋል . . .

« ፍሪቲ ! . . . ፍሪቲ ! » በማለት ዐይን ሥውሩ ሲጣራ ፣ ልጅቷ መለስ ብላ እናነረችው ።

የልጅቷን ስም ያዝኩት ።

ፍሪቲ ፣ ብዙም ሳትቆይ ትኪቱን ከቀጭኑ ሰው ተቀብላ ወደ መቀመጫዋ ስትመለስ ፣ አንላብጣ አየችው ።

« ጋሼ ! . . . መሶቦርቆቹ ሁለት ሆነዋል ። »

« ቅድምስ ፣ መች በደንብ አየሽው ? »

«አይቼው ነበር ፣ አይቼው ነበር ፣ አይቼዋለሁ ! ምስት ነበር ፣ አሁን ሁለት ብቻ ! . . . »

« ዕውነት ተናገሪ አላልኩሽም ? . . በይ ተንሽ እንሒድ ? » —በቁጣ ።

« ዕውነቴን ነው ፣ አባቴ ይሙት ! »

« በደንብ አላየሽውማ . . . እንሒድ ! » ብሎ ጠረጴዛውን ገፋ ፣ ገፋ አደረገው ።

ፍሪቲ ብስጭት ብላ ከንፈሯን ጣለች . . . ዐይኗን ሬት ለሬት ካለው ግድግዳ ላይ ወረውራ ተገተረች . . .

. . . . እንዳች ነገር ራሴን መታኝ ። ልቀበለው የማልችል ግጭበርበር ዐይኔ ሥር ሲፈጸም ማየት ፣ ለሕሊናዬ እምቢ አለኝ ። 'በምን ተአምር ትኪቱ ላይ የነበረው ይለወጣል ?' — ድፍን ያለጥያቄ ሆነብኝ ። የሆነ ስሜት ከውስጤ ገንፍሎ ይነዝረኝ ጀመር . . .

« ፍሪቲ ነይ ! »ጩኸቴ አልታወቀኝም ።

ወጣቱ ዐይን ሥውር ከመቀመጫው እየተንቀሳቀሰ በዳበሳ ሊይዛት ሲል ፣ . . . በራ ወደኔ መጣች— ፍሪቲ ።

« ምን ሆንሽ ? » አልኳት ፣ ጉንበስ ብዬ ።

« እንዲ መሶቦርቅ ጠፋች . . . ቅድም አይተኸው አልነበር ? . . . እንይ የለችም ! » ስትል ፣ ዕንባዋ ዱብ ዱብ ይላል ።

« ሦስት ያለው አይደል የሚያሸንፈው ? . . . አሁን በቃ ! ጋሼ ተሸንፈ ! . . . አይደል ? ሲያሳዝን ! . . . »

ሳማ ይተናነቃታል ።

ቀና ስል ፣ ያ ቀጭን ሰውዬ ጓደኞቹን ለመሰናበት ቆሞ እጄን ሲዘረጋ አየሁት ። ብርክ ያዘኝ ። የደም

http://ethioliberty.wordpress.com/

ይችላል ? » አረ እንዳመጣልኝ በእልህ ተናገርኩት ።

ሰው ሁሉ ያፈጠጠበት መሰለው ። ጓደኞቹ እል ተነፈሱም ።

ፍራቲ ከስሬ ቆማ ፣ እንጋጣ ታየኛለች . . . በሰ ማያዊ ሸሚዟ ትናፈጣለች ። ዐይነ ሥውሩ ወጣት ፣

«ፍራቲ ! . . . ፍራቲ ! ነይ ነው— የምልሽ ! ነይ እን ሒድ እንች ዘዋሪ ! » አላት በቁጣ ። እኔ ቀጭኑ ሰውዬ ላይ እንዳፈጠጥኩበት ስለሆነ ፣ እሱና ጓደኞቹ ዐይነ ሥውሩ ወጣት የተናገረውን አልሰሙም ።

« የልጅቷ ትኪት ሦስት መሶቦርቆች እንዳሉት አይተሃል ፣ መጀመሪያ እኔ ነኝ ባይኔ ያየሁት . . . ምና ልባት እዚህ ተለዋውጠባት ከሆነ እንዲመልስላት ነው ! » አልኩት ። ንዴቴ እየጨመረ ሒዶ ።

ሰውዬው ኪሱን ይባበሰው ።

« ቆይ እስቲ ! . . . » አለኝ ። ከፍራቲ የተቀበልኩትን ትኪት መሰደና እየው ። የኩትና የሱሪ ኪሶቹን ምንም ሳያስቀር በረበራቸው ። እያረሳሳ ዐይኑን ወደ ጓደኞቹ ይወረውራል —በዘዴ ። « ምን ዝም ትላላችሁ ? እርዱኝ እንጂ ! . . . ከጉድ አውጡኝ ! » በሚል ስሜት መሰለኝ ። የጓደኞቹን ሐሳብ ከገጽታቸው ለማየት ዕድል አላገኘሁም ። ዐይኔ ሙጭጭ ያለው በዚያው ቀጭን ሰው ላይ ነበር ።

ዝውውሬ የተፋጠነ ቢመስለኝም ፣ የመደንዘዝ ያህል እግሬ ተሳሰረብኝ ።

« እይዞሽ ! . . . » ብዬ ፣ ከፍራቲ የሎተሪውን ትኬት ተቀብልኳት ።

« . . . ቅድም ሦስት ሆኖ ባይኔ ያየሁት ፣ አሁን በተገላጮር እንዴት ሁለት ሊሆን ይችላል ? . . . »

ምንም ሳላወላውል ወደ ቀጭኑ ሰውዬ አመራሁ ። ለመውጣት እንድ ሁለት ርምጃ እንደ ተራመደ ደረስኩበት ። ተፋጠጥን ።

« የልጅቷ ትኪት ተለውጠባታል መሰለኝ ? የቅድሙና ያሁኑ የተለያየ ነው ። » ራሴን እረጋግቼ ልጠይቅ ብልም ፣ የፈነዳብኝን ስሜታዊ ግንፍልነት መግታት አልቻልኩም ።

ሳፈጥበት ፣ ሰውዬው ቀስ እያለ ወደ ኋላው ተመ ለሰ ። ከነበረበት መንበር ላይ ተቀመጠ ።

« እንተ ምንድነህ ? . . . ተቀብያት ከየሁ በኋላ መልሼላታለሁ ! » አለኝ ። ግንባሩ ላይ ያለው የደም ሥር እንደ ውሃ ቱቦ አብጧል ።

« የወንድሜ ልጅ ነች . . . ይህን ዐይነ ሥውር ወደ ቤቱ የምታደርሰው እሷ ነች ። ቅድም ትኬቱን ይዛ ስትሄዋት ላንተም አሳይታህ ነበር ። አይቻለሁ ። ሦስት የነበረው መሶቦርቅ በተአምር ሁለት ሊሆን

http://ethioliberty.wordpress.com/

« ቆይ እስቲ . . . » ደገመና ፥ ኪሶቹን አራገፈ ። ከወረቀቶች መሐል የፈጣን ሎተሪ ትኬት እንዳየሁ ፥ ከመቅጽበት የመቀማት ያህል ከእጁ መነተፍኩት ።

« ተለውጦ ይሆናል » ሲል ፥ ትኬቱን እየተመ ለከትኩ ወደ ቦታዬ ተመለስኩ ። ፍሪቲ ተከትላኛለች ...


መጀመሪያ ያየሁት ነው ።

«ፍሪቲ ይዘሽ ሒጂ ! እንዳትጥይው ! » አልኳት ።

እየፈነደቀች . . . ከወጣቱ ወይን ሥውር ጋር ስት ወጣ ፥ ያን ቀጭን ሰው በምላሷ ታሾፍበት ነበር . . . ወይን ሥውሩ ወጣት ወደ ኋላው ገልመጥ ፥ ገልመጥ ሲል . . . እንዳች ነገር የከነከነው መሰለኝ ።

. . . አራቱም ከእኔ ተፋጠው ግማሽ ሰዓት አሳ ልፈዋል . . .

http://ethioliberty.wordpress.com/



AMH Ber
Berehan Dana
Sabat
ihvu
030104225080001
199
1